

# ቀናሁባቸው

## ኦርቴፊሻሏ ሀገር እና ሌሎች

## የጉዞ ማስታወሻ

(በታሪቀኝ አሰፋ)

# የጉዞ ማስታወሻ

## ቀናሁባቸው

### አርተፊሻሏ ሀገር እና ሌሎች

(በታረቀኝ አሰፋ)

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
@ታረቀኝ አሰፋ ወልዴ

ISBN 978-99944-3-025-3

ለማንኛውም አስተያየትዎ
brooktarekegn@yahoo.com
ስልክ 0910-462933

አከፋፋይ፡- ምንጭ መፅሀፍት
አድራሻ፡- ገርጂ ኢምፔሪያል ከመብራቱ ወረድ ብሎ

ሌይ አውት ግራፊክስ ዲዛይን ህትመት
በብዕር ማተሚያ ቤት

ሽፋን ዝግጅት፡ ተመስገን ፀጋዬ

## መታሰቢያነቱ

እኛ ልጆቿን ለማሳደግ ብቻዋን ለደከመችውና የሥራ ባህል በውስጤ እንዲሰርፅ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በዘለቀው የሥራ ሕይወቷ አርአያነቷን በተግባር ላሳየችኝ እናቴ በዛሽ ገላን መታሰቢያ ይሁንልኝ።

# ማውጫ

## አርእስት


፩. አርቴፊሻሏ አገር ቤልጂየም ........ 4

፪. ሻንዛ ሊዜ ፓሪስ ........ 21

፫. አሜሪካኖች ካለ መንገድ ........ 32

፬. ኩባ ወዳጃችን ........ 45

፭. ከአምቦ እስከ አፋምቦ ........ 53

፮. የጥረት ተምሳሌት ሕንድ ........ 61

፯. የሮማውያን አገር ጥልያን ........ 71

፰. ጋና የመቻቻልና የይቅርታ አገር ........ 81

፱. የበረሀ ገነት ........ 91

፲. ቀናሁባቸው ........ 98

፲፩. ስዊዘርላንድ ሰላማዊ አገር ........ 103

፲፪. የእንቢታ ትግልና ደቡብ አፍሪካ ........ 110

፲፫. ባንኮክ ........ 117

፲፬. ድንበሩ የቱ ነው ........ 124

፲፭. አገር ሲወለድ ደቡብ ሱዳን ........ 132

፲፮. ዓረብ ዓረብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም ........ 139

፲፯. ጠንካሮቹ ጀርመኖች ........ 146

፲፰. ጎረቤታችን ኬንያ ........ 152

፲፱. አዳዲ ማርያም ........ 157

፳. በሎንዶን ጎዳና ላይ ........ 164

፳፩. በጦርነት ማግስት /War Hangover/ ........ 178

፳፪ . ጉዞ ሲጠቃለል ........ 217

# መግቢያ

በሕይወቴ ከሚያስደስቱኝ ነገሮች አንዱ ሀገርና ሥፍራዎችን መጎብኘት ነው:: ማስታወሻ የመያዝ በጎ ልማድ ባይኖረኝም ነገር ግን አስተውሎቴ በተቻለ መጠን ትክክል እንዲሆን በደንብ ትኩረት ሰጥቼ ነው የምጎበኘውና ውይይቶችን የምከታተለው:: የጉዞ ማስታወሻ የመፃፍ ዝንባሌና ፍላጎት ያሳደረብኝ ብዙ ሰው ያስታውሰው እንደሆነ ባላውቅም ጋዜጠኛ መፅሐፈ ሲራክ ነው:: ድሮ የመፅሐፈ ጉዞ ማስታወሻዎች በሬድዮ ሲነበቡ በተመስጦ ነበር የማዳምጠው:: ለመፃፍ ድፍረቱን የሰጠኝ ነፍሱን ይማረውና የብሪቱ መፅሔት ዋና አዘጋጅ የነበረው ጌታቸው ገብረወልድ ነው:: ሂስ የማልፈራ ደፋር ነበርኩና የሞነጫጨርኩትን ይዤለት ስሄድ “ውስጥህ ከሰሉ አለ መጫሪያውን ፈልግ” ይለኝ ነበር - ይኸው ስፈልግ ባጀሁ::

የጉዞ ትዝታዬን በባንክና መድን እንዱስትሪ በምትታተም ብሪቱ መፅሔት ላይ ሁለቱን አሳትሜ ነበር:: ሆኖም ከዚያ በኋላ ወደ ፅሁፍ ሳልመለስ ብዙ ቆየሁ:: ሳልጓዝ ቀርቼ እንኳ አይደለም:: ቀድመው የተጻፉትንና ያልቀጠሉትን የጉዞ ማስታወሻዎቼን የሚያውቁት የልጆቼ ጉትጎታ ታክሎበትና ዘንድሮ ብዙዎቻችንን ቤት ያዋለን የኮሮና ዘመን ጻፍ ጻፍ ብሎኛል!

የዛሬ 25 ዓመት ገደማ በታተሙት ፅሁፎቼ ከሀገር ውስጥ አዳዲ ማርያምን አስቃኝቼ ወደ ሎንዶን ጉዳና ነበር አንባቢያንን ያወጣኂቸው፡፡ ከዚያ በኂላ ከውጪው ዓለም 14 ሀገራት እንዲሁም መላውን ኢትዮጵያን ዋና ዋና ከተሞች ከሞያሌ በስተቀር በተለያየንባቸው ዓመታት ጐብኝቻቸዋለሁ፡፡ ስለ ሀገሮቹ በተናጠልና ከሀገር ውስጥ በ1983 ዓ.ም. ካበቃው የርስበርስ ጦርነት በኂላ በማግስቱ ያየሁትን፣ እና ሌሎች በጠቅላላው 21 አጫጭር ማስታወሻዎቼን ከማጠቃለያ ጋር አቅርቤላችኂለሁ፡፡

ከቀረቡት ማስታወሻዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ለመወለድ ረጅም ጊዜ የጠበቁ ሲሆን፣ ከ22 ዓመታት በኂላ ከአእምሮዬ ጓዳ በርብሬ ነው የፃፍኂቸው፡፡ ትዝታዎች ያረጁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሰው በድሮ ትውስታዎቹ ጭምር አይደል የሚኖረው፡፡ ታትመው ለታሪክ ቢቆዩ ወደፊት በውስጡ ያለፉ አይጠፉምና ከኔ ግድፈት ካለ ያርሙት ይሆናል፡፡ ወዳጄ ዶ/ር አክሊሉ እንዳለኝ መጻሕፍት ለወደፊቱ ትውልድ ነው የሚተላለፉት (Books are for future generations) አብሮኝ ከሚቀበር በሚል ነው ያቀረብኩት፡፡ የአንዳንድ ሀገሮች ማስታወሻ ከቆይታዬ ውስኑነት በወፍ በረር እይታና ከሁለተኛ የሰው ምስክርነት ወይም የጽሁፍ መረጃዎች ምንጭ ነው ያዳበርኂቸው ባያረካችሁ አትዘኑብኝ፡፡

እነዚህን ሥፍራዎች በተለያየ ጊዜ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በሀገር ውስጥ ቅርንጫፍ ባንክ ለማስፋፋት ጥናት ለማድረግ፣ ለትምህርትና

ሥልጠና የሄድኩባቸው ሀገሮች፣በግል ግብዣ በእንግሊዝ፣ ኩባና ጋና የጥናት ወረቀት ለማቅረብ እንዲሁም ሌሎቹን በተፈጠረልኝ መልካም አጋጣሚዎች የጎበኘኋቸው ናቸው።

በተለያየ ጊዜ ማስታዎሻዎቹን አንብበው አስተያየት የሰጡኝ ሰዎች ብዙ ናቸውና ዘርዝሬ አልዘልቀውም። በጽሁፍ ከሰጡኝ ውስጥ የሥራ ባልደረባዬን ዳኛቸውና የወዳጆቼን ዶክተር ኤልያስና ዶክተር መስፍንን የእንግሊዝኛ ሀሳባቸውን ከነትርጉማቸው አቅርቤዋለሁ። እንደዚሁም ዶክተር አክሊሉ ኪዳኑ በአጋጣሚ ተገናኝተን በመቀራረባችንና በሥነ-ጽሁፍ ዙሪያ እንወያይ ነበር። ቆይቶም ግለ-ታሪኩን (ያገርቤት መንገዶች በሚል ርዕስ) በማሳተሙና በሥጦታ ካበረከተልኝና ካነበብኩት በኋላ ይበልጥ ተቀራረብን። እኔም ተጽፈው ለብዙ ጊዜ ቁጭ ያሉትን ማስታወሻዎቼን ሰጥቼው ካነበበው በኋላ እንድገፋበት ስላበረታታኝና ለሰጠኝ አስተያየት ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው። የመጨረሻውን ማስተካከያ የሚደረግባቸውን ጉዳዮች ካላቸው የተጣበበ ጊዜ ቀንሰው አስተያየት ለሰጡኝ የቀድሞ የሥራ ባልደረባዬ ደራሲ ገስጥ ተጫኔ እንደዚሁም ለጎረቤቴ አየለ ገላነህ፣ ወንድሜ ሁነኛው ጥላሁንና እህቴ ፀሀይ ይስማው ምስጋናዬ እጅግ ላቅ ያለ ነው። በአጠቃላይ በትየባውና ማስታወሻዎቼን በማንበብ ላበረታቱኝ በቅርብም በሩቅም ላሉት ሁሉንም ክብረት ይስጥልኝ እላለሁ።

*ታረቀኝ አሰፋ*

## ፩ አርተፌሻሏ ሀገር- ቤልጂየም

ቤልጂየም ከጫፍ እስከ ጫፍ 360 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላት በስም የገዘፈች በምዕራብ አውሮፓ ምትገኝ ሀገር ናት። በሰሜን ኔዘርላንድ በደቡብ ምሥራቅ ሉክሰንበርግ፣ በደቡብ ምዕራብ ፈረንሳይ እና በሰሜን ምሥራቅ ሰሜን ባህር ያዋስኗታል። የቆዳ ስፋቷም 30685 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው። የተመሠረተችው እ.ኤ.አ. በ1830 ዋሎንያ የምትባል ግዛት ከፈረንሣይና ቭላንስ ከሆላንድ ተቆርሶ ሲሆን፤ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ ጀርመን በሀገሪቱ ላይ ላደረሰችው የጦር ጉዳት ካሣ ይሁንሽ ብላ የራሷን ሊምበርግ ግዛትን ከሃምሳ አምስት ሺህ ኗሪዎቿ ጋር መርቃላት ተስፋፍታለች።

ቤልጂየም የ11.5 ሚሊዮን ሕዝብ መኖሪያ ነች። ከዚህ ውስጥ 2.4 ሚሊዮን ወይም 21 በመቶ ከሀያ ከሚበልጡ ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ኗሪዎች ናቸው። 59 ከመቶ ደች፣ 40 ከመቶ ፈረንሳይና 1 ከመቶ ጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው። እንደዚሁም 58 በመቶ የሚሆኑት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ናቸው።

ቤልጂየም ዋና ከተማዋ ብራስልስ ሲሆን፣ የአውሮፓ ህብረት ሲመሠረት ብራስልስ የህብረቱ መቀመጫ ሆና ተመርጣለች። የተመረጠችውም በወቅቱ ካሉት አባል ሀገራት ዋና ከተሞች

መሀከል በፊደል ቅደም ተከተል (Alphabet) ቀዳሚ ሆና የተገኘው እንዲሆን ኔዘርላንድ ፈረንሣይና ጀርመን ባቀረቡት ሓሳብ መሰረት ነው፡፡ ካሉት ዋና ከተሞች ብራስልስ በቅደም ተከተሉ መጀመሪያ ረድፍ ላይ በመምጣቷ የህብረቱ መቀመጫ ልትሆን በቅታለች፡፡ ሆኖም የታሪኩ ውስጠ ሚስጥር ሲመረመር የዳች (ፍሌምሽ) እና የፈረንሣይ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነችው ሀገር ለማንም ሳትወግን በገለልተኝነት ታገለግለናለች ብለው ያሴሩት ነገር እንደሆነ ይገመታል፡፡

ይህን በመዋጮ ግዛት መመስረት በአሜሪካም ተመልክቻለሁ፡፡ በአሜሪካ ታሪክ የሚታወቀው በ17ኛው ክፍለ ዘመን የተደረገው የመገንጠል ጦርነት አብቅቶ በኮንፌዴሬሽን ለመተዳደር ተስማምተው ሲዋሃዱ የመንግስት መቀመጫ በጋራ ወስነው ነበር፡፡ ለሁሉም አማካኝ ቦታ ዋሽንግተን ዲሲን (District of Colombia) በወረዳ ደረጃ ያቋቋሟት ከቨርጂኒያ ከፖቶማክ ወንዝ መለስ ተቆርሶ እንዲሁም ከሜሪላንድ የተወሰነ ግዛት ተዋጥቶ ነው የተመሰረተችው፡፡

የቤልጂየም ታሪኳን ራቅ አድርገን ስንመረምር ግዛት ቆርሰው ያዋጡት ሀገሮች መሠረታዊ ምክንያቶቻቸው እንደሚጠቀሰው አይደለም፡፡ እነዚህ በድንበር አካባቢ ያሉ ሕዝቦች በአመፃቸው ምክንያት ለማዕከላዊ መንግስት አስተዳደር ስላልተመቹ ሆን ብለው ከነሱ ለመገላገል ሲሉ ያደረጉት እንደሆነ በአፈ ታሪክነቱ ይነገራል፡፡ ለዚህም ነው የሰው እጅ ስራ የሆነች “አርተፊሻል ሀገር” እያሉ

የሚጠሯት፡፡ ሆኖም ቤልጂየሞች  በዚህ አይስማሙም፡፡  እኛ ከሁሉም ሀገር ቀደምት ነን ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ እንዲያውም ሌሎቹ ሀገሮች ከኛ የጎን አጥንት የተፈጠሩ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡

የመንግስት ፌደራላዊ አወቃቀሯም-አንዱ በቋንቋና ሌላው በቦታ ክልል ነው፡፡ ከፈረንሣይና ሆላንድ የተቆረሱት ግዛቶች ማለትም ዋሎንና ቭላንስ ከተሞች እንዲሁም ብራስልስ  የሶስት ፓርላማ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ቤልጂየም ባላት ሰፊ የፓርላማዎች ነፃነት እ.ኤ.አ. በ2011 መንግስት ለመምረጥ እርስ በርስ መስማማት ባለመቻላቸው ለሁለት ዓመታት ያህል መንግስት አልባ ሆና መቆየቷ የቅርብ ጊዜ አስደናቂ ታሪኳ ሆኖ ተመዝግቦላታል፡፡ ነገር ግን መንግስታዊ ሥራው ምንም እንከን ሳይገጥመው በመዝለቁ ወይ ስልጣኔ ብላችሁ ትገረማላችሁ፡፡ ይህ ዐይነት ክስተት የጣሊያንም የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው፡፡ መንግስት እንደ ቅጠል በየስድስት ወሩ የሚረግፍበት ወቅት ነበር፡፡ ታዲያ አንዱ የሕዝብ አመኔታ አጣ ተብሎ ስልጣን ሲለቅ ሌላው በምርጫ እርሱም እንደቀደመው ዕድሉን ለመሞከር ይመረጥ ነበር፡፡

ቤልጂየም በአፍሪካ ውስጥ በነበሯት በማዕድን የበለፀጉ ቅኝ ግዛቶቿና በመጨረሻም በተባበሩት መንግስታት አስገዳጅ የክተት ዘመቻ በግድ ተገፍታ ከየሀገሮቹ በመውጣትም በሰፊው ትታወቃለች፡፡  በኮንጐ፣ ሩዋንዳና ቡሩንዲ በአልማዝና በሌሎች ማእድናት ምርታቸው

ተንደላቃ መኖሯና ሀገሯን በመገንባቷ ለመልቀቅ እንዳሳዘናት ይነገራል፡፡ በኮንጐ እኛም እ.ኤ.አ. በ1960 ከተባበሩት መንግስታት ጦር ጐን መዝመታችን ማስታወሻ ሆኖ በስታዲየማችን የቀረው ካታንጋ የሚባል ስም በዚህ ቦታ ላይ ጀግኖቻችን ጠንክረው መዋጋታቸውን ያስታውሰናል፡፡

በወቅቱ እንደ ጦር መላ የተጠቀሙበት ከገደሉት ሬሳ ላይ ስጋ የሚቆርጡና የሚበሉ አስመስለው ማሳየታቸው ጠላትን ለሽብር ዳርጐት እንደነበርና ሰው በላ የኢትዮጵያ ጦር መጣብኝ ብሎ እንደበረገገና እንደሸሸ የኮንጐ ዘማቾች ሲያወሩ አድምጠናል፡፡ በርግጥ ከኮሮጆአቸው የያዙትን ጥሬ ሥጋ ሬሣው ላይ ቁጭ ብለው መብላታቸው ትልቅ የጦር ስልት እንደሆናቸውና ለድል እንዳበቃቸው ተመስክሮአል፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ወደ አድዋ ድልድይ አካባቢ አሁንም የኮንጐ ዘማቾች ሰፈር የሚባል ቦታ እንዳለ አውቃለሁ፡፡

ብራስልስ በቆየሁበት ጊዜ ያገኘሁት ኢትዮጵያዊ የሰማውንና የነገረኝን ባካፍላችሁ እናንተም ዕድሉ ባጋጠማችሁ ጊዜ ብታረጋግጡት ምን ይላችኋል፡፡ ቤልጂየሞች በኮንጐ ቆይታቸው ለሀገሬው ብዙ መሠረተ ልማት እንዳልሰሩለት በተለይ በወቅቱ የነበረው ንጉሥ ሌዮፓርድ ሁለተኛ የተባለው የቤልጂየም ገዥ ይወቀስበታል፡፡ እንደ ትምህርትና መንገድ የመሳሰሉት መሠረተ ልማቶች በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የነበሩ ቅኝ ገዢዎች ከሰሩት ጋር ሲነፃፀር ትንሽ

በመሆኑ ዛሬ ላይ እንደሚያፍሩበት ሰምቻለሁ። ቤልጂየሞች ከዚህ ይልቅ አገዛዛቸውን ለማስንበት ሲሉ ህዝቡን እንዴት ከፋፍለው እንደገዙት ሲናገሩ በዚያን ጊዜ ማንኛውም የኮንጎ ዜጋ ሲያወራ ጮክ እንዲል ይገደድ እንደነበር ነው። ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ሚስጢር እንዳያወሩ ለመከላከል ነው። በዚህ ልማድ የተነሳ ዛሬም ጯሂ ህብረተሰብ እንዳፈሩ ትገነዘባላችሁ። ሌላው የሰማሁት እርስ በርስ እንዳይተማመኑ ያሰፈኑት የመጠራጠር ባህል ነበር። ለምሣሌ መጠጥ በብርጭቆ ተቀድቶ ለሰው አይሰጥም። በጠርሙስ ብቻ ነው። መጠጡን ጠጥተው ሳይጨርሱ ወደ ሽንት ቤት መሄድ ከፈለጉ ጠርሙሱን ይዘው ይሄዳሉ እንጂ ትተው አይሄዱም ይባላል።

ቤልጂየም እ.ኤ.አ. 1908 ኮንጎን በቅኝ ግዛትነት ከያዘችበት ጊዜ ጀምሮ የጎማ መሥሪያ ግብዓት ወደ አገሯ በገፍ ወስዳለች። ንጉሥ ሊዮፖልድ አገሪቱ የግል ገንዘቡ ሆና የተሰጠችው ሲሆን፣ በኮንጎ ለአርባ ዓመት  በጭካኔ የተሞላ አገዛዝ አስፍኖ ቆይቷል። ንጉሡ ኮንጎን ለመግዛት ሲደርስ ከነበሩት ዜጎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር ትቶት የሄደው ግማሹን ነው። በአገዛዙ ዘመን እስከ 10 ሚሊዮን የኮንጎ ዜጎች እንደተገደሉ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል።

በሩዋንዳ በቅርብ ጊዜ  በሁቱና ቱትሲ መሀከል ለተፈጠረው እልቂት መነሻ ሲመረመር ቤልጂየሞች በሊጎ ኦፍ ኔሽን በውክልና ሞግዚት አስተዳዳሪ ሆነው እዚያ በነበሩበት ዘመን በሁለቱ ዋና ጐሣዎች መሀል የፈጠሩት ልዩነት እንደሆነ ይነገራል። በዚያን

ዘመን የዘወትር መቀስቀሻቸው የነበረው እናንተ እኮ ንፁህና ቆንጆ ዘር ናችሁ በተቃራኒ እነርሱ ትንሽ ናቸው የሚል እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡ ይህ አጉል ቅስቀሳ በመሀከላቸው ትምህክት መናናቅና ጥላቻ ብሎም በቀል አርግዘው እንዲኖሩ ከማድረጉም በላይ አንዱ አንዱን አጥፍቶ የበላይ ለመሆን የሚያደርጉትን ፉክክር ስር እንዲሰድ አድርጎታል፡፡ በመጨረሻም ይህ የጊዜ ቦንብ ፈንድቶ ከሁለት አስርተ አመታት በፊት ለተፈጠረው ለዘር ጨራሽ እልቂት ዳርጕአቸዋል፡፡ በዚህ ድርጊታቸው ዛሬ ላይ ቤልጂየሞች እንደሚጸጸቱበት ሰምቻለሁ፡፡ ግን ምን ያረጋል አንድ ሚሊዩን የሚጠጋ የዚያች ሀገር ዜጐች ነፍስ በምን ይመለሳል?

ለማስታወስ በጋራ ሰላም የማስከበር መርህ ኢትዮጵያ በገባችው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ኢትዮጵያውያን ከኮንጎ ዘመቻ በፊት ኮሪያ ዘምተዋል፡፡ ኮሚኒስት ሰሜን ኮሪያና ቻይና በደቡብ ኮሪያ ላይ በቀሰቀሱት ጦርነት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያቀረበውን ጥሪ ተቀብላ እ.ኤ.አ. በ1951 በሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የሚመራ ከሶስት ሺህ በላይ የቃኘው ሻለቃ ጦር ዘምቷል፡፡ ከዘመቱት ከአስራ ስድስት ሀገሮች የተውጣጣ ጦር ውስጥ የኢትዮጵያ መዋጮ ከአሜሪካ ቀጥሎ ትልቁ ነበር፡፡ ደቡብ ኮሪያን ከሰሜን ኮሪያ ወረራ ለመከላከል ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አህጉር ውጪ ስትዘምት በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር፡፡

እነዚህ አንድ ባታሊዮን የክብር ዘበኛ ሠራዊት አባሎች ከጣሊያን ወረራ በኋላ በስዊድኖች የሰለጠኑ ቢሆኑም የታጠቁት መሣሪያ

ግን ዘመናዊ አልነበረም፡፡ አሜሪካኖች በስምንት ሳምንት ጊዜ ውስጥ በነሱ ዘመናዊ መሣሪያ አሰልጥነዋቸውና አስታጥቀዋቸው ለውጊያ ብቁ አድርገዋቸዋል፡፡ በዚህም ጠላት ሳይቀር የመሰከረላቸውን ጀብዱ ፈጽመዋል፡፡ በጦርነቱ ወቅት ቻይና አንድ የኢትዮጵያ ሠራዊትን አባል በሕይወት ማርኮ ወይም ሬሳውን ላመጣ እሸልማለሁ ብትልም ከንቱ ሕልም ሆኖ ቀርቷል፡፡ በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን ተፈጥሮአቸው የሰው አይደለም እንዲያውም ሰው በላ ናቸው እስከማለት ደርሰው ነበር፡፡ ጥቁር እንደዚሁም እንዲህ ያለ ጀግና አይተው ስለማያውቁ ነውና አይፈረድባቸውም፡፡ አሜሪካኖቹም ቢሆን የማታ ቅኝት የተለየ ዘዴ ከኢትዮጵውያን እንደተማሩ ይገልጻሉ፡፡

እዚህ ላይ ከነወንድማቸው ኮሪያ ዘምተው የነበሩት የወንድሜ አማት የአባዬ ይመኙሻል ወንድም የክብር ዘበኛ ሠራዊት አባል የነበሩት ሻምበል ሥዩም (ካፒቴን መባልን ይወዳሉ) ያጫወቱኝ ትዝ አለኝ፡፡ ጦርነት ከተጀመረ ሮጠን ነበር ዘለን የምንገባው ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ነበር የምንዋጋው፡፡ አንድ ቀን እንደዚሁ ድንገት ጦርነቱ ተጀመረ ወደ እሳቱ ውስጥ ለመሮጥ ስዘጋጅ አንድ አሜሪካዊ እቅፍ አድርጎ ይዞኝ እባክህ እኔ ልሙትልህ አንተ ቅር ብሎ ፍቅሩንና አድናቆቱን የገለጸልኝ ሁኔታ መቼም አይረሳኝም ብለውኛል፡፡

እንዲያው ነገር አበዛህብን ባትሉኝ ወንድማቸው ኮሎኔል ተፈራ ስለመንግሥት ሥርዐቶች አወዳደቅ የነገሩኝን ለብዙ ሰው

አካፍየዋለሁና እናንተም ብትሰሙት:: ከጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ በኋላ ከነወንድማቸው (የሁለቱንም ነፍስ እግዚአብሔር ይማርልን) ከሠራዊቱ ቤት ተለይተው ሁለቱም በተማሩት የሲቪል ምንድስና ሙያ ይሠሩ ነበር:: እየተቆጣጠሩ ካሰሩት ሕንፃ ውስጥ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ሕንፃ አንዱ ነው:: በባለቤትነት ለሚያሠራው ድርጅት ተቆጣጣሪ ለሆነው ባለሥልጣን ሪፖርት ከሚያደርጉላቸው ሰው ጋር በሥራው አጋጣሚ ቅርበት ይፈጥራሉ:: ሥራው ካለቀ በኋላም ይጠያየቁ ነበር:: እኚህ ባለሥልጣን በጊዜው በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ ትንሽ ጊዜ ቆይቶ ወደሌላ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ይቀየራሉ:: እዚያ ትንሽ ጊዜ እንደሠሩ ውጭ ሀገር በአምባሳደርነት ይሾማሉ:: እንኳን ደስ አለህ ለማለት ቢሮው ስሄድ ተከፍቶ አገኘሁት አሉኝ:: በጣም ገርሞኝ ወዳጄ ምነው ልትደሰት ሲገባህ ብዬ እንዲህ አልኩት “አንተ እግዚአብሔር ከሚወዳቸው ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነህ:: እናንተ ውስጥ ሆናችሁ አይታወቃችሁም እንጂ እኛ ከውጭ ሆነን ለምናየው ሥርዐታችሁ ለመውደቅ ወደ አንድ ጎን እጅግ ዘሞ ይታየናል” ብዬው ተሰናብቼው ወጣሁ:: ኮሎኔል እንዳሉት ብዙም ሳይቆይ የደርግ ሥርዐት ወድቆ አምባሳደሩም እዛው በተመደቡበት ሀገር ስደተኛ ሆነው ይኖራሉ::

በኮሪያ ጦርነት ወቅት 121 የሚሆኑት ኢትዮጵውያን ሲሰዉ 536 የሚሆኑት ቆስለዋል:: ዘማቾቹ ኢትዮጵያውያውያን በድል

አገራቸው ሲገቡ የሞቱባቸውን ጓዶቻቸውን አስከሬን ሁሉ ይዘው ነው የተመለሱት። ዛሬ ያ ውለታችን ለደቡብ ኮሪያውያን ትልቅ ዕዳ ሆኖባቸው እኛ ብዙ የማናስታውሳቸውን ጀግኖቻችንን ውለታ ለመመለስ በየጊዜው ሲደክሙ እናያለን።

በቤልጂየም ቆይታዬ ከዋና ከተማው ብራስልስ ወጣ ብላ ያለችዋን ትንሿን ሉቨን ከተማ ውስጥ የመቆየት እድሉ አጋጥሞኝ ነበር። ይህች ፀጥ ያለች የትምህርትና የሀይማኖት ማዕከል የሆነች ከተማ ከብራስልስ በ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ናት። ሉቨን ብዙ የካቶሊክ ዩኒቨርስቲዎችና ቤተ ክርስቲያናት ይገኙባታል። ሆኖም የዛሬው ትውልድ እንዳባቶቻቸው ሀይማኖት አጥባቂ ባለመሆናቸው ቤተ ክርስቲያናቱ ዛሬ ላይ የሚጠቀምባቸው ባለመኖሩና በአገልጋዮችም እጥረት ብዙዎቹ ተዘግተዋል ወይም ለሌላ አገልግሎት ውለዋል። ለምሣሌ ያየሁት የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት የሆነው ቤተ ክርስቲያን እንደነበረ ተነግሮኛል። በብራስልስ ሌላ ትልቅ ሬስቶራንት የሆነ ቤተ ክርስቲያን አጋጥሞኛል።

በቤልጂየም በተለይ ሉቨን በአዘቦቱ ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ ብዙ ሱቅ ዝግ መሆኑን ቅዳሜና እሁድ የቢሮ ሥራ እንደሌለ አይቻለሁ። ይህ የካቶሊክ እምነት ቤተ ክርስቲያን በአማኞች ላይ ያሰረፀው ቀኖና ይመስለኛል።

ቤልጂየሞች ሥራ በልኩ የሚል መርህ አላቸው። አንድ ሰው በቀን ከ8 ሰዓታት በላይ እንዲሰራ አይፈቀድም። ከሰራም በዘዴ

በግብር ጭማሪ ምክንያት ብዙ መስራት ትርፉ ዘጭ ዘጭ ነው ብሎ እንዲሰበሰብ ያደርጉታል፡፡ የቤልጂየም መንግስት መሠረታዊ እምነት አንድ ሰው ሰርቶ በበቂ ማረፍ አለበት የሚል ነው፡፡ አንድ ሥራ ሠርቶ ለኑሮ በቂ ገቢ ይገኛል፡፡ በገቢውም ለሰው ልጅ ኑሮ የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች ሟሟላት ይቻላል፡፡ አንድ ሰው በልቶ ማደር ሰብአዊ መብቱ ነው ብለውም ያምናሉ፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት ይሰራሉ፡፡ ለምሣሌ የውጪ ስደተኞች እንኳ አንድ ጊዜ ወደ ሀገራቸው ከገቡ መሠረታዊ ፍላጐቶቻቸው እንዲሟሉላቸው ይደረጋል፡፡ ሠርተው እንዲኖሩም ስልጠና በመስጠት የሚረዱ ማህበራዊ ጉዳይ መ/ቤቶች በየከተማው በብዛት ይገኛሉ፡፡ የተረጂነት መንፈስን አጥብቀው ይዋጋሉ፡፡

ቤልጂየም በጣም የምትታወቅበት ዋና ምርቷ ቸኰሌት ነው፡፡ የቸኰሌት ባዛር የመሰለ ሠፈር ዋናው ከተማ ብራስልስ መሀል አለላችሁ፡፡ መብላት ነው ፡፡ በጣም ነው የሚጥመው-- ነገር ግን 68 ከመቶ በላይ ከዓለም ኮኮዋ ምርት ከአፍሪካ መሄዱን አትርሱ!

እዚህ ላይ ጥንት አባቶቻችን የሚኮሩበትን ቤልጂግ ጠብመንጃን የምንረሳ አይመስለኝም፡፡ የአባቶቻችን በዚህ ጠብመንጃ መመካትና የፍቅራቸውን ልክ የምንገነዘበው ለልጆቻቸው ቤልጂጌ ብለው ስም እስከመሰየም መድረሳቸው ነው፡፡ ከቤልጂየም ለመጀመሪያ ጊዜ ጠመንጃ ግዥ የተካሄደው በአፄ ምኒልክ እ.ኤ.አ.1888 እስከ 1896 ባለው ጊዜ ነበረ፡፡ ምኒልክ የሶስቱ ኃያላን መንግሥታት (እንግሊዝ፣

ፈረንሳይና ጣሊያን) ሴራ ተቋቁመው ሲቻል በዲፕሎማሲ ሳይቻል በድብቅ ግዥ እየመጣ የነበረውን ወረራ ለመመከት መሳሪያ ለማግኘት ብዙ ጥረዋል። ሰርኪስ ታርዛን በተባለ እና ሌሎች  የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች አማካይነት መነሻውን ቤልጂየም ያደረገ ብዙ የጦር መሣሪያ በድብቅ አስገብተዋል። አፄ ምኒልክ በተለያየ ጊዜ ካስገቡአቸው ጠብመንጃዎች ውስጥ የራሺያ ግራዝ የስፔን ሬጂመንተን ወ.ዘ.ተ. ይገኙበታል።

ቤልጂየም በሌሎች የምዕራብ ሀገሮች እንደተመለከትኩት ለአካባቢ ጥበቃ ያላቸው ግንዛቤና ጥንቃቄ ከፍተኛ ነው።  በመሀል ከተማ ውስጥ አረንጓዴ ደን በብዛት ይታያል። ለሰው መዝናኛ  በየቀበሌው ፓርክና ልዩ ልዩ የሰውነት እንቅስቃሴ መስሪያ የውሀ ዋና ቦታን ጨምሮ በበቂ ተዘጋጅቶ ይገኛል። እንዲሁም  በማንኛውም አውራ ጐዳና ጐን ለብስክሌት መሄጃ ለብቻው ተዘጋጅቶለታል። ይህም ከመኪና ጭስ ብክለት የነፃ አካባቢን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ያግዛል።

በትምህርት ረገድ በጓደኞቻችን ልጆች እንዳስተዋልኩት ተማሪው ባለው ዝንባሌና ችሎታ ትምህርት እንደሚሰጠው ተገንዝቤአለሁ። ለምሣሌ አንደኛዋ ልጃቸው ሳሌም ብዙ ቋንቋ በመማር እራሷን ፈትናለች- ማለትም ላቲን፣ ግሪክ፣ ፈረንሣይኛ፣ ደች (ፍሌሚሽ) እና እንግሊዝኛ ተምራለች። ላቲንና ግሪክ  ቋንቋዎች ትምህርት አይሰጥባቸውም። እነዚህን ቋንቋዎች መማር ጥንታዊ እውቀትን

ለመመርመርና ለመተርጐም ይረዳሉ። እሷም የላቲንና የግሪክ ቋንቋዎችን በሁለት ዓመታት አጠናቃ አሁን ዩኒቨርሲቲ ገብታ በህክምና ዘርፍ ሣይንሣዊ ምርምሮችን መፈተሽ ጀምራለች። አቅሙ ካለ አውቀትን ፍለጋ ገደብ የለውም። በተለይ በተግባር የተደገፈ እውቀት--- የኛስ ግዕዝ ትንሣኤ መች ይሆን?

እንግሊዝኛ እንደ ፈረንሳይ ቤልጂየምም ውስጥ ብዙ ቦታ የለውም። እንደሰማሁት ከአካባቢ ሀገሮች እንግሊዝኛ በት/ቤት የሚጠቀሙበትና ልጆችንም እንዲማሩ የሚያበረታቱ ሆነው ያገኘኂቸው ሆላንዶችን ነው። ለምሳሌ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰራ ፊልም ወደነሱ ቋንቋ ለተጠቃሚዎች አይተረጉሙላቸውም። ይህ በመንግስት ደረጃ ያለ አቋም ነው። ይህን የነገረኝ ደጉ አክሊሉ (ጓደኞቹ እንደሚጠሩት አኬ) ፓሪስ ሰርቶ በሣምንቱ መጨረሻ ቤተሰቡ ጋ ወደ ሆላንድ ስንጓዝ ነው። ከፓሪስ እስከ ብራስልስ ከጓደኛው ጋር እየተፈራረቁ እየነዱ ከልጆቼ አቢና ናቲ ጋር ሲወስዱን ያጫወቱን ነው። በጠቅላላው 480 ኪሎ ሜትር ነድተው ሁለት ሀገሮችን ፈረንሳይንና ቤልጂየምን አቋርጠው ቤታቸው ሆላንድ ለመድረስ ከፓሪስ የተነሣነው ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ነው። በህብረቱ አባል ሀገሮች መካከል የትም ተዘዋውሮ መስራትም ሆነ መኖር ይቻላል። በስምምነትና በፊርማ 27 ሀገሮች አንድ የሆኑበትና የደረሱበት ሥልጣኔ የሚገርም ነው።

ቤልጂየም ያረፍንባቸውን ጓደኞቻችንን ካነሳሁ አይቀር ባልና ሚስት ጐረቤቶቻቸውን ማርሌንና ማርሴን ለምን አላስተዋውቃችሁም? እነዚህ የቤልጂየም ተወላጆች እዛው ተወልደው ያደጉ በተለይ ወንዱ በተወለደበት ቤት ሲኖር ዛሬ የ65 ዓመት ሚስቱ ማርሴይ የ64 ዓመት አዛውንት ሆነዋል፡፡ ጓደኞቻችን የገዙት ቤት የማርሌ እናት  ይኖሩበት የነበረ ቤታቸውን ነው፡፡ ታዲያ አብሮ ከመኖርና ከመቀራረባቸው የተነሣ እንጀራችንን በማርና በስኳር ጠቅለው እንደ ሳንድዊች ይገምጡታል፡፡ አብረን ከቁርስ ቡና መጠጣት እስከ ምሣ ባሳለፍነው ሰንበት ዶሮ ወጡንም በጣቶቻቸው ሲበሉ ተመልክቻለሁ፡፡ ብቻ ከቀረቡአችሁ እንደ ቤተሰብ ነው የሚያዩአችሁ፡፡ ቤልጂየሞች ስራ ይወዳሉ የሚሰራንም ያከብራሉ፡፡ እንደ አብነት የኢትዮጵያ አየር መንገድን ያነሳሉ፡፡ አንድ በጥቁር የሚመራ ኩባንያ ለዚህ ሁሉ ዓመታት በስኬት በመዝለቁ ትልቅ አድናቆትና አክብሮት አላቸው፡፡

በመጨረሻ ዮሴፍ አፍጋኑን ላስተዋውቃችሁ፤ ፌርማታ ላይ አቶቡስ ስንጠብቅ ነው የተገናኘነው፡፡ እኔና አስጉብኚዬ በአማርኛ ስናወራ የማወቅ ጉጉቱ ጨመረና ከይቅርታ ጋር ቋንቋው የእስራኤል ነው ወይ ሌላ ብሎ በድፍረት ጠየቀን፡፡ አማርኛ የኢትዮጵያ ስንለው እንዲያውም ዳዊት የሚባል ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቅ ነገረን፡፡ ከዚህ በኂላ የውይይት በሩ ተከፈተ አቶቡሷም መጣች አንድ

ወንበር ላይ ተቀምጠን ቀጠልን:: በዚህች የ30 ደቂቃ የአውቶቡስ ጉዞ ያልነካካነው አርእስት የለም::

ከሰላሳ አምስት ዓመታት በፊት ራሺያ ከአፍጋኒስታን ተሸንፋ ስትወጣ ከሀገሩ እንደተሰደደ ነገረን:: አሁን እናቱ እህት ወንድሞቹ አብረው በቤልጂየም እንደሚኖሩ ገለፀልን:: እህሳ ጦርነቱ ማለቂያው የት ነው አልነው:: አሁንማ 40 ዓመት የጦርነት ልምድ አዳበርን-- በዚህ ሁሉ ጊዜ አንዱ የአንዱን ወንድም፣ አጐት፣ ወ.ዘ.ተ. ገድሏል:: ያንን ለመበቀል እንዲሁ ስንጠፋፋ ዘልቀናል:: ታዲያ ማን ልበ ሰፊ ሆኖ ይቅርታ ያድርግና ጦርነቱ እልባት ያግኝ? ይህ እኮ አንዱ ይቅር የማይልበት የሰው ልጅ አስቸጋሪው ባህሪ ነው አለን::

መኖር በሰው ሀገር እንዴት ነው አልነው:: ጥሩ ነው ቢሆንም ደስታው መሬት አይረግጥም አለን:: አሁን ይህን ሁሉ ወሬ በቋንቋችሁ በአማርኛ ባወራችሁ ምን ዓይነት ደስታ ይሰማችሁ ነበር በማለት ውስጣዊ ሀዘኑን አጋራን:: ስንለያይ ለሶስት እጃችንን አጠላልፎ ይዞ የሞቀ የስንብት ሰላምታ ሰጥቶን ለየአገሮቻችን መልካሙን ተመኝተን ተሰነባበትን:: አፍጋኒስታን በረሃማ ሀገር ስትሆን የጋዝ፣ አልሙኒየም፣ ኤመራልድ፣ ጨው ማዕድናት አላት::

ወዳጄን ይህ አፍጋናዊ ምነው ይህን ያህል ተደሰተ አልኩት:: ቤትም ገብቼ ቤት ውስጥ ላሉት ጓደኞቻችን ስነግራቸው በዚህ ስደተኛን ብዙ

አነጋጋሪ በሌለበት ሀገር ብሶቱን የሚሰማው ማግኘቱና የዘመናት ብሶቱን መተንፈሱ ደስታውን አንሮት ይሆናል አሉኝ፡፡ ለካ በሰው ሀገር የሚያናግርም ችግር ነው፡፡ ይህን ሲሉኝ ድሮ አንድ የማውቀው ዶክተር ያጫወተኝ ትዝ አለኝ፡፡ ገና ከዩኒቨርስቲ እንደተመረቅኩ ገጠር ተመደብኩና ሄድኩ አለኝ፡፡ ጤና ጣቢያ ውስጥ ብቸኛ ዶክተር ነኝ እንዲሁም ቤትም ብቻዬን ነኝ፡፡ ታዲያ ሥራዬን ጨርሼ ቤት ስገባ የማናግረው የለም፡፡ ብቻየን ስሆን ይጨንቀኝ ጀመር፡፡ አንዳንዴ ቋንቋ ልረሳ ነው እንዴ እልና ወደ ጤና ጣቢያ እሄድና የተኙትን በሽተኞች በእረፍት ጊዜዬ እጠይቃቸው ጀመር፡፡ አልጋቸው ጫፍ ቁጭ ብዬ አወራቸዋለሁ፤ ያወሩኛል፡፡ ይህ የዘወትር ሥራዬ ሆነ፡፡ ታዲያ በሽተኞቹ እንዴት ያሉ የተባረኩ ዶክተር ናቸው ይሉኛል፡፡ እኔም በልቤ እንዴት የተባረካችሁ በሽተኞች ናችሁ እላለሁ፡፡

ከሚላን ኢ.አ ጉዞ ላይ ጳጉሜ 5 ቀን 2009 ዓ.ም. ተፃፈ

---

*Dear Tarekegn:*

*Please forgive for my belated response; it wasn't for lack of interest. Both articles are superb travel memoirs and great reads. I have lived in Belgium for two years but learned quite a lot from your piece. I like the Belgian people if not its colonial past. I had once referred to King Leopold II of Belgium's edict letter to his missionaries*

*in Congo on my public speech on Adwa celebration to portray the evil intent of colonialism and how Ethiopia has successfully repulsed the European transgressor thanks to our heroic forefathers. The missionary forgot the letter in his bible and later found by one Congolese in a second-hand market. Here is the link: The Wickedness of King Leopold II Revealed By His Letter To The Missionaries | The African Exponent.*

*Mesfin Genanaw, PhD (Houston Texas, USA)*

*ውድ ታረቀኝ፣*

*የሳክልኝን ሁለቱ የጉዞ ማስታወሻዎችህ ድንቅ ናቸው:: ለሁለት ዓመት ቤልጂየም ብኖርም ካንተ ጽሁፍ ግን ብዙ ነገር አውቄበታለሁ:: ያሳለፉትን የቅኝ አገዛዝ ታሪካቸውን ትቼ የቤልጂየም ሕዝቡን ግን እወደዋለሁ:: ባንድ የአድዋ ድል መታሰቢያ በዐል ላይ ባደረኩት ንግግር የቤልጂየም ንጉሥ ሌዎፖልድ ሁለተኛ በኮንጎ ለነበረው የሱ መልክተኛ በላከው ደብዳቤ ላይ ያስተላለፈውን አዋጅ ይዘትን ጠቅሼ የቅኝ ገዥዎች እኩይ ዓላማ ምን ያህል አስከፊ እንደነበር በመልእክቴ ገልጬ ነበር:: በአንፃሩ የኢትዮጵያ ቀደምት ጀግኖች አባቶቻችን እንዴት የአውሮፓ ወራሪዎችን አሳፍረው እንደመለሱና*

ለእንደዚህ ዓይነት ግፍ እንደታደጉን እንደማሳያ ተጠቅሜበታለሁ። መልእክተኛው ደብዳቤውን መጽሀፍ ቅዱሱ ውስጥ ረስቶት ኖሮ ለብዙ ጊዜ በኋላ ያገለገሉ ዕቃዎች መሸጫ ገበያ ውስጥ አንድ የኮንጎ ዜጋ  አግኝቶት ነው። ስለ ደብዳቤው ይዘት ምንነት የምታገኙበት በይነ መረብ አድራሻ የሚከተለው ነው፤The Wickedness of King Leopold II Revealed By His Letter To The Missionaries / The African Exponent.

መስፍን ገናናው (ዶ/ር) ከሂውስተን ቴክሳስ፣ አሜሪካ

## ፪ ሻንዛ ሲዜ -ፓሪስ

ፓሪስን በጸሐፊዎቿ ትረካ ተመስጬ ለማየት ብዙ ጊዜ ባጅቼአለሁ:: እውነትም የምትጎበኝ ድንቅ የኪነ-ሕንፃ ጥበብ የፈሰሰባት ውብ ከተማ ናት:: ብዙ መቶ ዓመታት ያስቆጠሩ ሕንፃዎቿና በዓለም የምትታወቅበት ኢፍል ታወር (ሐውልት) እና የራሷ አርክቴክቶች የሰሯቸው አንድ የሚመስሉ በረድፍ በያቅጣጫው የተሰደሩ ውብ ቅርጽ ያላቸው ብዙ ሕንፃዎች፣ ቤተክርስቲያናት፣ ሙዚየሞች፣ ቤተ-መንግስቶች፣ ጎዳናዎች እጅግ የሚደነቁ ናቸው::

ከጐዳናዎቹ ውስጥ ታዲያ ይኸ ርዕሱን የሰየምኩላችሁ ሻንዛ ሲዜ ጎዳና (champs-elsee) ዋናው ነው:: ይህ ጐዳና በኰብል ድንጋይ የተሰራ ሰፊ የመኪና መንገድና ዳርና ዳሩ ከዋናው መንገድ የሚሰፋ በውብ ግራናይት ድንጋይ የተነጠፈ የእግረኛ መንገድ አለው:: መንገድ ዳሩ በጣም በሚያማምሩ በዕቃዎቻቸው ዋጋ ውድነት የሚታወቁ ሱቆች፣ ምግብ ቤቶች፣ ካፌዎች፣ መሥሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም ብዙ ጐብኚዎችና ደራሲ ጋሽ ስብሀት እንደሚለው ሥጋ የለበሱ አበቦች ጭምር ይታያሉ::

ይህን ረጅም ጐዳና እ.አ.አ. በ1789 ዓ.ም. ከተሰራው ሐውልት ጀምረው ወደ ቤተ መንግስቱ መጓዝ እጅግ ትዝታ የሚተው ገጠመኝ

ነው፡፡ ከዚህ አደባባይ የከተማ መጐብኛ ባለፎቅ አቶቡስ የቀን ሙሉ ወይም የ2 ሰዓት ቲኬት ቦታው ላይ ቆርጠው ከተማውን በሰፊው መጐብኘት ይቻላል፡፡ የቀን ሙሉ ቲኬት በ20 ዩሮ ከገዙ እየወረዱና እየወጡ የሚጎበኙ ቦታዎችን ማየትና ሌላ ያንኑ መሳይ አውቶቡስ ሲያዩ መሳፈር ይችላሉ፡፡ እንደዚሁም የሚበላና የሚጠጣ ወርደው ገዝተው እየቀማመሱ የጆሮ መስሚያ ሰክተው የሚፈልጉትን ቋንቋ መርጠው ስለእያንዳንዱ የሚጎበኝ ስፍራ ገለጻ እየሰሙ መጓዝ ነው፡፡

ከቸኰሉም ባለ ሁለት ሰዓቱን ቲኬት በ17 ዩሮ ገዝተው ከመኪናው ሳይወርዱ በሁለት ሰዓት ከተነሱበት ቦታ ዞረው እስኪመለሱ ድረስ ሁሉንም ማየት ይቻላል፡፡ በግልዎ መጎብኘት ከፈለጉ የመንገድ ሥያሜውን ካነበቡ የፈለጉበት ቦታ ያደርሳል፡፡ ለዚህም ከሆቴል፣ ከአቶቡስ መቆሚያ፣ ባቡር ጣቢያ በቂ መረጃ የሚሠጡ ካርታዎች ይገኛሉ፡፡ ከሚጐበኙ ቦታዎች ውስጥ ዓመታት ያስቆጠረው ቤተ መንግስት ወርቅ የፈሰሰበት የሥነ-ሕንፃ ጥበብ ዛሬ ላይ ሆነን ስንመለከተው ዳግም መሰራቱ ያጠራጥረናል፡፡ ይህን የምለው ለሙያው መጨነቅና የአእምሮ ጭማቂያቸውንና የጥበቡን ዋጋ የሚረዳ እና መሬት ላይ ለማውረድ የሚኖራቸው እድል ስለሚያጠራጥረኝ ብቻ ሳይሆን ለሙያውም መታመን አንዱ ነው፡፡

ከሶስት አሥርተ ዓመታት በፊት ያነበብኩት ልብወለድ መሣይ መጽሐፍ ''The fountain head'' በታዋቂዋ የነባራዊ ፍልስፍና

(objectiivism) አራማጅ ፀሐፊ ኤይን ራንድ (Ayn Rand) የሙያውን ፍልስፍና በእጅጉ ጠልቄ እንድረዳና እንዳከብረው ረድቶኛል፡፡ አሁን የማየውን ጥበብ ከዚያ ዓለምን ለብቻው እንደሚዋጋው ገፀ-ባህሪ ሃዋርድ ሮርክ ጋር እያነፃፀርኩ በሃሳብ ወደኋላ ተጓዝኩ፡፡ ያ! ያመነበትን የሥነ ሕንፃ ሓሳብ የሚሰራ በተጽእኖ ወይም ለሚያገኘው ገንዘብ ሳይሣሣ በራሱ  ትክክል የመሰለውን ለመሥራት የሚታገል ነው፡፡ ሓሳቡን ባይቀበሉትም እንኳ እስከ መጨረሻው ድረስ የሚሟገት ነው፡፡ ይህ ጥረቱ ካልተሳካም የማያምንበትን ሰርቶ ገንዘብ ከማግኘት ረሀቡን የሚመርጥ ነው፡፡  ለእምነቱ የሚቆም ይህን ቆራጥ አርኪቴክትን ሳስብ እስከዛሬ ብዙዎችን የሚሞግት የፍልስፍና ዘርፍ  ትቶ ያለፈ ይመስለኛል፡፡

ፀሐፊዋም ብትሆን ያመነችበትን በነፃነት መፃፍ የምትችልበትን ቦታ መርጣ ከሀገሯ  ከኮሚኒስት ራሺያ ተሰዳ እድሜዋን በአሜሪካ ያሣለፈች ፈላስፋ ነች፡፡ እውነትም ያመነችበትን እየፃፈችና ሀሳቧን የሚያራምድ በርካታ መጻሕፍትን ትታልን አልፋለች፡፡ በዚህ ሥራዋ ብዙ ተከታዮች እንዳፈራች መጻህፍቷ እስከ ዛሬ  ደጋግመው መታተማቸው ለዚህ ምስክር ናቸው፡፡

በቅርቡ ያነበብኩት የአሜሪካ ማዕከላዊ ባንክ ገዢ የነበሩትና የቅርብ ጓደኛዋና በኒዮርክ መኖሪያዋ ጐረቤቷ አለን ግሪንስፓን (Allan Greenspan) የሰጡት ምስክርነት አንዱ ነው፡፡  በግል ታሪካቸው መጽሀፍ (The Turbulent Age) ውስጥ እንደጠቀሱት በብዙ

አጋጣሚዎች ወይም በቋሚነት እየተገናኙ የሚያደርጉት ሓሳብን በሓሳብ የማሸነፍ ፍልስፍና ነክ ክርክራቸው አንዱ ነው። ከዚህ ክርክራቸው የሚወጡ ጽሑፎችና እሳቸው በጽሑፍ የሚሰጡዋትን የመነሻ ሓሳቦች ወደ መጽሐፍ እየቀየረቻቸው ብዙ እምነቷን እንዳጋራችን መስክረዋል። ነገርን ነገር እያነሣው ብዙ አልኩ እንጂ ፈረንሣይም እንዲሁ እነ ቮልቴርን፣ ቪክቶር ሁጐን የመሳሰሉ ፈላስፎችና ፀሐፊዎች አሉዋት። በጉብኝታችን ወቅት የሁጎ ስም ደጋግሞ ሲነሣ ሰምቻለሁ። እንዲያውም ከተሰሩት ሕንፃዎች ውስጥ አንዱ ኖተር ዳም ላይ ተነስቶ መጽሐፍ መጻፉን ተገልጾልናል።

ከዚህ በተጨማሪ በፈረንሣይ እ.ኤ.አ.1789 በተነሳው አብዮት ወቅት ስለደረሰው እልቂት መታሰቢያ ሆኖ የፃፈው ሌ ሚዜረብል /Les Miserable/ “ምንዱባን” ተብሎ በሀገራችን ደራሲ የተተረጐመው እንዲሁ ተደጋግሞ ተነስቶአል። በዚያ ወቅት በአደባባይ በሰይፍ አንገታቸውን እየተቀሉ ለተጨፈጨፉት መታሰቢያ አደባባይ ተሰይሞላቸዋል።

በነገራችን ላይ ፈረንሣይን በየዓመቱ 42 ሚሊዮን ቱሪስቶች የሚጎበኞት ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 20 ሚሊዮን ፓሪስን እንደሚጉበኙ ተገልፆልናል። ይህን ለማሳለጥ የመጓጓዣው መንገድ፣ የአስጐብኚዎች ዝግጅት፣ ጥበቃው ሁሉም ከዚህ ጢስ አልባ ኢንዱስትሪ የሚገኘውን ገቢ የትየለሌ ያደርገዋል። ፓሪስን ሲጉበኙ ዋና የቱሪስቶች መዳረሻ ባለ 328 ሜትር ርዝመት ያለው ኤፍል ታወር ( Eiffel Tower)

አንዱ ነው፡፡ የተሰራው በእ.ኤ.አ.1889 ዓ.ም. በአንድ ጉስታቭ ኤፍል በተባለ መሀንዲስ ሲሆን፣ በወቅቱ ብዙ እምነት ያልተጣለበትና የእብደት ሥራ ተደርጐ ተቆጥሮ ነበር፡፡ ይህ መላ አካሉን ከብረት ያደረገው ማማ በቀን ብዙ ሺህ ቱሪስቶች ይጐበኙታል፡፡



ይህ ሀውልት ዋና የፓሪስ መታወቂያ ምልክት ሆኗታል፡፡ እብድ የተባለው ሰው ለፈረንሣይ በየቀኑ የሚታለብ ጥገት ላም ፓሪስ መሀል ላይ አስሮላት እንዳለፈ ማንም በቦታው የተገኘ ጐብኚ የሚመሰክረው እውነት ነው፡፡ በየቀኑ በአራት ማዕዘን ብዙ ቱሪስቶች

ለመጎብኘት በረጅሙ እየተሰለፉ የ11 ዩሮ ቲኬት ቆርጠው እስከ ወገቡ ሁለተኛ ፎቅ ድረስ በተሽካሚ ጋሪ ይወጣሉ ወይም 674 ደረጃዎችን በእግር መውጣት ይችላሉ። ከዚያ ወደታች ፓሪስን ተዘዋውረው ፎቶ እያነሱ ይቆያሉ። ከሁለተኛ ፎቅ በኋላ ደረጃው ለእግረኛ ዝግ ስለሆነ ለቀጣዩ ጉዞ ሊፍት ደጃፍ ሌላ ሂሣብ ከፍለው ተሰልፈው ወደ ላይ ይጓዛሉ። በአጠቃላይ እስከ መጨረሻው ጫፍ ድረስ 1665 ደረጃዎች አሉት። ፓሪስን በውሀ ላይም ይጎበኟታል። ከተማዋን እንደ መቀነት የሚዞራት ሴን (Sein) የተባለ ረጅም ወንዝ ላይ የተኮለኮሉ ረጃጅም መርከቦች ላይ ተሳፍረው ለሁለት ሰዓት እየወረዱና እየወጡ መጐብኘት ይችላሉ። እኔና ባለቤቴ በእለቱ ተረኛ በሆነው ወገናችን በካፒቴን ዳዊት ግብዣ እስከ ማምሻው ድረስ ተዘዋውረን ጐብኝተናል።

የፓሪስ የምድር ውስጥ ባቡርም እንዲሁ የፈለጉት ቦታ ድረስ በቀላሉ ያደርሶታል። ቢፈልጉ የቀን ሙሉ ትኬት ገዝተው በምድር ውስጥ ወይም ወደ መሬት ላይ ብቅ እያሉ በዛው ቲኬት በአውቶቡስ መንቀሳቀስም ይችላሉ። ባቡሩ ውስጥ ከኪስ ቀበኞች እንዲጠነቀቁ ግልጽ ማስታወቂያዎች ይነገራሉ፣ ፖስተሮችም ተለጥፈዋል። ታዲያ ገንዘብዎን ጠንቅቀው መጠበቅ ይኖርቦታል። በዚህ የምድር ውስጥ ባቡር /ሜትሮ/ ጉብኝታችንን ለመጀመር ካረፍንበት ሆቴል ማልደን ተነስተን መጥተን ቲኬት ከማሽኑ ላይ ቆርጠን ወደ

ምድር ባቡር መሳፈሪያው ውስጥ ገባን፡፡ የምንፈልገውን ቲኬት ከካርታው ላይ አንብበን ጥበቃ ቆምን፡፡ እንደተፃፈው በየስድስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ የምትመጣው ባቡር ከተፍ አለች፡፡ ከአፍ እስከ ገደፏ በሰው ጢም ብላ ሞልታለች፡፡ እናሣልፋት አልንና መጠበቂያ ወንበሩ ላይ ቁጭ አልን፡፡ ሆኖም እንዳመጣጧ ባቡሯ አልንቀሣቀስ አለች፡፡ ምን ነካት እያልን ስንጠያየቅ በመሀል በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሆነ ነገር ተነገረ፡፡ ቀስ በቀስ አንዳንድ ሰው ወረደ፡፡ አሁንም አልሄድ አለች ቢቸግረን አጠገባችን የተቀመጠች አንዷን ጉብል ጠየቅናት፡፡ በተሰባበረ እንግሊዝኛ መንገዱ መዘጋቱን ገልጻልን በዚህ መስመር ላይ ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጥም ነግራን ኑ ተከተሉኝ አውቶቡስ መሣፈሪያውን አሳያችኋለሁ አለችንና ተከትለናት ወጣን፡፡ ይህ የቋንቋ ነገር እንዴት እንደሆነ እያወራን ያሰብንበት ደረስን፡፡ ፓሪስ እንደዚያ የቱሪስት ሀገር ሆና እንግሊዝኛ ለማውራት ምነዋ ፈረንሣዮች ብዙም አይዳዳቸውም ብለን ተገረምን፡፡

ፈረንሣይ በቀደምት ታሪኳ 26 ሀገሮችን በቅኝ ግዛትነት ይዛ እንዳስተዳደረች ይታወቃል፡፡ በነዚህ ጊዜያት ለየአገሮቹ መሠረተ ልማት እንደ መንገድ፣ ትምህርት፣ ጤና እንደሠራች ይታወቃል፡፡ ሆኖም በዚያው ልክ የየሀገሩን ሀብት ለፓሪስ ግንባታ እንዳዋለች ይታመናል፡፡ ከነዚህ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ የሚመጡ ሰዎች ለመብታቸው ከሚያነሱት ክርክር እንደሚደመጠው ለምሣሌ

የተገነባው የምድር ውስጥ ባቡር የአያቶቻቸው ደምና ላብ እንዳለበት መናገራቸው ከብዙ በጥቂቱ ማሳያ ይሆናል።

በፓሪስ ውስጥ የኢትዮጵያን ባህላዊ ምግቧን የሚያስታውስ አብዛኛው ነጮች የሚያዘወትሩትን ደ ክሊቼ ጎዳና ላይ የሚገኘውን የደጉን የአቶ ሰለሞንን ምኒሊክ ሬስቶራንትን መጐብኘት ለእንጀራ ናፍቆቶ ማስታገሻ ይበጅዎታል። ምኒልክ ሬስቶራንት እንደ ትንሽ ሙዚየምም ይቃጣታል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሳ ቅርሶችና ፎቶዎች ግድግዳውን ሞልተውታል። በዚህ አጋጣሚ ብዙ የውጪ ዜጎች  አገራችንን ይተዋወቁበታል።

የፍቅር ከተማ የሆነችው ፓሪስን ለመጐብኘት የሲጋራውን ጭስ፣ የሆቴሉን ዋጋና የመንገድ ላይ ፍቅሩን መቻል ይጠይቃል። በፍቅር ጉዳይ እፍረት ሲያልፍም አይነካቸውም። ለእንደኛ በዓይነ አፋርነት ለአደገ ሀበሻ ለመቀበል ትንሽ ያስቸግራል። እንደዚያ መፈጠርን ለነሱ ትተን ለምን ስለፍቅር ማጀቢያ ወይን ጠጃቸው አናወራም። ፈረንሣይ ከምትታወቅበት አንዱ የወይን ጠጅ ምርቷ ነው። ከዓለም ጥሩ ወይን ጠጅ ጠማቂዎች ውስጥ በግንባር ቀደምነት የምትጠቀስ ሲሆን፣ የፓሪስ ሻምፓኝ፣ ሽቶና ፋሽንም ሌላው መታወቂያዋ ነው።

የፓሪስ ከተማ ፕላን ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተሰራ ቢሆንም ከሥር መሠረቱ አንድ ዓይነት መስፈርት standard ያላቸው ለምሣሌ በቁመት፣ በቀለም፣ ጐን ለጐን የተያያዙ ሕንፃዎች መሆኑ ለውበቱ

ተጨማሪ ድምቀት ሰጥቶታል፡፡ ይህ ሁሉ ዘመን የተጠበቀው የሕንፃ ሕግ /Building code/ ለተፈፃሚነቱ ሁሉም ተገዢ በመሆኑ ነው፡፡ ይህቺን የምታምር ከተማ ሂትለር ሳይቀር ሣስቶላት በጦርነት እንዳትፈርስ ብዙ ጊዜ ባህርይው ባልሆነው በምህረት እጁ ዳሶ አልፎአታል፡፡ የወቅቱም መሪዎቿም ብልሆች ነበሩና ቀድመው ተደራድረውት ከተማዋን በሰላም ለቀውለት እንደወጡ በአፈ ታሪክ ይነገራል፡፡ ውቧ ፓሪስ!

መስከረም14 ቀን 2008 ዓ.ም.ከብራስልስ አዲስ አበባ ጉዞ ላይ ተጻፈ፡፡

---

*Nice memoir...by the way there is an account that Paris was saved by a Nazi General named von Choltitz, who was acting as the city's new military governor. Hitler had given order to the General to destroy the city using explosives.....As ordered, the General placed explosives at key locations such as bridges, major buildings and historic landmarks. However, Von Choltitz continuously disobeyed Hitler's orders to detonate the bombs...*

*Dagnachew Asnake*

*ጥሩ ማስታወሻ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ስለ ፓሪስ በናዚ ቦንብ ከመፍረስ መዳን አጠቃስከው ታሪክ ሌላ የሚነገር እሳቤ አለ፡፡*

*በወቅቱ ሂትለር ለፓሪስ ከተማ አዲስ ጊዜያዊ ወታደራዊ ገዥ አድርጎ ለሾመው ጄኔራል ቮን ሾሊዝ ከተማዋን በቦንብ እንዲያጋያት ትዕዛዝ ሰጥቶት ነበር:: የናዚ ጄኔራሉም እንደታዘዘው በዋና ዋና ቁልፍ ቦታዎች ላይ ማለት ድልድዮች ሥር፣ ዋና ዋና ሕንፃዎች እና ታሪካዊ የከተማዋ መለያዎች ላይ ቦንቡን ጠመደ:: ሆኖም ቮን ሾሊዝ ተደጋጋሚ የሂትለርን ቦንቡን የማፈንዳት ትዕዛዛት ሆን ብሎ በዳተኝነት ሳይፈፅም ቀረ::*

*ዳኛቸው አሰናቀ (አዲስ አበባ)*

*You are one of the lucky ones who have the habit of putting thoughts and observations on paper, and your literary style is excellent. I fully agree with your reflections that the aesthetics in the various heritages in Paris (and other European cities) are products of minds and souls such as Howard Roark, a character in Ayn Rand's 'Fountainhead'. Such minds regard their brain children as ends-in-themselves and that is why they transcend centuries.*

*Elias.*

*ሓሳባቸውንና አስተውሎታቸውን በወረቀት ላይ የማስፈር ልማድ ካላቸው ዕድለኞች መካከል አንዱ ነህ፡፡ የሥነ ጽሁፍ ዘይቤህ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡  በፓሪስና ሌሎች አውሮፓ ከተሞች ስለሚገኙት የተለያዩ ቅርሶች ውበት ላይ ባንፀባረቅከው ሓሳብ እኔም እስማማለሁ፡፡ እነዚህ ቅርሶች፣ በኤይን ራንድ "ፋውንቴን ሄድ" ልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ በሆዋርድ ሮርክ ከተወከለው ገፀ-ባህሪ ጋር የሚመሳሰል አዕምሮና ልቦና ያላቸው ሰዎች የሥራ ውጤቶች ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የሥራቸውን ውጤቶች እንደ አዕምሮ ልጆቻቸው የሚያዩ ከመሆናቸው ባሻገር፣ ሥራዎቻቸውን በራሳቸው እንደ መጨረሻ ግባቸው ነው የሚቆጥሯቸው፡፡ ለዚህም ነው ብዙዎቹ ዘመን ተሻጋሪ  የሆኑት ፡፡*

*ኤልያስ*

## ፫ አሜሪካኖች ካለመንገድ!

ይህን ስፊ ሀገር ብተርክ ምን ብዕርና ወረቀት ይበቃኝና እሞክራለሁ! ብቻ ከግርምቴ ውስጥ የመጀመሪያውና በወቅቱ ለአራስዋ ባለቤቴ የጻፍኩላት ደብዳቤ እነዚህ አሜሪካኖች ካለ መንገድ ምን ሠሩ ብዬአት እራሷ ሄዳ እስካረጋገጠችበት ጊዜ ድረስ ትስቅብኝ ነበር፡፡ እነዚያ ኢትዮጵያን የሚያካክሉ 52 ግዛቶቻቸውን የሚያገናኙ አውራ ጐዳናዎች ዲዛይን እጅግ ይደንቃሉ፡፡ አሜሪካ ወስጥ የትም ግዛት በምድር መጓጓዣ መድረስ ይቻላል፡፡ የእድገት መሠረቱ መንገድ ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ የመጀመሪያው ልጄ ሲወለድ እዛ ነበርኩና ከ39 ሀገሮች የደስታ መግለጫ ደርሶኛል (እ.ኤ.አ. 1996 በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ኢንስቲትዩት ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ ከ39 ሀገሮች ከመጡ አብረን ከነበርን ተሳታፊዎች ነው)፡፡

ከሁሉ የሚደንቀው እነዚያ አሜሪካንን የመሠረቱ ብልህና አስተዋይ መሪዎች የጻፉት ሕገ መንግስት ትናንሽ ማሻሻያዎች እየተደረገበት ይኸው ከ200 ዓመታት በላይ ማገልገሉ ምን ያህል አርቆ አሳቢነታቸውን ያሳያል፡፡ እነዚህን ቀደምቶች ሕዝቡም ማክበሩን ያውቅበታል፡፡ በስማቸው ጐዳና፣ ሐውልት፣ ሙዚየም ወዘተ… እየሰየመ ያዘክሯቸዋል፡፡ ይህንና ሌሎች ታሪኮቻቸውን በወጉ ይዘው ዓለም እንዲያውቅላቸው ቤተ መንግስታቸውን ሳይቀር

ያስጉበኛሉ፡፡ በየጊዜው ከሀገር ውስጥና ከውጭ ብዙ ጎብኚዎች ሀገሩን ያጨናንቁታል፡፡

ሀገረ አሜሪካ ብዙ ወገኖቻችን ሰርተው፣ ወልደውና ከብደው ይኖሩባታል፡፡ በተለያየ ወቅት በጎበኘኋት ጊዜ ከብዙ ሰዎች ጋር በተለያየ ጉዳዮች ላይ ሀሳብ ለመለዋወጥ እድል አግኝቻለሁ፡፡ በተለይ ትንሽ የቆዩት ወገኖቼ ሁሌም ሕልማቸው አገራቸው እንደሆነ ተገንዝቤአለሁ፡፡ በአንድ ወቅት አንዱን የተዋወኩት ሰው በወሬአችን መሀል እዚህ ሀገር ከመጣህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ አልኩት ትንሽ ቆየሁ አለኝ፡፡ ምን ያህል ጊዜ ነው ትንሽ ቆየሁ የሚያስብለው አልኩት፡፡ አንድ ሃያ ዓመት ሲያልፍህ አለኝ፡፡ በርግጥ እስከ ግማሽ ክፍለ ዘመን እዛ የቆዩ እንዳሉ በቅርቡ እየሰማን ነው፡፡ በትምህርት፣ በሥራና በኑሮ የሚያስቡት ደረጃ ላይ የደረሱት ወደ ማምሻ ዕድሜአቸው ላይ ያተረፉትን ካጡት ጋር ሲያሰሉት ለእናት አገራቸው ምን ሠራን የሚለው ትልቅ ጥያቄ እንደሚሆንባቸው ተረድቻለሁ፡፡ በዚህም ብዙዎች ባላቸው እውቀትና ገንዘብ ሀገራቸውንና ወገናቸውን ለመርዳት ይተጋሉ፡፡

ሌሎች እንደዚሁ ከኑሮ መስመር የወጡም አጋጥመውኛል፡፡ አሜሪካ የሀገሩን ሕግ አክብረው የርስዎም መብት ተከብሮ የዓለም ሕዝብ ተወካይ የሚኖርበት ትልቅ ሀገር ነው፡፡ ከመስመር አዳልጦት ከወጡ ዜጋ አይልም መጤ ሁሉም አስከፊውን የጎዳና ላይ ኑሮ ይጋፈጣል ፡፡ ለዚህ ዓይነት የኑሮ ፈተና የሚያጋልጡ ብዙ የተመቻቹ

ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሕጋዊ ሆነው ኑሮ ሲጀምሩ የባንክ የዱቤ ካርድ ያገኛሉ፡፡ በተፈጠረው እድል ለኑሮ የሚያስፈልጎትን በማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡ ነገር ግን ከወር ገቢዎ በላይ ከኖሩ ብድርዎን በወቅቱ ካልከፈሉ በቀላሉ ሜዳ ወጥተው ይቀራሉ፡፡ ለእንደዚህ ዐይነት አደጋ የሚያጋልጡ ብዙ አታላይ ነገሮች እንደልብ ይገኛሉ፡፡ ከመጠጥ እስከ አደንዛዥ እፅ ድረስ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአስገዳጅ የሀገር ኢኮኖሚ ቀውስ ልክ እንደ እ.ኤ.አ. 2008 እንደደረሰው ዓይነት ቀውስ ያፈሩት ሀብትና ጥሪትዎን ያሳጣዎትና የመንግስት ተጧሪ ያደርጎታል፡፡ ሆኖም ከበረቱ እንደገና ወደ ቀድሞ ቦታዎ ለመመለስ ይችላሉ፡፡

ወገኖቻችን በአብዛኛው የአሜሪካ ግዛቶች ከአላስካ እስከ ፍሎሪዳ ተሰባጥረው ይኖራሉ፡፡ ሆኖም እንደ ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው የሚበዙበት የለም፡፡ በአንዳንዶች ግምት በቨርጂኒያ፣ ሜሪላንድና ዲሲ ከ 500 ሺ በላይ ወገኖቻችን (መረጃው በወጉ ተደራጅቶ ስለማይገኝ ነው) በአብዛኛው ባህላቸውንና አመጋገባቸውን ሳይተዉ ይኖራሉ፡፡ ታዲያ ከልማድም መጥፎ ልማድ አለና የቀጠሮ አካባበር ልማዳችንም አብሮአቸው ውቅያኖስ ተሻግሯል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ሠርግ ላይ በእንግድነት ተጋብዤ ታድሜ ያየሁት ይህንኑ ያስረዳል፡፡ ሠርጉ ሆቴል ወስጥ ነው፡፡ ጥሪው ከምሽቱ 12 ሰዓት ድረሱ ይላል- እኛም በሰዐቱ ደርሰናል፤ ሆኖም አብዛኛው ተጋባዥና ሠርገኞቹ የደረሱት ሶስት ሰዓት አካባቢ ነው፡፡ ሠርጉን ጨርሰን የወጣነው

እኩለ ሌሊት አልፎ ነው፡፡ አብሮኝ ያለው ወዳጄ እንደነገረኝ በዚህ ሰዐት ያለማክበር ልማዳችን ብዙ ሆቴሎች ለሀበሻ ሥርግ አዳራሽ ለማከራየት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ አንደኛ በጊዜ አይገቡም፣ ሁለተኛ ዘግይተው ይወጣሉ፤ በተጨማሪ የወጡ ቅመም ሽታ በየመጋረጃው ላይ ይቀርና ለማስለቀቅ ያስቸግራል ይላሉ::

ምግባችንን ብዙ የውጭ ሀገር ሰዎች በጣም ይወዱታል፡፡ በአንድ ወቅት አንድ ፈረንጅ ከኢትዮጵያዊ ጓደኛው ጋር አንዱ የአበሻ ሬስቶራንት ገብቶ ከበላ በኂላ እናንተ ኢትዮጵያውያን ለምን እንደማትወፍሩ አሁን ገባኝ አለ፡፡ እንጀራው ከስንዴ ስለሚሠራ ትንሽ ሲበሉ ሆድ ይወጥራል፤ ብዙ ሳይበሉ ይጠግባሉና፡፡

የቀጠሮ ነገር ሲነሳ ድሮ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለደን ልማት እገዛ የስዊድን ዜጎች በእርዳታ ከገንዘቡ ጋር አብረው ይመጡና ሥራና ኑሮውን ይላመዱና እንደኛ ይሆኑ ነበር:: በዚያን ጊዜ ከመጡት የስዊድን ዜጎች አንዱ እዚያ ደን መሥሪያ ቤት ከሚሠራ ታሪኩ ተሰማ ከሚባል ዘመዴ ጋር ወዳጅ ሆነው ጥሬ ስጋውንም ቀጠሮ ማርፈድንም አስለምዶት ነበር:: በአንድ ወቅት ቅዳሜ ከሥራ በኂላ ለመዝናናት ካዛንችስ ሲገናኙ መጀመሪያ ላይ ከአገሩ ሰዎች ጋር በ9፡00 ሰዓት ቀጠሮ እንዳለበትና ብዙ እንደማይቆይ ነግሮት ምግቡንም መጠጡንም ይጀምራሉ፡፡ ከዚያ ሰዓቱ ሲቃረብ ሃሳብ የገባው ዘመዴ ሊያስታውሰው ሞከረ፡፡ ይደርሳል ትንሽ እንጨምርበት እያለ ከመጠጡ ይደጋግማል ፡፡ በመጨረሻ ብሎ ብሎ ሰዓቱ አለፈ፡፡

እህሳ ሲለው እደርሳለሁ ተወው የአገሬ ሰዎች ኢትዮጵያ እንዳለሁ ያውቃሉ ብሎት እርፍ አለ።

በአብዛኛው የውጭ ሀገር ኑሮ ከሚያስተምረው አንዱ የሥራ ዲስፒሊን በተለይ ተቀጥረው ለሚሠሩበት መሥሪያ ቤት በሰዓት መግባቱን አያዛንፉም። በሚጮህ አላርም ሰዓት እየተረዱ ሌሊት ሆነ ቀን በተባለው ሰዓት ሥራ ላይ መገኘት በእጅጉ ያስተዋልኩት ተግባራቸው ነው። አርጩሜው ገንዘብ ከመሆኑ ባሻገር ሥራ መቅጠርም ሆነ ማሰናበት (Hire and Fire ይሉታል) ቀላል እንደሆነ ስለሚረዱት ነው ። አሜሪካ እንደኔ በእንግድነት ሲያዩት እንጂ ሲኖርበት ጣር አለው!

ሌላው እዚያ ሀገር የተወለዱ ልጆች አገሩ የሚሰጠውን የልጅነት መብት አላግባብ ሲጠቀሙበት ያስተዋልኩት ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ አይቦዙንም። ከትምህርት ቤት በኋላ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንዲያደርጉ ለልጆቻቸው በተለይ እናቶች ሲደክሙ አስተውያለሁ። የጥናት ቦታ ከማድረስ ውጭ ስፖርት መስሪያና መጫወቻ ቦታዎች እንዲሁም ልጆች የሰጡአቸውን ሌሎች ፕሮግራሞች ባላቸው ጊዜ ሁሉ ሲተገብሩ አይቻለሁ። ከዚህ ሁሉ ልጅ የማሳደግ ድካም በኋላ አንዳንዶች 18 ዓመት ሲሞላቸው ከቤት ወይም ከመስመር ይወጡና ወላጆቻቸውን ሲያዝኑም ታዝቤአለሁ። እንደ አገሩ ባህል ያድጉና ገንዘባቸውን ወይም የግል ነፃነታቸውን ይወዳሉና የወላጆች ውለታ ሳይከፈል

የሚቀርበትም አጋጣሚ ብዙ ነው - ትልቅ ዋጋ ያለውን ፍቅር በመንሣት፡፡ ብቻ ወላጆች በሀገር ቤቱ ወይም በዛው ሀገር ባህል ለማሳደግ ሲቸገሩ አያለሁ፡፡ ልጅም የሁለት ሀገር ባህልና ወግ ተደባልቆበት ያድጋል፡፡ በአንፃሩ ብዙዎች አገሩ የሰጠውን መልካም ዕድል በአግባቡ በመጠቀም የወላጆቻቸውንና የኢትዮጵያን ስም በበጎ የሚያስጠሩ ይሆናሉ፡፡

ከተሞቻቸውም እንደ የባህሪያቸው ተጨማሪ ስም ተለጥፎላቸው ይጠራሉ፡፡ በተለያየ ጊዜ ከጎበኘኋቸው 14 ግዛቶቻቸውና ታሪካቸውን ከሰማኋቸው ለምሳሌ ኒዮርክ የማታንቀላፋ (City that never sleeps) ይሏታል፡፡ በርግጥ ኒዮርክ ቀንም ሆነ ማታ እርሶን የሚይዞት ትዕይንት እንደልብ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ምሽት ላይ አብሬ ከነበርኩት የክፍል ጓዶቼ ጋር ከሆቴሉ ስለከተማው የምሽት ክንዋኔዎች የሚገልፅ በራሪ ወረቀት አንብበን ሊሞዚን ታክሲ ጠርተን ከተማውን ጎብኝተን ቲያትር ገብተን ወደ ስድስት ሰዐት ላይ ወደ ሆቴል ስንመለስ ከተማው ገና እየነጋለት ነበር፡፡

ኒዮርክ በጣም ቱሪስት የሚጎበኛት የፎቅ ጫካ የከበባት ከተማ ስትሆን በየቀኑ ከ9 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ከተማው ውስጥ ይገባል ይወጣል፡፡ ኑሮውም በዚያው ልክ እጅግ ውድ ከሚባሉት የአሜሪካ ከተሞች ከነ ሳን ፍራንሲስኮ እና ቺካጎ ጋር የምትመደብ ነች፡፡ በተለይ የመሬትና የቤት ዋጋ እንዲሁም የቤት ኪራይ ውድ ናቸው፡፡ የፎቅ ነገር ሲነሳ በእ.ኤ.አ. ሴፕተምበር 2001 (ናይን ኢለቨን 9/11 እያሉ

የሚጠሩት) በአሸባሪዎች የወደሙትን መንትያ ባለ 102 ፎቅ የንግድ ማዕከል ሕንፃዎች በቁማቸውና ትቢያ ሆነውም አይቻቼዋለሁ:: አሁን ለማስታወሻ ተብሎ ባዶ ቦታው (Ground Zero) በአጥር ተከልሎ ይጎበኛል:: ታዲያ በምትኩ 7 በጣም ረጃጅም ውብ ፎቆች ዙሪያውን ተሰርቷል:: ያለው ማማሩ!!

ፍሎሪዳ የፀሀይ ሀገር (Sunshine state) ይሏታል:: ትልቅ የውሀ ዳር መዝናኛ (Beach) ያላትና ነጭ ገላቸውን በፀሀይ ለማጥቆር ሲንከባለሉ የሚውሉበት ከመሆኑም በላይ የዲዚኒ ወርልድ መጫወቻ ዋና ማዕከሉ እዛ ነው የሚገኘው:: ሲያትል ዝናቧ (Rainy city) የሚሏት ይህቺ ከተማ በአሣ አስጋሪዎች ለገበያነት እንደተመሠረተች የሚነገርላት ሲሆን[1] ከዓመቱ ውስጥ ዘጠኙን ወራት ዝናብ ሲያጠምቃት ነው የሚከርመው:: አትላንታ የኮክ ምድር (Peach state) ይሏታል:: የአትላንታን ስፋት ከአየር ላይ ሆነው ሲመለከቱት ይረዱታል:: ታዲያ የሚመለከቱት አብዛኛው ጥቅጥቅ ያለ ደን ነው:: እሱን አይተው ያ የሀገሬ ዘፋኝ የደንሸ ማማሩ ያለው ዘፈን ቀልድ ሆኖ ነው የሚሰማዎ:: ሚኖሶታ የመንትዮቹ ከተማ (twin cities) ሚኒያፖሊስና ሴን ፓል ማለታቸው ነው:: ባለ አስር ሺ ሀይቅ ግዛት ነች:: እንግዲህ ልቁጠር ካሉ ኩሬውንም እንዳይረሱ::

ቺካጎ ነፋሻማ (Windy city) ቢሉትም አይበዛበትም:: ጆሮ የሚጠብስ ንፋስና ቅዝቃዜ እውነት እዚያ ነው ያለው:: የብርዱ ዓይነት እዚህ

ሀገር አምሳያም የለው። ያለ ስሙ ስም ሰጡት አይባልም። ቺካጎ በዓለም ትልቁ የሚባል 110 ፎቅ አለው በኋላ የዱባዩ ቡርጂ ከሊፋ መጥቶ እስከተገዳደረው ድረስ። ይህ በአንድ ፓኪስታናዊ አርክቴክት የተሠራው ሲርስ ታወር ቲኬት ቆርጠው እስከ 102ኛው ፎቅ ድረስ በ26 ሰከንድ ሙዚቃ እያዳመጡና ፊልም እያዩ  ይወጣሉ። ከላይ ሆነው ዙሪያውን ፎቶ እያነሱ መጎብኘት ይችላሉ።

በየከተሞቹ እንደሚገኘው የእንስሳት ፓርክ እዚህ ቺካጎ ውስጥም በጣም ትልቅ ፓርክ አለ - ታዲያ አንዳንዱ የዱር እንስሳ የኛን ባለ ጠቃጠቆ ጅብን ጨምሮ ከየሀገሩ የሰበሰቡት ነው። ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል አይደል ተረቱ! እሱ ብቻ አይደለም ዶልፊኖች የሚያሳዩት የውሀ ላይ ድንቅ ትርዒትም አንዱ መዝናኛ ነው። እዚህ ላይ ሁለተኛው ልጄ ይዲድያ የ2ኛ ክፍል ተማሪ ሳለ የክፍል ጓደኛው የነገረውና ተገርሞ ቤት ገብቶ የነገረን ታሪክ ትዝ አለኝ። ጓደኛው "እኛ ቤት የውኃ መዋኛና ሻርክ አለን። ማታ ማታ አባቴ ሻርኩን ያስረዋል" ያለውን ዴንቨር ኮሎራዶ ሄዶ ግዙፉን ሻርክ አኳሪየሙ ውስጥ ሲያየው ምን ያህል እንዳቄለው ነው የተረዳው። እርሱም በተራው ብልጥ ሆኖ ለሽርሽር አዲስ አበባ አንበሣ ግቢ የወሰዱትን ጎረቤቶቻችንን ያላቸው ነገር የሚደንቅ ነው። ሲጎበኙ ሳለ ድንገት ፊለፊት ያለው አንበሣ ደጋግሞ አጓራ ይህን ጊዜ ፈራሁ እንዳይል "ጋሼ እንሂድ አንበሣው ጉሮሮውን እንዳያመው" አለው።

የመዝናኛና የሚጎበኙ ቦታዎች ነገር ከተነሳ በብዙ የአሜሪካ ግዛቶች ሙዚየሞች፣ የዱር እንስሳት፣ የዕጽዋትና የውኃ ፓርኮች ይገኛሉ።

የሕዋ ሙዚየሞች (Air & Space Museum) ከጥንት እስከ ዛሬ የፈጠሯቸውን የሳይንስ ግኝቶቻቸውን ለወጣቱም ሆነ ለአዛውንቱ ያስጎበኙታል። መግቢያ ቲኬት የቀን ሙሉ ጥቅል (package) ገዝተው ከተማ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ መዝናኛ ቦታዎችን መጎብኘት ይችላሉ። ታዲያ ለአዛውንቶችና በውትድርና ላገለገሉ (Senior Citizens ይሏቸዋል) ቅናሽ አለው።

ላስ ቬጋስ የኃጢአት ከተማ (Sin city) ይሏታል። ሌሎችም ብዙ አሉ። ትንሽ ስለ ላስ ቬጋስ ብንጨምርበት። ይህቺ በኒቫዳ በረሃ ላይ የተመሰረተች ከተማ መተዳደሪያዋ አገልግሎት በማቅረብ ነው። ከነዚህም አንዱ ተጠቃሽ የምትታወቅበት የካዚኖ ቁማር ነው። ትላልቅ ሆቴሎች በብዛት አሉ። አንዳንዶቹ አስከ ሰባት ሺ መኝታ ክፍሎች አላቸው። ከዓለም ማዕዘን ገንዘቡን በቁማር ለማጥፋት በየቀኑ ብዙ እንግዳ ይጎርፋል። በዓመት ወደ 40 ሚሊዮን የሚጠጋ ቱሪስት ላስ ቬጋስን እንደሚጎበኛት ይገመታል- ገንዘቡን ለማስላስ።

ለቱሪስቶች ሁኔታውን ቀላልና የተመቻቸ ለማድረግ በሌሎች ከተሞች የሚተገበሩ ሕጎች እዚህ ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ተደርገዋል። ለምሳሌ መኪና ሲነዱ ቀበቶ ማሰር አይገደዱም። መጠጥ በየመንገድ ላይ መጠጣትና ወሲብ ንግድ ይፈቀዳል። እንደዚሁም የኢኮኖሚ መሰረቷን ሌሎች እንዳይሻሟት የሕግ ከለላ አላት። በሌሎች ከተሞች ካዚኖ ማቋቋምና ቬጋስ ውስጥ ሎተሪ መሸጥ ክልክል ነው። ሎተሪ

ከፈለጉም 40 ደቂቃ ነድተው ከከተማ ወጥተው ጉረቤት አሪዞና ግዛት ገብተው መግዛት ይችላሉ፡፡

ያ ቀን ሲያዛጋ የሚውለው  ከተማ ማታ በመብራት ተንቆጥቁጦ የሰውን ገንዘብ ለማጫረስ ቆሞ ያድራል፡፡ አንደኛው ሆቴል ቤት ገብተው ካዚኖ መጫወት ከጀመሩ እንክብካቤ አይጎድልቦትም፡፡ መጠጥ ከማቅረብ ጀምሮ አያያዞ ታይቶ አልጋም በነፃ ይቀርብሎታል፡፡ ላስ ቬጋስን አይተው ሀገርም እንደ ሰው ዕድል አለው ወይ ብለው ያስባሉ፡፡ እዚህ ኢትዮጵያ ቢሆን ኖሮ በረሀ ተብሎ ጠፍ ይለቀቅ የነበረ መሬት እዛ ገንዘብ የሚታተምበት ማዕድን ነው፡፡ እንደ የከተሞቹ ባህሪ የሚስማማ የኢኮኖሚ ፓሊሲ አውጪዎቻቸውም አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል፡፡

በአገሪቱ ከፍተኛ እስረኛ ይገኛል፡፡ የወንጀሉ ምንጭ ቢለያይም በአብዛኛው እጽ ማዘዋወር ተራ ዘረፋና የግድያ ወንጀልን ያካትታል፡፡ መንገድ ላይ በመኪና ጡሩንባ ነፋህብኝ በማለት ወይም ቅድሚያ ባለመስጠት ምክንያት ሁለት የማይተዋወቁ ሰዎች ከሱቅ እንደልብ የሚገዛውን የጦር መሣሪያ ሊማዘዙ ይችላሉ፡፡ እንደዚሁም ምንም ይህ ነው የሚባል ምክንያት ሳይኖራቸው ት/ቤት ገብተው ወይም ከመሀከላቸው አንዱ ይነሳና የሕፃናት ተማሪዎችንና መምህራኖቻቸውን ሕይወት በከንቱ ይቀጥፋል፡፡

የእስር ቤቶች አይነት በፌደራል፣ በግዛቶች፣ ወጣት ጥፋተኞች ማረሚያ ፣ የአካባቢ፣ የስደተኞች ማቆያ እና የሕንድ ዝርያዎች ተብሎ

ተከፋፍሎ ዛሬ ላይ ቁጥሩ ከሰባት ሺ በላይ ይደርሳል፡፡ እንደዚሁም የእስረኞችም ቁጥር 2.3 ሚሊዮን ይጠጋል፡፡ ይህም በዓለም ከታላላቅ የእስረኞች ብዛት ካላቸው ሀገሮች ጋር ያወዳድራታል፡፡ የመሳሪያ ሕግ እንዲወጣ በብዙ የአሜሪካ ፕሬዜንደቶች ተሞክሮ እስከዛሬ ሊሣካ አልቻለም፡፡ እንደዚሁም ብዙ አቅመ ደካማ ዜጎች የሕክምና ኢንሹራንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተሞክሮ በኦባማ ዘመን በከፊል የተሣካ ቢሆንም እሱንም እድል ለመሻር አሁንም ትግሉ እንደ ቀጠለ ነው - ሁለቱም የሀብታሞች የገንዘብ ማምረቻ ስለሆኑ ነው፡፡

አሜሪካ ካየሁት ነገር ውስጥ የህዝቡ በተለይ ጥቁሮች የፖሊስ ፍራቻቸውን ነው፡፡ መንገድ በመኪና ስንሄድ ድንገት በመንገድ ላይ ወይም ከመንገድ ወጣ ብሎ ሰወር ብሎ ካሜራ ጠምዶ ለቁጥጥር የቆመ የፖሊስ መኪና ካዩ ሲደነግጡ ተመልክቻለሁ፡፡ ለነገሩ ቢደነግጡ አይፈረድባቸውም፡፡ በአንዳች ጥፋት ፖሊሶቹ ሰው ሲይዙ ድርጊታቸው ጭካኔ የተሞላበት ነው፡፡ በተለይ ጥቁሮች ላይ ብዙ ጊዜ በግልጽ የማያሳዩት በውስጣቸው ተደብቃ ያለችው የዘረኝነት መንፈስ ትከሰታለች፡፡

አሜሪካኖች በብዙ ነገር አንደኛ መባልን ይወዳሉ፡፡ ዓለም ማለት እኛ ነን ብለው ስለሚያስቡ የፈጠሩትን የቅርጫት ኳስ ጫወታ እርስበርስ ተጋጥመው እንኳ አሸናፊው የዓለም ሻምፒዮን ተብሎ ነው የሚጠራው፡፡ በአጠቃላይ አሜሪካ የብዙ እውቀትና ጉልበት ባለቤት የሆኑ ሰዎችን ከሁሉም የዓለም ማዕዘን የምትስብ ሀገር በመሆኗ እድገቷ እስከ ዛሬም አልተቋረጠም፡፡

ይህን ሰፊ ውቅያኖስ የሚያህል ሀገር ታሪክ ከማቋረጤ በፊት በአንድ አጋጣሚ ቨርጂኒያ ስካይ ላይን አካባቢ ያገኘኋቸው ኮሎኔል ታደሰ ይመር በአጭሩ ቆይታችን ያጫወቱንን ታሪክ ላጋራችሁ፡፡ ኮሎኔል ታደሰ በቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ጄነራል ከበደ ገብሬ ረዳት ፀሐፊ (ኤዲሲ) ነበሩ፡፡ እ.ኤ.አ. 1973 ለጉብኝት አሜሪካ አብረዋቸው ይመጣሉ:: በወቅቱ ጄኔራል ከበደ ብዙ ጊዜ ስላልነበራቸው የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የሆኑት ወዳጃቸው ኡታንት መምጣታቸውን እንዳይሰሙ ጭንቀታቸውን በወቅቱ በተባበሩት መንግሥታት የኢትዮጵያ ተወካይ ለሆኑት ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ይነግሯቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅ እንዳልካቸው አይ ጋሼ አሉ (አንተ ነው የሚሏቸው የሥጋ ዝምድና አያጡም) እንዲያውም ቀጠሮ ይዤልሀለሁ ሳታገኘውማ አትሄድም ይሏቸዋል፡፡ ሁለቱ በኮሪያ ጦርነት ወቅት ጄነራሉ የሁለተኛ ዙር የኢትዮጵያ ዘማች ጦር መሪ ሳሉ ይተዋወቃሉ:: ወዳጃቸውን ማየት ባይጠሉም የጊዜ እጥረት ሆኖባቸው ነው መግደርደራቸው ::

በተባለው ቀጠሮ ቀን በዋና ፀሀፊው ቢሮ ተገናኝተው ተወያዩ፡፡ በዚህ ጊዜ ዋና ፀሀፊው በጣም እንደሚፈልጓቸው በድርጅቱም ውስጥ ትልቅ የሀላፊነት ቦታ ላይ ሊመድቧቸው እንዳሰቡ ይገልፁላቸዋል፡፡ እኔ አሁኑኑ ለንጉሡ በስልክ እነግራቸዋለሁ ብለው እጃቸውን ወደ ስልኩ እጀታ ሰደዱ:: ጄነራል ከበደ ግን ሹመቱን አልተቀበሉትም፡፡ በወቅቱ እኔ በጣም

ተናደድሁ፡፡ ለብቻችን ስንሆን ጉዳዩን አነሳሁባቸው፡፡ ጨምሬም ይህ አጋጣሚ ለሀገራችን ብዙ እድል ይፈጥራላታል ብዬ ጠቆምኳቸው፡፡ “ስማኝ እኔ ለሀገሬ ኢትዮጵያ ብዙ አልሠራሁላትምና ወደ እዛ ነው መመለስ የምፈልገው” ብለው ቅጭም ብለው ገለፁልኝ፡፡ ቆይታችንን ጨርሰን እንዳሉትም ወደ ሀገር ቤት ተመለስን፡፡ በዓመቱ ለውጥ መጣ፡፡ ያሰቡትንም ሳይከውኑ ከ60 የንጉሡ ባለሥልጣኖች ጋር ተገደሉ፡፡ እኔ ባጋጣሚ ለስብሰባ ኬንያ ነበርኩና በዚያው ቀረሁ፡፡

## ፬ ኩባ ወዳጆችን

በደቡብ አሜሪካ በካሪቢያን ባህር የምትገኝ ትንሽ ደሴት ሀገር እንዴት ይህን ሁሉ ውቅያኖስ እና አየር ቆርጣ ወዳጃችን ሆነች ብለው ይገረማሉ፡፡ ኩባ በስም ገንና በዓለም እንድትታወቅ የታሪክ አጋጣሚ ወይም የታጋይ መሪዎቿ የትግል አቅጣጫ ማለት ኮሚኒስታዊ አስተምህሮና ፍልሰፍና ለዚህ እንዳበቃት ይገነዘባሉ፡፡

ኩባ ከአሜሪካዋ ፍሎሪዳ ግዛት ሚያሚ (Miami) ከተማ በ90 ማይልስ ርቀት ላይ የምትገኝ ስትሆን በአቅምም ሆነ በሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም የተለያዩ ናቸው፡፡ ሆኖም ኩባ እንደ አንድ ትልቅ ጠላት እየታየች ከ60 ዓመታት በላይ በጎሪጥ ከመተያየት አልፈው በጦር ተፈታትነዋል፡፡ የፀቡ መነሻ በርዕዮተ ዓለም ጎራ መከፋፈል የተነሳ ነው፡፡ ኩባ ውግናዋን ከቀድሞዋ ሶቪየት ህብረት በማድረጓና ለሩሲያ ኑክሊየር መሳሪያ መትከያ ቦታ መስጠቷ ነው፡፡ በአሜሪካው ፕሬዜዳንት ኬኔዲ ዘመን ሁለቱ ሀገሮች ለኑክሌር ጦርነት አፋፍ ደርሰው እንደተመለሱ ታሪክ ይነግረናል፡፡ በዚህ የተነሳ ላለፉት ረዥም ዓመታት አሜሪካ በዚች ትንሽ ሀገር ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ጥላባት በችግር ትኖራለች፡፡ አሜሪካ ለባህር ሀይል ቤዝ ከኩባ በሊዝ እ.ኤ.አ.1898 ጓንታናሞን ተከራይታ እየተጠቀመችበት ነው፡፡ ጓንታናሞ ቤይ ዛሬ እ.ኤ.አ. 2001 በአሜሪካ ላይ የሽብር ጥቃት ያደረሱት የአልቃይዳ አባላት እስር ቤት ሆኖም በተጓዳኝ እያገለገለ ነው፡፡

ኩባ እኔ በጎበኘኋት ጊዜ መሪዋ ፊደል ካስትሮ በሥልጣን ላይ ነበሩ፡፡ ሕዝቦቿ ሰውና መሪውን ወዳጅ ሆነው ነው ያገኘኋቸው፡፡ እኔም ፍቅራቸውን ልመሰክር ከበቃሁበት አጋጣሚዎች አንዱን ላውጋችሁ፡፡ ከአየር ማረፊያ ሊቀበሉኝ ከመጡት የአስጎብኚ ድርጅት ባልደረቦች የሆኑት ወንድና ሴት ላይ ያየሁት ፍቅር የመጀመሪያ አጋጣሚዬ ነበር፡፡ ወንዱ እንደ ደረሰ የሞቀ ሰላምታ ሰጠኝና ካራማራ ድሬዳዋ የሚሉ ቃላትና በእጅ ምልክቶች ጭምር በወታደርነት እዛ እንደነበረ ነግሮኝ ተሰናብቶኝ ሄደ፡፡ ሴቷ ተቀባዬ እንዳስረዳችኝ ከኢትዮጵያ የሚመጣ እንግዳ ለመቀበል ወደ አየር ማረፊያ እንደምሔድ ስነግረው ተከትሎኝ ሊያገኘኝ እንደመጣ ገለፀችልኝ፡፡ እነዚህ በሶሻሊስት አጋርነት የሶማሊያን ወረራ ለመቀልበስ ለኛ ሊሞቱልን እንደመጡ (የመናውያንም አብረው መጥተዋል) ሳስብ እኔም በፍቅር ወደኩላቸው፡፡ ሌላው ባረፍኩበት ሆቴል የአሣማ ስጋ አልበላም ብያቸው የተጨነቁትና የጆሬ አሞራ እግር የሚያክል የዶሮ ስጋ ለብቻዬ ሰርተው ሲያቀርቡልኝ የነበራቸው ክብካቤና ፍቅር እስካሁን ከልቤ ተፅፎ ይኖራል፡፡

ቋንቋቸው እስፓኒሽ ስለሆነ እንግሊዘኛ በትምህርት ቤት ጭምር ብዙ አይነገርም፡፡ በቅድሚያ ስፔን ቀጥሎ ብራዚል ያቺን ደሴት በቅኝ ስለገዟት የህዝቡም መልክ የነዚህ ድብልቅ ነው፡፡ በአብዛኛው ቆንጆ ቡናማ ከለር ሲሆን እኛን የመሰሉ በጣም ጥቁሮችም አሉ፡፡

የኢትዮጵያና የሶማሊያ ጦርነትን ሳስብ አንድ በ1974 ዓ.ም. የተፃፈ አቶ ሀይለማሪያም ወልደአረጋይ (የቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ የስራ ባልደረባዬና አባቴ የነበሩ) አውሰውኝ ያነበብኩት ትንሽ መፅሀፍ ትዝ አለኝ፡፡ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የጂቡቲው ፕሬዜደንት የነበሩት ጉሌድ አፕቲዶንና የኩባው ፊደል ካሰትሮ (ሁለቱም ወደ እውነተኛው ቦታ ሄደዋልና ነፍሳቸውን ይማርልን) ሽምግልና ይዘው ነበር፡፡ የነበረውን ሁኔታ ፕሬዜደንት አፕቲዶን ትዝታቸውን ሲናገሩ የሶማሊያው ፕሬዜደንት ዚያድ ባሬ በወቅቱ ለያዥ ለገራዥ አስቸግሮ ነበር አሉ፡፡ በቂ የጦር ዝግጅት አድርጎአል፡፡ የሶቪየት ህብረት ጦር መሳሪያ እስከ አፍንጫው ታጥቆ ስለነበር በጦርነት አባዜ ሰክሮአል፡፡ እሱንና ፕሬዜደንት መንግስቱን አስቀምጠን ለማወያየት ብዙ ጣርን፡፡ ነገር ግን በወቅቱ ኢትዮጵያ በለውጥ ሽግግር ላይ ነበረችና ደክማ ታየችውና ቶሎ ወግቶ ያሰበውን ግዛት ለመጠቅለል አቅበጥብጦት ነበር፡፡ ምንም መፍትሄ ማምጣት አልቻልንምና ካስትሮም አዝነውበት ወደ መጡበት እኔም ቤቴ ገባንና የፈራነው ጦርነት ተጀመረ፡፡ በመጨረሻ ሰዐት ጎራው ተደባለቀ፡፡ የተማመነባት ሶቪየት ህብረትም ፊቷን ወደ ኢትዮጵያ አዞረችና እሱ የታጠቀውን ለሷም ሰጠቻትና በአንድ ዓይነት መሣሪያ ሁለት የአፍሪካ ልጆች ተዋጉ፡፡ ዚያድ ባሬ ያሰበው ሳይሆን ቀረና ሽንፈትን ቀመሰ፡፡ በዚህም ሕዝቡ ተነሣበትና ሀገር ጥሎ ተሰደደ፡፡ በዚያው በተሰደደበት ሞቶ ለሀገሩ አፈር ሳይበቃ ቀረ፡፡

የኩባ ዋና ከተማ ሀቫና የከተማውን ዳር የካሪቢያን ባህር ሲያዋስናት የፍቅርና የመዝናኛ ቦታ ሆና ነው ያገኘኋት ። ትንሿ ሀገር ያላት ትልቁ ሀብት የእርሻ ምርቷ ውጤት የሆነው ስኳር ነው። በሕክምና ረገድም ማንም ከሚገምተው በላይ ርቃ ተራምዳለች የምትታወቅበትንም ወፍራሙ ቶሰካኖ ሲጋራዋን ሳንረሳ ማለቴ ነው።

በወቅቱ ብዙ ባይሆኑም የሚነዱት መኪናዎች የዱሮ ኦፔልና ላዳ ናቸው። በሰው የሚነዱ እንደ ጋሪ ቱሪስት የሚያንሸራሽሩ ባለ ሶስት እግር ብስክሌት መጓጓዣ ተጠቅሜአለሁ። ኩባ በወቅቱ ያላት የተዘጋ ኢኮኖሚ በመሆኑ የሥራ እንቅስቃሴ ውሱን ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ወጣቶችን ያለሥራ በየደጃፋቸው ተቀምጠው ይመለከታሉ። ጧት ተነስተው ሲጋራቸውን እና መጠጣቸውን መግዣ ካገኙ የምግብ ኩፖን ከመንግስት ስለሚሰጣቸው ለምግባቸው ብዙ አይጨነቁም። ሙዚቃቸውን ከፍተው የሚታወቁበትን የሳንባና ሳልሳ ዳንስ ዳንኪራ መርገጥ ነው።

የባህር ዳር መዝናኛ ከሀቫና ወጣ ብሎም ይገኛል። ቫራዴሮ ይሉታል። ጧት በአቶቡስ ተጉዘው ውሎ ገባ ተዝናንተው መመለስ ይችላሉ። ባህሩም ካሪቢያን (Caribbean sea) ነው። ይህ ባህር በሥርአቱ የተከፉ ዜጎች በድብቅ በጀልባ ወደ አሜሪካ የሚሻገሩበት (የፊደል ካስትሮን ባለቤት ጨምሮ) የውሃ መንገዳቸው ነው። በዚህ ባህር ተሻግረው በሚያሚ ከፍተኛ የኩባ ማህበረሰብ ይገኛል።

በኑሮ የተሳካላቸውና እስከ አሜሪካ ኮንግረስ አባል የሆኑና ለአሜሪካ ፕሬዜደንትነትም የተወዳደሩ ኩባውያን ይገኙበታል፡፡

ኩባ የተጓዝኩት በአንድ ዓለም አቀፍ ታሪካዊ ከተሞችን እድገት በተመለከተ እ.ኤ.አ. በ1998 በተደረገ ኮንግረስ ላይ በግል ተጋብዤ ነው፡፡ ኩባም የተመረጠችው ታሪካዊ ከተሞች ለሚለው የስብሰባው ዋና ትኩረት ማሳያ እንደምትሆን ስለተገመተ ይመስለኛል፡፡ ታዲያ በዚህ አጋጣሚ የሀቫና ታሪካዊ ሕንፃዎቿን ለመጎብኘት እድል አግኝቼአለሁ፡፡ አንዳንዶቹ እርጅና ተጫጭኖአቸው በመፍረስ ላይ ነበሩ፡፡ እንዲያውም ባንድ የምሽት የቴሌቪዥን ዜና ላይ ሕንፃ በቆመበት ሲወድቅ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደገለፅኩላችሁ የኢኮኖሚ እድገቷ በአብዛኛው  በመንግስት እንቅስቃሴ ላይ ብቻ የተመሰረተ (የግል ዝግ ነው)  ከመሆኑም ባሻገር በወቅቱ የሶሻሊስቱ ካምፕ በመፍረሱ ከሶቪየት ህብረት ታገኝ የነበረው ዓመታዊ ድጎማ በመቋረጡ ችግር ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡

ከተቸገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል  በሶማሊያ ጦርነት ወላጆቻቸውን ያጡ የወታደርና የተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን ችግረኛ ልጆችን በነፃ ለማሳደግ ኩባ የወሰደቻቸው የኛው ዜጎች አጋጥመውኛል፡፡ እንዳጋጣሚ የስብሰባው አስተናጋጅ በጎ ፍቃደኛ የኮሌጅ  ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ከነዚህ መካከል አንዲት ናሚቢያዊት ተማሪ ከኢትዮጵያ የሚመጣ ብቸኛ እንግዳ መሆኔን ተረድታ ፈልጋ አገኘችኝ፡፡ በችግር ስለሚኖሩ የአገሬ ልጆችም አዋየችኝ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ዮናስ የሚባል የክፍላቸው ኢትዮጵያዊ ተማሪ ይዛ መጥታ አስተዋወቀችኝና ብዙ ተወያየን፡፡ ዮናስ እንደነገረኝ በየዩኒቨርስቲው ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚቀበላቸው ዘመድ አዝማድ ሀገር ቤት ባለማግኘታቸው የኩባ መንግስት እየረዳቸው ያለ ሥራ ቁጭ ያሉ ብዙ ወገኖች እንዳሉ ተረዳሁ፡፡ ምን ማድረግ እንደምችል ለሶስት ተወያየን፡፡ ለጊዜው የታየኝ ስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበረው እንግሊዛዊ ወዳጄን ፕሮፌሰር ሪቻርድ ሪክስን ማማከር ነበር፡፡ ሪክስ ስነግረው ልቡ በሀዘን በጣም ተነካ፡፡ ዓይኑ እንባ አቅርሮ ሄደን እንድንጎበኛቸው ጠየቀኝ፡፡ በናሚቢያዊቷ አስተናጋጅነት ላዳ ተከራይተን ወደ ዩኒቨርሲቲያቸው ሄድን፡፡ ገና ስንደርስ ሕንፃው በር ላይ ዳቦ የሚቸርችር ወገኔን ሳገኝ ልቤ በሀዘን ተሰበረ፡፡ ወደ ውስጥ ስንዘልቅ ችግራቸውን ሊነግሩን ተሰባስበው ጠበቁን፡፡ እኔ አስተርጓሚ ሆኜ ያሉበትን አሳዛኝ ሁኔታ አወጉን፡፡ እኔም ሆነ እንግሊዛዊው ወዳጄ ምንም ማድረግ የማንችል ደካሞች ነበርንና ሰምተን እርሱ ትንሽ ገንዘብ አበርክቶላቸው ተሰናበትናቸው፡፡ እኔም በተራዬ መኪና ውስጥ እያነባሁ  ተመለስን፡፡

በወቅቱ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እዛ ተዘግቶ ካናዳ ያለው በተደራቢነት ተወክሎ ነበር፡፡ እሱም በተራው ኩባ ውስጥ ላለው የናሚቢያ ኤምባሲ ውክልና ሰጥቶ ነበር፡፡ የናሚቢያ አምባሳደርን እንዳናግር ያቺው ናሚቢያዊት ቀጠሮ አመቻችልኝና በመመለሻዬ ቀን ክቡር

አምባሳደሩን በጽህፈት ቤታቸው ተገኝቼ ሀሳብ ተለዋወጥን። አምባሳደሩ ሲገልጹልኝ ልጆቹን ለመርዳት በቅርቡ ነፃ የወጣችው ናሚቢያ አቅም የላትም። እንዲሁም መንግስታችሁም ሊረዳኝ ስላልቻለ  የልጆቹ ችግር እንቅልፍ ነስቶኛል አሉኝ። በግሌ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ባላውቅም ጉዳዩን ግን ማሰማት የምችልበት ድረስ ለማሰማት እሞክራለሁ ብየ ለመልካም ተግባራቸው አመስግኛቸው ተለየኋቸው።

ስዋፖ የነፃነት ተዋጊዎች አርበኞች ግንባር  ለናምቢያ ነፃነት ትግል በሚያደርግበት ወቅት ከድል በኋላ ሀገሪቱን በሚረከቡበት ጊዜ ሕዝብ አስተዳደር ላይ እንዳይቸገሩ ቅድመ ዝግጅቱን ለማገዝ የኢትዮጵያ መንግስት ታጋዮቹን በማሰልጠን ይረዳ ነበር። ታጋዮች ከጫካ እየመጡ እኔ የምሰራበት ቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክን ጨምሮ በየመሥሪያ ቤቱ እየተመደቡ የሥራ ላይ ሥልጠና ሲሰጣቸው የነበሩና በወዳጅነት የተቀራረብን ብዙ ናሚቢያውያንን አውቅ ነበር። ይህንኑ ውለታ ለመመለስ ጊዜ ፈቅዶላቸው እየረዱን መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።

ኩባውያን እንደዚሁ ባለውለታን አይረሱም። ከአገሩ አርጀንቲና በዓለም አቀፋዊ ሶሻሊስት ትብብርና አጋርነት መርህ ተመርቶ ኩባ ድረስ መጥቶ  ከነ ካስትሮ ጎን ለነፃነት የተዋጋላቸውን የቼ ጉቬራን ፎቶ ከመሪያቸው ካስትሮ ባላነሰ ሁኔታ በየቦታው ተሰቅሎ

ያገኙታል። ከነፃነት በኋላ የሚኒስትርነት ሥልጣን ተሰጥቶት ትንሽ ጊዜ ከሰራ በኋላ እንዲሁ የነፍስ ጥሪውን በመከተል ሌሎች ሀገሮችን ለማገዝ በኮንጎና ቦሊቪያ ጫካ ሲንከራተት በአሜሪካው ሲ.አይ.ኤ. መገደሉን አንብበናል። በአገራችንም ቢሆን ፋኖ ተሠማራ እንደ ቼ ጉቬራ… እየተዘመረ ለ1960ዎቹ የኛው ታጋዮች እንደ ትግል አርአያ ይወሰድ ነበር - ሀኪምና ታጋይ ዶክተር ቼ ቀላል ተጽዕኖ ፈጣሪ አልነበረም!!

ለኩባውያን ለወዳጅነታችን ማስታወሻ በኢትዮጵያም ከትልቁ ፖስታ ቤት ፊለፊት የሚገኘው ድላችን የተሰኘ ሀውልት ቆሞላቸዋል።

## ፰ ከአምቦ እስከ አፋምቦ

ደሳለኝን ያገኘሁት አፋር አሳኢታ ባሻ አማረ ሆቴል ቤት ሲያስተናግደን ነው። ትሁት ሳቂታ ለመቅረብ ቅልል ያለ በሀያዎቹ መጨረሻ ዕድሜው ላይ ያለ ወጣት ነው። አሳኢታ ወደ ጂቡቲና አሰብ ከሚወስደው ዋናው አውራ ጎዳና ተገንጥላ ከሰመራ 60 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ገብታ ነው የምትገኘው። ለረጅም ጊዜ የአፋር ክልል መቀመጫ የነበረች ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ሰመራ ላይ አዲስ ከተማ ተቆርቁሮ ወደዚያ ተዛውሯል።

አሳኢታም የተንዳሆ እርሻ ልማትን ተከትሎ እሯሷን እያነቃቃች ስትሆን በከተማው ዳር ላይ ትልቅ የስኳር ፋብሪካ እየተገነባ ነው። ለፋብሪካው ሠራተኞች መኖሪያ የሚሆን አንድ ከተማ የሚያክል የኮንዶሚኒየም ህንፃዎች ግንባታ ከተማው ውስጥ ተከናውኗል። በርግጥ በሕንዳውያን እየተገነባ ያለው ፋብሪካ በመዘግየቱና ቤቶቹ ውስጥ እየተኖረበት ስላልሆነ የህንፃዎቹ ጣሪያ በንፋስ ተገነጣጥሎ ይታያል።

ለስኳር ምርት ግብዓት የሚሆነው ሸንኮራ አገዳ ልማት ከዱብቲ ጀምሮ እስከ አሳኢታ ድረስ የአዋሽ ወንዝ መስኖ ልማትን ተከትሎ በስድሳ ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ተዘርቶ ያን የተንጣለለ የአፋር ዝርግ ሜዳ አረንጓዴ አልብሶታል። እጅግ ዓይን ይማርካል። ታዲያ

አሳኢታ ከመድረሶ በፊት ሰማይና ምድር የተጋጠሙ በሚመስል ሁኔታ ከርቀት ሲያዩ አሸዋው ጥቁር ባህር መስሎ ይታይዎታል። በየመሀሉ እንደ ባህር ዛፍ እንጨት ቀጥ ብሎ ቆሞ ሸክርክሪት እየሰራ የሚነጉደው አውሎ ንፋስ እይታዎን ያቋርጦታል። እሱን አልፈው ሲሄዱ ከዚያ በረሀ ፓርክ ብቅ የሚሉት የሚገርሙ ትላልቅ ገመሬ ዝንጀሮዎች የመንገዱን ጠርዝ ይዘው ቆመው ይቀበሎታል። ትንሽ ቆም ካሉ መኪናዎን ይከቡና ለማመን በሚያስቸግር ፍጥነት መኪናው ጣራ ላይ ቁብ ይሉና በመስታዎት መስኮት በኩል የሚበላ ካለ በሚል ዙሪያውን ያማትራሉ። ምግብ ከሰጡአቸውም ከምስጋና ጋር ተቀብለው ወርደው ይሄዳሉ። መንገዱ ዳርና ዳር ከእርዳታ እህል ጋር እንደገባ የሚታመነው አረም ዛፍ እየሆነ መምጣቱን ተመልክቻለሁ። ለነዚህ የዱር እንስሳት መጠጊያ የሆናቸው ይመስላል፣ እንደኔ ግን ከርቀት ከሚታየው ጋራ ላይ መውረዳቸው ለመሆኑ ግምቴ ያመዝናል።

የአፋር ሕዝብ የአዋሽ ወንዝ ውለታን መቼም ከፍሎ የሚጨርሰው አይመስለኝም። በድሮ ጊዜም አሳኢታ ውስጥ ይህን የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስን ተከትሎ የጥጥ እርሻ ልማት በውጭ ሀገር ሰዎች ይካሄድ ነበር። አሁን ደግሞ እሱን ተክቶ ለስኳር ምርት የሚሆነው የሸንኮራ አገዳ ልማት ማሳውን ሞልቶታል።

ይህ አርብቶ አደር የኢትዮጵያ ድንበር ጠባቂ ሕዝብ ባሕሪይ እጅግ የሚገርም ነው። እንደተገነዘብኩት የበረሀ ሰው ግለኝነት ባሕሪው

አይደለም። ተሳስቦ ያለውን ተካፍሎና ተዛዝኖ ነው የሚኖረው። እርግጥ ቁጠባ ብዙ አትታወቅም። ሌብነት ወይም ስርቆትን ይጠየፋል። የአፋር ሕዝብ የራሱ የዳበረ የአስተዳደር፣ የመረጃ ልውውጥ (ዳጉ)፣ የሽምግልናና ሌሎች ሊጠኑ የሚገቡ ባህሎች አሉት። በኢትዮጵዊነቱ እጅግ የሚኮራና ለአገሩ የሚሞትላት ሕዝብ ነው። የአፋር መንፈሳዊ መሪ የነበሩት የተከበሩ ሡልጣን አሊ ሚራህ በአንድ ወቅት ሲናገሩ "የኢትዮጵያን ባንዲራ እንኳን ሰዉ ግመሎቻችን ያውቁታል" ብለዋል።

የአፋር ሕዝብ ተወላጅ ከአዋሽ ሰባት ኪሎ ጀምሮ እስከ ጂቡቲና በኤርትራ (አሰብና ዳህላክ ደሴት) ይኖራል። በአፋር ክልል በተዘዋወርኩባቸው አሳኢታ፣ ዱብቲ፣ ሎጊያ፣ ሰመራና አፍዴራ ያየሁት ከሌላ አካባቢ ለሥራ መጥተው ኑሮአቸውን እዚያ ያደረጉ ብዙ ሰዎች አጋጥመውኛል። በተለይ ከወሎ አካባቢ የመጡ ብዙ ሰዎች ወልደው ከብደው ይኖራሉ። በቀደመው ጊዜ የአውሳ አውራጃ ተብሎ በወሎ ጠቅላይ ግዛት ሥር ትተዳደር እንደነበር ያስታውሷል።

የአዋሽ ወንዝ ከጊንጪ ተራራ ግርጌ ተነስቶ በቾ ሜዳን አቋርጦ የጉራጌን ምድር አረስርሶ ቲማቲም ድንች አብልቶ በመተሀራ በሸንኮራ ማሳ አድርጎ አሚባራንና መርቲን አልምቶ አፋር ምድር ደርሶ ግመሎቹን ውሀ አጠጥቶ ድንበሩን ሳይሻገር አፋምቦ ላይ ረጅሙን ጉዞውን ያበቃል። ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እንዳለው

ሀገር ወዳድ ነው፡፡ ታዲያ ደሳለኝ ከተወለደባት አምቦ አጠገብ ካለችው የአዋሽ መነሻ ተነስቶ መጨረሻውን ለማየት ከ800 ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዞ መድረሻው አፋምቦ አጠገብ አሳኢታ የመጣው ለምን እንደሆነ ተገርሜ ጠይቄዋለሁ፡፡ በርግጥ አጎቱን ብሎ እንደመጣ ነግሮኛል፡፡

ይህን የአዋሽን ማሳረጊያ ለማየት ብዙ ሀገር ጎብኚዎች አሳኢታ መጥተው አይቻለሁ፡፡ እንዲያውም ባሻ አማረ ሆቴል ጓሮ ደጅ ላይ በተዘረጋው አልጋ ላይ እዚህ ሀገር ይወድቃሉ ደጅ እንዳይወጡ ተብለው የሚከለከሉ እናት ከሴት ልጃቸው ጋር ከፈረንሳይ ሀገር ድረስ መጥተው ፀሀዩን ለማሳለፍ ጋደም ብለው ተመልክቻለሁ፡፡ አፋምቦ ከአሳኢታ ወደ ውስጥ ከ6 እስከ 10 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ ከመሆኑም በላይ ለመኪናም ያስቸግራል ስላሉን ሳላየው ተመልሻለሁ፡፡ የአዋሽን የመጨረሻ መንፈሱን ለመሰናበት ድልድዩ ሥር ወርጄ ወንዙ ዳር የአፋሯ ጉብል ለመስተንግዶ ካዘጋጀችው ዳስ ውስጥ ቁጭ ብዬ ያፈላችውን ሻይ ይዤ እንደ ወትሮዬ በውሀው ብዙ ተመስጬአለሁ፡፡ ስለ አዋሽ በግጥምና በሥነ ጽሁፍ ከተነገረው በላይ ለማሰላሰል የተቻለኝን ሞክሬአለሁ፡፡ ይህ የሀገር ሲሳይ የሆነ ወንዝ ከማንም ጎረቤት ሀገር ጋር ሳያነካካን በሰላም ቀዬ ለቀዬ ከ1200 ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዞ በረከቱን አዳርሶ መጨረሻዬን በአገሬ ያርገው ያለ  እውነትም ሀገር ወዳድ ነው፡፡

የውጭ መኝታ ሲባል እኔና የሥራ ባልደረባዬ ብዙነህ ሎጊያ በከረምንበት ወቅት በከተማው እንግዳ መጣ ተብሎ ብዙ ጊዜ ከማይገኘው የአየር ማቀዝቀዣ ካለው ክፍላችን አስለቅቀውን ወይዘሮ ዘነበች ሆቴል ውስጥ ቀን ሰውና መኪና ሲተራመስበት ከሚውለው ግቢ ውስጥ መደዳ ማታ ማታ ከሚደረደረው አልጋ ላይ አድረናል፡፡ አልጋው የወባ መከላከያ አጎበር ተወጥሮለት በራስጌው በኩል ቀስ ብለው ገብተው ይዘጋና ኮከብ ሲቆጥሩ ማደር ነው፡፡ አዲስ ገጠመኝ በመሆኑ አልጠላሁትም፡፡ ብቻ ችግሩ በጧት ለመሄድ የፈለገ እንግዳ ሊነጋጋ ሲል ተነስቶ ጓደኛውን ለመቀስቀስ የሚንኳኳ በር ወይም ቁጥር ስሌለ እያንዳንዳችንን እየገለጠ መፈለጉ ከፋ እንጂ፡፡

የናዝሬት ሆቴል ባለቤት ወይዘሮ ዘነበች ልክ እንደ እናቴ በሥራ ወንድ የማያሸንፋት ሆና ነው ያገኘኋት፡፡ ሳያት እናቴን ነው ያስታወሰችኝ፡፡ ቢሆንልኝ የናቴን ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የዘለቀውን የሥራ ገድሏን ብጽፍላት ምንኛ ህይወቴ ሀሴት ባደረገች፡፡ ወይዘሮ ዘነበች በአርባዎቹ የዕድሜ ክልል የምትገኝ ሲሆን ለንግድ ወደ ጠረፍ ከተሞች ስትመላለስ ቆይታ ማረፊዋን ሎጊያን መርጣ የሰራችው ልማት በፈር ቀዳጅነቱ የሚመሰገን ነው፡፡ እንደልብ የማይገኘውን ሁለት ትላልቅ የእንግዳ ማረፊያ የሆኑ ሆቴሎች አጭር በሚያስብል ጊዜ የገነባች የሥራ ጀግና ናት፡፡ እሱ ብቻ አይደለም በግቢው ውስጥ በአፋር ብዙ የማይታየውን ዛፍ በመትከል አርአያ ሆናለች፡፡ ለዚህ ተግባሯ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እውቅና ሰጥቷታል፡፡

ለሥራ በተመላለስኩ ጊዜ ሁሉ እንደተመለከትኳት ሥራን ሠርታ ነው የምታሠራው። እንደተረዳሁት ከሷ ጋር ተጠግተው በሥራ ይረዷት የነበሩ ዛሬ እሷ መሰላል ሆናቸው እነሱም እንዳቅማቸው የራሴ የሚሉት መተዳደሪያ የንግድ ቤት አላቸው።

ዱብቲ ቀደም ብላ እርሻ ልማቱን ተከትሎ የተመሰረተች ከተማ ናት። ብዙ ተያያዥ ልማቶችም እንዳቅሟ አላት። ውሀ፣ ኤሌክትሪክ፣ ቴሌፎንና 40 ዓመት ያስቆጠረ ንግድ ባንክም አላት። ሆኖም ከተማዋን አንድ ሶስት ጊዜ አይቻታለሁ ግን የመንገዷ ቅያስ ሊገባኝ አልቻለም። ከእግር መንገድ ትንሽ ሰፋ ያለ ሲያገኙ እሱን ይዘው በመኪና ሲሄዱ የሰው ቤት አጥር ይመልሶታል። ይህን ለማስተካከል በመጨረሻ ጉዞዬ ወቅት መንገድ ሲሰራ ተመልክቻለሁ።

ሰመራ በቅርብ የተወለደች ቢሆንም ብዙ መሰረተ ልማቶች ተሟልተውላት ነው ርዕሰ ከተማነትን የተቀዳጀችው። ከንግድ ማዕከሏ ሎጊያ በ7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ሰመራ በውስጧ ዩኒቨርሲቲ፣ የፕሬዝዳንቱ ቢሮና መኖሪያ፣ ብዙ መሥሪያ ቤቶችንና የአስተዳደር ቢሮዎች ይዛለች።

በአፋር ባህል ያየሁት ለስብሰባ ሲጠሩ ከተባሉበት ሰዓት ቀድመው ሲደርሱ አስተውያለሁ። የሥራ ሰዓት በሙቀቱ ምክንያት በጧት

ነው የሚጀምረው:: ቀን ከ6 እስከ 8 ሰዓት ድረስ እረፍት የግድ ነው፣ ሆኖም ሞቃታም ሀገር በቀን ድብን ያለ እንቅልፍ መተኛት አይመከርም በዚያው መቅረት ሊያጋጥም ይችላልና ነው:: በሙቀቱ ምክንያት ውሀ ጥም የሚቆርጥ ትኩስ ነገር ስለሆነ ሻይና ቡና በብዛት ይጠጣል::

ከሎጊያ ወደ መቀሌ በሚወስደው መንገድ 200 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘው ጨው የሚመረትበትን አፍዴራን ያገኟታል:: ይህቺ በበረሀ መሀል የራሷ መተዳደሪያ የተፈጠረላት ምድር ውሀው ከቀይ ባህር ወደዚህ የሰረገ እንደሆነ ተረድቻለሁ:: በርቀት ቀይ ባህር ከሰማይ ጥግ የሚፈስ ይመስላል:: ያ ውሀ አፍዴራ ሜዳ ላይ ይተኛና ሲተን ጨው ይሆናል:: በእያንዳንዱ የመሬቱ ባለቤት መሀከል ያለውን ድንበር ማካፈያ እንዴት እንደሚለዩት ባላውቅም የአካባቢው የአፋር ተወላጆች የጨው ማሳ አላቸው:: በርግጥ ብዙዎቹ ለአልሚዎች አኮናትረው ከኪራይ ገቢ ነው የሚጠቀሙት:: የበረቱት ግማሾቹ በማህበር ተደራጅተው ነዲዱን ችለው ጨዉን ገንዘብ ይሰሩበታል:: እንዳየሁት ውሀ ከእጅ አይለይም:: እንደነገሩኝ በከፍተኛው የሙቀት ጊዜ ሸርጣቸውን ውሀ ነክረው አንገታቸው ላይ ጠምጥመው ትንሽ ትንሽ ምላስን እያረጠቡ ነው እንጂ ዝም ብሎ መንቀሳቀስ አይቻልም::

ከጨው ክምር ማሳ ተመልሰን ከተማው ውስጥ ሆቴል ገብተን ምግብ አዘን ሁሉም የወጥ መሥሪያ ፊታችን ቀርቦ እዚያው ሽንኩርቱ ተከትፎ ሽሮው ተንተክትኮ ተሰርቶ በልተናል። የበረሀ ምግብ ወዲያው ወዲያው ተሰርቶ ነው የሚበላው። ምሳም ሆነ እራት ላይ ሰዓቷን ጠብቀው መገኘት የራሰዎ ጉዳይ ነው የተሰራው ነገር ማደር አይችልም። በአማራጭ የሚጣፍጥ  መጋላ ተደርጎ የተጠበሰ  የፍየል ጥብስም ይመገባሉ። ካጋጠመዎትም የበከልት ጥብስ (ልጅ ፍየል) ያገኛሉ።

## ፮ የጥረት ተምሳሌት- ሕንድ

ሕንድ ከዓለም ሕዝብ አንድ ሰባተኛ እጅ የያዘች ትልቅ የዲሞክራሲ ሀገር ነች። ሕንድ ጥንታዊ ሥልጣኔ አላቸው ከሚባሉት የሩቅ ምስራቅ ሀገሮች አንዷ ስትሆን ጥንት በቅመማ ቅመም ምርቷ ንግድ ታዋቂ ነበረች። ዛሬም ድረስ ቅመም የበዛበት በዋነኛነት ሩዝ ምግባቸው ታዋቂ ናቸው። ሕንድ በምትታወቅበት ሰፊ የዲሞክራሲ ነፃነት አንድ አዋጅ በፓርላማ ለማለፍ አሳሩን እንደሚበላ ተረድቻለሁ። አንዳንዴ የበዛ ነፃነት እንዴት ወደ ስምምነት ለመድረስ እንደሚያስቸግር ሕንዳውያኑ ይገልፃሉ።

እንግሊዝ ለጨርቃ ጨርቅ እንዱስትሪዋ ግብዓት ጥጥ ፍለጋ መጥታ ለሁለት መቶ ሀምሣ ዓመታት በቅኝ ገዝታታለች። እንግሊዝ እ.ኤ.አ. 1947 አገሪቱን ሕንድና ፓኪስታን ብላ ሁለት ቦታ ከፍላ (በወቅቱ ብዙ ተቃውሞ ቢቀርብም) እያንዳንዳቸው እራሳቸውን የቻሉ ነፃ ሀገር አድርጋ ለቃ ወጥታለች። ቆይቶም ባንግላዴሽና ሲሪላንካም ከእንግሊዝ በ1948 ነፃ ወጥተዋል።

ሕንድን አንስቶ ታዋቂውን የሰላሙንና የነፃነት አባት ማህተመ ጋንዲን አለመዘከር አይቻልም። ጋንዲ የማይቻል በሚመስለን የሰላማዊ ትግል ሀገሩን ሕንድ ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ እንድትወጣ ያደረገ ጀግና መሆኑን ታሪኩን ስንመረምር መገንዘብ እንችላለን።

በዚህ ትግል ወቅት ጋንዲ በመሰደድ በግዞትና እስር ብዙ እንግልት የሞላበት መስዋትነት ለሀገሩ ሕንድ ከፍሏል፡፡ ሆኖም ከዓላማው ዝንፍ ሳይል ሀገሩን ለነፃነት አብቅቷታል፡፡ ጋንዲ ከነፃነት በኋላ ሂንዱና ሙስሊም እምነት ተከታዮች በአንድነት እንዲኖሩ ጥረት እያደረገ ባለበት ሰዐት በእ.ኤ.አ. 1948 ምሽት ላይ ለፀሎት ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ ላይ እያለ በአንድ አክራሪ ሂንዱስታን ጥይት በ77 ዓመት ዕድሜው ተገደለ፡፡

ከነፃነት በኋላ የትግል አጋሩ የነበሩት ጃዋህራል ኔህሩ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ሀገሪቱን መርተዋታል፡፡ ከሳቸው በኋላ ልጃቸው ኢንዲራ ጋንዲ (ባጋጣሚ ጋንዲ የባላቸው ስም ነው እንጂ ከማህተም ጋንዲ ጋር ምንም ዝምድና የላቸውም) ሕንድን መርተዋታል፡፡ በአሸባሪ ጥይት እናቱ ኢንዲራ ጋንዲ ሕይወታቸውን ሲያጡ ልጃቸው ራጂቭ ጋንዲ ተክተዋቸው ሲመሩ ቆይተው እሳቸውም በተራቸው በአሸባሪ ሴት አጥፍቶ ጠፊ በፈንጂ ለሀገራቸው ህይወታቸውን ገብረዋል፡፡ በአጠቃላይ የጋንዲ ቤተሰብ በሕንድ ትልቅ ቦታና ታሪክ ያላቸው ሲሆን በሕንድ ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ተፅዕኖ ፈጣሪም ናቸው፡፡

እንግሊዝ በቅኝ ግዛትነት ባስተዳደረችበት ጊዜ ትልቅ ነገር ትታላቸው ያለፈችው የትምህርት መሠረተ ልማት ነው፡፡ በዚህም ያመሰግኗታል፡፡ ሕዝቧም ድህነትን ማሸነፊያው መንገድ አንድና አንድ ትምህርት እንደሆነ በመረዳት ተቀዳሚ ሥራቸው ትምህርት

ነው፡፡ በአንዳንድ ግዛቶች ለምሳሌ ኬሬላስቴት 100 ፐርሰንት የተማረ ሕዝብ አላት፡፡ ኬሬላ በትምህርት ረገድ ያስመዘገበችው ውጤት ምንም እንኳ ፕሮግራሙ ሲጀመር ከብዙ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሳይቀር ትችትን ያስተናገደ ቢሆንም የትምህርት ቤት ምገባ ለዚህ ከፍተኛ ወጤት እንዳበቃት ይታመናል፡፡ ልጆች ብቻ አይደሉም ከዚህ ፕሮግራም እናቶችም ተጠቅመዋል፡፡ የቀን ምሳ ያተርፉበት ስለነበር እናቶችም ልጆቻቸውን ይዘው እየመጡ ራሳቸውም እንዲማሩ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሮላቸዋል፡፡ በመጨረሻም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሌሎች ሀገሮች ፕሮግራሙን እንዲከተሉት እንደ ማሳያ ወስዶታል፡፡ ብዙ ጊዜ ሲቀለድ ድንገት ከአይሮፕላን ላይ ብትወድቅ አንዱ የተማረ ሕንድ አናት ላይ ታርፋለህ ይባላል፡፡

ሕንድና ፓኪስታን ወደፊት ለመራመድ ትምህርት በእጅጉ ረድቷቸዋል፡፡ ሕንድ በሃምሣ ዓመታት የነፃነት ጊዜ ውስጥ የኒውክሌርና የጠፈር ሳይተላይት ባለቤት ለመሆን አስችሏታል፡፡ በሌላ በኩል የሕንድ ሕዝብ ብዛቷ ለሀገር ውስጥ ምርቶች ትልቅ ገበያ  መፍጠሩ እንደ ጥሩ እድል ቢቆጠርም የዚያኑ ያህል በኑሮ በተለይ በሀብታምና በድሆች መሀከል በጣም የተራራቀ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ከቴውንም ሕንድ “Land of extremes” ተብላ ትታወቅ አይደል፡፡ ብዙ የአገሪቱ ምሁራን መሃከለኛ መደብ (Middle Class) ባለመዳበሩ  የኑሮ ልዩነቱ ብዙ እንዲሰፋ እንዳደረገው ይከራከራሉ፡፡ ታዲያ ይህ የኑሮ ትግል ሰውን ሁሉ የጥረት እናት አድርጐታል፡፡

ገበያው ውስጥ ሰው በረጅም ጋሪ እቃ ጭኖ በትከሻው ሲጐትት ተመልክቻለሁ፡፡ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው በተለይ ከኬሬላ ስቴት የመጡ ወጣቶች ሙምባይ ከተማ ጐዳናዎች ዳር የሚጠጣ ኦቾሎኒ ሲሸጡ አግኝቻለሁ፡፡

በርግጥ ሕንዶች በትምህርት በመግፋታቸው ዕውቀትን ወደ ውጪ በመላክ ይጠቀማሉ፡፡ ከ25 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጐቿ በዓለም ዙሪያ ተበትነው በተለያየ መስክ ተቀጥረው ይሠራሉ፡፡ በትላልቅ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ልክ በአፍሪካ ጋናና ናይጀሪያውያን እንደሚባለው ሁሉ አንድ ሕንዳዊ አይጠፋም ይባላል፡፡ ዛሬ ዛሬ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ልቀው በመሄዳቸው በአሜሪካ ሳን ፍራንሲስኮ ግዛት የሚገኘውን የቴክኖሎጂ ማዕከሉን ሲልከን ቫሊን (Silicon Valley) ሥራ ወደ ሕንዳዊቷ ባንግሎር አምጥተውታል፡፡ የአሜሪካ ኩባንያዎች የሠራተኛ ደመወዝ ፔሮል ሳይቀር ባንግሎር ተሰርቶ ወደ አሜሪካ ይላካል፡፡ ታዲያ ሕንዳዊያኑ የትም ሠርተው ገንዘባቸውን ወደ አገራቸው (በዓመት ከ10 እስከ 20 ቢሊዮን ዶላር) በመላክ ለአገራቸው ኢኮኖሚ ብዙ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ መንግስትም ይህን ለማበረታታት የፖሊሲ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ገንዘባቸውን በፈለጉት የምንዛሪ ዓይነት እንዲያስቀምጡ ይፈቅዳል፡፡ በፈለጉትም የምንዛሪ ዓይነት መልሰው ያገኙታል፡፡ ከሃምሣ ዓመታት በፊት በብዙ

ድህነት እና በምግብ እራስ አለመቻል ትታወቅ የነበረች ሀገር እኤ በጎበኘኗት እ.ኤ.አ. 1998 የምግብ እህል ተርፏት ወደ ውጭ ላኪ ሆናለች፡፡

ለሕንድ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ዋና ተዋናዮቿ የራሷ ልጆች ናቸው፡፡ ከእ.ኤ.አ.1990 ወዲህ ላስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ቀዳሚ መሀንዲሷ የነበሩት ሞሀሚን ሲንግ ይባላሉ፡፡ እኚህ ትልቅ ሊቅ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የሠሩ የተከበሩ ኢኮኖሚስት ናቸው፡፡ የምንም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልነበሩ ሙያቸው ብቻ ተፈልጎ ራጂቭ ጋንዲ በሚመሩት ፓርቲ የተሾሙ የፋይናንስ ሚኒስትር በኋላም ጠቅላይ ሚኒስትር ነበሩ፡፡

በወቅቱ አንድ ፕሮፌሰር እንደነገሩኝ ሕንድ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እንድታደርግ እና የርዳታ ገንዘብ እንድታገኝ አንዳንድ የፖሊሲ እርምጃዎች እንድትወስድ ከፍተኛ ጫና ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ይደረግባት ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የመጠባበቂያ ገንዘብ እንድታሳይ (የተመናመነ ስለነበር ከየትም አታመጣም በሚል እሳቤ ይመስላል) ካልሆነ የድርጅቱን አስገዳጅ ሁኔታዎችን እንድትቀበል የሚያሳስብ ነበር፡፡ ሆኖም ሞሀሚን ለነዚህ ሁኔታዎች አልተንበረከኩም፡፡ በአንፃሩ የራሳቸውን እርምጃ በመውሰድ አይሮፕላን ተከራይተው ሶስት ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወርቅ አስጫኑና እንግሊዝ ባንክ ወስደው አስገቡ፡፡ ይኸው የምትፈልጉት

ሪዘርቭ ብለው አፋቸውን አሲያዟቸው፡፡ በነገራችን ላይ ሕንዳውያን ወርቅ በመውደድም ሆነ በመግዛት ከዓለም ቀዳሚ ናቸው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በቁጠባም ረገድ እንደዚሁ ከገቢያቸው እስከ 45 በመቶ ይቆጥባሉ፡፡

ለሀገር ዕድገት በየጊዜው እና በየቦታው መሪዎች ተፈጥረዋል በተለይ በእስያ አህጉር፡፡ በቅርብ ዘመን ከተነሱት መሲሆች መካከል የሲንጋፖሩ ሊ የቻይናው ዚያኦ ፔንግ የማሌዥያው መሀመድ ማክቲያር ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በሰላሳና አርባ ዓመታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ አገሮቻቸውን ወደ ከፍታና ልቀት የወሰዱ ናቸው፡፡ የሲንጋፖር አባት ተብለው የሚታወቁት ሊ በአስተዳደር ዘመናቸው ያቺን ሀገር አከል ከተማ (City State) ከምንም አንስተው በሀብት ማማ ላይ ያስቀመጧትና ዛሬ ከሀብታም ሀገራት ተርታ እንድትመደብ ያደረጓት ናቸው፡፡ ሊ አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና በህይወት በነበሩ ጊዜ ስለአጠቃላይ የእስያ ሀገሮች የኢኮኖሚ እድገት ሲናገሩ “ዋናው የእድገታችን መሰረቱ የእስያውያን  ባህላችንና ዕሴቶቻችን (Asian Values) ነው” ብለው ያምናሉ፡፡ የሥራ ዲስፕሊናችን፣ ሙስናን መጠየፋችን፣ መከባበራችን፣ መደጋገፋችን፣ ወ.ዘ.ተ. ለእድገታችን አስተዋፅኦ አድርጓል ይላሉ፡፡

ለመደጋገፋቸው ጃፓን ጥሩ ምሳሌ ናት፡፡ የኢኮኖሚ ፍልስፍናዋ የዝይ አሞራዎች (The Flying Eagles) አካሄድ ነው፡፡ ዝይዎች ሲበሩ በቪ ቅርፅ ሰርተው ነው፡፡ አንዱ ከፊት ይመራል ሌሎቹ ያንን

የቪ ቅርፅ ይዘው ይከተላሉ፡፡ ከፊት ያለው ሲደክም ወደኂላ ይሄዳል ተከታዩ መምራት ይቀጥላል፡፡ እንደዚሁም ከመሀከላቸው አንዱ ደክሞት ወደ ኂላ የቀረ እንደሆነ ሌላው ወደ ኂላ ቀርቶ እያጀበው ከድካሙ እስኪያገግም ድረስ ያበረታዋል፡፡ ከሞተም ትቶ ወደ ሰልፉ ይመለሳል፡፡ ጃፓንም ብዙ የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገራትን ይዛ አብራ ለማደግ በየሀገራቱ ፋብሪካዎችንና ተቋማትን በማቋቋም ረድታለች፡፡ እንደሚታወቀው እ.ኤ.አ. 1997 በእስያ የደረሰው የፋይናንስ ቀውስ ክፉኛ ጎድቷት ያለፈውና እስከዛሬ ከሁለት አስርተ ዓመታት በላይ በቅጡ ሳታገግም የቀረችው በእነዚህ ሀገራት ያላት ብዙ ኢንቨስትመንቶቿ በመጎዳታቸው ምክንያት ነው፡፡ ከዚያ ጉዳት በኂላ በዓለም ኢኮኖሚ የነበራት የሁለተኛነት ደረጃንም ለቻይና አስረክባለች፡፡

የሕንዳውያን ጋብቻ ሥርዓታቸውም ሴትን የሚበድል እንደሆነ አስተውያለሁ፡፡ ሴት ልጅ ለምታገባው ወንድ ብዙ ጥሎሽ መክፈል ይጠበቅባታል፡፡ ይህ ጎጅ ልማድ በአንድ ወቅት በእርግዝና ጊዜ ሴት ልጅ መሆኗ ከተረጋገጠ ወላጆች ፅንስ እስከ ማስወረድ ይደርሱ ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ የወንድና የሴት ቁጥር ሚዛን እንደተዛባ ዋቢ ጠቅሰው የሰብአዊ መብት ተሟጓቾች መንግስትን ሲከሱ ይደመጣሉ፡፡ በተረፈ የሠርግ ሥርዓታቸው እንደኛው የተንዛዛና ድል አድርገው የመደገስ ልማድ እንዳላቸው ተረድቻለሁ፡፡ ሕንዳውያን ከሚታወቁበት አንዱ የትም ይኑሩ ከአለባበሳቸው ጀምሮ ባህላቸውን አለመተዋቸው ነው፡፡ በጋብቻም ረገድ ከሌላ ዘር ጋር ሲቀላቀሉ ብዙ አይስተዋልም፡፡

ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ብዙ ሕንዳውያን በአስተማሪነት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀጥረው ይሰራሉ። በንጉሡ ጊዜ የሰማሁት ታሪክ ከውጭ ሀገር የተማረ ሰው ለማምጣትና እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ለማስፈር ጥናት እንዲደረግ ንጉሡ አዘው ነበር። ሕንድን በተመለከተ የአጥኚዎቹ የመጨረሻ መደምደሚያ ይሄው ከሰው አለመደባለቃቸው ነበርና በዚሁ ምክንያት ሓሳቡ እንደቀረ ሰምቻለሁ። በርግጥ በተለያየ ጊዜ ብዙ ባኒያኖች (እዚህ ሀገር ሕንዶች ድሮ የሚጠሩበት ስም ነው) ሀገራችን መጥተው ኑሮአቸውን እንደመሰረቱ ይታወቃል። የማህተመ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታልም በሕንድ መንግስት እርዳታ እንደተሰራ ልብ ይሏል።

በሕንድ ውስጥ በጠቅላላው ሃያ ሶስት ቋንቋዎች ሲኖሩ ብሔራዊ ቋንቋቸው ሂንዱና እንግሊዝኛ ናቸው። የሂንዱ ሀይማኖት ከ900 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች ያሉት ሲሆን፣ ክርስትናንና እስልምና የሚከተሉ ብዙ ሕንዳውያንም አሉ። ሕንድ ውስጥ ካስተዋልኩት አንዱ የጣዖት አምልኮ ስርዐታቸው ነው። የተማረውም ሆነ ሌላው የግሉ አንድ አማልክት አለው። ቢሮአቸው ወይም መኪናቸው ውስጥ አንድ የሚያመልኩት አማልክት ምስል ተቀምጦ ወይም ተሰቅሎ ያገኛሉ። ጧት ሲነሱ ፊቱ ቀርበው በቀኑ ውሎአቸው ጥበቃው እንዳይለያቸው ፀሎታቸውን ያደርሳሉ፤ ቀለም ጠቀስ አድርገው ግንባራቸውን ነካ አድርገውም ከቤት ይወጣሉ። ቢሮአቸው ውስጥም ሻማ ያበሩለታል። በየቦታውም ለአማልክቱ ቤተ መቅደስ ይቆምላቸዋል።

አንድ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ የማውቀው ሕንዳዊ በአጋጣሚ የዓለም ዋንጫ የሚካሄድበት ወቅት ነበርና ሲያጫውተኝ "ይህን ሁሉ ሕዝብ ይዘን በኢኮኖሚ እድገት ከቀዳሚዎቹ ተርታ ለመሰለፍ እየተጋን ባለንበት ጊዜ እንኳ እንዴት ነው በዓለም እግር ኳሰ ለመሰለፍ ያልቻልነው?" ሲል ይጠይቃል፡፡ ምንም አይደል እናንተ ብቻ በእድገቱ ጠንክሩ ሀብቱ ሲኖር ሌላው በገንዘብ ሀይል ይመጣል፡፡ ይኸው አሜሪካንን አታይም ድንገት ተነስታ የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ተፎካካሪ ሆነች አይደል ብዬ ለማፅናናት ሞከርኩ፡፡ እነርሱ የሚታወቁበት ክሪኬት የሚባል ከእንግሊዞች የወረሱት ጨዋታ ነው ፡፡

በሕንድ ከገረመኝ ነገር አንዱ የመኪናው ብዛትና የጡሩንባው ድምቀት ነው፡፡ ከመኪናቸው ጀርባ ላይ በትልቁ ጡሩንባ እንዲነፉ የሚያሳስብ ማስታወቂያ (Please Horn) በትልቁ ተጽፎ ይታያል፡፡ ባለሶሰት እግሩ ባጃጅ እነሱ ሪክሾው ይሉታል፣ሞተር ብስክሌት እና ሕንድ ስሪት የሆኑ መኪኖች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ከሕዝብ ብዛትና ከመንገዱ ጥበት አንፃር ሲታይ ንፉ ቢሉ አይገርምም!

ሕንድ ካላት የሚጎበኙ ሥፍራዎች አንዱ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው በአግራ አንድራ ፕራዴሽ ግዛት የሚገኘው ታዋቂው የታጅ ማሀል ሀውልት ነው፡፡ከእ.ኤ.አ.1628 እስከ 1658 የነገሠው ሻህ ጃሀን ያሠራው ይህ ሀውልት 14ኛ ልጃቸውን ስትወልድ ለሞተችው ለሚወዳት ሚስቱ የሙንታዝ ማሀል መቃብር ነው፡፡

ከአሥራ ሰባት ሄክታር በላይ በሆነ ቦታ ላይ ያረፈው ይህ ግዙፍ ሀውልት ዶሙ ብቻ 35 ሜትር ይረዝማል፡፡ ከሀውልቱ ግራና ቀኝ መስጊዶች ያሉት ሲሆን፣ ለመሥራት 21 ዓመታት ፈጅቷል (እ.ኤ.አ.1632-1653)፡፡ በጠቅላላው 22000 ሰዎችና ዕቃ በማጓጓዝ ያገለገሉ 1000 ዝሆኖች ተሳትፈውበታል፡፡ በወቅቱ 32 ሚሊዮን ሩፒ ወይም በዛሬ ዋጋ 916 ሚሊዮን ዶላር ወጥቶበታል፡፡ በየዓመቱ ከ7 እስከ 8 ሚሊዮን ቱሪስቶች ይጎበኙታል፡፡

በመጨረሻም እንግሊዝ በትምህርት ዘርፍ ጥሩ የሠራችውን ያህል በነፃነት ትግሉ ፍፃሜ ግዛቶቹን ስትከፋፍል ትታው የሄደችው የጊዜ ቦንብ ዛሬ በየጊዜው እየፈነዳ ሲያቆስላቸው ይስተዋላል፡፡ ሕንድና ፓኪስታን በካሽሚር የይገባናል ጥያቄ ብዙ ጊዜ በጦርነት ይቆራቆሳሉ፡፡ ሁለት ጊዜ (እ.ኤ.አ.1965 እና 1971) ብዙ እልቂት ያስከተለ ጦርነትም አድርገዋል፡፡ ለዚህ0 ይመስላል ሁለቱም ተሽቀዳድመው የኒውኪሌዩር መሣሪያ ባለቤት ለመሆን የተጉት!

በሕንድ ቆይታችን ወቅት የተመደበልን አስተናጋጃችን ሚስተር ማኒሽ ሀገሩ ሕንድ እ.ኤ.አ. 1998 የኒውክሊየር ሙከራ ባደረገችበት ዕለት የተሰማውን ደስታ ሲተርክልኝ “መንገድ ላይ ሆኜ ነበር ዜናውን የሰማሁት-ታዲያ ቤት እስክደርስና ገብቼ እስከማወራ ድረስ መንገዱ አላልቅልህ ብሎኝ በደስታ እያለቀስኩና እየሮጥኩ ነበር የተጓዝኩት” አለኝ፡፡

## ፯ የሮማውያን ሀገር-ጥልያን

ይህች ለኛ ሀገር ሰውና ታሪክ ቅርብ የሆነች በመሃል አውሮፓ የምትገኝ የሮማውያን ምድር ለትምህርት ሄጄ አንድ ዓመት ያህል በእንግድነት አስተናግዳኛለች፡፡ በዚህ ቆይታዬ ከትምህርቱ ጎን ብዙ ታሪካዊ ሥፍራዎቿን አስጎብኝተውናል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ብቻ ብፅፈው (በርግጥ ያቺ በውኃ የተከበበቺውን ዋና የቱሪስት መዳረሻዋን ቬኒሲያን ባጋጣሚ ስላላየኋት ሳልጨምር) ብቻውን ትልቅ ድርሳን ይወጣዋል፡፡ የቦት ጫማ ቅርፅ የመሰለ ካርታ ያላት ሜዲትሪያናን ባህር በረጅሙ የሚያዋስናት ጣሊያን የጥንታዊ ሮማውያን መኖሪያ ሀገር ነች፡፡ ምናልባት ከዓለም በጥንታዊነታቸው ከሚጠቀሱ ሥልጣኔዎች የሮማኖች አንዱ ነው፡፡ ከ2000 ዓመታት በላይ የኖረውን የሥነ ስዕልና ኪነ ሕንፃ ጥበብ ሲያዩ እጅግ ይደነቃሉ፡፡ በተጨማሪ ይህቺ ሀገር የካቶሊክ ሀይማኖት መሠረት ነች፡፡ ዋና መንበሩም ሮም የሚገኘው ቫቲካን ሲቲ (a city within a city) ነው፡፡

የጣሊያን ዋና ከተማ ሮም በአንድ ቀን አልተገነባችም የሚባለው ሥነ ሕንፃዎቿ ልቅም ተደርገው መሠራታቸውን ሲያዩ ሮም ለመሠራት ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደች ይገነዘባሉ ፡፡ ሮም ውስጥ በእድሜ ብዛት ምልክት ሆኖ የቀረውን በጥንት ጊዜ ሰውና አንበሣን የሚያታግሉበት ኮሎሲየም (ስታድየም) ቅጥርና እንደዚሁም ቫቲካን

ሲቲ (የኛው ፒያሣ ከራስ መኮንን ድልድይ እስከ ደጐል አደባባይ ድረስ ርዝመት ያላት ሀገር) ከሚጐበኙ ቦታዎች ውስጥ ናቸው፡፡

ቫቲካን ሲቲ ከመግቢያው ጀምሮ ግራና ቀኝ የሚከራዩ ሕንፃዎቿ የቤተክርስቲያኗ የሀብት ምንጭ ሆነው እያገለገሉ ነው፡፡ ወደ ውስጥ ሲዘልቁ የቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይና ካቴድራልን ያልፉና ግራና ቀኙ ሙሉውን የሥዕል ጥበብ የሞላውን ሙዚየም ያገኛሉ፡፡ ወደ ካቴድራሉ ሲዘልቁ የሥነ ሕንፃውን ጥበብ አድንቀው አይበቃዎትም፡፡ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ከ 1.2 ቢሊዮን በላይ ተከታዮቿ አስተምህሮና የቤተክርስቲያኒቷ ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚመነጨው ከዚህ ማዕከል ነው፡፡ የእኛን ሀገር ጨምሮ በዓለም ዙሪያ ያሉት ኤምባሲዎቿና የልማት ሥራዎችን ለሚያስተባብሩት ክፍሎች መመሪያ የሚፈሰውም ከዚሁ ነው፡፡ ለዓለም ሰላም ግጭቶችን ለመፍታት ያደራዳሪነትና የሽምግልና ሥራዎቿ ተጠቃሽ ተግባሯ ናቸው፡፡

መላው ጣሊያንን ቢዞሩ በየኪሎ ሜትሩ ርቀት በሚያስብል ደረጃ አንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያገኛሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ ላይ ትውልዱ እነዛ ተግተው ሀይማኖቱን ሲያስፋፉ እንዳለፉት አባቶቹ አይደለምና ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በተከታዮችና አገልጋዮች እጥረት ተዘግተዋል፡፡ እኔም ከጎበኘኋቸው ውስጥ በአንዱ የተዘጋ ገዳም ውስጥ ያገኘኋቸው አስጎብኚ ኤርትራዊ ካህን ብዙ እንዳሉ አረጋግጠውልኛል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ጣሊያን በነበርኩበት ጊዜ ኢትዮጵያውንና ኤርትራውያን በጋራ የሚያስቀድሱበት የግብፆች ቤተ ክርስቲያን ነበር፡፡ በእ.ኤ.አ. 2000 በተካሄደው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞች ቤተ ክርስቲያኑን ለቀው ወጥተው ሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተጠግተው በፈረቃ እምነታቸውን ሲያከናውኑ አይቻለሁ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ይህንኑ ችግራቸውን ለሚላን ከንቲባ አመልክተው መሀል ፒያሣ ላይ ለሃያ ዓመታት ተዘግቶ የኖረ ቤተ ክርስቲያን አስከፍተው አስጥቷአቸዋል፡፡ የቅዱስ ገብርኤል ታቦተ-ሕጉ ከሮም መጥቶ ተመርቆ ሲገባ በቦታው ነበርኩ፡፡ ፅድት ያለ ሰፊ ግቢና የምድር ቤት አዳራሽ ያለው የሚያምር ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ጊዜ በአገልጋዮችና ተገልጋዮች እጥረት መዘጋቱን ሳይ ምናልባት ዛሬ በአገሬ በየእምነቱ ዘንድ ቤተ እምነቶችን ለማስፋፋት በተከታዮች የሚደረገውን የቦታ ሽሚያና እሽቅድድም እኛ ካለፍን በኋላ ይህ እድል ይገጥመው ይሆን ወይ ብዬ እሰጋለሁ፡፡

ድሮ ሻሸመኔ አዌ ናዖድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አብረን የተማርን በለጡ ከበደ የምትባል ሮም የምትኖር የአገሬ ልጅ ጋብዛኝ ሮም ውስጥ ከጎበኘሁት ሙዚየም ውስጥ አንዱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተገደለበት ሥፍራ ነው፡፡ እዚህ ሙዚየም ውስጥ ከዘጠኝ በላይ የሚሆኑ ክብ ክብ ጥቋቁር ድንጋዮች ዙሪያውን ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህ ድንጋዮች ላይ የሐዋሪያው ጳውሎስ አንገት ሲቀላ በያንዳንዱ

ድንጋይ ላይ እየነጠረ ማረፉን ለማመልከት የተቀመጡ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በጥንት ጊዜ የቄሳር ግዛት ሰፊ ነበርና ከዚያ እስከ መካከለኛ ምሥራቅ ዛሬ እሥራኤል ድረስ ስለነበረ ግብር ከዚሁ ሁሉ ይሰበሰብ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ሀዋርያው ጳውሎስ ከእሥራኤል ምድር ጀምሮ  የመፅሀፍ ቅዱስ ቃልን እየተዘዋወረ በማስተማሩ ተወንጅሎ ሮም ውስጥ ተይዞ ለዚህ ፍርድ እንደበቃ ይነገራል፡፡

ጣሊያን ውስጥ በየቦታው ሲሄዱ አንድ የሚኀበኝ ታሪካዊ ሥፍራ ያገኛሉ፡፡ ሚላን ውስጥ በሎናርዶ ዳቬንቺ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተሳለውን የመጨረሻው እራት (The Last Supper) የተሰኘው ኦሪጅናል ስዕል ቀጠሮ አሲዘው ለረጅም ሰዐት ተሰልፈው ይጎበኛሉ። ቪዲዮ መቅረጽ ክልክል ሲሆን ፎቶ ያለ ፍላሽ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ ፍላሹ የቅርሱን ቀለም ይጎዳዋል በሚል በሳይንስ የተደገፈ ጥንቃቄ ያደርጉለታል፡፡ ፍሎረንስ የተባለው ከተማቸው ሲሄዱ የማይክል አንጄሎ፣ የራፋኤል፣ የዳቬንቺ እና ሌሎች  ዘመን የማይሽራቸውን በ15ኛ ክፍለ ዘመን የሳሉአቸውን ሥዕሎችና የሰሯቸውን ቅርፃ ቅርፆች በተንጣለለው ሙዚየም ውስጥ እየተዘዋወሩ ይጎበኛሉ፡፡ ወደ ፒሣ ከተማ ሲሻገሩ አስገራሚውንና የዘመመውን የ800 ዓመት በላይ እድሜ ባለፀጋውን ፒሣ ታወርን (ሕንፃ) ይመለከታሉ፡፡

ያ ረጅም ሕንፃ እርሶ ከዚያ ቦታ ሳይነቃነቁ የሚወድቅቦት ይመስላል። ነገር ግን  እነርሱ ሲናገሩ ዘሞ የተሠራው ሆን ተብሎ እንደሆነ ይረዳሉ፡፡ በወቅቱ በዕድሜ ብዛት አንዳንድ አካሉ የመሰነጣጠቅ

አደጋ አጋጥሞት በረጃጅም ሽቦ ተወጥሮ አይቻለሁ፡፡



እነዚህ ሥራዎች የሀገሬው ጠቢባን የብዙ እውቀት ባለቤት እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ለምሣሌ ዳቬንቺ ከሥዕል ሙያው ባሻገር የሥነ ሕንፃ (አርክቴክቸር)፣የሥነ ፈለክ፣ የምንድህስና፣ የሕዝብ አስተዳደርና ሌሎች የብዙ ጥበብና እውቀት ባለቤት ነበር፡፡ የሥነ ፈለኩ ተመራማሪ አስተሳሰቡ ከጊዜው በመቅደሙ በተለይ ስለ ፀሐይና መሬት ዙረት ባቀረበው ፍልፍስና ነክ አስተሳሰቡ ዙሪያ

ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጋር በመጋጨቱ የተጋዘው ጋሊሊዮ ጋሌሊ ጣሊያናዊ መሆኑንም አትዘነጉትም ብዬ ነው፡፡ ጋሊሊዮ ከኖረበት 77 ዓመት ዕድሜ ዘመኑ ውስጥ ዘጠኙን ዓመት በቤት ውስጥ በቁም እስር ነው ያሳለፈው፡፡ ይህ ሊቅ የብዙ የፊዚክስና ሂሳብ መላምትና ቀመሮች ባለቤት ነው፡፡

በአንድ ገዳም ጉብኝት ያየሁት በፀሐይ ጥላ የሚቆጥር ሰዓት በጣም ይገርማል፡፡ ከሕንፃው አናት ፀሐይ የሚገባበት ክብ ቀዳዳ ተበጅቶለታል፡፡ በዚያ የሚያልፈውን የፀሐይ ጥላ ዙረት እየተከተሉ ሰዓቱ ስንት እንደሆነ መሬቱ ላይ ያነቡታል፡፡ በሌላ አንድ የቤተ መንግስት ቦታ የነገሩኝ በወቅቱ ፈረንሣይ ጣሊያንን ወግቶ አሸንፎ በቅኝ ይዞአት ነበረ፡፡ የአገሩ ገዥ ናፖሊዮን ይተኛበት ከነበረው ጠባቡ ዋሻ ውስጥ መኝታ ቤቱ አልጋው ግርጌ የተቦረቦረ ነገር ይታያል፡፡ ይህ የሆነበት ናፖሊዮን አጭር ስለነበርና ሚስቱ ወይም ፍቅረኛው ረዥም ስለነበረች የሷ እግር ከአልጋው እየተረፈ የቦረቦረው ነው ብለው ትንሽ ያስፈግጉአችኋል፡፡

በትምህርት ቤት ውስጥ ካገኘኋቸው ኘሮፎሰሮች አንዱ ኘሮፎሰር ማውሪ ይባላሉ (አፈሩ ይቅለላቸውና) ኢትዮጵያ ውስጥ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በሞርጌጅ ባንክ ውስጥ ሥራ ተቀጥረው ይሰሩ እንደነበር አጫውተውኛል-መጽሐፍትም ጽፈዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ቢሮአቸው እየተገናኘን እንወያይ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነትን እንዴት ያዩታል ብዬ በጥያቄ መልክ አንስቼባቸው

ነበር፡፡ እውነተኛ ውስጣዊ ስሜታቸውን ሲገልፁልኝ “ያ ጦርነት“ አሉኝ “እብደት የወለደው ሀገርን ለውድቀት የዳረገ ሥራ ነው፡፡ ያ ሁሉ የሰው፣ የማቴሪያል እና ጊዜ ሀብት ለደቡብ የኢጣሊያ ግዛቶቻችን ልማት ውሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ከሰሜኑ የጣሊያን ግዛት ጋር የምናየውን ሰፊ የእድገት ልዩነት ባልነበረ” አሉኝ፡፡ ደቡቧ ሲሲሊ ግዛት የማፊያ ወንጀለኞች መፈልፈያ ሆና አትቀርምም ነበር በማለት በቁጭት ጨምረው ነገሩኝ፡፡ በእርግጥ በሁለቱ መሀከል በትምህርት በመሠረተ ልማትና ቁሳዊ ሀብት ልዩነቱ እጅግ ጐልቶ የሚታይ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ሚላን በአንድ ዓመት የትምህርት ቆይታዬ ከተለያዩ 49 ዩኒቨርሲቲዎችና ሀገሮች የመጡ ኘሮፎሰሮች አስተምረውናል፡፡ በተጨማሪ ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እየወሰዱን ትምህርታዊ ሴሚናሮች ይሰጡንና መሥሪያ ቤቶች ያስጎበኙን ነበር፡፡ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ከብዙ አዋቂዎች ተሞክሮና ጥበብ ለመማር ብዙ እድል ይሰጣል፡፡ የተማሩ ዜጎቻቸውም በአገራቸው ጉዳይ በዕውቀታቸው መንግሥትን ያማክራሉ፡፡ የትምህርት ቤታችን ዋና ዲን የነበሩት ፕሮፌሰር ጋራቤሎ በየሰሳምንቱ ዓርብ ማታ ወደ ሮም በአውሮፕላን ይሄዱና የሳምንቱን መጨረሻ በኢኮኖሚ ጉዳዮች ከአገሪቱ ኢኮኖሚ ካውንስሉ ጋር በመሆን ለአገራቸው የድርሻቸውን ተወጥተው ይመለሳሉ፡፡ ይህን ሰኞ እለት ባጋጣሚ ረፍዶባቸው ሲመጡ ነው ክፍል ውስጥ የነገሩን፡፡

ጣሊያኖች ሲያወሩ ጮክ ብለው በእጃቸው ጭምር ነው፡፡ ቤተሰባዊ ግንኙነታቸውም እጅግ ጠንካራ ነው፡፡ ከአያት እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ተሰባስበው አንድ አካባቢ መኖርና መጠያየቅ ጠንካራ ባህላቸው ነው፡፡ ጐረቤታሞች ወይም ጓደኛሞች ተገናኝተው ለማውራት እራት ወይም ምሣ ላይ ይቀጣጠሩና ከአንድ እስከ ሶስት ሰዓት ለሚደርስ ጊዜ ሆቴል ውስጥ እየበሉና እየጠጡ ያወራሉ፡፡ እርግጥ ሂሣብ በግል ሊሆን ይችላል፡፡ በማዕዳቸው ውስጥ ፓስታና ወይን ጠጅ የዘወትር የማዕድ አድማቂዎች ናቸው፡፡ ወይን ጠጅ እንደኛ ጠላ በየቤቱ ሁሉ ይጠመቃል፡፡ ጣሊያን ዛሬ ላይ በኮሮና ቫይረስ የደረሰባቸው ከፍተኛ ጥቃት ከዚህ ቤተሰባዊ ቅርርብ የመጣ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡

ሰውን ለመርዳትም እጅግ ይተጋሉ፡፡ ብዙ ስደተኛን ተቀብለው ያስተናግዳሉ፡፡ ከአፍሪካ ከመካከለኛ ምሥራቅ እና ከምሥራቅ አውሮፓ እና ሌሎች ሀገሮች የፈለሱ ስደተኞችን ያኖራሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በቴሌቪዥን እንደምንመለከተው በባህር የሚመጡ ስደተኞችን ከመስመጥ አደጋ ለመታደግ ሲታገሉ እናያለን፡፡ ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች እንደ መሸጋገሪያም ስለሆነች የብዙ አፍሪካና መካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች ስደተኞች ምርጫቸው ነች፡፡ በቀይ ባህርና ሜዲቴሬያንያን ባህር እየተሻገሩ የሚጎርፉ ስደተኞች በብዛት ያጨናንቋታል፡፡ አንቺ በርሽን መዝጋት አቅቶሽ ነው ለኛ ችግር የሆንሽው በማለት ከብዙ የአውሮፓ ሀገሮች ወቀሳ ሲቀርብባት ይደመጣል፡፡

ለኔ የደግነት ቅርብ ምስክሬ አስተማሪዬ ኘሮፌሰር ላውራ ቪጋኖ ናት፡፡ እዚያ ለትምህርት በሄድኩ ጊዜ የተማሪዎች ዲንና አስተማሪያችን ነበረች፡፡ በቆይታዬ በጣም ተቀራርበን ነበርና በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ለማሳደግ ያመጣችው ልጅ እንዳላት አጫወተችኝ፡፡ ማሞ ወይም ማሲሞ (በጣልያን ትልቅ እንደማለት ነው) ገና በ6 ወሩ ከእኋለ ማውታን እንዳመጣችው ነገረችኝ፡፡ የሀገሩን የኢትዮጵያ ቋንቋ ቢለምድ ደስ ይለኝ ነበርና እንዳንተ ሰው ሳገኝ ላስተዋውቀው እሞክር ነበር፡፡ ታዲያ ልጅ በመሆኑ ቋንቋውን ከለመደ ወደ አገሩ የምመልሰው መሰለውና ስጋት ገባው ስለዚህ ተውኩት አለችኝ፡፡ ሆኖም ይህንኑ ስጋቱን ለመቅረፍ ወደ ሀገር ቤት ከተመለስኩ በኂላ በተደጋጋሚ ከቤተሰቡ ጋር አመላልሳው እሱም አድጐ ስጋቱ ተቀረፈ፡፡ ይህች ሰፊ ለጋስ ልብ ያላት ጣሊያናዊት እዚህ ሀገር እኔን ጨምሮ ለብዙ ኢትዮጵያውያን የትምህርት ዕድል ከማመቻቸት ጀምሮ በኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ውስጥ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በመመስረት ለልማት ሥራው እንደ አማካሪ ሆና ታገለግላለች፡፡ እሷና ባለቤቷ ማሪዮ ከወለዷት ሴት ልጃቸው ማሪያ እና ካሳደጉት ማሞ ጋር አብረው በመጡ ቁጥር እንደቤተሰብ እንጠያየቃለን፡፡

የሷ ልግስና በእኔ አማካኝነት ለቀድሞ የሥራ ባልደረባዬም ተርፏል፡፡ ይህች ልጅ ድሮ በቤቶችና የገንዘብ ቁጠባ ባንክ አንድ ክፍል ውስጥ አብረን እንሠራ ነበረ፡፡ ተወልዳ ያደገችውና የተማረችው

ደጃች ውቤ ሰፈር ሥራ የጀመረችውም እዚሁ አዲስ አበባ ነበረ። በእ.ኤ.አ.1998-2000 በተፈጠረው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ኤርትራዊ ነሽ ተብላ ከሥራ ገበታዋ ላይ አንስተው ከእናትና እህቷ ነጥለው ወደ ማታውቀው አሥመራ ላኳት። ከብዙ እንግልት በኂላ ባጋጣሚ እዚያ ተወርሶ የቀረ የቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ ቅርንጫፍ ነበረና አሥመራ ውስጥ ሥራ ቀጠለች። በወቅቱ ከሶስት ኤርትራውያን ጋር በጣሊያን አብረን እንማር ነበር-እንዲያውም ፀጉሬን እነርሱ ነበረ የሚያስተካክሉኝ። እነዚህ ልጆች ያውቋት እንደሆነ ጠየኳቸው። ከቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ ከመጣው ከአንደኛው ጋር አብረው እንደሚሠሩ ነገረኝና የፖስታ አድራሻዋን ሰጠኝ። ደብዳቤ ጻፍኩላት። በምላሹ ግን ትልቅ ጥያቄ አቀረበችልኝ። በሚቻልህ ሁሉ ለምርቃትህ እንድገኝ አድርገኝ የሚል ነበር። አባቷ አዲስ አበባ ኖረው ያለፉ እዛ ብዙ የምታውቀው ዘመድ እንደሌላትና ጭንቀቷን ስገነዘብ ለመርዳት ተነሣሁ። ኘሮፌሰሬን አማከርኳት። እሷም ኤርትራ ለሚገኘው የጣሊያን ኤምባሲ በኔ ስም የግብዣ ወረቀት ፃፈችልኝ። በቢሮ ፀሀፊዋ በደጓ እማማ ማሪያ ፒያ አማካኝነት ለኤምባሲው በቀጥታ ፋክስ አስደረኩላት። ከብዙ ውጣ ውረድ በኂላ ተሳክቶላት ለምረቃዬ እለት ሚላን ተገኘች። ዛሬ በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪ ነች። ምስጋና ለደጋጎቹ ይሁን!!

## ፰ ጋና የመቻቻልና የደቅርታ ሀገር

የዛሬዋ ጋና በምዕራብ አፍሪካ ከምድር ወገብ አጠገብ የምትገኝ ሲሆን፣የጋናና ሎንዶን ሰዐት በእንግሊዝ ግሪንዊች ሚን ታይም (GMT) አቆጣጠር እኩል ነው:: በጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ በአንድ ጎኗ አትላንቲክ ውቅያኖስ ሲያካልላት በሌላው በኩል ናይጄሪያና ቡርኪናፋሶ ያዋስኗታል:: ጋና በውቅያኖሱ በኩል ለአሜሪካ በጣም ትቀርባለች:: የአየር ንብረቷም ሁለት ነው:: ቀዝቃዛና እስከ 30 ዲግሪ ሴንትግሬድ የሚደርስ ደረቅ አየር ነው:: ጋና ከ7ኛ እስከ 13ኛ ክፍለ ዘመን ድረስ ባለው ጊዜ የዛሬዎቹን ማሊ ማውሪታኒያና ሴኔጋልን ጨምሮ ቆይቶ የማሊ አገዛዝ ጠንክሮ በመውጣት ቦታዋን እስካስለቀቃት ድረስ ሰፊ ግዛት የነበራት ናት:: በወቅቱ የነበረው ገዢ ወራሪው ንጉሥ ወይም ጋና (Warrior King or Ghana) ይባላል::

ከ2000 ዓመታት በላይ ከአፍሪካውያን ጋር በጦርነት ስታሳልፍ ከዚያም ለጥቆ በመጡት የተለያዩ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ስትተዳደር ኖራለች:: ከሀያኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በእንግሊዞች ቅኝ ግዛት ተይዛ በነበረችበት ዘመን ጎልድ ኮስት (የወርቅ ዳርቻ) ትባል ነበር:: ጎረቤቷን አይቮሪ ኮስት ወይም በቅኝ ገዢዋ ቋንቋ ፈረንሳይኛ እንደሚጠሯት ኮት ዲቯር እንደዚሁ የዝሆን ጥርስ ሀገር ይሏታል::

ጋና ከአፍሪካ አገራት ከቅኝ አገዛዝ ነፃነትን በመቀዳጀት (እ.ኤ.አ 1957) ቀዳሚ ሀገር ናት። ጋና በዓለም በሰላማዊነት መለኪያ (Peace Index) በመጀመሪያ ረድፍ ላይ የምትገኝ ሲሆን፣ከዓለም ትልቁ ሰው ሰራሽ የቮልታ ሀይቅ የሚገኘውም እዚያ ነው። ከእንግሊዞች ነፃ ለመሆን ጋናውያን ትግል የጀመሩት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከእንግሊዝ ጎን ሆነው ተዋግተው የተመለሱት ወታደሮች ባነሱት የነፃነት ጥያቄ ጥንስስ መሠረት ነው። ነፃነታቸውን ያገኙት ከብዙ ድርድርና ውጣ ውረድ በኂላ ነበር። በወቅቱ ከታጋዮችና ተደራዳሪ ወገኖች አንዱ የሆኑት ከነፃነት በኂላ መሪዋ ኩዋሜ ኑክሩማህ ይገኙበታል ።

የ30 ሚሊዮን ሕዝብ ሀገር የሆነችው ጋና በቅድሚያ ነፃ እንደወጣ ሀገር ለቀሩት አፍሪካውያን ወንድሞቻቸው የነፃነት ትግል በአጋርነት በመቆም በመሪዋ ክዋሜ ንኩሩህማ አማካኝነት ፓን አፍሪካኒዝምን በግንባር ቀደምትነት መርተዋል። ከኢትዮጵያ ጎን በመሆንም የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በመመስረትም ብዙ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ለዚህ አስተዋፅኦቸው መታሰቢያ በአሁኑ አፍሪካ ህብረት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለመሪያቸው ክዋሜ ንኩሩህማ መታሰቢያ ሀውልት ቆሞላቸዋል። በእርግጥ በቅርቡ ለኛም መሪ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘግይቶም ቢሆን እዛው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሀውልት ቆሞላቸዋል።

ጋናውያን እንደ አንዳንድ በምዕራብ አፍሪካ እንዳሉት ሕዝቦች በተለይ እንደ ናይጄሪያውያን ሲያወሩ ብዙ ድምፃቸው ጎላ ብሎ አይሰማም።

በባህሪያቸው ረጋ ያሉና ሰላማዊ ከመሆናቸውም በላይ ትምህርትም የዘለቃቸው ናቸው። ጋና ውስጥም የእንግሊዞች የትምህርት ሥርዓት ተዘርግቶ ይገኛል። በዚህም ሥርዓት የተማሩና ለትልቅ ሃላፊነት የበቁ ብዙ ጋናውያን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ጭምር ይገኛሉ። በአንድ ወቅት የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ ሆነው ያገለገሉትን ኮፊ አናንን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ዩኒቨርስቲዎች ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

ጋና ካሏት ትልልቅ ከተሞች ኩማሲ እና አሻንቲ ግዛቶች ይገኙበታል። በአሻንቲ ወርቅ በስፋት ይመረታል። በቅርቡም ነዳጅ እንዳገኘችም ይወራል። በአንድ ወቅት በኢኮኖሚ እድገቷ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ስትንቆለጳጰስ ነበር። ለአፍሪካ እንደማሳያ (Success Story) ተደርጋ ትወሰድ ነበር። በድርጅቱ የተነደፉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አርምጃዎችን ወስዳ ነበር። ከተወሰዱት እርምጃዎች ውስጥ የአገሪቱ ገንዘብ ሴዲ (Cedi) ከአሜሪካ ዶላር ጋር ያለው የምንዛሪ መጣኔ እንዲስተካከል ተብሎ እኔ እዛ በነበርኩ ጊዜ አንዱ ዶላር እስከ 80 ሴዲ ደርሶ ነበር። ታዲያ እንዲህ የሾቀውን ገንዘባቸውን ለመመንዘር ገበያ ውስጥ ገብተን ነበር። መንዛሪዎች ገንዘቡን በፌስታልና በማዳበሪያ ከረጢት ሞልተው በየሱቁ በረንዳ ላይ ተኮልኩለው በነፃነት ይገበያያሉ። አንድ መቶውን ዶላር መንዝሬው ከአምስት ቀን በላይ ቆይቼ አልጨረስኩትም። ቆይቶ እንደሰማሁት ከዓለም አቀፉ ድርጅት ጋር የነበረው የጫጉላው ጊዜ አብቅቶ

የተባለው ውጤትም ብዙሀኑን ሳያረካ ወደ ራሷ ቤት አፈራሽ እርምጃ ገብታ አሁን ላይ ምንዛሪው ከአምስት እስከ ሰባት ሴዲ እንደሆነ ነው የሰማሁት።

ጋና በጥንት ጊዜ አፍሪካውያን በባርነት ወደ አሜሪካ ሲጋዙ በመተላለፊያነት አገልግላለች። በእኛው የሀገር ልጅ በፕሮፌሰር ሀይሌ ገሪማ የተሰራውና ይህንኑ ሁነት የሚያሳይ «ሰንኮፋ» የተሰኘው ፊልም መነሻው ይህቺው ጋና ነች። ጋናውያን ከሚያስጎበኙት ቦታዎች አንዱ ይኸው የባሪያ ንግድ የሚካሄድበት ሥፍራና ወደ አሜሪካ ከመሻገራቸው በፊት ማቆያ ቦታ ሆኖ ያገለገለውን ነው። በመርከብ እየተጫኑ ለአሜሪካ ስኳር እርሻዎች ነፃ ጉልበት ለማበርከት እየተጋዙ የአፍሪካ ልጆች ብዙ ግፍ ተውሎባቸዋል።

የጋና ዋና ከተማ የሆነችው አክራ መሀል ከተማ ውስጥ እነዚህን ታሪካዊ ቀበሌዎችን ያስጎበኛሉ። አሮጌ መንደሩ እንዳለ የድሮ መልኩን ሳይተው በወግ ተጠብቆ የቆሙ ቀጫጭን ከበሮዎች ተደርድረው በዱላ ያለማቋረጥ እየደበደቡ ያለ ድምፃዊ ሙዚቃቸውን እያስደመጡ ያስጎበኟችኋል። ይህ ከበሮ ላይ የተመሰረተው ሙዚቃቸው መለያቸው እንደሆነ ከታሪክ መፅሐፍ አንብቤአለሁ።

ጋና ጎዳናዎች ላይ ከእንጨት የተሠሩ ትላልቅ በተለይ የአሣና አውሮፕላን ቅርጽ ያላቸው የእጅ ሥራ ውጤቶች ያያሉ። ብዙዎቹ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለው ስለሚያምኑ ለመቀበሪያ የሚሆን

እንደ ሰውዬው ታዋቂነት የተለያየ መጠን ያለው የአስከሬን ሣጥን ሆኖ የሚያገለግል ተምሳሌት የእደ ጥበብ ውጤት ነው። ታዲያ ጠጋ ብለው ከመረመሩት እንዴት በጥንቃቄ እንደተጠበቡበት ይገነዘባሉ። እኔም ለማስታወሻ የአንዲት ልጅ ያዘለች ሴት ምስል የተቀረጸበት ጣሊያን አብረን የተማርን ሰባስቲያን የተባለ ልጅ በመኪና ከተማዋን ሲያስጎበኘን ትራፊክ መብራት ላይ ገዝቼ ይዤ መጥቻለሁ።



በጣሊያን ትምህርታችንን ማጠናቀቂያ ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው ምረቃ በዓል ላይ ንግግር እንዲያርግ የወከልነው የክፍላችን ተማሪ የካሜሩን ተወላጅ ገማንዜ ሲናገር ተራሮች ብቻ ናቸው የማይገናኙት ብሎን ነበር። እኔም ሁለቱን ጋናውያን ሰባስቲያንና ሳሙኤልን በአገራቸው እንዲሁም ግብፃዊውን

መሀመድን በአሜሪካ ሳገኛቸው እውነቱን ነው የቆመ ሰው ይገናኛል ብያለሁ:: በነገራችን ላይ ከአፍሪካ ከመካከለኛው ምሥራቅና ቻይና በጠቅላላው ከአሥራ ስድስት ሀገሮች ከመጡ 28 ተማሪዎች ጋር የደጉን ጣሊያን መንግሥት ዓለም አቀፉን የነፃ ትምህርት ዕድል አብረን ነው የተቋደስነው::

ጋና ከምትታወቅበት ታሪኳ አንዱ የመንግስት በምርጫ መምጣትና መሄድ ሥርዓት አንዱ ነው:: በብዙ የአፍሪካ ሀገራት ቀደም ባለ ጊዜ አብዝቶ ይስተዋልና ይሰማ እንደነበረው የመንግስት ግልበጣ ለረጅም ጊዜ የጋና ታሪክ አካል አልነበረም:: ሆኖም በአንድ ወቅት አንድ የወታደር መኮንን የተመረጠን መንግስት ገልብጦ ሥልጣን ይዞ ነበር:: በዚህ የተቆጡት የአየር ሃይል ተዋጊ ጄት አብራሪ የነበሩት መቶ አለቃ ጄሪ ሮውሊንግ ይህንኑ መሪ አባረው ሥልጣኑን ለትንሽ ጊዜ ይዘው ቆይተው ለሲቪል አስተዳደር መልሰው አስረክበው ነበር::

መቶ አለቃው ትንሽ ቆይተው ሲያዩት የሲቪሉ አስተዳደር እንዳሰቡት ጋናን በቅጡ አላስተዳደረም ብለው  ሥልጣኑን መልሰው ነጥቀው እራሳቸው ያዙት:: ለሕዝቡ አስበው ይሁን ወይም ያቺ ለትንሽ ጊዜ የቀመሷት የሥልጣን አረቄ ሱስ ሆኖባቸው አይታወቅም ብቻ

በድጋሚ መንበሩ ላይ ተቆናጠው ለአስራ ሁለት ዓመታት ቆይተው ምርጫ እንዲደረግ ፈቀዱ፡፡ ሁለት የምርጫ ዘመን ተመርጠው በጠቅላላው ከሀያ ዓመታት በኋላ ሥልጣኑን በምርጫ ላሸነፉት ለህግ ባለሙያው ጆን ኩፎር ሲቪል መንግስት አስረክበው እዚያው አክራ ውስጥ በሰላም ይኖራሉ፡፡

እ.ኤ.አ. 2002 ዓ.ም. እዛ የተገኘሁት በአንድ በከተማ ነክ ጉዳይ ላይ የሚመክር ስብሰባ ለመካፈል ነበር ፡፡ በአንደኛው ቀን ከስብሰባው ወደ ማረፊያችን በመኪና ሲመልሱን በአጋጣሚ ከጎኔ ተቀምጠው የነበሩት ጋናዊ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር በአንድ ሰፈር ስናልፍ ይህ የቀድሞው መሪያችን ጄሪ ሮውሊንግ መኖሪያ ነው ብለው መንገድ ዳር ያለ ቪላ ግቢ አሳዩኝ፡፡ በወቅቱ ለኔ ትንሽ አስገራሚ ሆነብኝና በሰላም እዚህ ይኖራሉ አልኳቸው? አዎ አሉኝ፡፡ እኔ ግን ያልለመድኩት ነበርና አድናቆቴን ሳልሸሽግ ገለጥኩላቸው፡፡ በአገሬ አንዳንድ በደል ያደረሱ መሪዎች ወይም አድርሰዋል ተብለው የተጠረጠሩ መሪዎች መጨረሻቸው እስር ቤት፤ ስደት ወይ ሞት ነው አልኳቸው፡፡ ሲመልሱልኝ እኛ ጋናውያን የትናንቱን ማስታወስ አንፈልግም በይቅርታና በመቻቻል ነው የምናምነው ብለው ግርምቴን አበዙት፡፡

እዛ በነበርኩበት አጋጣሚ ፕሬዜደንት ኩፎር ለመስክ ጉብኝት ወደ ገጠር ሄደው ሲመለሱ የሚጓዙበት መኪናቸውን ጭቃ ይዞት ሲገፋ በእግራቸው ሲጓዙ ዜና ሆኖ ተመልክቻለሁ፡፡

በተካፈልኩበት ስብሰባ ላይ በክብር እንግድነት ከተገኙት መሀከል የጋናን የባህል ልብሳቸውንና የክብር መቋሚያቸውን ይዘው ከፊት ረድፍ ላይ ተቀምጠው ሳይ ማንነታቸውን ጠይቄ የመሬት ባለባቶች እንደሆኑ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ጋና ያላት የመሬት ሥሪት እንደኛ የቀድሞው ሥርዓት በመሬት ከበርቴዎችና በጎሣ መሪዎች የተያዘ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ስብሰባውን የከፈቱት የከተማ ልማት ሚኒስቴሩ በንግግራቸው መግቢያ የተገኙትን እንግዶች ሲዘረዝሩ ስማቸው ሲጠቀስ የሰማሁት በሌላው ዓለም አራተኛ ረድፈኞች (መንግስት) ተብለው የሚታወቁት የሚዲያ ባለሙያዎች “ጓዶች” ሲሉ «Friends from The media» ሰምቼ ተገርሜአለሁ፡፡ በወቅቱ አገሬ ውስጥ ሲሳደዱ አይ ስለነበር ነው፡፡

በዚህ ሰብሰባ የነበሩት የናይጄሪያ የተከበሩ ፕሮፈሰር የቀለዱትን ቀልድ ባካፍላችሁ ደስ ይለኛል፡፡ ፕሮፌሰሩ ሲናገሩ በአንድ ወቅት ሰማይ ቤት የዓለም የተለያዩ መሪዎችና ሰዎች ተገናኙ፡፡ ሁሉም ሰማይ ቤት እንደደረሱ አይናቸው ያረፈው አንድ የሚያምር በቦታው ያለ ብቸኛ ቪላ ቤት ላይ ነበር፡፡ የአሜሪካው መሪ ቀድሞ

እንዲህ ሲል ተናገረ “ይህ ማረፊያ የሚገባው ለኔ ለዓለሙ ሃያል መሪ ነው” አለ፡፡ የሮማ ካለቶሊካዊት ጳጳስ “ይሄ ቤት የሚገባው ለቢሊዮን ነፍስ ብቸኛ አባት ለሆንኩት ለኔ ነው” አሉ፡፡ ይቺን ቪላ ቤት ሁሉ ለራሱ ተመኛት የኬንያው ማታቱ ታክሲ ነጂው ሳይቀር፡፡ በመጨረሻ እግዚአብሔር ተናገረ “ለሁላችሁም አይገባም የሚገባው ለዚህ በየቀኑና በየደቂቃው ስሜን ሲያስጠራ ለሚውለው ታክስ ነጂ ነው” አለ፡፡ እንደሚታወቀው እነዚህ ማታቱ ታክሲዎች ሰው በሰው ላይ ደርበው  ጭነው ሲከንፉ ነፍስና ስጋ ሲያላቅቁ ነው የሚውሉት፡፡ ታዲያ ተሳፋሪው ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ደጋግሞ እየጠራ ሲማፀን  ውሎ ነው መድረሻው ጋ የሚወርደው፡፡

ጋናውያን በእግር ኳስ እንደ ብዙዎቹ የምዕራብ አፍሪካ አገራት በጣም ጎበዞች ናቸው፡፡ የባንዲራቸው ቀለማት የኛን ቢመስልም ጥቁር ኮከብ በመደቡ ላይ አድርገውበት ቡድናቸውን ጥቁር ኮከብ ብለው ሰይመውታል፡፡ ብዙ የአፍሪካ አገራት ነፃ ሲወጡ የባንዲራቸውን  ቀለማት ሲመርጡ ከኛ ጋር በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ይመሳሰላል፡፡ ምናልባት በነፃነት በመኖራችን አርማችን ተምሳሌት ሆኗቸው ይመስላል፡፡

የጋና እግር ኳስ ቡድን እ.ኤ.አ. ከ1940ዎቹ ጀምሮ በዓለም ዓቀፍ ውድድሮች ሲሳተፍ የኖረ ነው፡፡ ጋናውያን እግር ኳስ ተጫዋቾች

የአካላቸው ጥንካሬ አንዱ ማሽነፊያቸው ነው። በአብዛኛው የሚመገቡት ካሳቫ ተብሎ የሚጠራ ተክል ሲሆን ይህ ካሳቫ ለጡንቻ ጥንካሬና የአጥንት ሥፋት እንደሚሰጣቸው ተገንዝቤአለሁ። ታዲያ ከኛ ጤፍ በሊታዎች ጋር ባታወዳድሩት። ይህ በ80 የዓለም ሀገሮች ከ800 ሚሊዮን በላይ የሚገመት ሕዝብ የሚመገቡት የስኳር ድንች (መጣጢሽ) የመሰለ ከመሬት ሥር የሚበቅል ተክል ነው። በሀይል ሰጪና በቫይታሚን እንዲሁም ሌሎች ማዕድናት የበለጸገ ስለሆነ እጅግ ጠቃሚ ምግብ ነው። ተክሉ መርዛማ ንጥረ ነገር ስለሚኖረው በጥሬው አይበላም።

በተጨማሪ ከኬንያ ጀምሮ እስከ ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ያለውን የበቆሎ ምግብ ባህል እነሱም ይጋራሉ። ኬንያውያን የሚያዘወትሩትን ከበቆሎ የሚሰራውን ዑጋሌ ጋናውያን ሆቴሉ ውስጥ ለብቻዬ ሰርተውልኝ አቅምሰውኛል። ለነዚህ እንግዳ አክባሪዎች እግዚአብሔር ክብረት ይስጥልኝ።

## ፱ የበረሀ ገነት

በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል የምትገኘውን ሱማሌ ክልልን ሳስብ በምናቤ ይታየኝ የነበረው ዝናብ የማይዘንብበትና የዛፍ ዘር የማይታይበት ጭው ያለ በረሀ ነበር የሚመስለኝ መሳሳቴን እስካረጋገጥኩበት ጊዜ ድረስ:: ያጋጣሚ ነገር ይሁን አላውቅም ጎዴ የተቀበለችን ዝናብ አርከፍክፋ ነው:: ከአየር ላይ ሆነን ወደ መሬት ሳይ በየቦታው መሬቱ የዝናብ ውሀ አቁሮ ይዞ ነበር:: ከአይሮፕላን ስንወርድ ቀዩ አፈር ጭቃ ይዟል ግርምቴ ከዚህ ጀመረኝ::

ከአዲስ አበባ 1215 ኪሎ ሜትር ከአንድ ሰዓት ከሩብ የአውሮፕላን ጉዞ በኋላ በዝና አውቀው ከነበረው የሱማሌ ክልል ጎዴ ከተማ ጥቅምት 2005 ዓ.ም. ባጋጣሚ ተገኘሁ:: የሄድኩት ክልሉን ለመጎብኘት ወደዚያ የተጓዘውን በከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን የሚመራውን የባለ ሀብት ቡድን ተቀላቅዬ ነበር:: በርግጥ የወከልኩት ባለሀብቱን የምሥራበት ባንኬን ነው:: ለጉብኝት የሄደውን ቡድን ለመቀበል አውሮፕላን ማረፊያ የተገኙት የክልሉ መስተዳድሩን ጨምሮ የአካባቢው ማህበረሰብ ብዙ ነበር:: በዚህ ጊዜ ከተቀበሉን ውስጥ አንዲት ሙሉ የአበሻ ቀሚስ የለበሱ ሴት ሲጨብጡኝ ሊቀበሉን ከሌላ አካባቢ መጥተው መስሎኝ ነበር:: ቆይቼ እንደተረዳሁት ይህን የጠረፍ አካባቢ ለመጠበቅ ከ1940ዎቹ ጀምሮ ከመሀል ሀገር

የተሰማራው የጦር ሠራዊት አባል የተወሰነው ከጡረታም በኋላ ኑሮውን እዚያው አድርጓል፡፡

የኦጋዴንን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን ብንመረምር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጎረቤት ከፊል ሱማሌን በቅኝ ይገዙ የነበሩት እንግሊዞች ጦርነቱ እስኪያልቅ ኦጋዴንን እንጠቀምበት ብለው ለተወሰነ ጊዜ ከኢትዮጵያ ጋር ውል ገብተው ሰፍረው ነበር፡፡ ፋሽስት ጣሊያንን ከሀገራችን ለማስወጣት በተደረገው ጦርነት እንግሊዞች ረድተውን ከአፄ ኃይለሥላሴ ጋር አብረው ሀገራችን ገብተው ነበር፡፡ በዚህ ቆይታቸው ጊዜ ሀገራችንን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ከጅለው ላለመልቀቅ ብዙ አንገራግረው ነበር፡፡ በወቅቱ በከፍተኛ ዲፕሎማሳዊ ጥበብና ትግል ነው የለቀቁት፡፡ እነዛ ብዙ ያልተዘመረላቸው በጠቅላይ ሚኒስትር ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው የተመራው እነ አቶ አክሊሉ ሃብተወልድ፣ ይልማ ዴሬሳ ፣ መኮንን ደስታ እና ሌሎች በጊዜው የተማሩ ሀገር ወዳድ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ባደረጉት ብርቱ ትግል ነው ይህንን ግዛታችንን የለቀቁት፡፡ ይህን እልህ አስጨራሽና ብዙ የዲፕሎማሲ ጥበብ የጠየቀ ትግል ክቡር አምባሳደር ዘውዴ ረታ “የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት 1923-1948” በተሰኘው መጽሀፋቸው በሰፊው ዘግበውታል፡፡

ሶማሊያ ለሁለት ከተቀራመቷት ከጣሊያንና እንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ በእ.ኤ.አ.1960 ነፃ ወጣች፡፡ ከነፃነት በኋላ መሪዎቿ ለመስፋፋት

በነበራቸው ህልም ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም ጊዜ የወሰደ የድንበር ላይ ፍጥጫና በ1954 እና1969 ዓ.ም. ሁለት ከባድ ጦርነቶች አድርገዋል፡፡ ጄኔራል ዚያድ ባሬ በእ.ኤ.አ. 1969 በወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ እንደ ጀርመን ናዚዎች የበላይ የመሆን ከንቱ ምኞት እርሱንም ተጠናውቶት ነበር፡፡ ሱማሌዎች የሚኖሩበት ሁሉ የሶማሌ ግዛት ነው በሚል ቅዠት በ1969 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ወሯል፡፡ በዚህ ዕቅድ መሰረት ከኢትዮጵያ ኦጋዴንን ከጂቡቲ ቢያንስ ግማሹን ክፍል ከኬንያ የሰሜኑን ክፍል ወደ ሱማሌ ግዛት መቀላቀል ነበር፡፡ ይህንን አካባቢ እዉቁ የኢትዮጵያ ጠበቃ የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም "አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ" በተባለው መጽሀፋቸው ውስጥ በጂኦ ፖለቲካዊ ምርምራቸው በሰፊው ተንትነውታል፡፡ እዚህ ላይ ፕሮፌሰር መስፍንን ባስታወስኩ ቁጥር የሚታሰበኝ ሰው በመርሁ ላይ ፀንቶ ቆሞ ዘመኑን ያሳለፈ ለኔ ትልቅ ተምሳሌቴ እሳቸው ናቸው፡፡ ገዝፈህ ለመታየት ከፈለክ በመርህ ላይ ቁም ይባል አይደል (If You want to look taller stand on your principles)!

እነዚህን ጦርነቶች ለመመከትና ረጅሙን ከሱማሌ ጋር ያለውን ድንበራችንን ለማስከበር እጅግ ጠንካራ የሆነ ዝነኛ የሶስተኛ አንበሳው ክፍለ ጦር በዚያ ከሰፈረ ረጂም ጊዜ አስቆጥሯል፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች የዚህ ክፍለ ጦር አባላት በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ አሻራቸውን አኑረዋል፡፡ የወታደራዊ ደርግ መንግሥት ሲመሰረት

የመጀመሪያው ሊቀመንበር የነበሩት ጄኔራል አማን አንዶም ሚካኤል የዚህ ክፍለ ጦር አዛዥ የነበሩ ናቸው:: እንደዚሁም ለረጅም ጊዜ ሀገሪቷን የመሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ደርግ ሲቋቋም ከዚሁ ክፍለ ጦር ተወክለው የመጡ ናቸው::

ከአምስት የማያንሱ ወንዞች ወደ ሱማሌ ክልል ይፈሳሉ:: ከነዚህ ውስጥ ከኛ አልፈው በበረከታቸው ለጎረቤት ሀገር ሱማሊያ ሕይወት የሚታደጉ ሶስት ታላላቅ ማለት ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌና ዳዋ ወንዞች ይገኙበታል:: የጉብኝቱ ዓላማ ይህን ተፋሰስ ተከትሎ መንግሥት የመስኖ ግድብ በመስራቱ ባለሀብቶች አጋጣሚውን እንዲጠቀሙበትና አካባቢውን በማልማቱ ላይ እንዲተባበሩ ነው:: ይህንን አስመልክቶ በአዳራሽም ውይይቶች ተካሂደዋል::

በጎዴ በተደረገው ውይይት የገረመኝን ባጋራችሁ እወዳለሁ:: ውይይቱን የመሩት ሁለት ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ሲሆኑ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት እየተጋበዙ መልስ ይሰጡ ነበር:: እዚያ ከመደረሱ በፊት ግን ከባለሥልጣናቱ የመክፈቻ ንግግር በኋላ መድረኩን የያዙት የአካባቢ የጎሣ መሪዎች ወይም ኡጋዞች ነበሩ:: በምን ቅደም ተከተል እንደሆነ ባላውቅም የዘጠኙም ጎሣ መሪዎች ወይም ኡጋዞች በየተራ እየተነሱ ያለ ገደብ በቃላቸው ንግግር አንዳንዶቹም ዘፈን ወይም ሽለላ ያሰሙ ነበር:: በዚህ ጊዜ የመድረኩ መሪዎች በጥሞና ከማዳመጥ ውጭ ተናጋሪዎቹን በንግግራቸው መሃል እየገቡ አያቋርጧቸውም

ወይም አያስቆሟቸውም ነበር፡፡ የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህል ማወቅ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ተረድቼበታለሁ፡፡

በአብዛኛዎቹ ኡጋዞች ከተነገረው ውስጥ በአካባቢው ሰላም ለረጅም ጊዜ ባለመኖሩ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ በነበሩ ሶስቱም መንግስታት ዘመን ከልማት ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ነው፡፡ ዛሬ ደስ ብሏቸው መዝፈናቸው ያ ሲናፍቁት የነበረ ሰላም በመመለሱና የልማት ተስፋ በመታየቱ እንደሆነ ነው የተናገሩት፡፡ በርግጥ በአጭር ጊዜ የተሰራውን ልማት ላስተዋለ የጠፋው ጊዜ እጅግ ያስቆጫል፡፡ ክልሉ ከተሰራበት ኢትዮጵያን በሙሉ ሊመግብ የሚችል እምቅ አቅም ያለው ነው፡፡ የቅባት እህል፣ ኦቾሎኒ፣ ጥጥ፣ ቅመማ ቅመም፣ ወ.ዘ.ተ. ያመርታል፡፡ በተጨማሪ ክልሉ ያለው የእንስሳት ሀብት እጅግ ብዙ ነው፡፡ በንፋስ ሃይል የሚሰራ የኤሌክትሪክ ሃይል ሃብቱ ከተሰራበት ከአፍሪካ ትልቁ የሚባል እንደሆነና ለአፍሪካውያን እንደሚተርፍ ተገልጾልናል፡፡ በርግጥ የአይሻ ንፋስ ሐይል ፕሮጀክት መጀመሩን አስተውያለሁ፡፡ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአጠቃላይ 85 በመቶ ያለው ሃብት ገና እንዳልተዳሰሰ ነው ፡፡ ታዲያ ከዚህ የበለጠ የበረሀ ገነት ከወዴት ይመጣል?

ክልሉ በቆዳ ስፋት ከኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ በብዙ ጎኑ ከተለያዩ ጎረቤት ሀገሮች ጋር ስለሚዋሰን ህብረተሰቡ አካባቢውን የሚያዳምጠው በንቃት ነው፡፡ ባለው ሰፊ መሬት ተበታትኖ የሚኖረው የሱማሌ ህብረተሰብ ያለው ግላዊ ነፃነት የበዛ ነው፡፡

ነቃ ያለና ለእውቀት ክፍት የሆነ የአዕምሮ ባለቤት ነው። አትንኩኝ ባይም ነው። በተጨማሪ መረጃ በፍጥነት የሚፈስበት አካባቢ ነው። ጎዴ ውስጥ እንዳየኋቸው ሜዳ ላይ ቁጢጥ ብለው ወይም ብርኩማ ላይ ቁጭ ብለው ሻይ እየጠጡ መረጃ ይለዋወጣሉ።

ከጎዴ በኋላ ድንበሩ ጋ ለመድረስ ገና 700 ኪሎ ሜትር መጓዝን ይጠይቃል። ወደ መጣንበት ወደ አዲስ አበባ የተመለስነው እስከ ጂግጂጋ አዲስ በተሰራው 575 ኪሎ ሜትር በሚረዝመው አስፋልት መንገድ ነው። ታዲያ በመሃል የሚገኙትን ከተሞች በቅደም ተከተል ቀብሪ ደሀር፣ ሸኮሽ፣ ደገ ሃቡርና ቀብሪ በያህ ከተሞችን እየጎበኘን ነው ያለፍነው። ሕዝቡ መንገድ ዳር ወጥቶ ተሰልፎ የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ እያውለበለበ ነው የተቀበለን። ደስታውን በዚህ ብቻ አይደለም የገለጸልን በሰፊው ያዘጋጀውን ድግስ እየተቋደስን ነው የዘለቅነው። በቀብሪ ደሀር በህዝቡና በመስተዳደሩ ትብብር እየተሰራ ያለውን ባለ 3 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን የአውሮፕላን ማረፊያም ጎብኝተናል። ዛሬ ያ ሜዳ ሕዝቡን በማጓጓዝ እያገለገለ ነው። ከዚህ ጉብኝት መልስ በክፍለ ጦሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተደረገልን መስተንግዶ አስደሳች ነበር። በመንገዳችን ላይ በአፋር ያየነው ፕሮሲፒ (Procipi) የተባለው አረም እዚህም ሕዝቡ እንደ ችግር ያነሳው ጉዳይ ነው።

ወደ ማምሻው የክልሉ ዋና ከተማ የሆነችው ጂግጂጋ ገብተን የተዘጋጀውን የምሽት መዝናኛና እራት ተጋብዘን በሰላም ምንም

የማይገኝ ነገር እንደሌለ መስክረን አደርን። በማግስቱ ሀረርን ጎብኝተን ድሬዳዋ አዳር አደረግን። በጧት በድሬዳዋ በኩል የምትገኘውን የሱማሌ ክልል አካል የሆነችው ሺኒሌ ተጎብኝታ ከሰዓት በኋላ ድሬዳዋ ላይ የአራት ቀናት ጉብኝት ማጠቃለያ በሆቴል አዳራሽ ውስጥ ውይይት ተደርጎ በአውሮፕላን የመልስ ጉዞ ሆነ።

በዚህ ውይይት ወቅት አንድ ያነሳሁት ሀሳብ ከባንክ እንደመሄዴ በጎዴ ያየሁትን የባንክ አገልግሎት እጥረት ጉዳይ ነበር። በወቅቱ ከአካባቢ ነዋሪዎች የተረዳሁት በሥፍራው ካለው ብቸኛው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ  አገልግሎት ለማግኘት እስከ ሶስት ቀናት ወረፋ እንደሚጠብቁ ነው። እንደ አስተያየት ያቀረብኩት የግል ባንኮችም ልማቱንና ችግሩን በማቃለል እንዲያግዙ ወደዚያ እንዲገቡ ለጊዜው በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት ገንዘብ በአውሮፕላን አጓጉዘው ስለማያዋጣቸው ያለውን የንግድ ባንክ ገንዘብ  የመያዝ አቅሙን አሳድጎ እሱ በጎዴ ለሚከፈቱት ባንኮች ሁሉ ማዕከላዊ ቋት እንዲሆን ነበር። በዚህ መፍትሔ ይሁን ወይም ፀጥታው በመሻሻሉ ብቻ ዛሬ  ከአስር ያላነሱ ባንኮች ቅርንጫፎቻቸውን በጎዴ ከፍተው ህብረተሰቡን እያገለገሉ ነው።

”ስላንተ ከሰማሁት ያየሁት ከሁሉ በላይ ነው” ነበር ያሉት። በአጠቃላይ እጅግ የተዋጣለት ፕሮግራም ነበር።

# ፲ ቀናሁባቸው

እንዲያው ለመሆኑ በሕይወታችሁ ቅናት ሸው ብሎባችሁ ያውቃል? እኔን ግን በአንዱ ጉብኝቴ ወቅት ባየሁት ነገር ድንገት ብቅ ብሎ መንፈሳዊ ቅናት አንጨርጭሮኛል:: የጎበኘሁት ፕሮጀክት የሚሰራው ቀን በፀሀይ ብርሀን ማታ በባውዛ መብራት 24 ሰዓት ነው:: ሰዉ ማሽኑ ሁሉም ይተራመሳል ለወሬ ጊዜ የለም:: ታዲያ ተቆጣጣሪ ቆሞ አይደለም ያ ሁሉ የሥራ ሠራዊት ደፋ ቀና የሚለው በሀገር ፍቅር ስሜት ነው:: የያዙት እኮ ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው:: የኢትዮጵያውያን ዓይን ሁሉ እንደሚያያቸውና እንደሚከታተላቸው የተገነዘቡ ናቸው:: በዚያ ላይ በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩት ሠራተኞች ውስጥ 95 ከመቶ የሚሆኑት ወጣቶች መሆናቸውን ሳስብ ነው ምነው አንዳቸውን በሆንኩ ያልኩት:: አሁን የኔ አሟሟት አሟሟት ነው ወይ...እንዲህ ያለ ታሪክ አንድ ቀን ሳልሰራ ነው ያሰኘኝ:: ብቻ... "የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው" እንዲል መጽሀፉ::

ይህኛው ጉብኝቴ አሁንም የባንካችን ሀላፊ ስላልተመቻቸው እጄ ላይ በወደቀ ዕድል አጋጣሚ ነው:: ከሱማሌው ጉብኝት አንድ ዓመት በኋላ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት አዘጋጅነት በአሶሳ ከተማ የሚካሄደውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀንን ምክንያት አድርጎ የቀጠለ ነው:: በዚሁ አጋጣሚ የሕዳሴ ግድብ

ጉብኝትም አብሮ ተዘጋጅቷል። አሁንም ባለ ሀብቶች ተጋብዘዋል። እኔም የባንካችን ደንበኛ የሆኑ ትልቅ ባለሀብት አጋጥመውኛል። ታዲያ የእሳቸውን ኮት ጫፍ ይዤ ጉዞዬ የተመቸ ሆኖልኛል።

የብዙ ዘመን የቤት ሥራችንን ለመስራት የተነሳነው በሃሳብ ተረግዞ መሬት ላይ ወርዶ መልክና ቅርጹ ተነድፎ ሊወለድ ሲጠብቅ እንኳ ግማሽ ክፍለ ዘመን አልፎ ነው። ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሤ የተሰራውን የመጨረሻ ንድፉን በተረከቡበት ጊዜ "ዛሬ ግድቡን ለመሥራት ጊዜና አቅሙ ባይፈቅድልንም መጪው ትውልድ ይሰራዋል" ብለው ያደረጉት ትንቢታዊ ንግግር ዛሬ ተፈጽሞ ለማየት በቃን። በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ለግንባታው አሻራችንን ያኖርን እኛ የዚህ ታሪክ ተካፋይ የሆንን የዛሬው ትውልዶች በእርግጥ ዕድለኞች ነን።

በዘፈኑ በቅኔውና በትርክቱ ዓባይ ተገድቦ ለኛ ጥቅም እንዲውል ሲቀሰቅሱና በሕዝቡ ውስጥ ቁጭት ሲፈጥሩ የኖሩ ሁሉ እነርሱም ምስጋና ይገባቸዋል። ለሁሉም ጊዜ አለው እንዳለው ጠቢቡ ሰለሞን እግዚአብሔር በፈቀደው ጊዜ ይሄው የምናየውና የምንዳስሰው መሬት ላይ ያለ እውነት ሆኗል። ቀጥሎ ፍሬውን ስንቋደስ ደግሞ ሆድ የሚሞላ በረከት ይሆናል። ለሁሉም ሰላም ዕድሜና ጤና መለመን ነው።

የሀገሪቱ መሪዎች፣ ታላላቅ ባለሥልጣናትና እንግዶች በተገኙበት የሥራው አንድ ወሳኝ ምዕራፍ የሆነው የዓባይ ውኃን አቅጣጫ ማስቀየርና የግድቡን ከፍታ በአንድ ቀን ከ800 ሜትር ኩብ በላይ ኮንክሪት በመሙላት በዓለም ሪከርድነት የተመዘገበበት ዕለትን ለማዘከር የግድቡ አናት ላይ በተዘጋጀው ሥነ ሥርዐት ላይ ነው የታደምኩት፡፡ ብዙ ንግግርና ግጥም የቀረበበት የሀገሪቱ እውቅ ድምፃውያን ያቀነቀኑበት እጅግ አስደሳችና አዝናኝ ምሽት ነበር፡፡

ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ይሆናል አብረን ማረፊያ ክፍል ከተጋራን አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሹም ጋር ሥነ ሥርዐቱን አገባደን ወደ ማረፊያችን የሚወስደንን ሰው ምግብ ፍለጋ እንዲረዳን አስቸገርነው፡፡ የምግብ ካፊቴሪያው ዝግ ስለሆነ በግል ሆቴል ከፍተው የሚያስተናግዱበት ቦታ ወሰደን፡፡ ስንደርስ ከሥራ ሺፍት የወጡ እነዛ ሳተናዎች አዳራሹን ሞልተውታል፡፡ ትርምሱ ሌላ ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ዘጠኝ መቶ ኪሎ ሜትር ከቤተሰባቸው ርቀው በዚያ ከፍተኛ ሙቀት ቀን ከሌት የሚደክሙትን ስናይ ለጉብኝት ከቤቱ ለወጣ ሆዳችን ብለን ከነርሱ ጋር መሻማቱ አሳቀቀን፡፡ እንደምንም ኳሮ ላይ አንድ ጥግ አገኘንና ትዕይንቱን እየተከታተልን ርቦን ስለነበርም እራት ይሁን የቁርስ መክሰስ ብቻ ቦዘና ሹሮአቸውን ተጋራናቸው፡፡

ጉባ ዓባይ የሚገደብበት ቦታ ከሱዳን ድንበር 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ቆመን ነው ይህን ሁሉ የምነግራችሁ፡፡ ከአስራ አራት

ከሚበልጡ ገባሮቹ ከየቦታው የሰበሰበውን ውሀና አፈር ይዞ ከሀገር ሊወጣ ሲል የተያዘበት ቦታ ነው ጉባ። ጥናቱና ዲዛይኑ እ.ኤ.አ. 1960 አካባቢ መሰራቱን ተረድቻለሁ። አቧራው ተራግፎ ትናንሽ ማሻሻያዎች ተደርጎበት ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ወደ ሥራ ሲገባ ዘመን የተሻገረው የዲዛይነሮችም ዕውቀትና ሥራ በጣም ያስገርማል። እኛም ይህን ልንመሰክር በቃን። ይኸው የኛም ልጆች ከውጭ ሀገሮች ከመጡ ሥራ ተቋራጮች ጋር ሆነው መሬት ላይ አወረዱት። ለሁሉም ክብር ቆባችንን እናነሳለን።

" እኛ አሁን ለመገንባት አቅሙ ላይኖረን ይችል ይሆናል ፤ ነገር ግን ዛሬ እኛ በምናስቀምጠው ራዕይና አቅጣጫ ነገ ከነገ ወዲያ ልጆቻችን ይገነቡታል"

—ቀዳማዊ አፄ ሃይለስላሴ (1957 ዓም)

አባቶቻችን እሩቅ አሳቢ ስለነበሩ በብር ኖታችን ላይ ሳይቀር የግድቡን ፎቶ እንደዚህ አስቀምጠውት ነበር።



አሶሳ የተከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በዐል እንደዚሁ በጣም ደማቅ ነበር። በበዐሉ ላይ በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበሩት የጎረቤት ሱዳን ፕሬዜዳንት ኦማር አልበሽር ተገኝተው ብዙ የቤንሻንጉል ሕዝብ በሚችለው አረብኛ ቋንቋ  ንግግር አድርገዋል።

ይህን በዐል ምክንያት በማድረግ ብዙ የመሰረተ ልማት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰርቷል። በፊት አውቀው የነበረው በግምት 5 ሜትር የሚረዝመው መሀል ከተማው አደባባይ ተሰርቶ ቆሞ የነበረው ሀውልት ፈርሶ ሌላ የሚያምር ፏፏቴ ያለው አደባባይ ተሰርቷል። በተለያየ ጊዜ አሶሳ በሄድኩ ጊዜ እንደሰማሁት ይህ ሀውልት በወጣበት 5 ሚሊዮን ብር ምክንያት ብዙ ትችት አስተናግዶአል አሁን ፈርሶ እስከተገላገለ ድረስ።  ሕዝቡ በአጠቃላይ በአጭር ጊዜ የተሰራውን ልማት በማየት በዐሉ በየወሩ እንዲከበር ሀሳቡን ገልጿል።

## ፲፩ ስዊዘርላንድ - ሰላማዊ ሀገር

ስዊዘርላንድ ዙሪያዋን ከጣሊያን ተነስቶ እስከ ፈረንሳይ የሚዘልቀው አልፕስ ተራራ የከበባት ሀገር ናት። ስዊስ ከጫፍ እስከ ጫፍ 300 ኪሎ ሜትር ትረዝማለች። በሰሜን በኩል ከፈረንሳይ አዋሳኝ ከሆነችው ሎዛን ከተማ ተነስተው እስከ ጣሊያን ድንበር እስከምትገኘው ሉጋኖ ከተማ በባቡር በሶስት ሰዐት ጊዜ ውስጥ መድረስ ይችላሉ።

የስዊስ ሕዝቦች ዝርያቸው በዋነኛነት ጀርመኖች ቀጥሎ ፈረንሳዮች እና ሶስት በመቶ የሚሆኑት ጣሊያኖች ናቸው። ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ ብዙ የሀገሩ ሕዝብ ሶስቱንም ወይም ሁለቱን ቋንቋዎች ይናገራል።

ትንሿ ስዊስ መሀል አውሮፓ የምትገኝ ከአቅሟ በላይ ሀብት ያሸከማት ባለ 8.5 ሚሊዮን ሕዝብ ሀገር ናት። ከዚሁ ውስጥ ብዙ ስደተኛ አላቸው። እንደሚናገሩት ከመጠናቸው አንፃር ሲታይ ከሁሉ አውሮፓ ሀገራት የበለጠ ስደተኛ አለን ይላሉ። ስደተኛውም አንዴ ሀገራቸው ከገባ በጥሩ ሁኔታ እንደሚያዝ ይገልፃሉ።

ከውብ አረንጓዴ ምንጣፍ ተቀድዶ የተነጠፈ የሚመስል መልክዐ ምድር አላት። ትንሽ መሆን እንዴት ጥሩ ነው። በእንክብካቤ ለመያዝ ይመቻልና። ስዊስ ከምትታወቅበት አንዱ ጥራት ያለውና ለአውሮፓ ሀገሮች የምታቀርበው አይብ ሲሆን ከራሳቸው ባያልፍም ጥሩ የወይን ጠጅም ይጠምቃሉ።

የሀገሪቱ አስተዳደር በ19 ጠቅላይ ግዛቶች ካንቶን ይሉታል የተከፋፈለ ነው፡፡ በሁሉም መንግስታዊ ሥራ ውስጥ ውክልና አላቸው፡፡ ለምሳሌ የስዊስ ማዕከላዊ ባንክ ከ9 ካንቶን የተውጣጡ ምክትል ገዢዎች አሉት (Governing Board) ይሉታል፡፡ በዚህ ሰፊ የህዝብ ውክልና አንድ ጉዳይ ሲወሰን ለምሳሌ በአንድ መንደር ውስጥ የውሃ ጉድጓድ ለመቆፈር ህዝቡ ተሳትፎበት ድምፀ-ውሳኔ ተካሂዶ ነው ተግባራዊ የሚደረገው፡፡ በህዝቡ ውሳኔ ይሁንታ ማግኘት ካልቻለ ሳይሠራ ይቀራል ማለት ነው፡፡

ለሁሉ እኩልና ገለልተኛ ሀገር ስትሆን በእ.ኤ.አ. 2002 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል እስከሆነችበት ጊዜ ድረስ የምንም ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል አልነበረችም፡፡ ይህ የገለልተኝነት አቋም እ.ኤ.አ.1515 በመሰረቱት ኮንፌደራል ሥርዓታቸው ውስጥ ተደንግጎ ሲከተሉት ነው የኖሩት፡፡ በገለልተኛነቷ ይመስላል የአንዳንድ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ስዊዘርላንድ ነው ፡፡ ለምሳሌ ዓለም አቀፍ ጤና ድርጅት (WHO)፣ ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት (ILO) የሚገኙት ጄኔቭ ሲሆን፣ የዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፊፋ መቀመጫውም ስዊስ ዙሪክ ነው፡፡ በዚህ ገለልተኛ አቋሟ ሂትለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሳይነካት ወደ ሌሎች በወረራ ወደያዛቸው ሩሲያና አውሮፓ ሀገሮች ስላማዊ መሸጋገሪያ ስለሆነችው በጦርነት መሀል ተገኝታ ምንም እሳቱ ሳይነካት አልፏል፡፡ እንዲያውም ብዙ የሂትለር ጄኔራሎችና ሌሎች

ገንዘብና ወርቃቸውን ስዊስ ባንክ አስቀምጠው በዚያው ስለቀሩ የሀብት ምንጭ ሆኗታል፡፡

እንደሚታወቀው የስዊስ አንዱና ዋነኛ የሀብት ምንጯ ይኸው የባንክ አገልግሎት ነው፡፡ የስዊስ ባንክ የሚለየውም ምስጢር በመጠበቅ በመሆኑ ከየአገሩ በሙስና ሆነ በምዝበራ የተሰበሰበ ሀብት መቀመጫው ስዊስ ባንክ ነው፡፡ ያለ ወራሽና ያለጠያቂ ብዙ ገንዘብ ከነሚስጢሩ እዛ እንደቀረ ይገመታል፡፡ የማዕከላዊ ባንኩ ም/ ገዥ በእንግድነት ተጋብዘው ሲያስተምሩን የነገሩን ሀገሪቱ ካላት መጠባበቂያ ክምችት ውስጥ 93 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣ ወርቅ እንደሆነና ይህም ለዚህች ትንሽ ሀገር ብዙ እንደሆነ ገልፀውልናል፡፡

የስዊሰዘርላንድ ሰው ኑሮ በጣም ጥራት (Quality Life) አለው የሚባል ዐይነት ነው:: አንዱ ረዳት መምህር ሲያጫውተኝ እኛም ሀገር ድሀ አለን አለኝ:: ግርም ብሎኝ እንዴት ያለው ነው የናንተ ድሀ አልኩት:: አንድ መኖሪያ ቤትና አንድ መኪና ያለው አለኝ:: በገጠሩ ገበሬው ሳይቀር ሀብታም ነው:: ደጁ ላይ ትንሽና ለረጅም ርቀት የሚሆን ትልቅ መኪና ቆሞ ታያላችሁ:: በከተማም ውስጥ ተጨማሪ ቤት አለው:: ሀይቅ ላይ መንሸራሸሪያ ጀልባ አብዛኛው ገበሬ አለው:: ጄኔቭ ሀይቅ ዳር እንደ ጥጃ የታሰሩ ጀልባዎች አይተው ይህን የሀብት ልክ መመስከር ይችላሉ::

የሄድኩበት የሥልጠና ማዕከል ገርዘንሲ ተብሎ የሚታወቀው አካባቢ ውስጥ የሚገኝ ነው:: አንድ ትንሽ መንደር ነው የሚያክለው:: የራሱ

ሀይቅ ሁሉ አለው፡፡ እንደነገሩኝ ሀይቅም በግል ሀብትነት ይያዛል ፡፡ ፀሐይ እንደድሮ አልወጣ ካለችው አንድ ግለሰብ ላይ በ7 ሚሊዮን የስዊስ ፍራንክ ማዕከላዊ ባንኩ እንደገዛው ነው የተገለፀልን፡፡ ይህ ሥፍራ ከዋና ከተማው በርን በመኪና የ30 ደቂቃ መንገድ ተጉዘው የሚገኝ ሲሆን ገጠራማ አካባቢ ነው፡፡ እነዛ ከበርቴ ገበሬዎች ጂፕ መኪናቸው ደጅ ላይ ቆሞ ቃጭል የታሠረላቸው ላሞቻቸው ከሰፊው መስክ ላይ ሲንገዋለሉ ትመለከታላችሁ፡፡ በአንድ የሳምንት መጨረሻ ዓርብ የሥልጠና ማዕከላችን ውስጥ እነዚሁ የአካባቢው ማህበረሰቦች የምሽት መዝናኛ አዘጋጅተው የትምህርት ቤቱን አዳራሽ ሲጠቀሙ አይቻለሁ፡፡ ጂንስ ለብሰው ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እየተጫወቱ ሲዝናኑ አይቼ ወየሁ የአገሬ ገበሬ በናንተ ስም መጠራቱ አሰኘኝ፡፡

ሎዛን ውስጥ የፊፋ ንብረት የሆነ የስፖርት ሙዚየም ጎብኝቻለሁ፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ የዓለም ኦሎምፒክ ስፖርትን የሚያስተዋውቅ ሥዕሎችና ፎቶግራፎች ተመልክቼአለሁ፡፡ የኛው ጀግና ሀይሌ ገ/ሥላሴ ፎቶ በረጅሙ ጎልቶ ተሰቅሎ ሳይ እጅግ በኢትዮጵያዊነቴ የኮራሁበት አጋጣሚ ነው፡፡ ክብር ለጀግኖቻችን!

ያን እንደ እንጨት የቆመን የአልፕስን ተራራ በውሃ እንፋሎት የሚሰራ ባቡር ላይ ተጭነው ውሃ ሲያልቅበት ተራራ መንገድ መሀል ላይ ቆመው እያጠጡት እየተንዶቀዶቀ ይወጡታል፡፡ አናት ላይ ደርሰው ቁልቁል ከፊል ስዊስን ወዲያ ማዶ ደግሞ ፈረንሳይን

(45 ደቂቃ የመኪና ጉዞ ነው ከሎዛን እስከ ፈረንሳይ ድንበር ከተማ የሚወስደው ጊዜ) መጎብኘት ነው፡፡ በሽቦ መጓጓዣም ተራራውን መውጣት ይቻላል - ብቻ ለቱሪስት በሚሆን መልክ አስናድተውት ያስጎበኙዎታል፡፡ አናቱ ላይ የተለያዩ የሚቀማመስ ነገሮች እየገዙ መዝናናትና ፎቶ መነሳት ይቻላል፡፡

አልፕስ ተራራ በክረምታቸው ጊዜ በበረዶ ለመንሸራተት ብዙ ቱሪስት ይመጣል፡፡ አናቱ ላይ ወጥተው ሲዝናኑ ውለው ማደር ይቻላል፡፡ ለማደሪያ የተዘጋጁ ትኩል ቤቶች አሉ፡፡ ከሙቅ ሻወርና ቡና ጀምሮ የተለያዩ የጣሊያን ጣፋጭ ምግቦች ያገኛሉ፡፡ ዋጋው ትንሽ ቆንጠጥ ያደርጋል ታዲያ ዕቃው የሚጓጓዘው በሂሊኮፕተር መሆኑን አይዘንጉ፡፡

በዚህ አጋጣሚ ካስጎበኙን ቦታዎች አንዱ ጄኔቭ የሚገኘው የማዕከላዊ ባንኩ ሙዚየም ነው፡፡ እዚህ መካነ ቅርስ ውስጥ ከሚገኙት አንዱ ከየሀገሩ የሰበሰቡት የገንዘብ ኖት ናሙናዎች ናቸው፡፡ እኔም የሀገሬን ገንዘብ በስም ስፈልግ በኢትዮጵያ ቦታ ላይ ተሰቅሎ ያገኘሁት የኤርትራው ናቅፋ ነበር፡፡ በወቅቱ ለራሴ በማላውቀው ምክንያት ንዴቴ ጣራ ነካ ወደ አስጎብኚአችን ቀርቤ አምርሬ ተናገርኩ፡፡ ቀኔ በዚህ ተበላሽቶ ወደ ማረፊያችን ተመለስን፡፡

በማግስቱ ሊያስተምሩን የመጡት ም/ገዥ እና አስጎብኚአችን አዳራሽ ደጅ ሰዓት እስኪደርስ ስንጠብቅ ከቆምኩበት ቦታ በቀጥታ ተያይዘው

ወደ እኔ ሲመጡ ተመለከትኩ:: ሰላምታ ተለዋወጥን:: በማስከተል ም/ገዥው በባንኩ ስም በሙዚየሙ ውስጥ ስለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እጠይቃለሁ አሉኝ:: አያይዘውም ከቻልክ ወደ ሀገር ቤት ስትመለስ የሀገራችሁን የገንዘብ ኖቶች ብትልክልን እናርመዋለን ሲሉኝ የእኔ ሃፍረት ጨመረ:: ይሄን ያህል እነዛ ቆዳ ስሱዎቹን ሰዊሶች አስደንግጬአቸው ነበር እንዴ ብዬ በተራዬ ደነገጥኩ! በምላሹ እኔም ከመጠን ላለፈው ቁጣዬ ይቅርታ ጠይቄ ለመላክ ቃል ገባሁ:: እንደተመለስኩም የኛን የወቅቱን ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አስፈቅጄ አስላኩላቸው:: ለገዢው የምስጋና ደብዳቤ ሲፅፉ ለተባበረን ብለው የኔን ስም አክለው ነበር፡፡ በኋላ ሳስበው ለካ በወቅቱ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ላይ ነበርንና ሆን ተብሎ የተደረገና እንደጥቃት ወይም አድሎ ወስጄው ነበር:: ወይ የአበሻ ወኔ!!

ስዊስ ውስጥ ከተደነቅኩበት ነገር አንዱ የሰዐት አከባበራቸው ነው:: ተምረን ለምሣ 6 ሰዐት ወይም ለእራት 12 ሰዐት አዳራሽ ስንገኝ ቁጭ ከማለታችን ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ እናገኘው ነበር:: ተለቅ ተለቅ ያሉት እንቅስቃሴአቸው ዕድሜአቸውን የሚያስረሱ ሴቶች በየአይነቱ እያመላለሱ ይመግቡናል:: ዱሮ ሰዎች ሲቀጣጠሩ ሰዐት እንዳያዛንፉ የመጨረሻው ማሰሪያ ስዊስ ታይም ነበር የሚባለው :: የስዊስ ሰዐትም በዓለም ከሚገኙ ሁሉ የሚያምርና እጅግ ውድ የሚባል ነው::

ከዕለታት አንዱ ቀን ክፍል ውስጥ በምንማርበት እንደ ሕልም በመሰለ ቅፅበት መብራት የጠፋ መሰለን:: አስተማሪያችን ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ሴባስቲያን (የውጪ ምንዛሪ ፖሊሲ ኢኮኖሚ ሊቅ) የሚያስተምሩበት ፕሮጀክተር ይጥፋ አይጥፋ በማስያስታውቅበት ፍጥነት ተርገብግቦ ነበርና ግራ ተጋቡና መብራት ጠፍቶ ነበር ወይ ብለው ጠየቁን:: ሁሉም ተማሪ አንድ ዐይነት መልስ መስጠት አልቻለም:: በፍፁም በስዊስዘርላንድ እንዲህ ዐይነት ነገር «Never in Swiss» አሉና ወደ ትምህርቱ ተመለሱ:: እንግዲህ የስዊሶችን የብቃታቸውን ልክ ለመመዘን ማሳያ መሆኑ ነው::

ሕዝቡ ሕግና ሥርዓት አክባሪ ነው:: ለምሳሌ ከምሽቱ 5 ሰዐት በኋላ ገላዎን መታጠብ አይፈቀድም:: ሻወር መውሰድ ግድ ከሆነበዎት የአፓርታማ መኖሪያ ጎረቤቶን ማስፈቀድ ይኖርብዎታል:: በውሃ ድምፅ እንዳይረበሽ ማለት ነው::

ሀገሩን የሚጠብቀው በተጠራ ጊዜ የሚከት የሕዝብ ሠራዊት ነው ያላት:: ሁሉም የሁለት ዓመት ብሔራዊ አገልግሎት ሥልጠና ወስዶ ቤቱ ከአንድ ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ጋር ይመለሳል:: ቢሆንም በታሪኳም ብዙ ጦርነት አላጋጠማትም:: ወንጀልም ብዙ የለም:: ሰላማዊ ማለቴ በመንገድ ላይ ምንም ዓይነት ፖሊስ ባለማየቴ ነው::

## ፲፪ የእንቢታ ትግልና ደቡብ አፍሪካ

ከአፍሪካ ደቡብ ጫፍ በመገኘቷ ስሟም ደቡብ አፍሪካ ተሰኝቷል፡፡ ጥንታዊት ደቡብ አፍሪካ የተለያዩ የባንቱ፣ቦር፣ኩዋዙሉ ናታል እና ዞሳ የሚባሉ ጎሳዎች ከአራተኛውና አምስተኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ አስተዳድረዋታል፡፡ ቀጥሎ የፖርቹጋል ሀገር አሳሾች በእ.ኤ.አ. 1487 ደቡብ አፍሪካ ደርሰው እንደ ሰፈሩ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ከ1652 ጀምሮ እስከ 1810 ድረስ ከ150 ዓመታት በላይ ደቾች ገዝተዋታል፡፡ ቀጥሎ ደቾችን አስለቅቀው እንግሊዞች እንደዚሁ ገዝተዋታል፡፡ ከዚህ ውስጥ እንግሊዞች ከእ.ኤ.አ. 1948 እስከ 1994 ለሃምሳ ዓመታት አካባቢ የዘለቀ የአፓርታይድ (በአፍሪካነር ቋንቋ ትርጉሙ መለያየት ማለት ነው) ሀይል የተሞላበት የነጮች የበላይነት አገዛዝ አስፍነው ቆይተዋል፡፡ ከመሀከለኛ ምስራቅ አፍሪካ እና ከአውሮፓ ሀገራት በ18ኛ ክፍለ ዘመን ወርቅ ተገኘ ተብሎ በተለይ ከእንግሊዝ ማዕድን ሊቆፍሩ ብዙ ወጣቶች በመርከብ አካፋና ዶማቸውን ይዘው በመፍለስ ሀገሪቱ ላይ እንደሰፈሩ በታሪክ ይታወቃል፡፡

ከጥቁር ሕዝቦች መራራ ትግል በኋላ ከአፓርታይድ ሥርዐት በእ.ኤ.አ. 1994 ነፃ ወጥተዋል፡፡ ለዚህ ነፃነት ብዙ ዋጋ የከፈሉ ብዙ ልጆቿ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ 27 ዓመታት በእስር በመንገላታት ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉት ኔልሰን ማንዴላ-ማዲባ አንዱ ናቸው፡ ፡ማዲባ እያሉ ነው የሚጠሯቸው-አባት ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁሉ

ጊዜ ለመፈታት ከፈለጉ በሚል ብዙ ማባበያዎች እና ድርድሮች የአፓርታይድ ገዢዎች ሞክረዋል፡፡ እርሳቸው ግን የሚፈልጉት የሕዝባቸውን ሙሉ ነፃነት እንጂ የግላቸውን ነፃነት እንዳልሆነ በመግለጽ በጽናት ታግለዋል፡፡ በመጨረሻም ከብዙ ድርድር በኋላ የወቅቱ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዜዳንት ከነበሩት ፍሬድሪክ ዴ ክላርክ ጋር ስምምነት ላይ ደርሰው እ.ኤ.አ.1990 ላይ ከእስር ተፈትተዋል፡፡ ለዚህ የሰላም ስምምነት እውቅና የዓለም አቀፉ የኖቤል ሽልማት ድርጅት ለሁለቱም የዓመቱን የኖቤል ሰላም ሽልማት አጋርቷቸዋል፡፡ አንድ ድምጽ ለአንድ ሰው በማለት በደረሱበት ስምምነት መሰረት እ.ኤ.አ.1994 በተደረገው ሀገራዊ ምርጫ ኔልሰን ማንዴላ አሸንፈው የመጀመሪያው ጥቁር ተመራጭ ፕሬዝዳንት ሆነው ለአምስት ዓመታት ሀገሪቱን መርተዋታል፡፡

እርሳቸው በሥልጣን ላይ በነበሩ ጊዜ ስሟን አንስተው የማይጠግቧትን የሀገሬ ኢትዮጵያ ትዝታቸውን ብዙ ጊዜ አንብቤአለሁ፡፡ መጀመሪያ ለትጥቅ ትግል ሲዘጋጁ የውትድርና ስልጠና የወሰዱት አዲስ አበባ ውስጥ ነበር፡፡ ረጅሙ የነፃነት ጉዞ (Long Walk To Freedom) በተሰኘው የትግል ታሪካቸውን በተረኩበት መጽሀፋቸው ውስጥ እንዳስቀመጡት ወደ አውሮፓና አሜሪካ አስር ጊዜ ከምመላለስ ኢትዮጵያ አንዴ ብሄድ እመርጣለሁ ብለዋል፡፡ እርሳቸው ይህን ቢመኙም ከእስር ከተፈቱ በኋላ የኢትዮጵያን አፈር ተመልሰው ሳይረግጧት ነው ያለፉት፡፡ ታዲያ እኔም ፕሪቶሪያ ቤተ-መንግስታቸው

ደጅ ላይ እንዲያው ድንገት ሊናፈሱ ቢወጡና ባያቸው ብዬ ብዙ ቆሜአለሁ፡፡

በዘመነ አፓርታይድ ጥቁሮች ብዙ ግፍ እንደተፈፀመባቸው ተረድቻለሁ፡፡ ለምሳሌ፡ አንድ ነጭ አሳዳሪ ሠራተኛውን ለጥቁሮች ወደ ተከለከለ የነጮች መንደር ሲልከው የይለፍ ወረቀት ፅፎለት ነው፡፡ የተላከውም ጥቁር 12 ሰዓት ከመሆኑ በፊት መንደሩን ለቆ መውጣት አለበት አለበለዚያ ተይዞ ብዙ እንግልትና እስር ይደርስበታል፡፡ እንደዚሁም ለነጭ የሚሠራ ገበሬ ቢሞት ይህ አሽከሩ የሚቀበርበት መሬት ከአሳዳሪው ማግኘት አይችልም፡፡ ለዚህ የሚሰጠው ምክንያት ልጆቹ ወደፊት የአባታቸው አፅም ያረፈበትን ቦታ በባለቤትነት ይጠይቁኛል የሚል እንደሆነ ተነግሮኛል፡፡ ጥቁር ተወላጆች መሬት በባለቤትነት እንዳይዙ እ.ኤ.አ. 1931 በአዋጅ ተደንግጓል፡፡



በወቅቱ በጥቁሮች ተይዞ የነበረው መሬት ከጠቅላላው ከ7 በመቶ አይበልጥም ነበር። ብቻ ተወላጁ የኖረው ሀገር አልባ ተደርጎ ነበር። በነጮችና በጥቁሮች መሀከል የኑሮ መራራቅ ጎልቶ ይታይ ነበር። እኔ እዛ በነበርኩበት እ.ኤ.አ. 1999 ይህን ልዩነት ልገነዘብ ችያለሁ ።

ይህ ብቻ አይደለም ጥቁሮች የነጭ ፍራቻቸው ምን ያህል እንደሆነ በአንድ አጋጣሚ በጥቂቱም ቢሆን ልረዳ ችያለሁ። ባረፍኩበት ስልጠና ማዕከል ያገኘሁት ጥቁር ሹፌር የሬሰፕሽን ዴስክ ሀላፊ የሆነችውን ነጭ ሲያናግር በእንዴት ያለ ፍርሃትና መሽቆጥቆጥ መሆኑን አስታውሳለሁ። በአንድ እረፍት ቀናችን ከስልጠና ተሳታፊዎች ጋር ካረፍንበት ፕሪቶሪያ አካባቢ ስንሸራሸር አንድ የነጮች ፀጉር አስተካካይ ቤት አየሁ። ደጅ ላይ የቆመውን ጥቁር አስተናጋጅ መቆረጥ እፈልጋለሁ አልኩትና ለመግባት ወደ በሩ ሳመራ በሩን ይዞ የልመና ያህል ባትገባ እመርጣለሁ አለኝ። በልቤ እኔም ልፈትንህ ነው ብዬ ተመለስኩ። መቼ ነው ነፃ ወጣን የሚሉት ስል እራሴን ጠየኩ።

ደቡብ አፍሪካውያን በአፓርታይድ ዘመን ብዙ ሞትና እስር በትምህርት ቤትና በማዕድን ማውጫ ሥፍራዎች እንደ ደረሰባቸው እናስታውሳለን። የስዌቶ የሕፃናት ተማሪዎች ላይ በጥይት ድብደባ የደረሰው እልቂት መቼም የሚረሳ አይደለም። የማዕድን ነገር ሲነሳ ብዙ ወርቅና አልማዝ ማዕድናት የተገኙት በ18ኛ ክፍለ ዘመን

መጨረሻ እና 19ኛ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ታዲያ የአልማዝ ናሙና እንዴት እንደተገኘ ሲያጫውቱኝ እ.ኤ.አ.1867 በአንድ ዕለት የአንድ ነጭ ሀብታም ገበሬ አሽከር መሬቱን ሲያርስ አንድ የሚያብለጨልጭ ነገር ብቅ ይላል፡፡ አሽከሩ ሲያየው የሚያምር ነገር ነው፡፡ ይህማ ለጌታዬ ነው የሚገባው ብሎ ወስዶ ለጌታው ይሰጠዋል፡፡ ነጩ ጌታውም ጎበዝ ብሎ ጉርሻ ሰጥቶት ይሸኘውና ናሙናውን ወደ እንግሊዝ ይልክና ያስመረምረዋል፡፡ አልማዝ መሆኑ ተረጋግጦ ማልማቱ በሰፊው ቀጠለ፡፡ ሀብት በሀብት ላይ ለነጩ ዘር ጎረፈለት፡፡ ከበረበትም፡፡ እንግሊዝም በዚህ እስከዛሬ ተዝቆ በማያልቀው ሀብት አገሯን ገነባችበት፡፡

የሀገሬው ጥቁሮች የግፍ ቀንበርን ከላያቸው ላይ ለማራገፍ በመሪ ድርጅታቸው አፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ (ኤ.ኤን.ሲ.) ሲታገሉ አንዱ የትግል መሣሪያቸው የነበረው እምቢታ ነበር (Non-confirmity)፡፡ ማንኛውም ከነጮች የሚመጣ ትዕዛዝን አለመቀበልና አለመታዘዝ ዋናው የትግል ስልት ነበር፡፡ በዚህም ውጤታማ ሆነውበታል፡፡ ችግሩ ግን የተከሰተው ከነፃነትም በኋላ ይህ የትግል መስመር መቀጠሉ ነው፡፡ በሰላሙም ጊዜ ብዙ ወጣቶች ለህግ ያለመታዘዝ ወይም እንቢታን ሥራ ላይ በማዋላቸው ብዙ ወንጀል እንዲበራከት ሆኗል፡፡ በዋነኛነት ሥራ አጥነቱም ለዚህ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

የወንጀሉ ዓይነት ብዙ ነው፡፡ አንድ ወዳጄ ሲያጫውተኝ እሱ ጆሃንስበርግ በነበረበት አንድ አጋጣሚ በየቀኑ ጧትና ማታ የሚታተም ጋዜጣ ላይ ያነበበውን ሲገልጽልኝ ጧት በወጣው ጋዜጣ ላይ ለጉብኝት ጆሃንስበርግ የመጡ ካናዳውያን ባልና ሚስት በመንገድ ላይ ሲሄዱ ሌቦች ያገኙአቸውና ይዘርፏቸዋል፡፡ ባልየው በግብግቡ ይጎዳና ሆስፒታል ይገባል፡፡ ማታ በወጣው በዚሁ ጋዜጣ ላይ  እነዚሁ ሌቦች በአጋጣሚ የተኛበትን ሆስፒታል ሊዘርፉ መጥተው በድጋሚ እሱንም ዘርፈውት ሄደዋል፡፡ ግጥምጥሞሹ ይገርማል፡፡

በአፓርታይድ ዘመን ብዙ ጥቁሮች በትምህርት ስላልገፉ በለውጡ ጊዜ በየመሥሪያ ቤቱ ነጮቹ በሥጋት ሀገር ጥለው ሲወጡ ትተውት የሄዱትን ቦታ ክፍተት ወድያው መሙላት አልተቻለም ነበር፡፡ ሆኖም እየቆየ ኔልሰን ማንዴላ  ባፈለቁት ሐሳብ መሰረት ማለት ኃጢያትን በመናዘዝ በይቅርታና እርቅ (Truth and Reconcilation) አብሮ ለመኖር በተስማሙበት መሰረት ተመልሰዋል፡፡ ነጮች የግፉ ዐይነትና ልክ ለመገመት በሚያስቸግር  ሁኔታ ኃጢአታቸውን ተናዘው ይቅር ተባብለው ችግሩ ተፈቷል፡፡ ከዚህ በኋላ በሰላም ኑሮአቸውንና ሥራቸውን ቢቀጥሉም  የጥቁሩ ሥራ አጥነት ችግር እንዳለ ነው፡፡ ይህ የማንዴላ የዕርቅ ሐሳብ ለዓለም ተምሳሌትነቱ እጅግ

ትልቅ ነው፡፡ እሳቸውንም ለክብር ጥግ አድርሷቸው ዘመናቸውን በሰላም አሳልፈው በፍቅር እንዲሸኙ አድርጓቸዋል፡፡

ደቡብ አፍሪካ በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ ምንም ዐይነት የመንግሥት ግልበጣ ያላየች የ58 ሚሊዮን ሕዝብ መኖሪያ ሀገር ነች፡፡ ሀገሪቱ የተለያየ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎት ያላቸው ሶስት ዋና ዋና ከተሞች አላት፡፡ እነርሱም ፕሪቶሪያ የመንግሥት መቀመጫ፣ሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ የምትገኘው የመዝናኛ ማዕከል የሆነችው ኬፕ ታውንና የንግድ ከተማቸው ጆሀንስበርግ ናቸው፡፡ ብዙ የኛ ዜጎች እዚች አፍሪካ መሆኗን እስከሚጠራጠሩ ድረስ እጅግ ያደገች ሀገር ውስጥ ሰርተው ይኖራሉ፡፡

## ፲፫ ባንኮክ

በደቡብ ምስራቅ እሲያ የምትገኘው ታይላንድ ዋና ከተማዋ ባንኮክ ስትሆን የአገሩ ሕዝብ ብዛትም ከ70 ሚሊዮን በላይ ይሆናል፡፡ ባንኮክ ደርሰው በመጀመሪያ የሚያስተውሉት ነገር የሕዝቡን ፀጥታ ነው፡፡ ሰላምታቸው፣ ንግግራቸው፣ ዝግታቸውና ሰው አክባሪነታቸው ሁሉም ነገር በፀጥታ ውስጥ ነው የሚያልፈው፡፡ የሁለቱን እጆቻቸውን መዳፍ ፊለፊት በማጋጠም (ለፀሎት በሚመስል መልክ) ወደ ፊታቸው በማምጣት ከአንገታቸው ቀለስ በማለት ሰላምታ ሲሰጧችሁ በትህትናቸው ልባችሁ ይነካል፡፡ እንግሊዝኛ ቋንቋ በቅጡ ባይችሉም እንኳ የሚፈልጉትን አገልግሎት በምልክት ምንም ሳይጓደል ያቀርቡሎታል፡፡ ለእሲያውያን እሴቶች ማሳያ ሆነውኛል፡፡

ባንኮክ በንግድና ሕክምና ማዕከልነት እያገለገለች ያለች ቅልል ያለች ከተማ ነች፡፡ ከየትኛውም የዓለም ማዕዘን ወደዚች ከተማ በየቀኑ ብዙ ሺህ ሰው ይጎርፋል፡፡ ባንኮክ በገበያ ቦታዎች አካባቢ ባሉ መንገዶቿ ጠባብነትና መኪና እና ቱክቱክ (ባጃጅ) እንደመብዛቱ ያለምንም ጡሩንባና ትራፊክ አደጋ ሲጓጓዙ ይደነቃሉ፡፡ የሰዉ ሥርዓት አክባሪነት መግለጫ ቃላት የለውም፡፡

ባንኮክ የሥራን ክቡርነት መማሪያ ቦታም ናት፡፡ መንገድ ዳሩ የሥራ ቦታ ነው - ወይ ምግብ ይጠበስበታል ወይም ልብስና ሌሎች ዕቃዎች

ይነገድበታል፡፡ ጧት ሲነሱ ደጁ ለቁርስ ዝግጁ ሆኖ ያገኙታል፡፡ በሞተር ብስክሌት ወይም በቱክቱክ ዕቃዎቻቸውን ሌሊት ጭነው ይመጡና ይዘረጉታል፡፡ ምድጃው ይለኮሳል ምግቡ መጠባበስ ይጀምራል፡፡ እንግዲህ የሚጠበሰውን ነገር አትጠይቁኝ ዓሣ፣ ብስኩት እና ሌላም ሊሆን ይችላል፡፡ ቅቅል በቆሎም ያገኛሉ፡፡ ሰዉ ሁሉ ወደ ሥራው ሲሄድ አንደኛው ጥግ ላይ ተጣጣፊ ወንበርና ጠረጴዛ ተዘርግቶለት ምግቡን በሁለት ቀጫጭን ማማሰያ የመሰሉ እንጨቶች (ቸፕ ስቲክ) እየያዘ ቁርሱን በልቶ ወደ ሥራው ይነጉዳል፡፡ ይህ ብዙ ምግብ መጠቅለል የማያስችለው ማማሰያ እንዳይወፍሩ ረድቷቸው ይሁን እንጃ ወፍራም ሰው በስለት አያገኙም፡፡ በዚያ የፀሀይ ሙቀት በበዛበት ከተማ የምግብ ጠባሾች እሳት ተጨምሮበት ከተማው ሲንጨረጨር ነው የሚውለው፡፡ የሰው ጥንካሬ ይገርማል፡፡

እልፍ ሲሉ ደግሞ ልብስና ሌሎች ዕቃዎች ተዘርግተው ያገኛሉ፡፡ በውል ካስተዋሉ ያ ቦታ ቀንም ሆነ ሌሊት ገበያው እንዳለ ነው፡፡ በሚቀያየሩበት ወቅት ካጋጠሞት የሚሰካኩ ብረቶች አንዱ ሲነቅል ሌላው ሲተክል ያያሉ፡፡ ጠይቄ እንደተረዳሁት የከተማው ማዘጋጃ ቤት ያንን ቦታ በ24 ሰዓት ውስጥ ለሶስት ነጋዴዎች በተራ እንዲጠቀሙበት ውል አስገብቶአቸው አንድ ጊዜ ሰጥቶአቸዋል፡፡ እነርሱም የስምንት ሰዓቷን ተራቸውን እየጠበቁ መለዋወጥ ነው፡፡ ጩኸት የለ ክፉ ንግግር የለ - ሆቸው ጉድ ሥልጣኔ! ታዲያ አንዱ ለአንዱ ቦታ ሲለቅ አንድ

የቆሻሻ ዘር ሳይተው ፅድት አድርጎ ነው የሚረካከቡት።

እቃ ሲገዙ ሱቅ ውስጥ ካልሆነ ውጪ ላይ ተከራክረው ነው። በክርክር የሚገኘው የዋጋ ቅናሽ ብዙ ነው። ይህን የዋጋ ክርክር በሕንድም አይቻለሁ። የእሲያውን ባህል ይሆን? ባንኮክ በጣም ሰላማዊ ከመሆኑ የተነሳ ሌሊት ወጥተው ገበያ ውስጥ ገብተው ዕቃ ቢገበዩ ይችላሉ። እኔ ሌባ አላጋጠመኝም። ሆቴል ኪራይ በአቅም ከ30 ዶላር ጀምሮ አለ።

ባንኮክ  አንዱ የሚደነቁበት የሕክምና ቱሪዝም በጣም የተስፋፋ መሆኑ ነው። እጅግ ትላልቅ የሕክምና ተቋማት አሏት። እንደ ሰማሁት ሀኪሞቻቸው አሜሪካ ሀገር የሰለጠኑ እንደሆኑ  ነው። ብዙ አሜሪካውያን እዛ መጥተው ሲታከሙ አይቻለሁ። ዋናው ምክንያት ያ ለነሱ ከአገራቸው ጋር ሲነፃፀር የዋጋ ልዩነቱ ብዙ ነው። ሁለተኛ ሀኪሞቹ በነርሱ ሀገር የሰለጠኑ  ስለሆኑ እምነት በማሳደራቸው ይሆናል። ሆስፒታሎቻቸው በጣም ትላልቅና ንፅሕናቸው የሚያስቀና ነው። አቀባበላቸው እጅግ ማራኪና ከትህትና ጋር እየተቀባበሉ የመጨረሻ አገልግሎታቸውን እስከሚያገኙበት ድረስ ያደርሶታል።  የፈለጉት የሙሉ ጤና ምርመራ (General Check-up) ከሆነ በግማሽ ቀን አጠናቀው የተጠረዘ ሪፖርት ስላገኙት ህክምና ውጤት አስረድተዎት ይሰጦታል። የመሣሪያዎቻቸው ዐይነትና የሀኪሞቹ ውጤቱን የመተርጎም ብቃታቸው ድንቅ ነው። ለአንዳንድ የሰውነት ክፍል ለምሣሌ የዐይን፣ጥርስ፣ የአይን

ረቲና የመሳሰሉት ማከሚያ እራሱን የቻለ ለብቻ አገልግሎት የሚያቀርብ ትላልቅ ክሊኒክ ወይም ሆስፒታል ያገኛሉ፡፡

ብዙ ኢትዮጵያውያን ለሕክምና እና ለንግድ ከሚጓዙበት ሀገራት አንዱ ባንኮክ ነው፡፡ በተለይ ለሕክምና የሚጓዙት ብዙ ከመሆናቸውም በላይ ሀገሩ ብዙ ውስብስብነት ስሌለው አረጋውያን በተለይ እንግሊዝኛን ቋንቋ የማይናገሩትም እንኳ ያለማንም እርዳታ ሕክምናቸውን ሲከታተሉ ተመልክቻለሁ፡፡ በእርግጥ ይህ ሁሉ ሰው ሕክምና ፍለጋ ወደ ውጭ መሄዱ የሚያስወጣውን የሀገር ሀብት ሲገምቱት የሚያሳድርብዎት ቁጭት አለ፡፡ የሀገራችን ሕክምና ምን ገጥሞት ነው ብለው ይጠይቃሉ - ወይስ ቅንጦት ፍለጋ ነው፡፡ በእኔ ትዝብት እንደማስበው የሀገራችን ሀኪሞች እውቀት ከነሱ አንሶ አይደለም፡፡ ነገር ግን በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ያለን ትልቅ ልዩነት ታማሚውን ወደዛ እየገፋው ይመስለኛል፡፡ አንድ በሽተኛ በሀኪሙ በትዕግስት መደመጥን ይፈልጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ተገቢውን ማስረዳትና መረዳት እንዲሁም ተገቢውን ርህራሄና ማበረታታት ከሁሉም ጤና ባለሙያዎች ይጠብቃል፡፡ ይህን ግን ያለምንም ማጋነን ከባንኮክ ባለሙያዎች በጉልህ በሚታይ መልኩ ከክብካቤ ጋር ያገኛል፡፡

የጎብኚዎችን ፍሰት ለማቃለል የአገሪቱ የቪዛ ስርዓት የተመቻቸ ነው፡፡ እንደደረሱ ቪዛ ይሰጥዎታል፡፡ ካጋጠሞትም ለአዲስ

ዓመታቸው ከደረሱ በነፃ ሊስተናገዱ ይችላሉ። በእ.ኤ.አ. 1997 የደረሰው የደቡብ ምስራቅ እሲያ የፋይናንስ ቀውስ (South East Asia Fianacial Crisis) የጀመረው ታይላንድ ውስጥ ነበር። የታይላንድ ገንዘብ ባት (Baht) ይባላል። በአንድ ዕለት ባት ከዶላር ጋር የነበረው የምንዛሪ ዋጋ ወይም መጣኔው ድንገት ክፉኛ ይወድቃል። ሰው ገንዘቡን ለማውጣት ባንክ ቤቶች ደጃፍ መሰለፍ ይጀምራል። ከዚያ ሕዝቡ ወሬውን እየተቀባበለ ሰልፉ መቆሚያው ጠፋ መላው አጠረ። አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ ገቡ። በዚህ ቀውስ ክፉኛ ተጎዳች። ከቀውሱ ለማንሰራራት ከተለሙት መንገድ አንዱ ከውጭ ሀገር ማንኛውም መንገደኛ ያለ ቪዛ ክፍያ እንደደረሰ ይለፍ እየተመታለት እንዲገባ መፍቀዳቸው ነው። ይህ የፖሊሲ እርምጃ ቀስ በቀስ ኢኮኖሚያቸው ተመልሶ እንዲያገግም ረድቷቸዋል። የምንዛሬ አገልግሎት የሚሰጡ ፍቃድ ያላቸው የግል መንዛሪዎች በየሱቁ ሞልተዋል። የምንዛሬ ዋጋው በጣም የተረጋጋ ነው። ለሶስት አራት ዓመታት እንዳስተዋልኩት 1 ዶላር ከ30 እስከ 34 ባት ነው የሚመነዘረው።

ታይላንድ በንጉስ እንደምትተዳደር ያውቃሉ? መንግስታዊው ሥራ የሚከናወነው በጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን፣ንጉሡ የሀገር አንድነት ምልክት ነው። በቅርቡ ያረፉት ንጉሥ ቀብር ሲፈፀም በአካባቢው ነበርኩና የሚያስደንቅ ሥነ ሥርዐት ተመልክቻለሁ። አልጋ ወራሽ

ልጃቸው  በአባታቸው ሞት እጅግ በማዘናቸው የአባቴ አስከሬን ግባተ መሬት ሳይፈጸም ዙፋኑን አልወርስም ብለው ለገላጋይ አስቸግረው ነበር፡፡

ባንኮክ መንገድ ላይ የቡድሀ እምነት ተከታይ መነኮሳት ይታያሉ፡፡ አንድ እለት መንገድ ዳር ጥግ አንድ የቡድሀ መነኩሴ ቆመው ከሥራቸው ሁለት ሴቶች ተንበርክከው ፀሎት ሲያደርሱ ተመለከትኩ፡፡ የማየው ከርቀት ቢሆንም መነኩሴውም ቡራኬ ሲሰጧቸው ይታየኛል፡፡ ይህ እምነታቸው ምናልባት ለሚያሳዩት መልካም ሥነ- ምግባር መሠረት ሆኖ ያነጻቸው ይመስለኛል፡፡ በእስያ አንዱና ዋነኛ እምነታቸው ይኸው የቡድሃ እምነት ሲሆን መነኮሳቱ የሚለዩት ጸጉራቸውን ሙልጭ አድርገው ተላጭተውት በቀይ ብትን የሀር ጨርቅ ተጠቅልለው ባንድ ክንዳቸው በኩል እጃቸው ወጥቶ ትከሻቸው ተገልጦ ይታያል-ሱሪ ለብሰው አላየሁም፡፡

ታይላንድ ውስጥ ከዋና ከተማው ባንኮክ በቅርብ ርቀትና ወደ ክፍላተ ሀገር ብዙ የመዝናኛና የሚጎበኙ ቦታዎች አሏት፡፡ የግል መኪና ተከራይተው ወይም በሕዝብ ትራንስፖርትና በአየር መጓዝ ይችላሉ፡፡ ብዙ የውሀ ዳር መዝናኛዎች ከዘመናዊ ሆቴሎች ጋር ተዘጋጅተው ይጠብቋችኋል፡፡

ባንኮክ ውስጥ በብዛት የማሳጅ አገልግሎት የሚሰጡ በየቦታው ያገኛሉ፡፡ ለውበትም ብዙ ሰዎች ታቱ ሲነቀሱ ተመልክቻለሁ፡፡ የወሲብ ንግድ ተስፋፍቶም ይታያል፡፡ ብዙ በድህነት የሚኖሩ ዜጎችም በየገጠሩ እንደሚገኙ ተረድቻለሁ፡፡

## ፲፩ ድንበሩ የቱ ነው

አትፍረዱብኝ ቢቸግረኝ ነው ትልቅ የአጥር ግንብ ስጠብቅ በእግሬ መሰስ ብዬ የሰው ሀገር እንደገባሁ ሲነግሩኝ ነው ድንበሩ የቱ ነው ብዬ መጠየቄ:: ይህ ነገር ደግሞ ያጋጠመኝ በሁለት ቦታ ነው:: በሰሜን ሱማሌ ላንድ አዋሳኝ በሆነው ቶጎ ጫሌና በመተማ ዮሀንስ በኩል ነው:: ባላየውም በኬንያ በኩልም ሞያሌ ላይ ተመሳሳይ እንደሆነ ሰምቻለሁ:: እስቲ የሱማሌና መተማን ጉብኝቴን ተራ በተራ ላስቃኛችሁ::

### ቶጎ ጫሌ

ቶጎ ጫሌ የምትገኘው ከጂግጂጋ ወደ ምሥራቅ 60 ኪሎ ሜትር ወደ ጎን ወደ ሱማሌ ላንድ አቅጣጫ በአስፋልት መንገድ ተጉዘው ነው:: የሱማሌ አካባቢ ሜዳማ በመሆኑ ለመንገድ ሥራ ብዙ አስቸጋሪ አይደለም:: ቶጎ ጫሌ ብዙ ሰው የሰፈረባት የጠረፍ ንግድን ተከትሎ ሲሆን፣ ድንበሩንም እየተሻገሩ ጭምር እስከ ዋና ከተማዋ ሀርጌሳ ድረስ በመዝለቅ ንግድ ልውውጡ ይካሄዳል:: ድንበሩ ተብሎ የተለየው አንድ የዝናብ ጎርፍ የሚሔድበት ትልቅ ሸለቆ ላይ የተሰራው ድልድይ ነው:: ከዚህ ድልድይ ግራና ቀኝ እልፍ ብሎ ከወዲህ የኛ ድንበር ጠባቂ ወታደሮች ገመድ ዘርግተው ተላላፊውን ይቆጣጠራሉ እንደዚሁም ከወዲያም የሱማሌ ላንድ ጠባቂዎች

አሉ፡፡ እንግዲህ በመሀል ያለው ድልድይ አካፋይ ሲሆን፣ እርሱ የማንም ያልሆነ ነፃ መሬት (Free Zone) መሆኑ ነው፡፡ ለንግድ የሚመላለሱ መኪናዎች ከዚያም ከዚህም ድልድዩ ድረስ ነድተው ይመጡና አቁመው የሀገራቸውን ታርጋ ይፈቱና የሚገቡበትን የሰው ሀገር ታርጋ ገጥመው ይጓዛሉ፡፡ ጉዳያቸውን ጨርሰው ሲመለሱ እንደዚሁ ወደ ነበረበት መልሰው በህጋዊ መንገድ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ እንግዲህ ከጎረቤት ጋር ሰላም ካለ እንዲህ ያለ የሕዝቦች ዝውውርና የሸቀጦች ልውውጥ ማካሄድ ይቻላል፡፡ ከእኛ በኩል እስከ በርበራ ወደብ ድረስ ዕቃ እንደሚያጓጉዙ ተረድቻለሁ፡፡

እኔ እንኳ ድንበሩን ያቋረጥኩት በድልድዩ ጎን ውሀ ስሌለ በእግሬ ነው፡፡ ልክ ድንበሩን ሲሻገሩ ከዚያ በኩል የሚያርፉት ሱቆች ላይ ነው፡፡ እጅግ ብዙ የሸቀጣ ሸቀጥ፣ኤሌክትሮኒክስ፣ አልባሳትና ሌሎች መደብሮችን ነው የሚያገኙት፡፡ እንደልብ ተዘዋውረው የፈለጉትን ዕቃ በብር ከሱማሌዎቹ ሱቆች ይገበያሉ፡፡ እነርሱ የሚያስገቡት በበርበራ ወደባቸው በኩል ሲሆን ቀረጥ መኖሩን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ሱማሊያ ዙሪያዋን ሕንድ ውቅያኖስ ስለሚያዋስናት ብዙ መግቢያ በሮች ወይም ወደቦች አሏት፡፡ እንቁሊሊጩ ማለቴ አይደለም፡፡

የዋጋው ልዩነት እጅግ ስለሚያጓጓ እቃዉን ሁሉ ተሸክመውት ይዘው ቢመጡ ይወዳሉ፡፡ ነገር ግን ከቶጎ ጫሌ ሲወጡ ጉምሩክ ስላለ ከግል መጠቀሚያዎ በላይ ዕቃ ከያዙ ይወረሳል፡፡ አንዳንዴ ቁጥጥሩ

ይጠነክራል፡፡ በአንድ አጋጣሚ የባንካችን አመራር ቦርድ አባላት ያሉበት ቡድን ከጂግጂጋ ቅርንጫፍ ምረቃ በኋላ ሀገር እናሳያችሁ ብለን ወስደናቸው ነበር፡፡ በአጋጣሚ ያን እለት ከመግቢያው ጀምሮ ነው ፍተሻ የጀመሩን ታዲያ ትኩረታቸው የውጪ ሀገር ገንዘቦች ነበርና የኪስ ቦርሳችንን ገበር ሳይቀር ነበር እየገለበጡ የበረበሩን፡፡ በዚህ ፍተሻ ወቅት ያገኙት በቅርብ ከውጪ ሀገር የተመለሱ አንድ አባል 400 ዶላር ነበር እሱንም እዚያው በባንክ እንዲመነዝሩት ተደርጓል፡፡ የእኔን ጉድ ልንገራችሁ፡፡ አሜሪካ በምሄድበት ጊዜ የማርፍባት ዘመዴ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ቶማስ ጀፈርሰን ምስል ያለበት ሁለት ዶላር ኖት በኪስህ ያዘው ብላ ሰጥታኝ ነበር፡፡ ለምን እንደሆን ጠይቄአት በአገሩ የሚታመንበት ብር ያበረክታል የሚል አምልኮ መሳይ ነገር ነገረችኝ፡፡ እኔም ጉዱን አያለሁ ብዬ ተቀብዬ መጣሁ፡፡ ሆኖም ከተለመደው በላይ ብሬ ከኪሴ ውሎ ሲያድር ባላየውም ለዛሬ ህገ ወጥነት ዳርጎኛል፡፡

## መተማና መተማ ዮሀንስ

ከጎንደር ተነስተው ወደ ሶስት የተለያዩ ከተሞች ማለት መተማ፣ደባርቅና ሁመራ መሄድ ይቻላል፡፡ ሁለት መተማ እንዳለ ያወቅሁት ጎንደር ሄጄ ነው፡፡ ከጎንደር ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 100 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ዋናው መተማ ተብሎ የሚታወቀው ተጉዘው ነው የሚያገኙት፡፡ መተማ በአካባቢው የሚታወቀው ገንደ ውሀ ተብሎ ነው፡፡ መተማ ለመድረስ ከጎንደር ተነስተው በአዘዞ በኩል

ሙገጭት ብለው ደበቻ፣ድርማ፣አይምባ፣ዶቃሚት፣ቦሀና፣ጭልጋ/ አይከል፣ ታራብ (የወታደር ካምፕ ያለበት)፣ግንት፣ነጋዴ ባህር (ስንቋ)፣ግሳዋ፣ሜሻ-አውላላ፣ኩመር፣ ደረቅ ዓባይ፣ ግሹር መጨረሻ ላይ ገንደ ውሀ(ሰግዳ) እንደርሳለን።

እስከ ጭልጋ ወይም አይከል 60 ኪሎ ሜትር ደጋና ሜዳማ በሆነው መንገድ ከተጓዙ በኋላ ወጣ እንዳሉ ከከፍታው ላይ በአንዴ ቁልቁል ይወርዳሉ። እንግዲህ የበረሃ ስሜት መጀመሩ ነው። ወደ ጎን ሲመለከቱ ላይ አርማጭሆን ያያሉ እንዲሁም በርቀት ፀለምትን እየገረመሙ መጓዝ ነው። መተማ በሰሊጥ ምርት በጣም ትታወቃለች። ብዙ አልሚዎች ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች (ሜካናይዝድ) አሏቸው። ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ከሚያስገኙ የግብርና ምርቶች ውስጥ ከቡና ቀጥሎ ይኸው የቅባት እህል ነው። እርሻው እስከ አጎራባች ከተማ ሁመራ ድረስ ይዘልቃል።

ከገንደ ውሀ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ 60 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ትናንሽ ከተሞችን አፍጥጥ፣ ኩመር ማርያምና ኮኪትን አልፈው ነው መተማ ዮሀንስ የሚደረሰው። ሰማዕቱ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሀንስ ወራሪ ጠላቶች ከሆኑት ማሕዲስቶች ጋር ሲፋለሙ የተሰዉባት ቦታ ናት በስማቸው መተማ ዮሀንስ ተብላ የተሰየመችው።

ከተማዋ ጫፍ ላይ ያለውን ድልድይ ሲሻገሩ የሱዳን ከተማ የሆነውን ጋላባትን ነው የሚያገኙት። እዚህም ጅረቱን ተከትሎ ነው ድንበር

የተበጀው:: ከድልድዩ ወዲህና ወዲያ ማዶ ድንበር ጠባቂዎች አሉ:: ተሻግረው ቢሄዱ የሱዳን ትልቅ ከተማ ገዳሪፍ ያደርሶታል:: እኔም በድልድዩ ጎን በእግር ወርጄ ሱቅ ገብቼ የውሀ መጠጫ ኒኬል ብርጭቆ ገዝቼ ዳስ ውስጥ በሱዳን ቅመም ያበደውን ሻይ ከሱዳናውያን ወንድሞቻችን ጋር እያወጋሁ ጠጥቼአለሁ:: እዚህ ቦታ ተሻግረው ሻዩውን የሚነግዱት የኛው ሴት ልጆች ናቸው:: በጧት ይወርዱና ሲነግዱ ውለው ማታ 12 ሰዓት ላይ ብራቸውን ሰብስበው ወደ ዮሀንስ ለአዳራቸው ይመለሳሉ:: ሰዓት ማክበር ግዴታቸው ነው::

ሱዳናውያንም መተማ ዮሀንስ ገብተው ከፍተኛ ግብይት ሲያደርጉ ውለው ነው የሚመለሱት:: እንደማስበው እነሱ ከኛ የሚፈልጉት ምርት ብዙ እንደሆነ ነው:: እንደተረዳሁት ሰሜን ሱዳናውያን ለመግባባት የማያስቸግሩ ጥሩ ሰዎች እንደሆኑ ነው:: ይህንንም ያረጋገጠልኝ ደቡብ ሱዳን ውሰጥ ያገኘሁት በውጭ ድርጅት የሚሰራ ወገኔ ተስፋዬ ነው:: እዚያ በሥራ በቆየባቸው ዓመታት ባተረፈው ፍቅር ምክንያት ይመስለኛል ስለ እነርሱ አውርቶ አይጠግብም:: ወደ መጣንበት ተመልሰን ከዋናው መንገድ ተገንጥለን ወደ ሽንፋ ከተማ ተጉዘን ጎብኝተናል:: ታዲያ ጎርጎሮን፣ አጋም ውሀንና ዋለዋ ተራራን በርቀት አይተን ነው የደረስነው:: ከሽንፋ ወደፊት ቢዘልቁ የመይሳው ካሣ ትውልድ ሥፍራ ቋራን ያገኛሉ::

## ደባርቅ-ሲማሲሞ

እንደዚሁ ከጎንደር ተነስተው ወደ ሰሜን አቅጣጫ 100 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ደባርቅን ያገኛሉ፡፡ ወደ ደባርቅ ሲጓዙ ወጣ እንዳሉ መጀመሪያ የቤተ እሥራኤሎችን መንደር ያገኛሉ፡፡ ከዚያ 50 ኪሎ ሜትር ላይ አምባ ጊዮርጊስን ያልፉና "አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" ተብሎ የተዘፈነላቸው የደጃዝማች አያሌው ብሩ ሀገር ዳባት ይደርሳሉ፡፡ ከዳባት ቀጥሎ የሰሜን ጎንደር ጫፍ የሆነችው ደጋማዋ ደባርቅ ላይ ያርፋሉ፡፡ ደባርቅ ወደ ራስ ደጀን (ዳሽን) ተራራ መተላለፊያ በመሆኗ ብዙ ቱሪስት በከተማዋ ያርፋል፡፡ ደባርቅ እንደ ጎሬ ደጋና ብርዳም ከመሆኑም በላይ ባለብዙ የእድሜ ባለፀጋዎች ሰባት ከዘራዎች የሚባሉ የሀገር አድባር የሆኑ አዛውንቶች አግኝቻለሁ፡፡ እነዚህ በሚይዙት ከዘራ የሚታወቁት ሰባቱ ያገር ሽማግሌዎች ሀገርን በመምከርና ፀብም ሲኖር በማስታረቅ ያረጋጊነት መንፈስ የተላበሱ መሆናቸውን አብሬአቸው ቁጭ ብዬ ባሳለፍኩት ቆይታ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

እኔ እንኳ ያቀናሁት ወደ ሊማሊሞ መውረጃ 5 ኪሎ ሜትር ከከተማው ወጣ ብዬ ነው፡፡ አፋፉ ላይ እነዛ ትላልቅ ጭላዳ ዝንጀሮዎች የመንገዱን ጠርዝ ይዘው በሰልፍ ይቀበሏችኋል፡፡ ወደፊት ከቀጠሉ የሚያገኙት በዝና የሚታወቀውን የሊማ ሊሞን እንደ ዘንዶ የሚጥመለመለውን ጣሊያን የሰራውን መንገድ ነው፡፡ እንደሚነገረው አንድ የ17 ዓመት ዕድሜ ያለው የምንህድስና

(ጆሜትራ) ጣሊያናዊ ተማሪ ለመመረቂያው የሰራው ዲዛይን ነው ይባላል፡፡ እጅግ የሚደንቅ ጥበብ ነው፡፡ ገደሉ ማስፈራቱን የሚገነዘቡት በአውቶቡስ ሲጓዙ ዓይንዎን በጨርቅ እንዲሸፍኑ ሲጠየቁ ነው፡፡ እኔ እንኳ አፋፍ ቁሜ አንድ አውቶቡስ በዓይኔ ሸኝቼ ነው የተመለስኩት፡፡  ዛሬ ላይ ይህን መንገድ ለማደስ ተሞክሮ በአስቸጋሪነቱ የተነሳ ብዙ እንዳልተገፋበት ነው የተረዳሁት፡፡

## ሁመራ

ከጎንደር ተነስተው 220 ኪሎ ሜትር ወደ ሰሜን ምሥራቅ ተጉዘው ሁመራን ያገኛሉ፡፡ ሁመራ ከመድረሶ በፊት ዳንሻ፣ ሶረቃ ወንዝ፣ ሳንጃን፣ ማይካድራ፣ አብዱራፌ የመሳሰሉ ከተሞችን አቋርጠው ወይም በርቀት እያዩ ነው፡፡ ሁመራ በጣም ሰፊ ሜዳማ ለእርሻ ምቹ የሆነ መሬት አላት፡፡ የሰሊጥ ምርት በሰፊው ከሚሰበሰብበት የአገራችን ማሣ ይህ የሁመራ ክፍል ዋነኛው ነው፡፡ እንግዲህ ዙሪያውን ቢዞሩ የሚያገኙት ከአፍሪካ በቆዳ ስፋቷ አንደኛ የሆነችውን የሱዳንን ድንበር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ይመስላል ብዙ አዋሳኝ ቦታዎች ላይ የሚገኙት ከተሞቻችን ስሞች ለምሳሌ ማይካድራ፣ አብዴራፌ፣ ኦምናጅራ ወ.ዘ.ተ. የአረብኛ ቋንቋ ይመስላሉ፡፡

ሁመራ ላይ የተከዜ ወንዝ እኛና ኤርትራን ለሁለት ከፍሎ  ወደ ሱዳን ነው የሚፈሰው፡፡ ከተማው ዳር ወርጄ ወንዙ ላይ የተሰራውንና

በጦርነቱ ጊዜ ተሰብሮ የቀረውን የብረት ድልድይ ተመልክቻለሁ ከኛ በኩል ወንዙ ዳር መጠለያ ውስጥ ያለ ወታደር አለ። ከወንዙ ወዲያ ማዶ ደግሞ ኦምሐጀር የኤርትራው ግዛት ላይ ወታደር እንደዚሁ ቁጭ ብሏል። ኤርትራዊ ወታደር አጠገብ ፍየልም ቅጠሏን ለመበጠስ ወዲህ ወዲያ ትሯሯጣለች። የሚዋኙትን ልጆች ተመለከትኩ፣ወንዙ ዳር ፎቶም ተነሳሁ፣ እጄን ታጠብኩ ብቻ ዳሩ ላይ ቁጢጥ ብዬ ትንሽ ቆዘምኩ። ወደ ኊላም በ1979 ዓ.ም. የጎበኘኊት አሥመራን በምናቤ ቃኘሁ። እንደዚሁም ያሳለፍነውን ረጅሙን ጦርነትና የሁለት ወንድማማች ሕዝቦች እልቂት መሪር ትዝታን አስታወስኩ።



## ፲፫ ሀገር ሲወለድ- ደቡብ ሱዳን

ጁባ የደረስኩት ልክ የደቡብ ሱዳን ነፃነት በይፋ ከታወጀበት እ.ኤ.አ. ጁላይ 2011 ስድስት ወር በኋላ ነበር፡፡ አዲስ ሀገር አዲስ ጎረቤት፡፡ ብቻ ለኔ ሁሉም ነገር እንግዳ ነው የሆነብኝ፡፡ እንዲህ ነው እንዴ ልክ እንደ አዲስ ቤት ወይም ጎጆ ሀገር ሲመሰረት የሚሆነው በሚል በተገኘሁበት የታሪክ አጋጣሚ እጅግ ተደንቄአለሁ፡፡

መሥሪያ ቤቶች፣ ተቋማት[1] የሰው ሀይሉ፣ወ.ዘ.ተ. ሁሉም ነገር እንደ አዲስ እየተደራጀ ነበር፡፡ ይህን ሁሉ ለማገዝ ብዙ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ በአየር ማረፊያ ቆመው መቁጠር የቻልኩት 49 የተባበሩት መንግስታት፣ ዓለም አቀፍ የምግብ ድርጅትና የሌሎች ድርጅቶች አርማ ያላቸው ትናንሽ አውሮፕላኖች ቆመው ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ እንደ ታክሲ የሚያገለግሉ አውሮፕላኖች ተኮልኩለው ያየኋቸው ከዋና ከተማዋ ጁባ ወደ ቀሩት 10 ክፍላት ሀገር መጓጓዣው አየር ብቻ በመሆኑ ነው ፡፡

የመንግስት መቀመጫ የሆነችው ጁባ እራሷ ያላት አዲስ የተሰራላት 50 ኪሎ ሜትር የሚረዝም የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ብቻ ነበር፡፡ የእርዳታ ሰራተኞች መኖሪያና ቢሮዎች ፣ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና የፕሬዝዳንቱ ቤተ-መንግስት የተገነባው በነዚህ

እርዳታ ሰጪዎች ነው፡፡ ከአስራ አምስት በላይ የሚሆኑ መሥሪያ ቤቶች አንድ ግቢ ውስጥ ነው የተገነቡት፡፡

በደቡብ ሱዳን ነፃ አውጭ ድርጅት ኤስ.ፒ.ኤል.ኤ መሪነት ከሰሜን ሱዳን ጋር ከሃምሳ ዓመታት በላይ የዘለቀ ለነፃነት ጦርነት ተዋግተዋል፡፡ ከብዙ የሰላም ድርድር በኋላ እ.ኤ.አ. 2005 ዓ.ም. ናይሮቢ ላይ በተፈረመ የሰላም ስምምነት መሰረት ዝግጅት ሲደረግ ከርሞ ነው በይፋ ነፃነታቸው በእ.ኤ.አ. 2011 ሀምሌ የታወጀው፡፡ በዚህ ጦርነት ከአንድ ሚሊዮን ህዝብ በላይ እንደሞተ ይገመታል፡፡

ለረጅም ጊዜ ትግሉን የመሩት ዶ/ር ጆን ጋራንግ ከስምምነቱ በኋላ በሂልኮፕተር አደጋ ከሞቱ በኋላ ዘወትር ሰፊ ባርኔጣ የማይለያቸው ምክትላቸው ሳልቫ ኪር ነው የተሾሙት፡፡ ምክትላቸው የሆኑትም ዶ/ር ሪክ ማቻር ነበሩ፡፡ በወቅቱ የሕዝብ ቆጠራ ግምት መሰረት 11 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር 98 ከመቶ በላይ ገቢዋ ከነዳጅ ሽያጭ ነው፡፡

ብዙ የአካባቢ ሀገሮች የግልና የመንግስት ባንኮች ቅርንጫፍ ባንክ ለማቋቋም የተነሳሱበት ወቅት ስለነበር የእኔም የግል ባንክ ለዚሁ ጥናት ከሥራ ባልደረባዬ ከግሩም ጋር ልኮኝ ነው የማየት አጋጣሚ ያገኘሁት፡፡ በዚህ ጥናት ምክንያት ያልዞርንበት መሥሪያ ቤት አልነበረም፡፡ ብዙ የተደራጀ መረጃ ባይኖርም በውይይት ስለ ደቡብ

ሱዳን ብዙ ነገር ለማወቅ ችያለሁ፡፡ የሰላምን ቱሩፋት ለመቋደስ ሁሉም በየፊናው ደፋ ቀና ይል ነበር፡፡ ሆኖም ብዙ የሚሠራባቸው ሕጎች በወቅቱ ባለ መውጣታቸው ለምሳሌ የታክስ ህግ፣ የመሬት አጠቃቀም[1] የንግድ ምዝገባ ሥርዓት ወ.ዘ.ተ. አልነበረም፡፡ ብዙ ሥራ እንደሚጠብቃቸው ተረድቻለሁ፡፡ በዚያው ልክ ሕግና ሥርዓት ለማስከበርም የፀጥታ ሀይል መደራጀትም እንዳለበት ይገነዘባሉ፡፡ የገቢ አስተዳደሩም እራሱን የቻለ ፈተና እንደነበር ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ የነዳጅ ሽያጩ ገቢ በምን መልክ እንደሚመራ ባላውቅም ከጫካ የመጡ ታጋዮች ግን ቪ-8 የተባለ ትላልቅ የመስክ ላንድ ክሩዘር መኪናዎች በብዛት ሲነዱ አይቻለሁ፡፡ ከመንገድ መሰረተ ልማቱ ጋር ሲነፃፀር የእነዚህ መኪናዎች ቁጥር አይመጣጠንም ነበር፡፡

ብዙ የአካባቢ ሀገሮች ዜጎች ከዚች አዲስ ሀገር በረከት ለመቋደስ በንግድ ሥራ፣ ኮንስትራሪክሽን፣ ባንክ፣ ሆቴል፣ በትምህርት ዘርፍ፣ ቤት ገንብቶ ማከራየት እና ሌሎች የሥራ መስኮች ተሰማርተው ተመልክቻለሁ፡፡ ቤት ለመገንባት የመሬት ሥሪቱ በግል ይዞታ ስለሆነ ከግለሰቦች በኮንትራት ተከራይተው ወይም ሊዝ ገብተው ይገነባሉ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ አከራይተው ተጠቅመው እንዳለ ለባለ መሬቱ ከነቤቱ አስረክበው የሚወጡበት ሥራ መስክ ነው፡፡ እንደተረዳሁት የሚከራየው በተለያየ የሥራ መስክ ለመሣተፍ ለመጡ የውጭ ዜጎች በዶላር በመሆኑ ወጪን በትንሽ ጊዜ ለመመለስና ተጠቃሚ

መሆን እንደሚያስችል ተረድቻለሁ። ቤቱ የተሰራበት ወጪ በየወሩ ከሊዙ ላይ ተቀናሽ ሆኖ ይመለሳል። እኛ ያረፍንበት ሆቴል በአንድ ቻይናዊ ከላሜራ ተገንብቶ ለአንድ ምሽት በ120 ዶላር ተከራይተን ነው። እኔና ጓደኛዬ ጢት ለሥራ የምንቀሳቀሰው በግድግዳ በኩል በመጣራት ነበር።

ኬንያ አረብ ኤሜሬትስና የኛው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ከፍተው እየሠሩ ነበር። ለገቢ ንግድ ዕቃ ማስመጫ የሚውል የውጭ ምንዛሪ ከማዕከላዊ ባንኩ በየሳምንቱ በኮታ ለየባንኩ የሚሰጥ ስለሆነ በጣም አዋጪ ሥራ ነበር። ደቡብ ሱዳን ባህር በር ስለሌላት ከውጭ እቃ የሚገባላት በኬንያ ሞምባሳ ወደብ በኩል በዩጋንዳ በየብስ ተጓጉዞ ነው:: ዙሪያ ጥምጥም መሆኑ ለብዙ ወጪ ይዳርጋታል። ይህን ለማቃለል ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በመተባበር የጋራ ወደብ በጅቡቲና ኬንያ ላሙ ላይ ለማልማት የትብበር ስምምነት ሲፈረም አንብቤአለሁ። ብቻ የአዲስ ጎጆ ወጪ ሀገር ግንባታው በየፈርጁ እየተጣደፈ ነበር።

በተለያየ ኢኮኖሚ ዘርፍ ከተሰማሩት የውጪ ዜጎች መካከል ኤርትራውያን በሆቴል ንግድ ሥራ በብዛት ይገኛሉ። እንደዚሁም ኬንያውያን በባንክ ዘርፍ ተሰማርተዋል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ አነስተኛ ነበር። ዋናው የኢትዮጵያውያን እዛ በብዛት አለመገኘት የመገናኛው መንገድ መሰረተ ልማት

ባለመስፋፋቱ ይመስለኛል፡፡ ከዋና ዋና መሠረተ ልማቶች ውስጥ መንገድ ደቡብ ሱዳን የላትም፡፡ ከጋምቤላ ቅርብ ሆና የየብስ መገናኛ ከኛ በኩል ቢሠራም ከወዲያ ገና በመሆኑ በባሮ ወንዝ ላይ ሰውም እቃውም  በመርከብ ወይም በጀልባ ነው የሚጓጓዘው፡፡

ይህን በመመልከት አንዱ በተባበሩት መንግስታት የምግብ ድርጅት ውስጥ የሚሠራ ኢትዮጵያዊ እንደነገረን ደቡብ ሱዳናውያኑ እኛ ኢትዮጵያውያን በብዛት እዚያ ባለመገኘታችን ይቆጫሉ ብሎናል፡፡ በችግራችን ጊዜ እንደዚያ ስትረዱን ኖራችሁ አሁን በመጠቀሚያችሁ ጊዜ ጠፋችሁ ይላሉ፡፡ ይህ ወገናችን ጨምሮ እንደገለፀልን ብዙ የነፃ አውጪ ሰራዊት አባላት ከኪሳቸው የማትጠፋ አንዲት ትንሽ ወረቀት ኮፒ አላቸው አለን፡፡ ወረቀቷም በእጅ የተፃፈችው በወቅቱ የነፃ አውጪዎቹ አጋር ከነበሩት ከቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም ነው፡፡ የተፃፈችው ለጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ ለነበሩት ሰው ነበር፡፡ የወረቀቷ መልእክት የሚለውም «የደቡብ ሱዳናውያን ተዋጊ ወንድሞቻችንን  በሚቻላችሁ ሁሉ እርዷቸው፡፡ በጦርነት የመቁሰል አደጋ ቢደርስባቸው እስከሚያገግሙ ድረስ በቤታችሁ ውስጥ አኑራችሁ ተንከባከቧቸው፡፡ የምትሰጧቸው ብታጡ  እንኳ አውሬ አድናችሁ ቀልቧቸው» ይላል፡፡ ሁሉም ከኪሣቸው የማትጠፋ ይህችን ወረቀት እያወጡ ያሳያችኋል አለን፡፡ እንዲህ ነው እንጂ ባለውለታን አለመርሳት!!

በቢሮ ጉብኝታችን ወቅት ምክትል የማዕከላዊ ባንክ ገዥ ቢሮ ውስጥ ያገኘናቸው ረዳታቸው ስማቸው “አዲስ አበባ” ይባላል። ገርሞን የስሙን ምክንያት ጠየቅናቸው። እንደነገሩን እ.ኤ.አ. 1973 የመጀመሪያው የሰላም ስምምነት አዲስ አበባ ላይ ሲፈረም አባቴ ከተደራዳሪዎቹ አንዱ ነበር። በወቅቱ እኔ ተረግዤ ነበርና ቤት ሲገባ እኔ ተወልጄ ሲያገኘኝ ለሰላሙ ማስታወሻ ስሜን አዲስ አበባ ብሎ ሰየመው አሉን። አባታቸው የጀመሩትን ትግል ሁለተኛው ትውልድ አድገው ተቀላቅለውት አገራቸው ነፃ ወጥታ ተሹመው አገራቸውን በሙያቸው ሲያገለግሉ አየን!!

በወቅቱ እንዳስተዋልኩት ብዙ መስመር ያልያዙ ነገሮች እንዳሉ ታዝቤአለሁ። በዋና ፕሬዜዳንቱና ምክትላቸው ጎሳዎች ማለት ዲንጋና ኑዌር መሀከል የነበረው የሀብትና ሥልጣን ክፍፍል ላይ የተፈጠረ ቅሬታ ይስተዋል ነበር። ውሎ አድሮ ለከፋ ብጥብጥ እንደሚዳርግም ምልክቶች ነበሩ። ኑዌር ጎሣዎች በእኛው ጋምቤላ ከሚገኙት ኑዌሮች ጋር ዝምድና እንዳላቸው ተረድቻለሁ። ምክትል ፕሬዝደንቱ ከኦፊሴል ሥልጣናቸው ሲገፉና ብዙ ወደ አልረሱት የትጥቅ ትግል ተመልሰው ሲገቡ የተሰደዱት ወደ ጋምቤላ ወገናቸው ክልል ነበር። በዚህ አጋጣሚ በዋናው ትግል ወቅት ሚዛን ተፈሪ ውስጥ የቀድሞው መሪ ዶ/ር ጆን ጋራንግ ይኖሩበት የነበረውን

ቤታቸውን አይቻለሁ፡፡ ብዙ ደቡብ ሱዳናውያን እዛው ሚዛን ውስጥ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ት/ቤት ገብተው ይማሩ እንደነበርም ሰምቼአለሁ፡፡

ከነፃነት በኋላ ብዙ ሳይቆይ እንደገና ያገረሸው የርስ በርስ ጦርነት ብዙ እልቂት ያስከተለና ስደት እንደገና በሰፊው የቀጠለበት ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ብቻ ሥልጣንና ገንዘብ የአንድ ሀገር ሕዝቦችን ከዚያ ሁሉ እልቂት በኋላ ለዳግም እልቂት ዳርጎአቸዋል፡፡ አሳዛኝ ክስተት ነው፡፡

## ፲፮ ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም!

በወቅቱ ኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት የባለቤቴ እናት እማሆይ ፀሀይ ምክንያት ሆነውን ቅድስቲቱን ምድር ለመጎብኘት እድል ሳገኝ በእጅጉ እግዚአብሔርን አመስግኛለሁ፡፡ እስራኤል ከሀይማኖት አንፃር ብዙ የሚጎበኙ ቦታዎች ያላት ትንሽ ሀገር ነች፡፡ ነገር ግን ታሪኳ እጅግ ገዝፎ የሚሰማ በየቀኑ የእስራኤል ወሬ ከዜና አውታር የማይጠፋ የምትደንቅ ሀገር ናት፡፡ ብዙ የሚጎበኙት ቦታዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመላለሰባቸው፣ ያስተማረባቸው፣ የሞቱና መቃብሩ ሥፍራዎች ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ዘመዴ ጋሼ ግርማ የነገረኝ ትዝ አለኝ ፡፡ እዛ ለህክምና የከረሙትን ባለቤቱንና ልጁን ለማየት ሄዶ በቆየበት ወቅት ክርስቶስ የተመላለሰባቸውን ቦታዎች በማሰብ ዘወትር ስተኛ “ጌታዬ ምናልባት እዚህ ቦታ አርፎ ይሆናል እያልኩ አስብ ነበር” ብሎኛል፡፡

ኢየሩሳሌም ዋና ዋና የሚጎበኙ ቦታዎች ያላት ቢሆንም ከዚያ በቅርብና በርቀት የሚገኙ እንደ ገሊላ፣ ኢያሪኮ፣ ሙት ባህር፣ ገዳመ ቆሮንቶስ፣ቤተልሄም፣ጥብርያዶስ፣ደብረ ዘይት ተራራ፣ አላዛር፣ ወ.ዘ.ተ. ቦታዎች አሉ፡፡ ኢየሩሳሌም ውስጥ ጎሎጎታ የክርስቶስ ስቅለቱ የተፈፀመበትና መቃብሩ የሚገኝበት ሥፍራ ነው፡፡

በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩት ብዙ አይሁዳውያንና አረቦች ሲሆኑ[1] በተለያየ ምክንያት የመጡ ብዙ የውጭ ሀገር ሰዎች ይገኛሉ። ድንበሩን መለየት በማይቻልበት ሁኔታ መሀል አስፋልት መንገድ ላይ ቆመው ከዚህ በኋላ አረቦች ናቸው የሚኖሩበት ሲባሉ ግር ይልዎታል። የዘመናት ጭቅጭቅና ጦርነት ምንጩ ይኸው ነው። ለፍልስጤም ሕዝቦች የሀገር ባለቤትነትን ለማረጋገጥ የፍልስጤም ነፃ አውጭ ድርጅት ሲታገል ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ቢያልፍም እስከዛሬ ምንም መፍትሔ አልተገኘም።

እስከተረዳሁት ድረስ እኔም ትንሽ ጎሎጎታን ላስቃኛችሁ። በትልቁ ከተገነባው የግሪክ ቤተክርስቲያን አጠገብ እኛና ግብፆች የምንጋራው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እዚያው ጎሎጎታ ውስጥ አለ። ግብፆች መተላለፊያውን ስለዘጉት ቱሪስቱም ሌላውም ምዕመን ከመቅደሱ አጠገብ ባለው መንገድ ነው የሚሄደው። በዚህ በቤተ መድሀኒዓለም ቤተክርስቲያን ቅዳሴ እየተካሄደ እንኳ ሰው ይተላለፋል። ብዙ ዘመን በክርክር ሊፈታ ያልቻለ ጉዳይ በመሆኑ በጣም ያሳዝናል። ይህንኑ ንብረታችንን ለማስከበርና ለመጠበቅ ብዙ መነኮሳት በዙሪያው ተጠልለው እየኖሩ ብዙ መከራ አይተዋል። በተለያየ ጊዜ ከግብፆች ጋር በተነሳ ጸብ ብዙ ቀሳውስትና መነኮሳት ድብደባ ደርሶባቸዋል። ቤተ ክርስቲያኑንም ለማደስ በዚህ ጭቅጭቅ ምክንያት ከእስራኤል መንግስት ፍቃድ ማግኘት አልተቻለም።

የሚያስጎበኞት ሰው ካገኙ ኢየሩሳሌም ውስጥ እያንዳንዷ ሥፍራና የተቀመጠች ድንጋይ እንኳ ታሪክ አላት ይባላል፡፡ ለምሣሌ ከአየሁት የጎለጎታ ቤተ ክርስቲያን ረጅም መዝጊያ ላይ ያለ ትልቅ ስንጥቅ ምስካብ የምትባል ልጅ እንደገለፀችልኝ በአንድ ወቅት ለፀሎት የመጣ ጥቁር ወደ ውስጥ እንዳይዘልቅ በዘረኝነት መንፈስ የተሞሉ ሰዎች ይከለክሉታል፡፡ በዚህ አዝኖ ደጃፍ ላይ የመዝጊያውን ጉበን ተደግፎ ሲፀልይ እግዚአብሔር ተመልክቶ ተቆጥቶ በመብረቅ እንደተመታና ያ ከላይ እስከታች የተሰነጠቀው ምልክት ለዚህ ታሪክ መነሻ ሆኖ ከትውልድ ትውልድ በአፋዊ መልኩ ሲገለፅ ኖሯል፡፡

ይህ የዘረኝነት ነገር ሲነሣ በአንድ ወቅት እዚህ አዲስ አበባ በኤው አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለማስቀደስ በተገኘሁበት አንድ እለተ ሰንበት ያስተማሩን መምህር ዝናቡ የተናገሩት ሁልጊዜ ትዝ ይለኛል፡፡ በእንግሊዝ አንገሊካን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው የተፈፀመው አሉን፡፡ በአንድ ሰንበት ማልዶ ለፀሎት የደረሰው ጥቁር እንዳይገባ የበሩ አጥር ተዘግቶበት አዝኖ ከደጅ ሆኖ ጥግ ይዞ ሲፀልይ እግዚአብሔር አይቶት ተጠግቶ ጠየቀው:: እርሱም የደረሰበትን ገለፀለት:: እግዚአብሄርም አለው “ተዋቸው አትዘን እኔም ከዛ ውስጥ የለሁም “ ብሎ አጽናናው አሉን::

እዚያው ኢየሩሳሌም ኢትዮጵያ ጎዳና ተብሎ በተሰየመው መንገድ ተጉዘው በዳግማዊ አፄ ሚኒልክ ዘመን የታነጸችውን ኪዳነ ምህረት

ቤተ ክርስቲያንን ያገኛሉ። ይህ ብቻ አይደለም ልጃቸው ንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ለአገልጋዮች መተዳደሪያ ገቢ እንዲያመጣ ያስገነቡት ሕንፃም በቅርብ ርቀት ይገኛል። ይህ ማረፊያ እንደዛ የቤት ኪራይ ውድ በሆነበት ሀገር ለኢትዮጵያውያንና ለጎብኚዎች እጅግ በተመጣጠነ ዋጋ በማከራየት ድጋፍ ያደርጋል።

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ቢያቀኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንን ያገኛሉ። ይህ የቤተ ክርስቲያን ቦታ የተለገሰው እመት አማረች ዋለሉ በተባሉ ኢትዮጵያዊት መነኩሴ ነው። ቦታው ሰፋ ያለ ከመሆኑ የተነሣ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ በቆሎ እሸት፣ቃሪያ፣ጎመን ሌሎች ተክሎችን ያበቅሉበታል። ታክሲ ተኮናትሮ እዚያ የወሰደኝ የቀድሞ የቤቶችና ገንዘብ ቁጠባ ባንክ የሥራ ባልደረባዬ የነበረው መሀንዲሱ ጌታቸው አስፋው ምስጋና ይግባውና እነዚህ አባቶች የጋበዙን ከጓሮ ከመጣው ቃሪያ ጋር የሚጥም የምስር ወጥ ምሣ መቼም አይረሳኝም። ጌታቸው በሙያው አብያተ ቤተ ክርስቲያናቱን ስለሚረዳ ቅርበታቸው ከአባትም በላይ ነበር።

ከቤተ ክርስቲያኑ ፊለፊት በአጥር የተከበረ የዘኪዎስ ዛፍ ይገኛል። ምናልባት ከሁለት ሺ ዓመታት በላይ የቆመው ይህ የሾላ ዛፍ ልምላሜው እጅግ ይገርማል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ

ዘኪዎስ አጭር ስለነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሕዝቡ መሀል ማየት ስላልቻለ ዛፉ ላይ እንደወጣ አንብበናል፡፡ እኔ መሄድ አልቻልኩም እንጂ በዚሁ በእያሪኮ በኩል አልፈው በዓመት አንድ ጊዜ ድንበሩ ለጥምቀት በዐል የሚከፈተውን ዮርዳኖስ ባህርንም ያገኙታል፡፡

ከኢያሪኮ ተመልሰው ጋራ ላይ የተመሠረተውን ገዳመ ቆሮንጦስን ከበረቱ ወጥተው ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀንና ሌሊት የፆመበትና የፀለየበትን ቤተ መቅደስ መጎብኘት ይችላሉ፡፡ እዚያ ጋራ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በረንዳ ላይ ቆመው የግሪኩ ቄስ (ድሮ የኢትዮጵያ ንብረት ነበር ይባላል) በርቀት እያሳዩን ገለፃ ሰጥተውናል፡፡ ባሻገር የሙት ባህር ይታያል፡፡ እንደዚሁም የሎጥ ሚስት የጨው አምድ ሆና ደርቃ የቀረችበትን ቦታ እንደዚሁ በርቀት ይመለከታሉ፡፡ ይህን ሙት ባህር እኔ ባልሞክረውም የሞከሩት የነገሩኝ ታሪክ ይገርማል፡፡ ውሀው ጨዋማና የረጋ ነው፡፡ ምንም ለመዋኘት ሙከራ ሳያደርጉ ዝም ብለው ቢተኙበት አያሰምጥም አሉ፡፡ ምትሀቱን ለፊዚክስ ሊቆች ትተን ወደ ቤተልሄም እንዝለቅ፡፡

ቤተልሄም የፍልስጤሞች ግዛት ስትሆን ክርስቶስ የተወለደባትም ሥፍራ ናት፡፡ እዛ የተገኘሁበት ወቅት የገና እለት ስለነበር ሌሊቱን በኛው ቤተ ክርስቲያን ለማስቀደስ እድል አግኝቼአለሁ፡፡ ታዲያ የበዐሉ ሥነ ስርዓት ከቀኑ ጀምሮ ነበርና የሚከበረው ይህንኑ የኛን በዐል ለማድመቅ የፍልስጤም ባለስልጣናት በተገኙበት የስካውት

ዩኒፎርም የለበሱ ልጆች ደስ በሚል ሥነ ሥርዐት ምዕመኑን ትዕይንት ሲያሳዩት ነበር ያመሸን፡፡ ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቤተ መቅደስ ውስጥ ለመግባት ረጅም ሰልፍ ተሰልፌ ገብቼ ተመልክቼአለሁ፡፡ ምሽት ላይ በወቅቱ የፍልስጤም መሪ የነበሩት ያሲር አራፋት መጥተው ከምዕመኑ ጋር ያላቸውን አንድነትና አክብሮት ገልፀው ተመልሰዋል፡፡

ጥንት መጓጓዣ በሌለበት ዘመን እነዛ በእምነታቸው የፀኑ ለእምነታቸው እጅግ የተጉ  ቀደምት አባቶቻችን ብዙ ዋጋ የከፈሉ ናቸው፡፡ በእግራቸው ተጉዘው ባህር ተሻግረው በእስራኤል ውስጥ ለኢትዮጵያ  ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብዙ ንብረት ትተው አልፈዋል፡፡ አንዳንድ ቦታዎች በተተኪ ትውልድ መጥፋት የሌሎች ሀገር ቤተ እምነቶች እንደ ወሰዱት ታሪክ ነግረውኛል፡፡ አሁንም የተረፉትን ቅርሶቻችንን ለማቆየት ያለው ትግል ቀላል እንዳልሆነ ተገንዝቤአለሁ፡፡

በመጨረሻም ኢየሩሳሌም ዓርብ ዓርብ እንዴት እንደሚሸበር ያየሁበትን አጋጣሚ ልንገራችሁ፡፡  በመጽሀፍ ቅዱስ  እንደተፃፈው ጎልጎታ ዙሪያው ገበያ ነው፡፡  ዙሪያውና አካባቢው የአረቦች ሱቆች በብዛት ይገኛሉ፡፡  እዚሁ ቅጥር ውስጥ እኔም አንዳንድ ዕቃ ሳይ ቆየሁና  አሥር ሰዓት እልፍ እንዳለ (ወቅቱ ቶሎ የሚጨልምበት

ነበር) ከፍተኛ ሁካታና ጥሩንባ ሰማሁ። እነዛ እየዞሩ ጡሩንባ የሚነፉት ሱቆችን እንዲዘጉ ይናገራሉ። ባለ ሱቁም እየተጣደፈ ይዘጋል። ምንድነው ብዬ አብሮኝ የነበረውን ወዳጄን ጠየኩት። ሻባት ሊገባ ነው አለኝ - የአይሁድ ሰንበት መሆኑ ነው። ጀንበር ካዘቀዘቀ የተረሳ የበራ መብራት እንኳ ማጥፋት ክልክል ነው። መኪናም አይነዳም። ብቻ በትምህርት ቤት የአነበብኩት የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ መጽሐፍን አስታወሰኝ።

## ፲፯. ጠንካሮቹ ጀርመኖች!

ስለ ጀርመኖች የመንፈስና የሥራ እንዲሁም ሌሎች ጥንካሬአቸውን ለመመስከር ያሳለፉትን የጦርነትም ሆነ የኢኮኖሚ እድገት ጥረት መመርመር ይበቃል። እኛስ ብንሆን የብሔራዊ እግር ኳስ ቡድናቸውን ጫወታ በቴሌቪዥን ያየን አንመሰክርም እንዴ! ጀርመኖች በግብ ብልጫ እየተመሩ እንኳ እስከ 90ኛው ደቂቃ ድረስ ተስፋ የማይቆርጡ ጠንካሮች ናቸው።

የአርያንን ዘር የበላይነት በዓለም ላይ ለመጫን የለኮሱት የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ዓለምንም እራሳቸውንም ጎድቶ አልፏል። ጦርነቱ ካበቃ ሃምሳ አመት በኋላ እኔ ባየኋት ጊዜ የፈራረሰ ሀገር እንደገና ገንብተው ነው። ያፈሩትን ሀብትና የደረሱበትን የኢኮኖሚ እድገት ላስተዋለ በርግጥም ጠንካራነታቸውን ይመሰክራል። ዛሬ ከዓለም ጠንካራ ኢኮኖሚ አላቸው ከሚባሉት ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ናት። ከአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ውስጥ እንዲሁ ቀዳሚ ስትሆን በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ኢኮኖሚ ዘርፍ በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ናት። በዕቃዋ ጥንካሬ በተለይ በኢንዱስትሪ በሚመረቱት ለምሣሌ መኪናዎቿ በዓለም ዘመናዊ ጠንካራና ውድ የሚባሉ ናቸው። ሜርሰዲስ[1] ቮልስ ዋገን፣ ቢ.ኤም. ደብሊው የመሳሰሉት ይገኙበታል። በዚህ የኢኮኖሚ ጡንቻዋ በአውሮፓ

ህብረት ፓለቲካ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ሲኖራት፣ በተፅዕኖ ፈጣሪነቷም ትታወቃለች።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀርመንን መልሶ ለመገንባት ብዙ የሰው ሀይል በማስፈለጉ ለየሀገሩ ይህንኑ ጥያቄ ታቀርብ ነበር። እንደሰማሁት ከዚህ ውስጥ የኢትዮጵያው ንጉሥ አፄ ኃይለ ሥላሴም ተጠይቀው ነበር ይባላል። ሆኖም ሕዝቤን ለባርነት አልክም ብለው ባይሆን ለችግራቸው መውጫ ብለው አንድ መርከብ የቀንድ ከብትና ብርድ ልብስ ልከዋል። ይህንን ታሪክ በጀርመን ሀገር በቋንቋቸው መፅሐፍ ተፅፏል ብሎ የነገረኝ እዛው ፍራንክፈርት አካባቢ ከምትገኘው አሻፋንበርግ ከተማ ያገኘሁት የዘመዴ ጓደኛ ነው።

ከቱርክ ብዙ ሰዎች ሄደው መልሶ ግንባታውን እንዳገዙ ይነገራል። እንደ ማስረጃ የሚቆጥሩት ለዚህ ውለታቸው ከጀርመኖች ቀጥሎ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥረው ከሁሉም የውጭ ሀገር ስደተኛ ቅድሚያ ተሰጥቶአቸውና መብታቸው ተከብሮ መኖራቸው ነው። እነሱም ሠርተው እንደተጠቀሙ የቋጠሩትንም ጥሪት ወደ ሀገራቸው ቱርክ እየላኩ ብዙ ኢንቨስትመንት ሥራ ላይ መሳተፋቸውና ሀገራቸውን መርዳታቸው ይገለፃል። ዛሬ ከሶስት ሚሊዮን የሚልቁ ቱርካውያን በጀርመን ይኖራሉ።

ጀርመኖች ሕግን ያከብራሉም እነዚያ ጠንካራ ፖሊሶቻቸውም ሕጉን ያስከብራሉ:: ማንኛውም ሰው እዚያ ሲኖር ጠንከር ላለው ሕጋቸው ተገዢ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ ስደተኞች ከየትኛውም ዓለም ጀርመን ከገቡና ከተቀበሏቸው በኋላ በተመደበላቸው ክልል ውስጥ መቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መጠለያ ተሰጥቷቸውና የሚያኖራቸው ቀለብ መግዣ ገንዘብ በየወሩ እየተከፈላቸው ሕጋዊ እስኪሆኑ ድረስ ዓመታት ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ ታዲያ በመታወቂያቸው ላይ ከተፈቀደላቸው ክልል ወጥተው ከተገኙ ቅጣቱ ከበድ ይላል፡፡

ሕግን በማስከበር ረገድ ህዝቡም ተባባሪ ነው:: በአንድ ዕለት ከዘመዴ ጋር ከኮለኝ ወደ ካስል በባቡር ስንጓዝ ከአጠገባችን ትይዩ ካለ ወንበር ላይ የተቀመጠች አንዲት የውጭ ዜጋ እግሯን ወንበር ላይ በመስቀሏ አንዲት ጠና ያለች ጀርመናዊት ከኋላ ወንበር ተነሥታ መጥታ ተናግራት እንዳስወረደቻት ተመልክቻለሁ:: በነገራችን ላይ አሜሪካ ውስጥም በመኖሪያ መንደር ብዙ አሮጊቶች ከፎቅ መኖሪያ ቤታቸው መስኮት ላይ አይጠፉም:: አንዲት ያልተገባች ነገር ካዩ ወዲያው ለፖሊስ ስልክ ይመታሉ አጥፊውንም ያሲዛሉ::

ጀርመን በነበርኩበት አንድ አጋጣሚ የዘመዴ የሴት ጓደኛው እናት ያርፉና ከሀገር ቤት መርዶ ይመጣል፡፡ እርሱም ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ በአንድ ሰንበት አረዱአት:: እርሟን ለማውጣት  የደረሰባት ሲቃና

ሀዘን ብዙ ነበር፡፡ ጮክ ብሎ ማልቀስ የለ! እንደልብ ለቅሶ ደራሽ የለ! ብቻ ይሄን ሳስብ ለካ ሀዘንም በሀገር ነው የሚያምረው ብዬ ለራሴ ወደ ውስጤ ነገርኩት፡፡ እዚህ ላይ ወግ አዋቂው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስታስቲክስ ክፍል ጓደኛዬ በኃይሉ ገብረመድህን በሸገር ሬድዮ የኔን ትውልድ ታሪክ በሰፊው ከተረከበት ጫወታ ውስጥ በእንግሊዝ ትምህርት ላይ ሳለ ከዚህ የሚመሳሰለውን ገጠመኙን ባስታውሳችሁ፡፡ በኃይሉ የአክስቱ መርዶ ከሀገር ቤት ይመጣል፡፡ እንግሊዝ ሀገር ካለው ልጃቸው ጋር አንድ ላይ ሆነው እርማቸውን ለማውጣት የደረሰባቸውን ስቃይ ገላጭ በሆነ ምስል አውግቶናል፡፡ አንድ ለናቱ ለሆነው በኃይሉ የእናቴን ሞትማ በሰው ሀገር ሁኜ አልሰማም ብሎ ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ይህ ክስተት ለውሳኔ እንዳበቃው ያዳመጥነው ልብ እንላለን፡፡

ጀርመን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለሁለት ተከፍላ ኖራለች፡፡ ከሃምሳ አመታት በኋላ ስትዋሀድ በምዕራብና ምስራቅ ጀርመን ይታይ የነበረው የእድገት ልዩነት ሰፊ ነበር፡፡ ሆኖም ምእራብ ጀርመኖች ብዙ ዋጋ ቢያስከፍላቸውም ዛሬ ላይ ያን ልዩነት በእጅጉ ለማጥበብ ችለዋል፡፡ ይህ ጦርነት ወለድ መለያየት በኮርያና በሌሎች ሀገራት የምናስተውለው ክስተት ነው፡፡ ታዲያ በአብዛኛው መለያየቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ አመዝኖ ነው የምናየው፡፡

ጀርመኖች ብዙ ሲስቁ አይታይም ፊታቸው ዝግ የሚባል አይነት ነው፡፡ የጦርነቱ ጠባሳ ይሆን እስከ ወዲያኛው ሳቃቸውን የወሰደባቸው? ጦርነትን በእጅጉ ሰላዩት በተለይ የፊተኛው ትውልድ አሁን መስማትም አይፈልግም፡፡ በአንድ ወቅት ሀቫና ኩባ ውስጥ ስብሰባ ላይ ከተዋወቁኋቸው ጀርመናዊ መምህር ጋር በእግራችን ስንሸራሸር መሀል ከተማው አደባባይ ላይ አንድ መድፍና ታንኳ የሰንሰለት አጥር ተከልሎለት ቆሟል፡፡ ታጋዮቹ እነ ፊደል ካስትሮ በሽምቅ ውጊያ የባቲስታን አገዛዝ ጥለው በባህር ተሻግረው እንደመጡበት የሚተርክ ጽሁፍ ተደርጎበት አየሁ፡፡ ለመረዳት ጊዜ ወስጄ ለማንበብ ስሞክር እኚሁ ጀርመናዊ የማየት ፍላጎት እንደ ሌላቸው ገለፁልኝና ጥለውኝ ለመሔድ ሲነሱ ምክንያታቸውን የማወቅ ጉጉቴ ጨመረና ተከተልኳቸው፡፡ እኚሁ ሰው "እኔና በኔ እድሜ ያሉ ጀርመኖች ጦርነትን በበቂ አይተናል ከእንግዲህ ማየት አይደለም ወሬውን መስማት አልፈልግም" አሉኝ፡፡ ለካ የጦርነት ድምር ውጤት ዜሮ መሆኑን ሲረዱ እንደዚህ አምርረው ይጠሉታል፡፡

እሳቸው እንዲህ ይበሉ እንጂ ይህን የጦርነትን አስከፊነት ያላዩ ወጣቶች ዛሬ ላይ በሀገራቸው ጀርመን በዘረኝነት መንፈስ ተነሳስተው በቡድን ተደራጅተው ለራሳቸው ስም ሰጥተው ሰው ሲተናኮሉ በተለይ ስደተኞችን እንመለከታለን፡፡ በናዚ ጀርመን ጊዜ ይህን ሁሉ መከራ በሰው ልጅ ላይ ያወረዱ የጦርነቱ ተካፋይ ወንጀለኞች እስከ

ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲሳደዱ ሲያዙና ሲፈረድባቸው እንሰማ ነበር፡፡

ዓለም ስለጦርነት አስከፊነት መማር ከፈለገች ብዙ የታሪክ አጋጣሚዎችን አሳልፋለች፡፡ ሆኖም ግን ዛሬም በየቦታው የሚለኮሰው የጦርነት እሳት ዓለምን በልቶ ካልጨረሰ መቼም የሚቆም አይመስልም፡፡ በአንድ በኩል ጦርነት የኑሮ አንድ ዘርፍ እየሆነ በመምጣቱም ጭምር ይመስላል፡፡ ዛሬ በጦርነት ብዙ የሚተረፍበት ዘመን ላይ በመድረሳችን እንደ አንድ የስራ መስክ እየሆነ ነው የመጣው፡፡ በሞት እየተነገደ ግለሰብ ድርጅት ሀገር ይከብርበታል፡፡ ሰው ሰራሽ በመሆኑም በጸሎት ወይም በሽምግልና እርቅ የሚቆም አልሆነም፡፡ አንድ ትውልድ ሲያልፍ ከመቆም ይልቅ ይበልጥ ውስብስብና የመጫሪያውም ስልት እየረቀቀና ተዋናዮቹ እየበዙ ሲሄድ ነው ያስተዋልነው፡፡ ለማኛውም ዛሬም ዘወትርም ለዓለም ሰላም እመኛለሁ፡፡

## ፲፰. ጎረቤታችን ኬንያ

ያለን የጉርብትና ትስስር እንዲህ በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። የኛው የቦረናና ቡርጂ ኦሮሞ ጎሳዎች ወንድሞቻችን በኬንያ ይኖራሉ። የቦታ ስም እንኳ ሳይቀር የኬንያ ሞያሌ የኢትዮጵያ እያልን ታሪክና ሰውንም ስንጋራ ዘልቀናል። መተጋገዛችን እና መረዳዳታችን ከኬንያ የነፃነት ትግል ወቅት ጀምሮ የታየ ነው። በጆሞ ኬንያታ አመራር የማኦ ማኦ ንቅናቄ አማካይነት ከእንግሊዞች ነፃ ለመውጣት ሲታገሉ አብረናቸው ቆመናል። ከነፃነት በኋላም ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች ያለ ቪዛ እንዲገናኙ ሁለቱ መሪዎች ኬንያታና_አፄ ኃይለ ሥላሤ ባደረጉት ዘመን ተሻጋሪ ስምምነት ይኸው እንደ ልብ እንመላለሳለን። ኬንያውያን በስዋሂሊ ቋንቋ "ሓራምቤ" መተባበር በሚል መርህ ከአፍሪካ ወንድሞቻቸው ጋር በፍቅር በመዘመር ይኖራሉ።

በዚያ ዘመን ከኛው ሀገር ከባምቢስ ሱፐር ማርኬት ለፕሬዘዳንት ጆሞ ኬንያታ ቤተ መንግሥት ዕቃ ያቀርቡ እንደነበር ሚስተር ባምቢስ ሱፐር ማርኬታቸው ከተመለሰላቸው በኋላ በጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ አንብቤአለሁ። ሚስተር ባምቢስ በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው ላይ ስለ ንብረታቸው መመለስ ተጠይቀው የተሰማቸውን ሲገልጹ "ኢትዮጵያ እኮ በድህነትም በብልጽግናም ብዙ ያየሁባት አገሬ ናት። ደርግ ንብረቴን ከወረሰ በኋላ አቴንስ ገብቼ የኢትዮጵያን ባንዲራ

በራፌ ላይ ተክዬ ይህን ሁሉ ጊዜ ጠብቂያለሁ። የሀገሬ ሰዎች ሲቀልዱብኝ ባምቢስ የኢትዮጵያ አምባሳደር ይሉኝ ነበር"። ንብረቱ ሲመለስልኝ "እኔ አልቅሻለሁ አንተ አታለቅስም የጠፋ ልጅህ ሲገኝ" ብለዋል።

ከአርባ ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ያላት ኬንያ ስፋቷ የኢትዮጵያን ግማሽ ብታክል ነው። እንግሊዝኛ እና ስዋሂሊ ብሔራዊ ቋንቋዎች ሲሆኑ እንደ ኩኩዩ እና ሌሎች በህዝቡ የሚነገሩ ቋንቋዎችም አሉዋት። የትምህርት መሰረተ ልማት የተስፋፋ በመሆኑ ብዙ የተማሩ ዜጎች አሏት። ለዘመናዊ ትምህርትና ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ቅርብ በመሆናቸው ብዙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወለድ አገልግሎቶችን በመቀበል ረገድ ፈጣን እርምጃ አድርገዋል። እንደ አብነት የሚጠቀሰው የሞባይል ባንክ ክፍያ ሥርዓት እስከ ገጠሩ ድረስ ዘልቆ በመግባቱ ዛሬ እዛ የተጀመረው ኤም ፔሣ M-Pesa (ሞባይል ገንዘብ ማለት ነው በአገሩ ስዋሂሊ ቋንቋ) የክፍያ አገልግሎት ፈር ቀዳጅነቱ የሚወደስና ሌላው ዓለም እንዲኮርጀው ሆኗል። ኬንያ ፕሬዜደንት ኦባማንም ለአሜሪካ ያበረከተች መሆኗ አይዘነጋም። ኬንያዊ አባቱ ለትምህርት አሜሪካ ሄዶ ከአንድ ነጭ አሜሪካዊት ወልዶት የመጀመሪያው ጥቁር የአሜሪካ ፕሬዜዳንት በመሆን ታሪክ ለመሥራት የበቃ ነው።

ስዋሂሊ ቋንቋ (ከአረብኛ እና ከአፍሪካ ሰዎች የተዳቀለ ነው) ከኬንያ ጀምሮ እስከ ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ብዙ ሕዝብ የሚናገረው ቋንቋ ነው፡፡ ለዚህ ይመስለኛል  ኬንያ ኡጋንዳና ታንዛኒያ ሶስቱ በጋራ የምስራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመመስረት በጧት የወጠኑትና የተገበሩት፡፡ ቋንቋ ለሕዝቦች መቀራረብ በመግባቢያነትና ለእንዲህ ዐይነት የኢኮኖሚ ትብብር እንደ ድልድይ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ኬንያ የምትታወቅበት ምርቷ ሻይ ቅጠል ሲሆን ቡናና የፋብሪካ ምርቶች ዋና የንግድ መሰረቶቿ ናቸው፡፡ በቅርቡም የነዳጅ ዘይት በማግኘቷም ከአፍሪካ ጥሩ የኢኮኖሚ መሰረት አላቸው ተበለው ከሚጠቀሱት ሀገሮች ጎራ እየቀላቀላት ነው፡፡ ኬንያ ሌላው መታወቂያዋም ያላት የዱር እንስሳት ፓርክ ሲሆን ይህም ከፍተኛ የቱሪስት መስህብ ሆኗታል፡፡ አንዳንዶቹ እንስሳት ከኢትዮጵያ እንደተሰደዱ ይገመታል፡፡ ምን ያድርጉ መኖሪያ ደናቸውን ያለ አግባብ ስንጨፈጭፍባቸው፡፡

በኬንያ የኢኮኖሚው ዋና ተዋናዮች በተለይ በንግዱ ዘርፍ ሕንዳውያን ናቸው፡፡  ጥንት የእንግሊዞች ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሕንድና ፓኪስታን የመጡ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ከኬንያ ነፃነት በኋላ ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ቢሆንም አሁንም ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ሕንዶች በኬንያ ይኖራሉ፡፡ በአጐራባች ሀገሮች ታንዛኒያና ኡጋንዳ

(የኡጋንዳ ፕሬዳንት የነበሩት ኢዲ አሚን ከሀገር እስካስወጧቸው ድረስ) እንደዚሁ ብዙውን የአገሬውን ሀብት የተቆጣጠሩት እነሱው ናቸው፡፡ ሱቅ ገብተው ባንኮኒው ላይ ቁጭ ያለ የሱቅ ባለቤት ሕንዳዊ የቀጠረውን ኬንያዊ እያዘዘ ሲያስተናግዶት ሲያዩ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ብዙ ባለሱቅ አረቦችን ያስታውሶታል፡፡ እነዚያ ዝርያቸው ብዙዎቹ ከየመን የነበሩት አረቦች ኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ትናንሽ ንግድ ውስጥ ይሳተፉ ነበር፡፡ መቼም እነሱ ሻይ ቤት ገብቶ የአረቦችን ፉልና ፓስቲ ያልቀመሰ የከተማ ልጅ የለም፡፡ ብርቱዎቹ ጉራጌዎች ተጠግተው ቀስ በቀስ እስከተኳቸው ድረስ፡፡ በአንድ ወቅት የኛው አንድ ጋዜጠኛ ኬንያን ጎብኝቶ ሲመለስ በጋዜጣ ላይ ባሰፈረው ፅሁፍ ኬንያ የማናት ሲል ጠይቋል፡፡ በቅርቡ ያነበብኩት መረጃ በሶስቱም ሀገሮች ባላቸው ሀብት በቀዳሚ ቢሊየርነት የተመዘገቡት ሶስቱም ሕንዳውያን ናቸው፡፡

ኬንያ ናይሮቢ ባሳለፍኩት አንድ ምሽት የሆቴሉ አስተናጋጆች ከምሽቱ 12 ሰዐት በኂላ ከጓደኛዬ ጋር በዘራፊዎች እንዳንጠቃ ከሆቴሉ እንዳንወጣ የሰጡን ማስጠንቀቂያ በከተማው ምን ያህል ወንጀል እንዳለ ተረድቼበታለሁ፡፡ እንደዚያ የቱሪስት ፍሰት ባለበት ሀገር ይህ ክስተት በወቅቱ አልተዋጠልኝም ነበር፡፡ የፓሊስ ሀይልም ይህን ለማስቆም ከመትጋት ይልቅ አጋጣሚውን ለራሱ እንደሚጠቀምበት ተነግሮናል፡፡ በርግጥ ሌባን ተቆጪ ከሌለው ወንጀል ሊቆም አይችልም፡፡

ኬንያ ሌላው የቱሪስት መስህቧ በሚያዋስናት ሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ያለው ሞምባሳ ወደቧ ነው። ይህ ሰፊ የመዝናኛ ማዕከል የሆነ ቦታ ከናይሮቢ በርቀት የሚገኝ ቢሆንም ብዙ ቱሪስት በያመቱ ይጎበኘዋል። ሞምባሳ ለብዙ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች የዕቃ ማስገቢያና መላኪያ ወደብ ሆኖም ያገለግላል።

ለእኛ ኢትዮጵያውያን ጎረቤት ኬንያ በክፉ ቀን መሸሻና መጠጊያ ሆናም ታገለግለናለች። የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በወደቀ ጊዜ ብዙ ሰው በዚያ በኩል ወደ አሜሪካና እና አውሮፓ ተሰዷል። በ1983 ዓ.ም. የደርግ መንግሥት በተለወጠ ጊዜ እንኳ ብዙ የየኒቨርሲቲ ተማሪዎችና የጦር አባላት ከብላቴ ወታደር ማሰልጠኛ የተሰደዱት ወደዚያ ነበረ። እንደዚሁ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመሰደድ እንደ መተላለፊያ የሚጠቀሙባትና እስኪሳካላቸውም ጊዜያዊ ማረፊያቸው ሆና የምታገለግላቸው ነች። በዚሁ መንገድ ተጉዘው ሌሎቹን የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮችን እያቋረጡ የተሳካላቸው የተስፋቸው ምድር ሲደርሱ ሌሎች በባህር ላይ አደጋና በአውሬ ተበልተው ወይም በኮንቴነር ውስጥ ተጭነው ሲጓዙ ታፍነው የሞት ጽዋን ይቀምሳሉ። ይህ በጣም አሳዛኝ የየወቅቱ መርዶአችን ነው። ሌሎቹም እንደዚሁ ያሰቡበት ሳይደርሱ ይያዙና ወደ እስር ቤት ይላካሉ። ብቻ በዚህም አለ በዚያ ብዙ ስቃይ ወገኖቼን ያገኛቸዋል።

## ፲፱. አዳዲ ማርያም

በብሔራዊ አስጎብኝና የጉዞ ወኪል ድርጅት ጋባዥነት ከአዲስ አበባ በግምት 67 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ደቡብ ሸዋ ውስጥ ምትገኘውን አዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ታህሳስ 9 ቀን 1986 ዓ.ም. ጎብኝተናል፡፡ የፕሮግራሙም ዓላማ ሀገርንና ታሪካዊ ቅርሶችን ከማስተዋወቅ አንፃር ለቅርሶቹ ክብካቤ አግባብነት አላቸው ከተባሉ ድርጅቶችና ለረጅም ጊዜ የሥራና የደንበኝነት ግንኙነት ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ሊጎበኙ የሚገባቸው ቦታዎችን እንዲጠናከሩ የጋራ ውይይት ለማካሄድ ታስቦ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከአጭር የቅርብ ርቀት አካባቢ ጀምሮ ራቅ ወዳሉት የተፈጥሮ ውበትንና ታሪካዊ ቦታዎችን ለማስጎብኘት ይህን የመጀመሪያውን ትምህርታዊ ጉዞ ድርጅቱ አዘጋጅቷል፡፡ ከተጋባዥ እንግዶች መሀል ቤተ-ክህነት፣ ቱሪዝም ኮሚሽን፣ የኦሮሚያ ክልል ቱሪዝም ቢሮ፣ የድርጅቱ ደንበኛ ከሆኑ ት/ቤቶች ጥቂቶቹ፣ ባንክና መድን እንዲሁም በጉዞው ላይ ያልተገኙ ቢሆንም ባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር ይገኙበታል፡፡

የጉዞ ታዳሚዎች ተንጠባጥበው ቢደርሱም ጉዞው 1:20 ሰዓት ከዋናው መሥሪያ ቤት ደጃፍ ተነስቶ በስተምዕራብ አቅጣጫ ቀጥሎ ዓለም ገና ሲደርስ ወደ ግራ ይታጠፍና ከአዲስ አበባ ቡታጅራና ሆሳዕና በሚወስደው አውራ ጎዳና ነው፡፡ አዲስ አበባን እያለቀቅን ስንሔድ

ከበስተቀኝ በኩል በርቀት 3385 ሜትር ከፍታ ያለውን የወጨጫ ተራራን ጫፍ ሞግሌን እናያለን፡፡ በአስጎብኝአችን እንደተገለፀልን አፄ ምኒልክ አዲስ አበባን በ1887 ዓ.ም. ከመቆርቆራቸው በፊት እዚህ ተራራ ላይ ሰፍረው እንደነበረና ከዚያም 3085 ሜትር ከፍታ ወዳለው ዲልዲላ ወይም ዛሬ እንጦጦ ተራራ ወደሚባለው ቀጥለው እንደሰፈሩ ይነገራል፡፡ በስተግራ ደግሞ 2839 ሜትር ከፍታ ያለውን የፉሪን ተራራ ታገኛላችሁ፡፡ ወደፊት ስትገስግሱ ዳለቲን፣ በቾ ሜዳን፣ ጌጃ ሬዲዮ ጣቢያንና ሌመንን አልፋችሁ አዋሽ መልካ ትደርሳላችሁ፡፡ የአዋሽ ወንዝን ተከትሎ የተሰየመው ከተማ ከአዲስ አበባ 50 ኪሎ ሜትር የሚርቅ ሲሆን፣ ከዚህ ከተማ በስተቀኝ ድልድዩን እንደተሻገሩ መልካ ቁንጥሬ የሚባል ታሪካዊ ቦታ ይገኛል፡፡ መልካ ቁንጥሬ በአርኪዮሎጅስቶች ቀፋሮ የጥንት ሰው መገልገያዎች የሆኑ መሣሪያዎች የተገኙበት ቦታ ነው፡፡

ከአዋሽ ከተማ አምስት ኪሎ ሜትር እልፍ እንደተባለ ወደቀኝ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ 12 ኪሎ ሜትር ከዘለቁ በኋላ አዳዲ ማርያም ትገኛለች፡፡ «አዳዲ» በአካባቢው የኦሮሚኛ ተናጋሪ ኗሪዎች «አንፋር» ለሚባል እንጨት የተሰጠው ስም ነው፡፡ እንጨቱን በማፋጨት

እሳት በመፍጠር የአደን ውጤቶቻቸውን ይጠብሱበት እንደነበር ይነገራል፡፡

የአዳዲ ማርያም ቤተ ክርስቲያንም የምትገኘው ዋሻ ውስጥ ሲሆን የተሰራችውም እንደ ላሊበላ ከፍልፍል በሃ ድንጋይ ነው፡፡ ወደ 886 ዓመት የሚጠጋ ዕድሜ እንዳላት ይገመታል፡፡ ለአዳዲ ማርያም መገንባት የሚነገሩ ሁለት የተለያዩ አፈ ታሪኮች አሉ፡፡

አንደኛው በአሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉስ ነገሥት የነበሩት አፄ ላሊበላ ከላስታ መጥተው በአካባቢው ላይ አዳዲ ክስታኔ ዋሻና ሮጌ የተባሉ የዋሻ ቤተ ክርስቲያናትን እንዳነፁ የሚነገረው ሲሆን፤

ሁለተኛው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ለመጎብኘት ወደ ምድረ ከብድ አቦ ሄደው የነበሩ መነኩሴ በራእይ አይተው እዚህ ቦታ ቤተ ክርስቲያኗን እንደሠሩ የሚነገረው ነው፡፡

በሌላ በኩል አፄ ላሊበላ ይህንን ቤተክርስቲያን በማሠራት ላይ እንዳሉ ምድረ ከብድ ዛሬ ዝቋላ በሚባለው ተራራ ላይ የነበሩትን ከፍተኛ የሀይማኖት አባት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ለማየት ሄደው ሳለ ጊዜ እረፍታቸው እንደ ደረሰ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስለተነገራቸው ቤተ ክርስቲያኗን ሳይጨርሱ ወደ ላስታ ተመልሰው

እንደሄዱና ሰኔ 12 ቀን እንዳረፉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር ላይ ተፅፎ የሚገኘው ነው፡፡ በርግጥም ጅምር ሥራዎች ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ በስተምስራቅ በኩል ለቤተልሄም የሚሆነው ቤት ተጀምሮ ሲቀር በደቡብ በር ወደ ምስራቅ በር ሲኬድ ጣራው በደቡብ መስኮት ትይዩ ፍልፍሉ ቅርጹን ይዞ ሳይቀጥል የተቋረጠ መሆኑ ይታያል፡፡

በአስጎብኚአችንና በገዳሙ ቄስ እንደተገለፀልን በጥንት ጊዜ አካባቢው ጥቅጥቅ ያለ ደንና የተለያዩ የዱር አራዊት የበዙበት ስለነበር ቤተ ክርስቲያኗን የሚያገለግሉት ካህናት በዱር አራዊቱ ተፅዕኖ አገልግሎታቸውን በማቋረጣቸው ለብዙ ዘመን ተዘግታ እንደኖረች ይነገራል፡፡ ቤተ ክስርቲያኗ በአሁኑ ጊዜ እንደ ላሊበላና አክሱም በዩኔስኮ በታሪክ ቅርስነቷ የተመዘገበች መሆኗ ይነገራል፡፡

ወደ ቤተክርስቲያኗ በወንዶች መግቢያ በኩል ለመግባት ወደታች በጠቅላላ 22 ደረጃዎችን መውረድ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም እበሩ አፍ ላይ መጫሚያ ተወልቆ ወደ ዋሻ ውስጥ መዝለቅ ይቻላል፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ 10 በሮችና 24 መስኮቶች ያላት በመሆኗ በአራቱም ማዕዘን በቂ ብርሃን በያቅጣጫው ይገባል፡፡ ቤተ መቅደሱ ሶስት ክፍል ያለው ሲሆን ውስጡ አራት ማዕዘን ነው፡፡

ከጊዜ በኋላ በሮችና መስኮቶች ተገጥሞለትም በቁልፍ ተከብሯል፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ መጀመሪያ ስትገኝ የአፈር ደለል እስከ ወገቡ ድረስ

ሞልቶአት ስለነበር ይኸው አሸዋ በአካባቢው ነዋሪዎች እስከ ተወሰነ ድረስ ተዝቆ በመውጣቱ ዛሬ እንደ ልብ ለመቆምና ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሰፋት እንዳገኘ ተገልጾልናል፡፡ ነገር ግን አሁን ካለበትም ደረጃ ወደ ታች ሊቆፈር እንደሚችል ይነገራል፡፡

የውስጡ ጣራና ግርግዳ ከዕድሜና ከክብካቤ እጦት መሰነጣጠቅና መፈረካከስ ቢታይበትም የዚያን ዘመን የነበረውን የሥነ-ሕንፃ ጥበብ ከፍተኛ ደረጃን በዐብይ ምስክርነት ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ገዳም አንድ ሰዓት ከግማሽ ቆይታችን በካህናቱ እንደተገለፀልን ቤተ ክርስቲያኗ ታሪካዊነቷን ጠብቃ እንድትቆይ እድሳትና ክብካቤ እንደሚያሻት እንዲሁም በቅኔ ማሕሌቱ አናት ላይ መስነጣጠቅ መጀመሩን ከስጋት ጋር አስረድተውናል፡፡ ለዚህም የሚመለከታቸውን አካላትና በጎ አድራጊዎች በጎ ምላሽ ይማፀናል፡፡



እኛም እንደተገነዘብነው ከበሃ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራው ቤተ ክርስቲያን ከመዲናችን በቅርብ ርቀት ላይ ቢገኝም ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ የቱሪስት መስህብነቱ ደብዝዞ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ዛሬ ብሔራዊ አስጎብኝ ድርጅት የተያያዘው የበጎ ጥረት ጅማሮ የሚያስመሰግነው ቢሆንም የሌሎችንም ክፍሎች ድጋፍ ይሻል፡፡ በድርጅቱ እንደተገለፀልን ሚናው ታሪካዊ ቦታዎችን ማስጎብኘትና ማስተዋወቅ ቢሆንም እንደዚህ የተዘነጉ ተጎብኝ ቦታዎች ትኩረት እንዲያገኙ የሚመለከታቸውን እያሰባሰበ የችግሩን ስፋት ለማስገንዘብ ጥረቱን እንደሚገፋበት ከመግለፁም በላይ በቅርቡም ለሀገር ውስጥ ጎብኚ ቱሪስቶች የማስጎብኘት ፕሮግራም እንደሚጀምር በዚህ አጋጣሚ ተገልፆልናል፡፡

የቤተ ክርስቲያኗም ዓመታዊ በዓለ ንግሥ ህዳር 21 ቀንና ጥር 21 ቀን መሆኑንም በተጨማሪ አስታውሶናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የአንድ ምዕመንን በጎ ተግባር ማስታወስ ተገቢ ይመስለናል፡፡ እኚህ ግለሰብ ታቦቷን ለማንገስ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ ለሚመጡ ምዕመናን ማረፊያ የሚሆንና አሁን ለጊዜው የቤተ ክርስቲያኗ ንዋያተ ቅድሳት ግምጃ ቤት ሰርተው በማስረከባቸው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከገዳሙ ጉብኝት በኋላ ወደ መጣንበት ዋና መንገድ ተመልሰን ወደፊት ቀጥለን ጥያ ከተማ (ከአዲስ አበባ 85 ኪሎ ሜትር) በቁፋሮ የተገኙትን ትክል ድንጋዮችን ወይም የመቃብር ሐውልቶችን (Stelae) ተመልክተናል፡፡ እንደ ተረዳነውም ከጥያ እስከ ሲዳሞ

ድረስ ወደ 10,000 የሚጠጉ ሐውልቶች ይገኛሉ፡፡ ጥያ ውስጥ የተገኙት ሐውልቶች በቁጥር እስከ አርባ የሚደርሱ መሆናቸው ሲነገር አብዛኛዎቹ ወድቀው ነው የሚታዩት፡፡ እነዚህ ሐውልቶች ከ14ኛው እስከ 15ኛው መቶ ዓመት ባለው ጊዜ የቆሙ እንደሆነ ሲገመት የተከለውም ግራኝ መሐመድ በግራ እጁ ወርውሮ ነው የሚል አፈ ታሪክ አለ፡፡ ነገር ግን ሐውልቶቹ ከአንድ ወጥ ድንጋይ በደንብ ተጠርበው የጊዜውን የጦር መሣሪያ የሚያሳዩ እንደ ጦር ሰይፍ ጎራዴና የተገለባበጡ የደብልዩና ኤክስ የእንግሊዘኛ ፊደላት ምስሎች ተቀርፆባቸው ነው የቆሙት፡፡ አንዳንዶቹ ብዙ መሣሪያ የተቀረፁበት ሲሆን፣ ይህም የሟቹን የጀግንነት ደረጃ ለመግለፅ እንደሆነ ይገመታል፡፡

በአጠቃላይ ሐውልቶቹ የመቃብር ቦታ እንደሆኑ በቁፋሮ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን በቂ የጹሑፍ መረጃ ባለመገኘቱ ምንነቱን በደንብ ማወቅ ስላልተቻለ ለወደፊቱ የምርምር ሥራ የተተወ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሐውልቶቹን ለማስጠበቅ በር የሌለው የሽቦ አጥር ዙሪያውን ከመኖሩ ባሻገር ክረምት ሲመጣ በጎርፍና በደለል እንደሚዋጡና በየጊዜው እየተሸረሸሩ እንደሚሄዱ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ከዓመታት በኂላ ምንም ሐውልት እስከ ማናይበት ደረጃ እንደሚያደርስን ይገመታል፡፡ ስለዚህ አሁንም የሚመለከታቸውን ክብካቤ ይሻል፡፡

(በ1986 ብሪቱ መጽሄት ቁ.54 ላይ የታተመ)

## ፳. በሎንዶን ጎዳና ላይ

ባለፈው የብሪቱ መጽሄት እትም አዳዲ ማርያም አድርሼ መለስኳችሁ:: ዛሬ እንዲያው ለምን ታሰቸግረናለህ ባትሉኝ ስለ ሰው ሀገር ላወራላችሁ ነውና ላስቸገርኳችሁ ከወዲሁ ወፍራም ይቅርታችሁን እለምናለሁ::

በቀጥታ እንኳን ሎንዶን አልገባሁም በፍራንክፈርት (ጀርመን) አድርጌ ለአምስት ቀናት ቆይታ ያደረኩባት በርሚንግሐም ከተማ ለመድረስ ጉዞዬን በምሽት በሉፍታንዛ አየር መንገድ ከቦሌ ነበር እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 1994 የጀመርኩት:: ለምን ከመስተንግዶው አልጀምርላችሁም:: ለጉዞ ስንታደም ፈገግታ የተሞላበት አቀባበላቸው ከወዲሁ ምሽቱን አስረሳኝ:: እንደ ግምቴ ፈገግታ ብቻ አይደለም የፈለግነውን ሁሉ እየመገቡን ሳይታወቀን ነው ያደረሱን::

ገና ወደ አውሮፕላኑ ውስጥ ሲዘልቁ ስፋቱንና ግዙፍነቱን እንዲሁም በአንድ ጎን መደዳ አስር ሰው መቀመጡን ሲያስተውሉ ክቡሩን የሰው ልጅ ጥበብ ማድነቅ አሀዱ ብለው ይጀምራሉ:: ከሁለት መቶ በላይ የሆነውን መንገደኛ ደግሞ በአንድነት ሲገረምሙ ጉባኤ አዳራሽ የገቡ ይመስሎታል:: መጓዝ ስንጀምር በቋሚነት የት እንደ ደረስን የሚያሳይ ቴሌቪዥን ከአውሮፕላኑ ጣራ ወደ ታች ተንጠልጥሎ ስለሚገኝ መከታተል ይቻላል:: በየሙሉ ሰዓቱ

የቢቢሲ ዜና ይተላለፋል። እንዲሁም ከወንበርዎ ጋር በተገጠመው መክፈቻ ቻናል እየቀያየሩ ቪዲዮ ፊልም ሊያዩ ወይም የተለያዩ ሀገሮችን ሙዚቃ ማዳመጥ ይችላሉ። አውሮፕላኑ አንዴ አየር ላይ ወጥቶ መስመሩን ከያዘ መነቅነቅ የለም። ይሂድ ይቁም የደመና ግፊት ካላጋጠመው በስተቀር አይሰማዎትም።

በዚህ ሁኔታ አስመራን አቋርጠን ቀይ ባሕርን ተሻግረን ጄዳ (ሳውዲ አረቢያ) እንደርሳለን። እኛ እዚያ ባረፍንበት ሰዓት ውድቅት ሌሊት በመሆኑ የሚቃጠል የሚመስል መብራት ከሚታይ በቀር ከተማዋ እረጭ ብላለች። የሚወርደው መንገደኛ ወርዶ በምትኩ ተሳፋሪ ጨምረን ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ጉዞአችንን ወደፊት ቀጠልን። በጉዞው ላይ ምግቡ መጠጡ ሻይና ቡናው ምንም አይቀርም ጌታዬ ምን ላምጣሎት ከሚለው ትህትና ለበስ ንግግር ጋር። እንዲህ እያልን በስምንት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሶስቴ ከእህል ጋር ተገናኝተን በጧቱ ወፍ ሲንጫጫ ፍርንክፈርት ደረስን። አይ ብርዱ! አይ ቆፈኑ! እሱን አለማንሳት ነው። ለነርሱ ግን እንደ ሙቀት ጊዜ ነው የሚያዩት ምክንያቱም ከሁለት ሳምንት በፊት ቅዝቃዜው አሁን ካለበት ሶስት ዲግሪ ሴንትግሬድ ወርዶ ከዜሮ በታች 15 ዲግሪ ሴንትግሬድ ደርሶ ስለነበር ነው። ታዲያ ወደ ውጪ ሀገር ሲጓዙ ሁልጊዜም የሀገሩን የአየር ንብረት መረጃ ቢኖሮት ወይም ለምናልባቱም ካፖርት፣ የአንገት ልብስ (ሻርፕ) ወይም ወፍራም ሹራብ መያዙ ይጠቅማል።

ፍራንክፈርት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንደገና የተገነባች ድንቅ ከተማ ናት፡፡ በሃምሳ ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ ለነሱ ምን ይሳናቸዋል፡፡ ጀርመንን ከአየር ላይ ሁኜና ከአየር ማረፊያዋ በስተቀር ሌላ ያየሁት ነገር ስሌለ ምናለ ወደ ምድረ እንግሊዝ ብናቀና ደግሞም ቅርብ ነው የአንድ ሰዓት ከምናምን ጉዞ ነው፡፡ በየአውሮፕላን ማረፊያው የሚቀጥለው የሚጓዙበትን አውሮፕላን ለማግኘት መረጃ መከታተል ነው፡፡ የበረራ ቁጥሩን ጊዜውን የአየር መንገድ አይነቱን ከቲኬትዎ ላይ እያዩ በኮምፒውተር ላይ ተጽፎ የሚንጠለጠለውን መረጃ ማንበብ በቂ ነው፡፡ ካላነበቡም ሰው መረጃ በመስጠት በኩል እጅግ በጣም ተባባሪ ነው፡፡ ከሚሄድበት መንገድ እንኳ አቋርጦ እርስዎን ከመርዳት ወደ ኋላ አይልም፡፡ ይህ ባህል በሁሉም ዘንድ ያለ መሰለኝ ምክንያቱም እንግሊዝ ውስጥም ያጋጠመኝ በመሆኑ ነው፡፡ መለመድ ያለበት መልካም ባህል ነው፡፡ በአላዋቂነትዎ ሳያፍሩ ይጠይቃሉ፡፡ እነሱም ይህንን አጋጣሚ በመጥፎ ሳይጠቀሙበት ወዲያው ይረዱዎታል፡፡ መንገደኛን መጠየቅ የሚፈሩ ከሆነ ፖሊስ ፈልጎ መጠየቅም ይቻላል፡፡

እዚህ አውሮፕላን ማረፊያ ወዳጄ ሰለሞን ያጋጠመውን ባወራላችሁ ፈገግ ያሰኛችኋል፡፡ ሰለሞን ለአጭር ጊዜ ትምህርት ወደ ምድረ አሜሪካ ነበር በፍራንክፈርት በኩል የሚጓዘው፡፡ በእለተ እሁድ ጠዋት ጭር ባለው አየር ማረፊያ የደረሰው ሰለሞን ብዙ የውጭ ሀገር ጉዞ ልምድ የሌለው በመሆኑ የሚቀጥለውን አውሮፕላን

ለመሳፈር ወዴት እንደሚሄድ ይቸገራል፡፡ የሚጠይቀው ሰው ፍለጋ ወዲህ ወዲያ ሲያማትር አንድ የአየር መንገድ ዩኒፎርም የለበሰች ሴት ያገኝና ሲጠይቃት በዚህ ውረድ ብላ ወደ አንድ ደረጃ አመላክታው ትሄዳለች፡፡ እንደተባለው ደረጃው ላይ ገና ከመውጣቱ ደረጃው ቁልቁል መንቀሳቀስ ይጀምራል፡፡ እጅግ የደነገጠው ሰለሞን የያዘውን የእጅ ቦርሳ ወደ ላይ ይወረውርና ከቁልቁለቱ ወደ ላይ ለመመለስ ይታገላል፡፡ ለካ ሰው አጥቶ የቆመ የኤሌክትሪክ ደረጃ (እስካሌተር) ኖሯል እሱ ሲወጣበት የተንቀሳቀሰው፡፡ ካለፈ በኋላ ሰለሞን ሲናገር ነፍሴ ቁልቁል ወደ ሲዖል እየወረደች የኔ ቦርሳ ለማዳን ወደ ላይ መወርወር ምን የሚሉት ነው ይላል፡፡

## በርሚንግሀም

መድረሻዬ በርሚንግሀም ከተማ ከሎንዶን ቀጥላ የእንግሊዝ ሁለተኛ ትልቅና የኢንዱስትሪ ማዕከል ናት፡፡ ባለፈው አስር አመት ጊዜ ውስጥ ትልልቅ ግንባታ ተካሂዶባታል፡፡ ከነዚህ ድንቅ ግንባታዎች መካከል እ.ኤ.አ በ1992 የአውሮፓ የጋራ ገበያ ሀገሮች መሪዎች ስብሰባ ያስተናገደ ዘመናዊ ዓለም አቀፍ አዳራሽ አንዱ ነው፡፡ ወደ አዳራሹ ለመዝለቅ ከበር ጋር መታገል አያሻዎትም በአካል መጠጋትዎ ለበሩ መከፈት በቂ ነው፡፡ ካለፉም በኋላ ራሱ ይዘጋል፡፡ እናድንቅ ካልንማ ከዚህ ጀምረን አንዘልቀውም እንዲያው በደፈናው አውሮፓ ነው ያለነውና እነዚህን የመሳሰሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወለድ ነገሮች ብናልፋቸውሳ፡፡

በዚህ አጋጣሚ አላስችል ብሎኝ አብረውኝ ስብሰባ ላይ ለነበሩት ወገኔ ዶክተር ጀንበር ተፈራ « ወይኔ ሀገሬ » ብዬ የቁጭት ቃል ስናገር «ይህን ከዚያኛው አወዳድራለሁ ብለህ አታስብ ይህን መሳይ ሀሳብህን እዚያው ጥለህ ነው መምጣት ያለብህ» ብለው የመጨረሻውን ነገሩኝ (እርሳቸው ብዙውን የውጭ ሀገር አይተውታል)፡፡ እኔም በሀሳባቸው ተስማማሁ እና ዝም ብዬ መመልከትና ማድነቅ ብቻ ሆነ ተግባሬ ተደንቄም ጻፍሁላችሁ፡፡ ማነው ስሙን ዘነጋሁት አንድ ዘፋኝ አሜሪካንን አይቶ ሲመለስ ስለ ሀገሩ እዚህ አዲስ አበባ ስታዲየም ውስጥ በጨዋታ መሀል ባለ ወሬ ላይ ሰዎች ሲጠይቁት «የሰማዩን አላውቅም እንጂ የምድሩ ገነት ግን እዛ ነው» ነበር ያለው!!

ከተማ ለመጎብኘት የካርታ እርዳታ አይለየዎትም፡፡ አንድም ከየቦታው ያገኙታል አልያም በየአውቶቡስና ባቡር ፌርማታ ላይ ተለጥፏል፡፡ የከተማ ውስጥ ትራንስፖርት ትንሽ ወደድ ይላል፡፡ እንደደረሱ የያዙት ዶላር ከሆነ ባንክና መለወጫ ቦታዎች እንደ ልብ ስለሆኑ ወደ እንግሊዝ ፓውንድ መቀየር ግዴታ ነው፡፡ በወቅቱ አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ 1.57 ዶላር ያወጣ ነበር፡፡ ይህ ቋሚ አይደለም ተለዋዋጭ ነው፡፡ በዚህ ላይ ሎንዶን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ገበያ ማእከል መሆኗን አይዘንጉ፡፡ በቀን በቢሊዮን የሚቆጠር የተለያዩ ሀገሮች ገንዘቦች ይሻሻጣሉ - የሀብት ማእከል እንበላት፡፡

## ሎንዶን

በርሚንግሀም ይብቃን ወደ ሎንዶን እናዝግም፡፡ ወደዚያ ለመሄድ አውሮፕላን፣ ባቡር ወይም የክፍለ ሀገር አውቶቡስ (ኮች) መጠቀም ይቻላል፡፡ እኔ እንኳ ከአምስት ቀናት የስብሰባ ቆይታዬ በኋላ አውቶቡስ በአውቶቡስ ላይ በደረበው ኮች ነው ወደ ሎንዶን ያቀናሁት፡፡ አንድ መቶ ማይል (160 ኪሎ ሜትር) ይርቃል፡፡ ታዲያ የኮቹ ፍጥነትና የመንገዱ ምቹነት ከሁለት ሰዓት በላይ አይወስድበትም፡፡ በዚህ ላይ የአውቶቡሱ ምቾት ከኛ ጋር በፍፁም አይወዳደርም፡፡ ከረባት ያደረገ አውታንቲ ወይም ሴት አስተናጋጅ በገንዘብዎ ከፈላ ቡና አንስቶ እስከሚቀማመስ ነገር ድረስ ያቀርብሎታል፡፡ እያነበቡ ወይም መሀል ጠረጴዛው ላይ ካርታ እየተጫወቱ መጓዝ ይችላሉ፡፡ መነቅነቅ የለ ጋራ የለ ማን ሀገራቸውን ዝርግ አድርጎ እንደሰራላቸው አላውቅም!!

ገጠሩ የማያበቅለው ነገር የለም፡፡ አጠገቤ የተቀመጠው እንግሊዛዊ እንደነገረኝ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ፣ ወ.ዘ.ተ. ይበቅላል፡፡ እንዲሁም በግ፣ የቁም ከብት፣ ዶሮ፣ አሳማ፣ ወ.ዘ.ተ. ይረባል፡፡ ገጠሩም መሀል መኖሪያ ፎቆችም አብረው ይታያሉ፡፡ በአጠቃላይ ሀገራቸው በተፈጥሮውና የሰው ጥረት ታክሎበት ለም ነው፡ ከሰጠ አይቀር እንዲህ ነው እንጂ!! ይህን ሁሉ ጠይቄ ነው የተረዳሁት፡፡

እንግሊዞች እንደኛ የጭምትነትና የኩሩነት ባህሪ ያላቸው ይመስለኛል፡፡ እኛ እንግዲህ ሰው ካላናገረን ቀድመን እንደማንናገር አይነት ይታይባቸዋል፡፡ እንደኔ ላገሩ ባይተዋር ሆነው የጠያቂነቱን ቅድሚያ ካልወሰዱ እንደተዘጋጉ ውቅያኖስ ማቋረጥ ነው፡፡ አንዴ ከጀመሩ ግን ተጫዋች ሆነው ነው ያገኘኋቸው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሌላው በእንግሊዝ ባህል ያየሁት ነገር ሰውን ትኩር ብሎ ማየት ነውር መሆኑን ነው፡፡ አውቶቡስም ውስጥ ሆነ ባቡር ላይ ፊት ለፊት ተቀምጠው አጎንብሰው መሬት መሬት ወይም ወደ ውጭ በመስኮት እያዩ ነው የሚጓዙት፡፡ እኔም ጓደኛዬ ከነገረኝ ወዲህ እንዳይናፋር ልጃገረድ አርጎኝ ከረመ፡፡ ታዲያ ይህ ባህል ጥሩ አንባቢ ያደረጋቸው ይመስለኛል፡፡ ብዙ ሰው በየቀኑ እንደጉድ የሚታተሙትን ክምር ጋዜጦችና መፅሔቶች ከጁ አይለይም ማንበብ ነው ፌርማታው እስኪደርስ!!

ሎንዶን ውስጥ ለመጓጓዝ የአውቶቡስ ወይም የምድር ውስጥ ባቡር መጠቀም ይችላሉ፡፡ ባቡር ጣቢያ ውስጥ ጧት የገዙት የሙሉ ቀን ቲኬት እስከተወሰነ ክልል ወደ ፈለጉበት አቅጣጫ በተቆጣጣሪው ማሽን እያስመዘገቡ ማለት ካርዱን ሲከቱት ወደ ባቡሩ ጣቢያ መግቢያ በሩ ስለሚከፈት መጓዝ ይቻላል፡፡ እንዲሁም የአንድ ጉዞ ቲኬት ቦታውን ነግረው ከገዙ ባቡር እየለዋወጡ ቢጓዙ እንኳ መጨረሻ ጣቢያ ወይም ፌርማታ ጋ ሲደርሱ ይከቱታል በሩ ይከፈትሎታል ካርዷን ግን ማሽኑ ያስቀራታል፡፡ እዩት እንግዲህ

ንግግር የለ ጭቅጭቅ የለ ሰውን የተካው ተቆጣጣሪ የሚሠራውን ጉድ! ምናልባት የወር ቲኬት የገዙ እንደሆነ አይቶ በር የሚከፍትሎት አንድ ሰው ይቆማል፡፡ በነገራችን ላይ የቀን ሙሉውን ቲኬት ከምድር ውስጥ ብቅ እያሉ በአውቶቡስም ሊጓጓዙበት ይችላሉ ለሁለቱም ይሠራል ማለት ነው፡፡

ሎንዶን ከጫፍ ጫፍ 80 ኪሎ ሜትር ይረዝማል የሚል ወሬ ሰምቻለሁ፡፡ ስለዚህ ከተማዋን ከተወሰነ አካባቢ በላይ ማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የጓደኛዬ ወዳጅ በመኪናው ወደ ኳስ ሜዳ ይዞን ሲጓዝ የሚነዳው በካርታ እየተረዳ መሆኑ አስገርሞኛል፡፡ ይህን ከተማ ለማወቅ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅብኛል አልኩት፡፡ የኔ ወንድም አለኝ ሲመልስልኝ "እኔ እዚህ ከሀገሬ ደቡብ አፍሪካ ከመጣሁ 14 አመት አልፎኛል ነገር ግን አሁንም ከከተማው ከተወሰነ ቦታ በላይ አላውቅም" ሲለኝ ግርምቴ በዛ ፡፡

የኳስ ነገር ካነሳን ማንቸስተር ዩናይትድና ዊምብልደን ሲጋጠሙ ሜዳ ተገኝቼ ተመልክቼአለሁ፡፡ ያን በቴሌቪዥን እመለከተው የነበር የኳስ ፍቅራቸውን ጠጋ ብዬ ልመሰክር በቅቻለሁ፡፡ የድጋፍ ጩኸቱ ጭፈራው ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በስሜት ነው፡፡ ማንቸስተር የዘንድሮውን የአንደኛ ዲቪዝዮን ውድድር እየመራ ያለና ብዙ ደጋፊ ያለው የነ ኤሪክ ካንቶና ሺ ማይክል እና የአሠልጣኝ አሌክስ ፈርጉሰን ቡድንን በማየቴ እድለኛ ነበርኩ፡፡ እንደኛ ካታንጋ ላለው ቦታ መግቢያ ዋጋው አስር ፓውንድ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ተጫዋች ኳስ ይዞ ወደ

ጎል ከተጠጋ ጩኸቱ አይጣል ነው፡፡ «Here I said !» (ያልኩት ደረሰ እንደማለት ነው) የሚለው ጩኸት ይበረታል፡፡ እኔም አንድ ጊዜ ጥሩ ጨዋታ አየሁና አጨብጭቤ ወደ ላይ ብዘል ጊዜ ጓደኛዬ ጎትቶ አስቀመጠኝ፡፡ አታስፈጀን ነው መልዕክቱ፡፡ በዚህ ምክንያት አድናቆቴንና ድጋፌን ውጩ ጨዋታውን ጨርሼ ወጣሁ፡፡ በደጋፊ (ቲፎዞ) በሚነሳው ረብሻ ምክንያት የሚሰማራው የፖሊስና የፈረሰኛው ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፡፡ ቅዳሜ ቅዳሜ በቴሌቪዥን ኳስ ስንመለከት  የምናየው ቴምስ የሚለው ሕንጻ ፓርላማቸው ሲሆን ከቴምስ ወንዝ አጠገብ ነው የተመሰረተው፡፡ ወንዙ መርከብ ያስነዳል፡፡ ከተማ መሀል መንሸራሸሪያ መሆኑ ነው፡፡ አካባቢው ኋይት ሆል የሚባሉ የሚንስቴር መሥሪያ ቤቶች ሕንጻዎች ይበዙበታል፡፡

ሎንዶን ከተማ ሲሶው ፓርክ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለጥ ያለ ሠፋፊ አረንጓዴ ሳር የለበሰ (እኛ በዚህች ከተማችን የልጆች ኳስ መጫወቻ የቸገረን) ትላልቅ ሜዳ ሞልቷል፡፡ ሰውም ለጤንነቱ የአካል እንቅስቃሴ በመስራትና በመዝናኛነት በደንብ ይጠቀምበታል፡፡ የቤታቸው  አሰራር ጥንት የነበረውን የሥነ ሕንፃ ጥበብ የተከተለ ነው፡፡ እንግዲህ በሺ ዓመታት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ያንኑ ባህላዊ እሴት ጠብቆ ለማቆየት ሲባል አሁንም ብዙ ረጅም ፎቅ ያለው ሕንጻ አይፈቅዱም፡፡ የመኖሪያ ቤታቸው ባብዛኛው የቤተክስቲያን ቅርፅ የመሰለ ነው፡፡ ቤት በግለሰቦችና በመንግስት ተሰርቶ ይከራያል

ወይም ከ20 እስከ 25 ዓመት ተከፍሎ በሚያልቅ የባንክ ብድር ይገዛል (እንደቤት ኪራይ መክፈል ነው) ። ጓደኛዬ በወር 600 ፓውንድ የሚከፍልበት ባለ ሶስት መኝታ አፓርታማ ገዝቷል። የወለድ መጠኑም የሚጎዳ አይደለም ምክንያቱም ክፍያው ከአቅም ጋር የሚወሰን ነውና። አበዳሪዎቹም ባብዛኛው ቢልዲንግ ሶሳይቲ የሚባሉ ማህበራት ናቸው። በእንግሊዝ ሀገር የአንድ ቤተሰብ አማካኝ የሳምንት ገቢ 374 ፓውንድ እንደሆነ ከጋዜጣቸው አንብቤአለሁ። የዋጋ ግሽበት ሲከሰት ደሞዛቸው አብሮ ይስተካከላል።


በሎንዶን ጎዳና ላይ ፔካዴሊና ኦክስፎርድ ሴንተር የመሳሰሉ የቱሪስት ገበያ ቦታዎችና ሌሎች ያማሩ ነገሮች እንደሚገኙ ሁሉ የኔ ቢጤዎችም ሣንቲም ሲለምኑ ይታያሉ። አለማመኑም ከአፍ ከመለመን አንስቶ በሙዚቃ መሣሪያ እሚታጀብ ድረስ ነው። መተኛ ፍራሻቸውን ይዘው የሚዞሩ ቤት - አጥ /Home less/ (በረንዳ አዳሪ አይባልም) አጋጥመውኛል።እንዲሁም ወጣት አጥፊዎችም የቴሌፎን ሣጥን ሣንቲም ለማውጣት ሲጎረጉሩ ይታያሉ። መንግስት ለሚለምኑ ሕዝቡ ገንዘብ እንዳይሰጥ ያስገነዝባል። ምክንያቱም የማሕበራዊ ዋስትና ክፍያ ስለሚሰጣቸው ተጨማሪ ገቢ ፍለጋ መሆኑን በመቃወም ነው።

ተመጽዋቾቹ ግን በውስጥ ለውስጥ መተላለፊያዎችና በምድር ውስጥ ባቡር ጣቢያዎች ሰወር ብለው ይለምናሉ፡፡




እንዲሁም ፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴ የሚያራምዱ ነጮችና ጥቁሮች ባብዛኛው ነጮች መንገድ ላይ ገንዘብ ሲያስባስቡ ይታያሉ፡፡ እነዚህ

ቡድኖች ሰላማዊ ሰልፍ በማደራጀት ተቃውሞአቸውን በማሰማት ይታገላሉ፡፡ በዚህም ውጤታማ እንደሆኑ ተገልፆልኛል፡፡




መቼም የትልቅ ከተማ ባህሪ ነው ባትሉኝ የፖሊስና የአምቡላንስ መኪና ጩኸት አዘውትሮ የሚሰማ ሲሆን ሕዝቡ ግን በመላመዱ ይሁን አላውቅም ብዙ ትኩረት አይሰጠውም፡፡ እንደኔ ለሀገሩ እንግዳ ለሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ትንሽ መሸበሩ አይቀርም፡፡ ጠይቄ እንደተረዳሁት ትንሽ ሆነ ትልቅ ጉዳይ ቢሆንም አንደቀላል ስለማይታይ ተሯሩጠው ይደርሳሉ፡፡ የጥንቃቄአቸውን ደረጃ ጓደኛዬ ሲገልፅልኝ ምናልባት ሁለት ልጆች ተጣልተው ለመገላገልም ሊሆን ይችላል ብሎኛል፡፡ በእንግሊዝ የህግ ትንሽ ትልቅ የለውም ሁሏም እኩል ነው የምትከበረው፡፡ ለምሳሌ በኤሌክትሪክ ደረጃ (አስካሌተር) ላይ ቆመው ወደ ላይ ሲወጡም ሆነ ሲወርዱ መስመርዎን ይዘው መቆምና መጓዝ አለብዎት፡፡ ምክንያቱም የቸኮለ ክፍት በሆነው

ጎን በፍጥነት ስለሚራመድ ነው፡፡ ይህን ባለማስተዋል ቢቆሙ ይህች ትንሽ ሕግ መጣስ ለበለጠ አደጋ ምክንያት ይሆናል ብለው ሰለሚያስቡ በጥንቃቄ ነው ሕዝቡም የሚያከብረው፡፡ እንግሊዞች ግራ አይደሉ መኪና ሲነዱ ማለቴ ነው እርስዎም ይህን አስተውለው መስመሮን ማስተካከል ነው ፡፡ የሕግ ነገር ከተነሳ ልጆችና ሴቶች ትንሽ ከፍ ያለ የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ኑሮ ውድ ነው ርካሽ ለማለት የዚያው ሀገር ኗሪና ተቀጣሪ መሆን ያሻል፡፡ ምክንያቱም በኛ ሀገር ሁኔታና ምንዛሪ ካሰላነው ለምሳሌ አንድ ትልቅ ብርጭቆ ቢራ ብር 18 (አንድ ፓውንድ ከሰማንያ ፔንስ) ነው ቢባል ማመን ያስቸግራልና ነው፡፡ ስለዚህ እንግሊዝ ሲኖሩ እንግሊዛዊ ሆነው ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ መጠጥና ሲጋራ በታክስ ትልቅነት ምክንያት ዋጋቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የሆነው መንግስት ሕዝብ እንዳይበረታታና እንዳያዘወትራቸው በማሰብ ነው፡፡ ለነገሩ እነሱ የፈለገውን ቢጠየቁ ይከፍላሉ፡፡ በሲጋራውም ሆነ መጠጡ ላይ ሴቷም ወንዱም እኩል ተሰልፈው ነው የሚያመሹት፡፡ በሁለት አጋጣሚዎች ያየሁት የሪሴፕሽን ግብዣ እንዳሀገሬ እንደሚደረገው አይነት ትንሽ ተበልቶ ብዙ የሚጠጣበት አይነት አይደለም፡፡ ብዙ አማርጬ በላሁና ያገኘሁት ማወራረጃ ቀይና ነጭ ወይን ጠጅ ብቻ ነበር፡፡ ምክንያቱም እላይ እንዳልኩት መሆኑ ነው፡፡

በመሀል ሎንዶን ትራልፋልጋር ፏፏቴን ለቁጥር በሚያታክት እርግብና ቱሪስት ተከቦ ያገኙታል፡፡ ሎንዶን ደርሰው ጎበኘሁ ከሚሉት ነገር አንዱ እርሱ ነው፡፡ ሎንዶን በያመቱ ብዙ ቱሪስቶችን እንደምታስተናግድ ሰምቻለሁ፡፡ በተረፈ ሁሉንም አውርቼ አልጨርሰውም፡፡ ለማንኛውም ማየቱ ብዙ የግንዛቤ ለውጥ እንደሚያመጣ ለራሴው መስክሬ እንደ እንግሊዞች በይቅርታ ልመና የጀመርኩትን ጉዳይ አመስግኛችሁ ብንሰነባበት፡፡ Excuse me Sir Thank You! ከአፋቸው የማይለይ ትልቁ ባህላቸው ነው፡፡ ጥያቄ ለመጠየቅ ሲጀምሩ ኤክስኪዩዝሚ ሰርን ያስቀድማሉ፡፡ ላደረጉላቸው በጎ ነገር (ሱቅ ገብተው እቃ ቢገዙአቸው እንኳ) ታንክ ዩ ማለት በነርሱ ዘንድ ከቶ እንዴት ይረሳና! በቸር ይግጠመን፡፡

(በ1986 ዓ.ም. ብሪቱ መጽሄት ቁ.55 ላይ የታተመ)

## ፳፩. በጦርነት ማግስት /War Hangover/

አንጐቨር ስል ይሄ በቡናና በምናምኑ ለማስለቀቅ የምንታገለውን የመጠጡን የዞረ ድምር ሳይሆን የጦርነትን ማግስት ዋር አንጐቨር ማለቴ ነው። ይሄኛው አንጐቨር አዲሳባን ለቃችሁ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ስታመሩ ሰንዳፋ ስትደርሱ የታንክ መዓት በሸራ ተሸፍኖ ስታዩ ትላንት ምን ላይ እንደነበርን ትገነዘባላችሁ። ይህ ብቻ አይደለም ጉዞአችሁን እስከዳር ካዘለቃችሁት አካላቱ ተገፎ አጥንቱ ብቻ የቀረውን የጦር መኪና፣ መድፍ፣ ታንክ፣ ቢ.ኤም እና ሌላም ሌላም ትርፍራፊ ታያላችሁ። ምናለ እኔ እስከደረስኩበት ለማየት ከፈለጋችሁ አብረን ብንቆይ።

ጦርነቱ ብሎ ብሎት ያበቃለት አካባቢ በመሆኑ አንፃራዊ ሰላም የሰፈነ ቢመስልም አልፎ አልፎ ብቻ ወደ ከሚሴ ላይ አንዳንድ የጊዜን አጋጣሚ የሚጠቀሙ ዘራፊዎች እንዳሉ ሰዎች ይነግሯችኋል። እኔም ይህንኑ ብዬ ስንቄን በቅድሚያ በባንክ በድራፍት ቼክ ነው የቋጠርኩት። አያጋጥም እንጂ በኪሣችሁ እሷም ከተገኘች አሳኝከው እንድትውጡት ያስገድዳሉ አሉ እነዚያ ዘራፊዎች። ለማንኛውም እግዜር ይመስገን ብዙ ኪሎ ሜትር ዙሪያውን ስዞር ምንም አላጋጠመኝም። ለጨዋታው እንዲያመች አንድ በአንድ ከተሞቹን እየጠቀስኩ ባዞራችሁስ:-

## ሰንዳፋ

ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ቅርንጫፍ ባንክ ለመክፈት የሚያስችል ጥናት ለማድረግ ጉዞ የጀመርነው መስከረም 11 ቀን 1985 ዓ.ም. ነው፡፡ ሰንዳፋ ከአዲስ አበባ 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝና በውስጧም የእጩ ምክትል መቶ አለቃ ፖሊሶች ማሠልጠኛ/ፖሊስ ኮሌጅ/ ከማቀፏም በላይ ሌሎችም ተቋማት ይገኙባታል፡፡ ዛሬ ያ ኮሌጅ በፖሊስነት የሚሰለጥኑ ሳይሆን ሌሎች ጊዜ የጐደለባቸው የቀድሞ ሹሞችን በመጠለያነት ወይም በጊዜያዊ ማረፊያነት እያገለገለች ነው፡፡ ምናልባትም በግቢው ውስጥ በክብር ዘብ ሰላምታ እየታጀቡ ዋንጫና ሌላም ሽልማት በመስጠት የመረቁ ሹመኞች ዛሬ በሌላ መልኩ የምታስተናግዳቸው ይሆናል፡፡ አያምጣው ነው ጊዜ የማያሳየው የለ፡፡

ሰንዳፋን ቀረብ ስንል ከትላንቱ ሩጫቸውና ግዳጃቸው እፎይ ያሉ በርካታ የጦር መሣሪያዎች በላስቲክና በሸራ ተሸፍነው ታያላችሁ፡፡ በአንድ ወቅት የመጀመሪያው የአገሪቱ የሽግግር ጊዜ ፕሬዚዳንት ለንደን ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ (የመንግሥትነቱን ሥልጣን ለመረከብ ወደ አዲሳባ ከመነሳታቸው በፊት) አንድ ፈረንጅ ጋዜጠኛ የድርጅታቸው አርማ ላይ ያለውን የክላሽንኮቭ ጠብመንጃ አስመልክቶ ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ “ጠብመንጃውን ከእንግዲህ አንፈልገውም” ባሉት መሠረት መሰብሰባቸው ይሆን ብዬ ትንሽ አሰብ ሳደርግ መኪናው ይዞኝ እብስ አለ፡፡

## ሸኖ፤ደብረብርሃን፤ደብረሲና፤ሸዋሮቢት፤አጣዬ፤ኮምቦልቻ

ሸኖ ደረስን ቁርስ ላይ የነጭ ዳቦ ዘር ሳይ ቀደም ብዬ በጦርነቱ ወቅት ያላጋጠመኝ ነበርና ገረመኝ፡፡ በሰላም ምን የማይገኝ ነገር አለ?

የ600 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋዋ ደብረብርሃን የሰሜን ቀጠና የጦር ዘመቻ ማዕከል ነበረች፡፡ ዛሬ ያ ሁሉ የወታደር ሠራዊት ትርምስምስ የለም፡፡ እሷም እንደ ታንኮቹ ረጭ ብላለች፡፡ ታዲያ እንደበፊቱ የሰሜን ሸዋ ማዕከልነቷ ይቀጥል አይቀጥል የሚለው አልታወቀምና ልማቷ ቀዝቀዝ ብሏል፡፡ ይህ እንኳ የሚቀጥል አይመስለኝም፡፡

ያ ጥልያን መጥቶ ይህን የዋሻ መተላለፊያ ባይሠራው ኖሮ ከሰሜን ከተሞች ጋር እንዴት ነበር የምንገናኘው በማለት ትንሽ እንደ ጆሜትራ ለራሳቸሁ የቤት ሥራ የምትሰጣችሁ ደብረሲና ለመግባት ስትቃረቡ የጣርማ በር ዋሻን ስትመለከቱ ነው የምትገረሙት፡፡ እዚያ አፋፍ ላይ የተደረገው ጦርነት አፍርሶት ቢሆን ኖሮ ብላችሁ ትንሽ ይሰቅቃችኋል፡፡ ጦስኛችሁን ከዋሻው አፍ ላይ ሽምታችሁ ወደ ደብረሲና ማቅናት ነው፡፡

የደብረሲና ከተማ አቀማመጥ በጣም ያስገርማል፡፡ አናቷ ላይ በምን መሰላል እንደወጣችሁ ሳይታወቃችሁ ቁልቁል ያንን አሮጌ ከተማ በሙሉ ስጡን ሳይቀር ትመለከታላችሁ፡፡ ወረድ ብላችሁ ታዲያ የጦስኝ ሥጋ ከጥሩ ብልጣብልጤ /አረቄ/ ጋር ስታወራርዱ እዚያ

ደጋ ሀገር የኖረ ሰው ምን ያህል ዘመን ወይም ዕድሜ እንደሚኖረው ትገምታላችሁ፡፡

የሸዋሮቢትን ንዳድ መቻል ነው እንጂ ለአዲስ አበቤስ እንኳን ማደሪያ መቆሚያም አትሆን፡፡ ቢሆንም እንግዳን አባብላ ለማቆየት ነው መሰለኝ ሽንኮራውን፣ ሙዙን፣ ብርቱካኑን መንገድ ዳር ዘርግፋ ትቀበላችኋለች፡፡ የሚያመርቱት በከተማው ውስጥ በማረሚያ ቤት የሚገኙ የሕግ እስረኞች ናቸው፡፡ መታረምን፣ በወዝ ማደርን ማስተማሪያ ትልቅ ተቋም ነው፡፡

በድሮ ስሟ አጣዬ በክርስትና ስሟ ኤፌሶንን አልፋችሁ ስትሄዱ ካራቆሬን ታገኛላችሁ፡፡ ይህች ካራቆሬ የደሃ መሃረብ የምታክል ከተማ በጥንት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክ ተመዝግቦ የሚገኘውን የመሬት መንቀጥቀጥ ከቀመሰች በኋላ ከተማነቷ እንዲቀርና ነዋሪዎቿም ወደ አጣዬ እንዲሰፍሩ ቢባልም አሁንም ደጃፋቸውን የመኪናውን አስፋልት ያደረጉ ብዙ ቤቶችና ነዋሪዎች ታገኛላችሁ፡፡ እንዲያው ስታልፉ የእያንዳንዷን ቤት ጓሮ ለመመልከት ብትሞክሩ አለ ገደል ምንም አታዩም፡፡ የሚገርም የቀዬ ፍቅር!

ሞቅ ያለችውና የኮንትሮባንድ ዕቃ በተፈለገው ዓይነት የሚገኝባት የንግድና የኢንዱስትሪ ከተማ ይዘት ያላትን የኮምቦልቻ ከተማን ዝም ብሎ ማለፍ አይቻልምና እስቲ ሻይ ቡና እንበል፡፡ ኮምቦልቻ በባቲ በኩል አፋርንና አሰብን እንዲሁም ወረኢሉን የመሳሰሉትን

ከተሞች ለመድረስ ኮሪደር ነች። የቦርከና ግድብ፣የጨፋ እርሻ ልማት፣ የጨርቃ ጨርቅና የሶፕራን ሥጋ ፋብሪካ፣ የመሳሰሉት በቅርብ አካባቢና በከተማዋ ውስጥ ይገኛሉ። ታዲያ ጦርነት ክፉ አውሬ እነዚህን ተቋማት ሊበላና ሊያጨልማት ተወናጭፎባታል። የእግዜሩ ነውና የሚበልጠው ሰውሯት ዛሬም እንደ ትላንትና ወዲያው ደምቃ ትታያለች።

የጦሳን አቀበት ዝንጀሮ አትወጣውም ነበር ያለው ዘፋኙ አለማየሁ እሸቴ? እኛስ በዚህ በጃፖኖቹ መኪና ተሽከርክረን ተጥመዝምዘን ደሴ ጉድጓዳዋ ወደ ማምሻችን ብቅ አልን። ንጉሥ ሚካኤል ተመልሰው ቢመጡ ደሴን እንደተውአት ነው የሚያገኟት እንደተባለው እኔም ከአምስት ዓመት በኋላ ስመለስ የመንገድ ዳሩን እንቅፋት እንኳ አላጣሁትም። ደሴ ዛሬ ዛሬ ትንሽ ተንፈስ ብላ ነው አሉ እንጂ ከኤርትራ፣ ከአሰብና ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተፈናቀሉ ሰዎች ማረፊያ ሆና ነው የከረመችው።

በጧቱ ደሴን ለቀን ወደ ሎጊ ሀይቅ አቀናን። በመሀሉ የጢጣን የመኮንኖች ማሰልጠኛንም አይተን አለፍን። ሀይቅ የአምባሰል አውራጃ ዋና ከተማ ነች (በድሮው አጠራር)። ሀይቅ ስንደርስ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጓደኛዬ እዛ ግብርና ሚኒስቴር ስትሠራ የነገረችኝ ትዝ አለኝ። በወቅቱ የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ከደርግ ተለያይተው አሜሪካ የገቡበት

ጊዜ ነው፡፡ ወሬው በሰፊው የሚወራበት ነበርና የቢሲቲማው የገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር የነበሩት አንድ ቀን በስብሰባ ላይ "አሁንስ እንደዚያ ምርር ብሎት እንደጠፋው ሚኒስትር እኔም ልጥፋላችሁ" ብለው ብሶታቸውን የገለጹበት አጋጣሚ ነው ትዝ ያለኝ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ጓደኛዬም አሁን እዛ የለችም፡፡ እሷም ትዝ አለችኝ፡፡

ትዝታ ለመጨመር  ታሪካዊውን የእስጢፋኖስ ገዳም ለመጐብኘት ወደ ሀይቁ አመራን፡፡ የእስጢፋኖስ ገዳም ከተተከለ 1162 ዓመት በላይ እንደሆነው አስጐብኚአችንና ጠባቂው ነግረውናል፡፡ ታዲያ እዚያ ገዳም ሴት አይገባም መናንያን ካልሆኑ በቀር፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያውን ስናይ በጦርነቱ ወቅት በከባድ መሣሪያ የተመታውን ጐኑንም ተመልክተናል አሁን ግን ተጠግኗል፡፡ የሚገርመው እሱን ተገን ያደረጉ ባህታውያንና ፈሪዎች ምንም አደጋ እንዳላጋጠማቸው ሲነግሩን በእሱ ሥራ ብዙ ተደነቅን፡፡ እዚህ ቦታ ያየነውን ነገር ሳይጠቅሱ ማለፍ ጥሩ አይሆንም፡፡  በሀይቁ ዳር ለአካባቢው ጐብኚዎች መዝናኛ እንዲሆን ታስበው የተሠሩ  ዘመናዊ የጐጆ ቤቶች ከማለቃቸው በፊት ኢሕአዴግ አካባቢውን በመቆጣጠሩ ቤቶቹ ቆርቆሯቸው ተዘርፎ ያለ ጥቅም ሜዳ ላይ መቅረታቸው በጣም አሳዝኖናል፡፡ ይህን ቦታ የረገጠ ሰባት ትውልዱ ድረስ መርቄዋለሁ ብለው መልዕክታቸውን እስከ እኛ ያደረሱትን መሥራች የአባታችንን በረከት ተቀብለን ወደ ከተማው ተመለስን፡፡ ጥሩ የአሣ ወጣችንን ከበላን በኋላ ጉዞአችንን ወደፊት አቅንተን ውጫሌ ደረስን፡፡

ታሪካዊቷ ውጫሌ ያንን የውጫሌ ውል ተብሎ የሚታወቀውን ውል ከጣሊያን ጋር የተፈራረሙበትን ዋርካ ዛሬም በምስክርነት ይዛ ትገኛለች። ከዚያም ውርጌሳ ትደርሱና ትልቁን የብረት ድልድይ ታገኛላችሁ። ይህ ድልድይ በጦርነቱ ወቅት የፈረሰ መሆኑን ማንም ባይነግራችሁ ፍርስራሹ ድሮ እኔ ነበርኩ ይላችኋል።

ቀጥሎ መርሳ ከተማን ወይም መርሳ አባጌትዬ (የአካባቢው አዋቂ ናቸው) ታገኛላችሁ። ይህቺ በእጅጉ በጦርነት የተለበለበች ከተማ አሁንም አለሁ ትላለች። ያ በቴሌቪዥን የተመለከታችሁት ብዙ ሰዎችን ከአውሮፕላን ቦንብ ያስጠለለ ድልድይ አሁንም በግልጋሎት ላይ ይገኛል። መርሳን ለቃችሁ ወደ ወልድያ ስታመሩ ያቺን ዝርግ መሬት ለምለሚቷን ሲሪንቃን ሳያዘክሩ ማለፍ አይቻልም። የወሎን አካባቢ በተደጋጋሚ በድርቅ መመታት ለማስተባበል የቆመች ትመስላለች። ካለ አረንጓዴ ነገር አይታይም። እንጃ ወቅቱም ይሁን አላውቅም መስከረም እንደጠባ ነው ያየሁት ዓይኔ ሌላ ስላላየ ነው ይህን ማለቴ። እንክብካቤም የጐደለባት አትመስልም ምክንያቱም የእርሻ ምርምር ማዕከል ሥራውን በሠፊው ይዟልና ነው። ድሮም በድርቅ ኮሚሽን የሲሪንቃ ፕሮጀክት ሲባል እሰማ ነበር።

## ወልድያ

አሯሩጬ ወልድያ አደረስኳችሁ አይደል? ግዴለም እዚህ ትንሽ ቀን እንቆያለን። ወልድያ ከአዲስ አበባ 520 ኪሎ ሜትር ርቀት

ላይ በስተሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ ተራራ ዙሪያዋን ዘብ የቆመላት ከተማ ነች፡፡ ከተቆረቆረችም 85 ዓመት ይሆናታል፡፡ በቀድሞው አጠራር የየጁ አውራጃ ዋና ከተማ ነበረች፡፡ ዛሬ በክልል 3 የሰሜን ወሎ ዞን ማዕከል ነች፡፡ ድንበሯ በፊት አሸንጌ ሀይቅ ነበር፡፡ አሁን ኮረምና አላማጣ ወደ ክልል አንድ ሲጠቃለሉ ከዚያ መለስ ያለውን በጐንደር ወሮታ መስመር እስከ ጨጨኾ መድኃኒአለም ማለት ጋይንት አዋሳኝ ድረስ የሷ ነው፡፡

የጁ በእጁ ይባላል አሉን አንድ ጠላ ቤት የተዋወቅናቸው ወንድሞች፡፡ ለምን እንደሆን ባይዘረዝሩልንም መልዕክት እንዳለው ገምተናል፡፡ ወልድያ ዛሬ ከጦርነቱ በኋላ ለማገገም ሌት ከቀን ጥረት ላይ ነች፡፡ ኤሌክትሪክ ከቆቃ እየተሳበላት ነው፡፡ አውቶማቲክ የቴሌፎን ማዞሪያና ትልቅ የውኃ ፕሮጀክት ሥራም እየተካሄደ ነው፡፡ በአውሮፕላን ቦንብ የፈራረሱት አንዳንድ ተቋማት አሁንም እላያቸው እንደተገለበ ይታያል፡፡ አካባቢው በኢህአዴግ ቁጥጥር የዋለው ቀደም ብሎ በጥቅምት 1982 ዓ.ም. እንደነበረም ተረድተናል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደፊት ለቀጠለው ጦርነትም እንደ ዘመቻ ማዕከል እንዳገለገለችና የዛሬው መሪዎችም በከተማዋ ውስጥ እንደኖሩባት ሰምተናል፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት ከተማ ውስጥ በሚገኝ አዳራሽ ስብሰባ እንደተቀመጡ የጦር አውሮፕላን መጥቶባቸው እንደነበረና ቀደም ብለው ከአዳራሹ ለቀው ባዶ ቤት

ደብድቦና አፈራርሶ እንደተመለሰ ያን አዳራሽ ምነው ፈረሰ ብላችሁ ብትጠይቁ ትረዳላችሁ፡፡

ወልድያ በቆየንበት ወቅት አንዳንድ ቦታዎችን ለመጐብኘት ዕድል ገጥሞናል፡፡ ታዲያ ጠላ ቤቱንም አልዘነጋነውም፡፡ ነብሱን ይማረውና አንጋፋው ጋዜጠኛና ደራሲ ጋሼ ጳውሎስ ኞኞ ብዙ ጊዜ እንደሚለው ከነዚህ መሸታ ቤቶች ብዙ ቁም ነገር ይገኛል፡፡ እንዲያውም አንድ ምሽት ላይ የገነተ ልዑል ማርያም ቤተክርስቲያንን የመስከረም ንግሥና የመንገዱን ርቀት የነገሩንን ሰዎች ያገኘናቸው እዚያው ጠላ ቤት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም ነፃነት የተሞላው ጨዋታቸው አይረሳም፡፡ ብዙ ጨዋታቸው ግን ወደ ፍቅሩ ነው የሚያደላው፡፡ በፍቅር ጉዳይ ከፈረንሳዮች ጋር ያመሳሰለብኝን ሰው ዘነጋሁት፡፡ እኔስ ከጨዋታቸው አንዱን ብነግራችሁ “እንግዲህ አንድ ወዳጅ የያዝኩ እንደሆነ! ከጣፈጠችኝ ከጣፈጥኳት!በቃ! ሌላ ቦታ አልሄድም” ኸረ ብዙ ነው፡፡

ገነተ ልዑል ቤተ ክርስቲያን በእኛ ቀርፋፋ ጉዞ ሁለት ሰዓት ተኩል ነው የወሰደብን፡፡ ቢሆንም መንገድ ላይ ለማንገስ የሚሄደው ሰው ብዙ ነውና ባይተዋር አትሆኑም፡፡ እኛም እንዳጋጣሚ በብዙ ወጣቶች ታጅበን ነው የደረስነው፡፡ ወጣቶቹ የየጁን ጥንቅሽ አቀበት መውጫ እየቆረጡ ያስታቅፏችኊል፡፡ የጁ መጥታችሁ የየጁን ጥንቅሽ ሳትቀምሱማ አገራችሁ ስትገቡ ምን ብላችሁ ልታወሩ ነው ይሏችኊል እነዚያ ፀባየ ሸጋዎቹ አሊጋዝ፣ ደምሴ፣ ሽሽግ፣ወ.ዘ.ተ.፡፡

ያቺ የፍቅር ጨዋታቸውም አትቀር፡፡ ሽሽግ የሠፈሯን ልጆች አግኝታ "አንተ ደሚሴ አሁን እኮ የምትሉኝን አውቃለሁ" ትላለች፡፡ እሷ እንግዲህ ከገጠሩ ከተማ ገብታለች፡፡ "ይሄኔ እኮ ጠንቶባት ነው የሄደችው ትሉኛላችሁ አይደል" ይልቅ እሱን ተይውና ሽሽግ አድራሻሽን ንገሪንና መጥተን እንድንጫወት ይላታል፡፡ ከዚሁ ሁሉ ብዙ የማይሳተፈው አይናፋር መሳዩ አሊጋዝ ብቻ ነው፡፡

ገነተ ልዑል ማርያም የተቆረቆረችው በ1948 ዓ.ም. ሲሆን ያሠሯት አቡነ ታዲዎስ እንደሆኑ ሰዎች ነግረውናል፡፡ ታዲያ ታቦት ከመግባቱ በፊት ያለው ጭፈራ ለጉድ ነው፡፡ የዚያች ስንቱን ወንድ ያሸነፈች አንዲት ኮረዳ እስክስታ ዐይኔ ላይ ይመጣል፡፡ በሷው እስክስታ ፈዘን ታቦት መግባቱን የተረዳነው በታጣቂዎችና የመከላከያ ሠራዊቱ አባላት የደስታ ተኩስ ነው፡፡ ተኩሱ ግን ለምን እንደሆነ አሁንም አይገባኝም፣ ድሮ መኖሩም ትዝ አይለኝም፡፡ ከዚያ መልስ በቤተ ክርስቲያኑ በኩል ስድስት ወራት የተዘጋጁበትን ጠበል ጠዲቅ ቀምሳችሁ በጊዜ ወደቤት ለማዝገም ትነሳላችሁ፡፡ እኛም መስሎን ነው እንጂ ቤታችን የገባነው በአሊጋዝ ግብዣ እጅግ በጣም ዘግይተን ነው፡፡ አትለፉ ፀበል ሳትቀምሱ ይባላል! ያ የባላገሩ ባህል አሁንም እንዳለ ነው፡፡

እኛ እንኳ የገባነው የአሊጋዝ አማቾች ቤት ነው፡፡ መጀመሪያ የባለቤቱ ወንድም ቤት ልንገባ ስንል መግቢያው ላይ አንዲት የምታምር ጉብል አሊጋዝን በመሳም ለብዙ ደቂቃዎች አቆመችን፡፡ ገርሞን

ምንህ ነች ብንለው ሚስቴ ነበረች አለን፡፡ አሁንስ ብንለው ሰማንያ አልቀደድሁም እንጂ ፈትቻታለሁ፡፡ ለምን አልነው፡፡ ግብርናው ብለው ብለው በዝናብ መጥፋት አልሰጥ ቢለኝ በሽቀኝና ጥዬው ወደ እህቶቼ ጋ ዱብቲ ወረድኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ያለኝን ሰጧትና ወደ ቤተሰቦቿ ላክኋት እንጂ ፀብ የለም፡፡ አሁን እንዴት መጣህ እህቶቼ የአባታችን ስም እንዴት ይጥፋ ብለው መልሰው ሰደዱኝ፡፡

በመጨረሻ የገባነውና ብዙ ጊዜ ከእሷ አባት ጋር በጨዋታ ያሳለፍነው እነ እንጐቻ ቤት ነው፡፡ ምነው አሊጋዝ ትላንት ብቅ ሳትል ዋልክ ሣር ሳታጭድ ቀረህ ቢሉት ጊዜ ይሄ ሰው መቼ ነው የተፋታው ወይስ የአካባቢው ባህል ይሆን አማች እንደልጅ የሚቆጠርና የሚታዘዘው ብለን ገረመን፡፡ አባትዬው በጣም ጨዋታ አዋቂ ናቸው፡፡ ጠላችንን በሽክና ይዘን ብዙ አወጉን፡፡ እንዴት ነበር ጦርነቱ አልናቸው ጦርነቱማ እዚሁ ደጃችን ላይ ነበር፡፡ አየር ወለድ ኮማንዶ ምኑ ቅጡ እንዴት እንዴት ያሉ ሸበላዎች ወደቁ እዚህች እኛ ሠፈር! ብለው ትንሽ ተከዙ፡፡ ማ ነበር የሚሉሽ የእንጐቻ እናት ሲሉ ባለቤታቸውን ጠየቁ፡፡ ማተር፣ ማዘር ነበር አሉአቸው፡፡ ከቤታችን አይወጡም ነበር አሉ፡፡ ታዲያ ምን ያረጋል አለቁ፡፡

አሁን እንዴት ነው ጥሩ ነበር ግን ትንሽ ቅር ብሎናል፡፡ የአሁኖቹ መሬቱን በጣጠቁብን፡፡ 15 ዓመት ከሞላት እሷም ይህም ትንሹ ልጄም መሬት ማግኘት አለበት ብለው እኛ ከምናርሰው እየወሰዱ አከፋፈሉት ምንም ለማይሠሩበት! በዚህ ተቀይመናል፡፡ ምን

መሰለህ ገበሬ ልብሱ አዳፋ፣ አፉ ጐልዳፋ ይባላል፡፡ በዚህች ነገር ተቀይመናል፡፡ መሬት ጦም አሳደሩብን፡፡

በዚህ ጊዜ ታዲያ አሊጋዝና እንጐቻ አፍ ለአፍ ገጥመው ይንሾካሾካሉ፡፡ እሱ እንደነገርኳችሁ አይናፋር ነው፡፡ እሷ ደሞ የሁለት ወር ልጃቸውን አቅፋ አይን አይኑን እያየች አጠገቡ ቁጭ ብላ የናፍቆት ወሬ ታወራለች፡፡ ከአባትዬው ጋር ተሰነባብተን መንገድ ስንቀጥል እሱ እንዲቆይ ወተወቱት፡፡ መንገድ ብቅ ላርጋቸው ብሎን ተከትሎን ወጣ፡፡ ታዲያ አፋፍ ቁሞ ታች ላሉት በጨኸት እየተቀባበሉ ጥንቅሽ ቆርጠው እንዲያሲይዙን ነግሮልን ስንሰነባበት እኛም እንግዲህ እዛው ተመለስና እደር አልነው፡፡ እሱም ከጅያለሁ ብሎን ተሳስቀን ከምሥጋና ጋር ተለያይተን ወደ ሆቴላችን አመራን፡፡ ከሁለት ሰዓት በኋላ ደረስን ጠላው ግማሽ ሰዓት ቀነሰልን - ቁልቁል እየገፈተረ ፡፡

ወልድያ በክረምንበት ወቅት አንድ የአካባቢው የኢህአዴግ ሹም ሲያጫውቱን ከሰቆጣ ገበሬዎች ይመጡና ታምራትን አምጡ ይሉናል፡፡ ታምራት እዚህ የለም ስንላቸው አድራሻውን ንገሩን እንሄዳለን ይላሉ፡፡ ያለው አዲስ አበባ ነው እሱን ለማግኘት ትንሽ ያስቸግራችኋል፡፡ እሱ ያለበት ቦታ አያስገቧችሁም ስንላቸው ታምራት እንዲህ ሆነ - ወይኔ ወንፈልና ጅጊውን ረሳው ይላሉ፡፡ እንግዲህ ሰቆጣ /ዋግ/ የኢህዴን የመጀመሪያው ምሽግ ስትሆን በቁጥጥርም ያዋሏት እጅግ ብዙ ጊዜ ቀደም ብሎ ነበር፡፡ ሕዝቡ አቅፏቸው የኖረ

ነበረና በዚህ ጊዜ ውስጥ በሕብረቱ ሥራ ውስጥ እየገቡ ይሠሩ ነበር፣ በሥራውም አጋጣሚ የዕለት ምሣም ይተረፍበት ነበር አሉን፡፡ ይህን ማስታወሳቸው ነው፡፡ ምናልባት ዛሬ ጠቅላይ ሚኒስትሩን የፈለጓቸው ያኔ እነሱን በማቀፋቸው ልማታቸው በመንግሥት በኩል በመዘጋቱና ያለውም በጦር አውሮኘላን በተደጋጋሚ በመጠቃቱ ዛሬ እንካስ ለማለት ይሆናል፡፡ ብቻ ማን ያውቃል ቢገናኙ የሚሉትን፡፡

## ዶሮ ግብር፣ ቆቦ፣አላማጣ፣ኮረም

ወልድያ አይበቃችሁም ምነው ወደ ዶሮ ግብር ወጣ ብላችሁ እየተናፈስን ወደ ሰሜን ብናቀና፡፡ ዶሮ ግብር ጥንት የአካባቢው ገዥ ግብር ለመሰብሰብ ይጓዙ በነበረበት ወቅት እዚች ከተማ ግብር ሊያስበስቡ አርፈው ነበር፡፡ ታዲያ በዚች መንደር ትኖር የነበረች አንዲት ሴት በቤቷ ዶሮ ወጥ ሠርታ ተቀብላቸው በጥሩ ሁኔታ ስላስተናገደቻቸው መንደረተኛውን ሁላ የወቅቱን ግብር ምረዋቸው ስላለፉ የመንደሩ ስም ዶሮ ግብር ተብሎ እንደቀረ ይነገራል፡፡ እንግዲህ ዋቢ አትጠይቁኝ እዛው ጠላ ቤት ነው ያገኘሁት፡፡ ታሪክ እንግዲህ በአፋዊ መልኩስ ይተላለፍ አይደል፡፡ ሌላ ማስተባበያ ካለ እሰየው ብዬ ለመቀበል አሁንም ለወደፊትም ዝግጁ መሆኔን አስገነዝባችኋለሁ፡፡ ምነው ጠላ ቤት ብቻ ብለህ ሞትክ አትበሉኝ፡፡ ቢራው ቤትማ ከአቅሙም ጋር ተሟሙታችሁ ብትገቡ እንኳ የሚያናግራችሁ ብዙ አታገኙም፡፡ እኔ እንጃ ይህ የፈረንጁን ነገር መጨበጥ ያስኮፍሳል ልበል! እዛው እንደልቤ የማወራበት

የሚያወሩልኝ ቤት ልመለስ እሱው ይሻለኛል፡፡ አይመስላችሁም?

ጎብዬ፣ ሮቢት ብላችሁ ቆቦ ትደርሳላችሁ፡፡ ብቻ በቅርቡ ይህ ጄዳ ተብሎ የሚታወቀውን ሠፈር ሳትረሱ ነው፡፡ ይህ የባዕድ ስም የተሰጠው እንኳ ብዙ ሰው ወደ ሳውዲ እየሄደ ኑሮውን መደጐሚያ አይሱዙ መኪናውንም ወርቁንም ይዞ ስለሚመጣ ነው አሉ ይህ ስም የተለጠፈበት፡፡ እንግዲህ ወልደማሪያም መሐመድ ተብሎ ወይም አረጋሽ ፋጡማ ተብላ መሄዳቸውን አትጠይቁኝ፡፡

ቆቦ የከፋው ጦርነት አውድማ ነበረች አሉ፡፡ እጅግ ብዙ የመንግሥት ሠራዊት ሠፍሮባትም ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ብዙ የአውሮፕላን ድብደባም ደርሶባታል፡፡ እዚህ ላይ ብዙ የኢህዴግ ታጋዮች የሚያስታውሷትና ደጋግመው ስሟን የነገሩን ድላይ (ሴት ታጋይ) ታሪክ ላጫውታችሁ፡፡ እንግዲህ ወሳኝ ጦርነቶች ላይ የጋንታ መሪ እኔ እንጃ አዋጊ መኰንን ማለታቸው ነው መሰለኝ፤ ብቻ መሪ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ በጣም ደፋሮች ቆራጦችና ጨካኞች ስለሆኑ ነው አሉ፡፡ ድላይ በአንድ የጦርነት ውሎ ስታዋጋ ውላ በላውንቸር ሆዷን ትመታለች፡፡ የወጣውን አንጀቷን በዚያ በአንገት ልብሳቸው /ሽርይ/ ታስርና በል በል ስትለው ዋለችና አረፈች አሉ፡፡ አስደናቂ ገድል ነው፡፡ ቆቦ ውስጧ ዛሬም ብዙ የፈራረሱ ተቋማትን ትመለከታላችሁ፡፡ ከዚህ ዋና ትኩረት የሚሆኑት የፖሊስ ጣቢያ፣ የጦር ካምኘና ሌሎች ይገኙባታል፡፡

አላማጣ ሞቃታማ ነች፡፡ ድሮማ አንድ ቀንም አይታደርባትም ነበር ወባ ይዞ እልም ነው አሉ፡፡ የአላማጣን ስም ስትሰሙ ትዝ የሚላችሁ ያ ጥምዝምዝ የግራ ካሶ መንገድ ነው አይደል እሱን የምታገኙት ወደ ኮረም ስታዘግሙ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን ሜዳ ነው፡፡ ይልቅ ሜዳው መንገድ ላይ ያየሁትን ላጫውታችሁ፡፡ ብዙ የገል ስባሪ፣ እርቦ፣ ሠፌድ፣ ቆሎ፣ አመድ፣ ዶሮ፣ ወ.ዘ.ተ. እንደ ኬላ እንጨት አግድሞሽ ተደርድሯል፡፡ ከፊታችን አውቶብስ ነበር እኛ በቅርብ ርቀት እንከተለው ነበር፡፡ ድንገት ሲያቆምና በርቀት ያንን መንገዱን ያጠረውን ነገር ስንመለከት በቃ አልን እነዚያ ዘራፊዎች እዚህ "የነፃ አውጪው ሠራዊት" ምንጭ አጠገብም አሉ ብለን ተስፋ በመቁረጥ የኋላ ማርሽ ሹፌራችን ለማስገባት ሲዘጋጅ ከአውቶቡስ ሰዎች ዱብ ዱብ አሉ፡፡ እንግዲህስ እናጣራ ብለን ትንሽ ቆም አልን፡፡ ከዚያም ወርደን ልጆች ተሯሩጠው መጡና ነገሩን፡፡ እለቱ የመስቀል እለት ነበር መስከረም 17 ቀን በባህሉ መሠረት በሽታ፣ ድርቅ ሌላም ነገር ከከተማቸው እንዲጠፋ ዳር አድርሰው መመለሳቸው ነበር፡፡ እዩት ወደ አዲሳባ መንገድ መሆኑ ነው፡፡ ላዋጋ ፈልጌ አይደለም አቅጣጫውን መንገሬ ነው፡፡

ከአላማጣ ኮረም 20 ኪሎሜትር ነው ግን ርቀቷ ማነሷን አትዩ ያ ሁሉ ጋራ ነው የምትወጡት፡፡ የግራ ካሶ መንገድ በዝና ብዙ የተባለለት ስለሆነ እኔም አውርቼ አልጨርሰውም እንዲያው ዝም

ይሻላል፡፡ ብቻ እዛ የተራራ አናት ጫፍ ላይ ተመቶ ተንጠልጥሎ ያለውን ታንክ ግን አሁንም ሳስበው ይገርመኛል፡፡ እኔ በጣቴ ገፋ ባደርገው እኮ ታች ነው የሚገኘው!

የኮረም ሕዝብ እንግዳ ተቀባይ ነው አሉ፡፡ እኔ እንጃ የአጋጣሚ ጉዳይ ይሁን አናውቅም ይህን ልንመሰክር በቅተናል፡፡ እንደ ደረስን ጥሩ ሆቴል አልን ብቻ መኪና ማቆሚያ ያለው አታገኙም እንጂ እንዳቅማቸው አይጠፉም አሉን፡፡ መንገድ ዳር ያሉት የቦታ አቀማመጡ ገደላማ ስለሆነ ግቢ የላቸውም፡፡ ማረፊያችንን ከያዝን በኋላ ጥሩ ምግብ ቤት ስንል ብሔራዊ ሆቴልን ጠቆሙን፡፡ ቤቷና መስተንግዶው ለየቅል ነው፡፡ ገና ገባ ስትሉ እኛ ሥራና ሰው ወዳዱን አቶ ኃይሉ ተክሉን ታገኛላችሁ፡፡

እድሜያቸው ሃምሳዎቹ መግቢያ ላይ ቢሆንም ለሥራ ጉንበስ ቀና ሲሉ የሃያ ዓመት ጉረምሳ ነው የሚመስሉት፡፡ ምሣችንን ከጥሩ መስተንግዶ ጋር እዛ ብናደርግም ሹፌራችን የጠጅ ነገር ስላነሳ ጆሮአቸው ጥልቅ ከማለቱ ይዘውን ወደ ታዋቂው ጠጅ ቤት ከነፉ፡፡ እዛ በሹርቤ /አንገተ ረጅም ብርሌ/ አስቀድተውልን እያንዳንዷ ብርሌ ሁለት ሁለት ብር ናት ስጋብዝም፣ ስጋበዝም አንድ ነው በማለት ከፍለው ጥለውን ቶሎ ወደ ሥራቸው በረሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው የአቶ ተሾመ ለገሠ ጨዋታ የቀጠለው፡፡ አመጣጤ ከወልድያ ነው ለቀን ሥራ አሉኝ፡፡ ታዲያ እንግዶች ናችሁ የኮረምን ጠጅ ሳትቀምሱ

አይሆንምና መምጣታችሁ ደግ ነው አሉኝ። የወልድያ ትዝታቸውን ማስታወሻ ግጥም ሰጡኝ።

እንጀራው ወልድያ እየተጋገረ፣

ወጡ ጉባ ላፍቶ ቲሸተን አደረ።

ጉባ ላፍቶ የወልድያ ሌላው መጠሪያዋ ነው።

ከዚያ በኋላ ይዘውን ያመራነው ወደ ገበያ ነው። ገበያ ውስጥ የመስቀልን በዓል ምክንያት በማድረግ ባለውቃቢው፣ ወጣት ልጃገረዶችና ወንዶች ተሰብስበው ይጨፍራሉ። ባሕላዊ ጨዋታ ይጫወታሉ። ባለውቃቢዎች (አዶ ከበሬዎቹ) ተከበው በከበሮ ይዘፈንላቸዋል፣ እነሱ ራሳቸውን አያውቁም ይዘላሉ፣ ዙሪያ ይዞራሉ። ከዕድሜያቸው ጋር ሲታይ ዝላያቸው በነሱ ሳይሆን በሌላ ሀይል እንደሚከናወን ትገምታላችሁ። ከዚያ ጉን አማርኛ ዘፈንና እስክስታ ታያላችሁ። ከዚያ እልፍ ስትሉ ጉረምሶች ከበው እየተፈላለጉ፣ እየተፎካከሩ በጅራፍ የሚጋረፉበትን ጨዋታ ትመለከታላችሁ። እጁ ላይ ነጠላውን ይጠመጥምና ከተፎካካሪው ጋር መዣለጥ ነው። አልመጣጠን ካሉ የከበቡት በዘንጋቸው ለመገላገል ይገባሉ። ከሁሉም ጨዋታ ያልወደድኩላቸው ይህን ብቻ ነው። ዐይን ቢጠፋስ አልኩና አንዱን ጠየኩት። ይህማ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ የተከሰተ ነው አለኝ። በቅርቡ እንዲህ ሲያጋጥም ተካሰው ኢህአዴግ ጋ ሲሄዱ በማይገባ ጫወታ ስለሆነ ዞር በሉ

እያለ ሁኔታውን ለማስቀረት ጥረት እያደረገ ነው አለኝ፡፡ በርግጥም መቅረት ያለበት ባህል ነው፡፡

ኮረም ከትግራይ ቀጥሎ ወደ መሀል ሀገር በጦርነት የተሸጋገሩባት ስለሆነ የጦርነት ነገር ምንም አይጠየቅም፡፡ ከመሀል ከተማው ወደ ዳር ወጣ ብለን ጊዜያዊ ሀይቅ ያለበትን ቦታ ስንጐበኝ አንድ የመንደር ልጅ አገኘን፡፡ የመጨረሻዋን ቀን ሲያጫውተን "ኢሠፓ በዚህ በኩል ዕቃውን ሸክፎ፣ መኪናውን እዚህ ድረስ ነድቶ አምጥቶ አቁሞና አቃጥሎ በእግሩ በጋራው ጥግ ጥግ በባላገሩ በኩል ነው የሸሸው" አለን ፡፡ አውራ መንገዱ ስለተያዘበት መሆኑ ነው፡፡ እኛም በርቀት ተመለከትነው፡፡ ታዲያ አውሮፕላን ትመጣና ትደበድብ ነበር አለን፡፡ ያን ጊዜ ታጋዮች ስለሚነግሩን እንደበቃለን ንቆ ከተወ በስተቀር ማንንም አታገኝም፡፡ ታዲያ የምትመጣበት ሰዓትና የሚነግሩን ዝንፍ አትልም አለን፡፡ እጅግ ተገረምን ወደ ሌላ ሃሳብም ወሰደኝ ማነው "በእርስ በርስ ጦርነት መንግሥት አሸናፊ አይሆንም" ያለው? ለጊዜው ረሳሁት ብቻ በወቅቱ ይህ ነገር ትዝ አለኝ፡፡

ለሁለት፣ ሶስት ዓመት በጨለማ ውስጥ የመኖር ያህል ከኖሩ በኋላ አሁን ብርሃን ማየታቸው ነው፡፡ ቀን እንቅስቃሴ የለም፣ መብራት የለም፣ ንግድ የለም፣ ጭፈራ የለም፡፡ ብቻ ሰው ጠንካራ ነው እዚህ ደርሰዋል፡፡ በማግስቱ ወደመጣንበት ተመለስን፡፡ ታዲያ አላማጣ ላይ ያሳፈርናቸው ትሁንና ዓይናለም ሮቢት ላይ የራያን

ባህላዊ ልብስ አጋዝተውንና /በ115 ብር/ እማሆይ ጉልጉሌ ቤት የማር ጠጅ አጠጥተውን ውለታችንን እዚያው በዚያው ነው የመለሱት። እማሆይ እንደጠጃቸው ያምራሉ። ብርሌ አያያዟን ሲያውቁባት ለጉድ ነው።

**ገረገራ፣ንፋስ መውጫ፣ ጉና...**

ተመልሰን ወልድያ ደረስን። ወደ አዲስ አበባ የመመለሻ ጉዞአችን በመጣንበት ሳይሆን በወልድያ ወረታ ወዳጅ በነበሩት ቻይናውያን በሠሩት መንገድ ይሆናል። ወልድያ መሀል በተሰቀለው ማስታወቂያ "ወልድያ - ወረታ 300 ኪ.ሜ." ተመርተው ወደ ባህር ዳር አቅንታችሁ መጓዝ ነው መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባ ለመድረስ። የዚህ መንገድ ሥራ ሊጀመር የታሰበው እንኳ ከ1975 ዓ.ም. በፊት ሶስት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር አሉ። ሶስት ዓመቱ የት አለፈ? ብትሉ የሚሰጣችሁ መልስ በወቅቱ የአካባቢው የደርግ የለውጥ ሐዋርያ በነበሩት ሰው መከላከል የዘገየ መሆኑን የዓይን ምስክሮች ይነግሯችኋል። ለምን ብትሉ የሰውዬውን ምክንያት ትሰማላችሁ።

ይህ መንገድ ቢሰራ ወንበዴ ይስባል። ይህ ብቻ አይደለም ባንክ ቢከፈት (ንግድ ባንክም እንዳይከፈት ይከላከላሉ ነበር) ያው ወንበዴን መጥራት ነው ብለው በክርክር ሶስት ዓመት መንገዱ ከመሠራትም ሆነ ባንክ ከመከፈት እንዳዘገዩት ይነግሯችኋል። ዛሬ እኚሁ ሰውዬ ያ የፈራሁት ነገር ደርሶ በአይኔ አየሁት ብለው ይናገራሉ አሉ ካሉበት ጎንደር እስር ቤት ሆነው።

አስፋልት ሊለብስ የታቀደው መንገድ በክርክር ሶስት ዓመቱ አልፎ ሲሠራ ጠጠር እንደለበሰ የፀጥታው ችግር ስለተፈጠረ በዚሁ በጠጠር መንገድነቱ ቀርቷል፡፡ መንገዱ አንዳንድ ቦታ ጭቃው ዛሬ መኪና በክረምት አላሳልፍ ማለቱን በዓይናችን ተመልክተናል፡፡ ዋ! የአስፋልት መንገድ ተሠርቶ ቢሆን ምናለ! ያ የፈሩት ነገር መድረሱ ካልቀረ ብላችሁ ታዝናላችሁ፡፡ በዛሬ ዐይን ስታዩት ወልድያ- ወረታ መንገድ ተቃዋሚ ቡድኖች የሄዱበት መንገድ መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡

እስቲ አንድ በአንድ እንጐብኘው፡፡ ከወልድያ 25 ኪ.ሜ. እልፍ ስትሉ የወይና ደጋዋን የሸንኮራ፣ የሙዙን ሀገር ሳንቃ በርን ታገኛላችሁ፡፡ እሷን ስታልፉ ደረቅ ጣቢያ የሆነችው ቀበሮ ሜዳ የተረጂዎችን መዓት አፍሳ ትጠብቃችኋለች፡፡ እዚህ ብዙ ሕዝብ ከረጢቱንና አህያውን ይዞ የእርዳታ መኪናዎችን መምጣት ሲጠብቅ ታገኙታላችሁ፡፡ ሰውና አፈሩን መለየት እስኪያቅታችሁ ድረስ ታዝናላችሁ፡፡

እስታይሽ፣ ሐሙሲት / ይህን ስም በብዙ ቦታዎች ታገኙታላችሁ ሐሙስን ከመውደድ የመጣ ይሆን / ጋሸና ብላችሁ ገረገራ ትደርሳላችሁ፡፡ ገረገራ የንግድ ማዕከል ነች፡፡ የማይገኝ የእህል አይነት የለም፡፡ ገረገራ፣ ላሊበላ፣ መቄትን እንዲሁም ሌሎች ከተሞች የምታገናኝ ሴንተሪያ ናት፡፡ በዚህ ጉዞአችን ጊዜ ከገረገራ ገበያ መልስ ወደ ንፋስ መውጫ የሚጓዙትን ጋይንቴውን ባላገር ጭነን ነበር፡፡ ታዲያ ያጫወቱን ጉዳዮች እንኳን ነው ያሰኘን፡፡

ጊዜው እንዴት ነው አልናቸው፡፡ “በጣም ጥሩ ነው፡፡ ይኸው ደስ ብሎን አይደል በመኪና የምንሽራሽረው ይህ መቼ ቀደም ነበር?” አሉን፡፡ ቀድሞ እዚህ የከፋ ጦርነት ነው እንጂ እንዲህ መች ነበር፡፡ አውሮፕላኗ ስትመጣ ሶስት መቶአችን እዚህ እያትማ እዚች ጫካ ነበር ተደብቀን የምናሳልፈው፡፡ አየሁት ጫካው እንኳን ሶስት መቶ ሰው ለሽንት የተቀመጠን አይደብቅም፡፡ ብቻ እንግዲህ ይህ ጢያራ ነጂ አንድ አሥር እግር የባሕር ዛፍ ቅጠል ካየ ሰው አያሳየው እንደሁ እንጂ አልኩ በልቤ!

እዚህ ምን ይሠሩ ነበር አልኩአቸው፡፡ ቀደም የገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር ነበርኩ፡፡ በዚህ ታስሬ ነው አሉኝ፡፡ ታዲያ እነዚኞቹ ደግ ናቸው ምንም አያሰቃዩም ይዘው ቁጭ ነው የሚያረጉህ፡፡ አይገርፉህም፣ ብቻ እህ ምን አረክ እሺ ይሉሀል ሌላስ ጓደኛ የለህም ይሉሀል አዎ ስትል አምጣው - ብቻ ይሰበስቡሀል፡፡ ታዲያ ምን ብትናገራቸው ምንም አይሉህም ግን ግን ቂም አትረሳም!! ዝም ብሎ መታሰር ነው፡፡ ሰማህ

ለሴት ሚስጢር መንገር፣
ፍየል አስሮ ለነብር፡፡
ችጋር ላይ በሽታ፣
ኩንታል ተሸክሞ እስክስታ፡፡
ከባለጊዜ ጋር መከራከር፣
ጨው ይዞ ባሕር መንከር፡፡

አሉን፡፡ በዚህ እየተሳሳቅን መንገዳችንን እንደቀጠልን ለመሆኑ ያለፈውን ጊዜ እንዴት ያዩታል፣ ደግሞ እናንተ እኮ እንደሰማነው ቀደም ሲል በደንብ አይደል እንዴ የተቀበላችኊቸው አልናቸው፡፡ አይ ተው ! አቅም ብናጣ ነው እንጂ አሉን፡፡ ሁሉም አለፈ አሁን እንዴት ነው አስተዳደሩ አልናቸው፡፡ አይ ተወው የአሁኖቹ “ወንድነት ነው እንጂ ዳኝነት የለችም” እንዴት ማለት ይኸውልህ ሁለት ባልና ሚስት ተጣልተው ተካሰው ወደ ኢሕአዴጐቹ ጋ ሄዱ ኃላፊው ምንድነው አለ፡፡ አይ በሰማንያ ተጣልተው ነው አልነው፡፡ ታዲያ አርባ አርባ ይካፈሉ ብሎን ሁላችንንም አስቆን ወደ ቤታችን ተመለስን፣ በቀያችን አንደ ፍጥርጥራችን ለመሆን፡፡ አስቂኝ ገበሬ ናቸው፡፡

ይህ ሁሉ አህያ ምንድነው አልናቸው፡፡ አይ ልጄ አህያ የማይኖርበት፣ እህል የማይበቅልበት ሀገር የለም ደግሞስ ከከብት አህያ፣ ከአካል ጉያ ይባል አይደል ብለው ለጥያቄያችን በምሣሌ እዚያው መልሰውልን ተሰነባብተን መድረሻቸው ላይ ወረዱ፡፡

ንፋስ መውጫ ንፁህ የማር ጠጅ ከሚጣፍጥ ወጥና እንጀራ ጋር በላን፡፡ እንግዲህ የሙያ ነገር መጀመሩ ነው፡፡ ወደ ወሮታ ስናዘግም ጉብጉብ ብለን ያንን የወቅቱን ታሪካዊ ቦታ ክምር ድንጋይን ወይም ጉና ተራራን እናገኛለን፡፡

የጉና ተራራ አካባቢ ብርድ አይጣል ነው፡፡ ቆፈኑ አይቻልም፡፡ እንደሰማነው በዚያ አስከፊው ጦርነት ወቅት ብረት በእጅ መያዝ በጣም ይከብድ ነበር

አሉ፡፡ በእግር ነበር የድግን መሣሪያ የሚተኮሰው፡፡ “ጉና መስክሪ” የተባለላትም ምድር እውነትም እስከ ደብረ ታቦር አመድ በር ድረስ አስከፊ ረዥም ጊዜ የወሰደ ጦርነት ነው የተካሄደው፡፡ መንግሥትም ያለ የሌለ ሀይሉን አሰባስቦ ብዙ የመከላከል ውጊያ አድርጓል፡፡ በዚህ ጦርነት እጅግ የሰለጠኑ የስፓርታ ኮማንዶች ተሳትፈውበት ውጤቱ አላማረም፡፡ የጦርነቱን አስከፊነት የሚመሰክር እጅግ የብዙ መሣሪያ ውድመት ከደብረ ታቦር ከተማ ወጣ ብላ ካለችው አመድ በር ላይ ተከምሮ ያያሉ፡፡ የኢሕአዴግም አሸናፊነት የተረጋገጠው ከዚች ምድር በኋላ ነው አሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ወረታ ከተማ ዘልቆ አውራ መንገዱን ይዞ ወደ አዲሰ አበባ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ በዚህ በኩል ቡሬ ከተማ ሲደርስ ወደ ወለጋ ነቀምት ታጥፎ ሄዶ በአምቦ በኩል ወደ መጨረሻው ግብ ተጉዟል፡፡ ከወሎ ሰቆጣ በአከስታ በኩል ደግሞ መራቤቴ መራኛ ለሚ ብሎ በቆረጣ መንገድ ወደ አዲስ አበባ ተጉዟል፡፡ በዚህ ጦርነት ጊዜ ብዙ ኗሪ ወደ አዲስ አበባ ተሰዷል፡፡ ከወረታ ወደ ባህር ዳር መንገድ ሀሙሲት ላይ ቤታቸው ልንጠይቃቸው ጎራ ያልን እናት ሲያጫውቱን ልጆቹን ቀን አስኪያልፍ አዲሰ አበባ ወስደን ቤት ተከራይተን (ቤቱ የሹፌራችን የተስፋ ነው) አስቀመጥናቸው አሉን፡፡ ታዲያ አሁን ሰላሙ ሲመለስ ኑ ተመለሱ ብንል ግምኛ ለመዱና እንቢ አሉን፡፡ እንደዚሁም አንድ የማውቃት የአዲስ አበባ ልጅ ለሥራ ንፋስ መውጫ ሄዳ እህል ውሀዋ እዚያው ሆኖ

አግብታ ትኖር ነበር፡፡ በጦርነቱ አስከፊ ወቅት ላይ ባሏ፣ እናትና አባቱ አንድ ላይ ሆነው ከንፋስ መውጫ ተሰደው መጥተው አዲስ አበባ  ባባቷ ቤት ተጠግተው ሲኖሩ እናቱ ድንገት ታመው አረፉና እዚሁ ተቀበሩ፡፡ አባትና ልጅ በሰው ሀገር የደረሰባቸው ሀዘን አሰቃቂ ነበር፡፡ ሰላሙ ሲመለስ አስከሬኑን አስቆፍረው አስወጥተው ወደ ቀያቸው ወስደዋል፡፡

ጦርነቱ በያቅጣጫው ተጉዞ አዲስ አበባ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. ተደመደመ፡፡ ብቻ የአንድ እናት ልጆች እልቂት መሆኑ ከፋ እንጂ!!

## ኢሉባቦር

ወደ ኢሉባቦር በምታደርጉት ጉዞ መጀመሪያ የሰዎች ማስፈራራት ያጋጥማችኋል፡፡ እንደ ሰሜኑ አይደለም ጦርነት እዚያ ገና መለኮሱ ነው ነዶ አላለቀምና እንዳትቃጠሉ ይሏችኋል፡፡ በተግባር ግን በጣም የተለየ ነው፡፡ ፍፁም ሰላም ቢሆንም ስጋቱ ከምንም ነገር የመነጨ አይደለምና ጠጋ ብሎ ማዳመጡ አይከፋም፡፡

በዚህ ሀገር ስንቴ ነው በዚህ አጭሯ ዕድሜአችን አብዮት ያየነው አዎ ለኔ ሁለቴ ነው፡፡ ታዲያ ሁሌም በአፍላው ወቅት መሳከር እንዳለ ተገንዝቤአለሁ፡፡ መሳከር የፖለቲካ አቅጣጫው ወዴት እንደሚያመራ ካለመተንበይ ወይ ካለመረዳት ምን ልበለው ብቻ መሳከር ያጋጥማል፡፡ በዚህ ወቅት ነው ከሌላ አካባቢ የመጡ

ነዋሪዎች ችግር እንዳጋጠማቸው በአጋሮ አካባቢ ሰምቻለሁ፡፡ ግን ውሎ አድሮ ነገሮች ሲሰክኑ ነው ያ በስንት ትውልድ ደሙን የቀላቀለው ኀብረተሰብ እንደ ጥንቱ እንኑር ብሎ ራሱን በራሱ ዳኝቶ ዛሬ ያገኘውን ሰላም ለመቀዳጀት የበቃው፡፡ በዚህ የሰላም ባቡር እስቲ እንሳፈርና እንደ ልማዴ ላንሸራሽራችሁ፡፡

**ወሊሶ፣ ወልቂጤ፣ ጅማ፣ አጋሮ፣ በደሌ፣ ጎሬ፣ማሻ.....**

ከአዲስ አበባ ወደ ኢሉባቦር ጉዞው የሚጀምረው በጅማ በር በኩል ነው ፡፡ ሰበታን በሜታ ቢራ ታውቋታላችሁ አይደል በሱ በኩል ተፍኪ፣ ቱሉ ቦሎ ብላችሁ ወሊሶ ትደርሳላችሁ፡፡ ወሊሶ ባለፈው ጊዜ የምዕራብ ሸዋ ማዕከል ተብላ ደምቃ ደምቃ ሳታበቃ ያ ሁሉ የሕንፃ ጅምሮች ሳይጠናቀቁ ሌላው ለውጥ መጣባት ወይ መጣላት ብቻ ቁርጡ አልታወቀም፡፡ ሁሌም ሰላማዊ ሰልፍ ነው ማዕከልነቷ ይቀጥል እያሉ፡፡

የሰላማዊ ሰልፍ ነገር ሲነሳ ባለፈው ጉዞዬ ጎጃም ውስጥ ከአንድ ህክምና ዶክተር ጋር ስንወያይ “ሰው ቧንቧ ውሃ እያለ ለምንድነው የጉድጓድ ውሃ የሚጠቀመው  እንደምንም ተቸግሮ ቢያስገባ ይሻለው ነበር” አልኩት፡፡ ይህ የጉድጓድ ውሃ እኮ ለሱና ለቤተሰቡ በየወሩ የ3 ብር የወስፋት መድሃኒት ወጪ ያስከትልበታል አሉ ብዬ ጠየኩት፡፡ ሲመልስልኝ “ምን እሱ ብቻ ለመመርመር የሚያጠፋው ጊዜስ መቼ ታሰበ? አንደኛ ተሰልፎ ካርድ ያወጣል፣ ካርድ ካወጣ በኋላ መብራት ሊቋረጥ ይችላል ወይም የሆስፒታሉ ሠራተኞች

ሰላማዊ ሰልፍ ይወጣሉ"። ወይ ዘንድሮ የሰላማዊ ሰልፍ ነገር ብዬ ትንሽ ወደ ኋላ ተመልሼ በዚህ አንድ ዓመት ስንት ሰልፎች በያገሩ ተደርገው ይሆን አልኩ። እንግዲህ የጠፋውን ጊዜ በፈለጋችሁት መንዝራችሁ ማስላት ነው።

ከወሊሶ 30 ኪሎ ሜትር ወደፊት እንደተጓዙ የነዚያ የሥራ ወዳዶቹ የጉራጌዎቹ ሀገር የሆነችው ወልቂጤ ትደርሳላችሁ። በወቅቱ ወልቂጤ ከተማ ብዙ አላደገችም። ልጆቿ አዲስ አበባና በመላው አገሪቱ ለሥራ ተሰማርተው በንግዱ የተሳካላቸው ቢሆንም የትውልድ ቀያቸውን ግን ብዙ ያስታወሷት አይመስልም። የሚታወቁበትን ክትፎ ካልሆነ በቀር አማራጭ ጥሩ ምግብ ቤት እንኳ እንደልብ አይገኝም። ወልቂጤን አልፋችሁ ጥልቁ የጊቤ ወንዝ ከወልቂጤ ትንሽ ወጣ እንዳሉ የሚገኝ ሲሆን የሚፈሰውም ወደ ሩዶልፍ ሀይቅ ጋሞጎፋ ነው። ታዲያ ብዙ ጊዜ ስንወቅሰው እንደኖርነው ዓባይ ወንዝ ሳይሆን ጊቤ ወንዝ ላይ ሶስት የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች ተከናውኖበታል። በዚህም በጊቤ አንድ ሀይል ማመንጫ 184 ሜጋ ዋት ፣ ጊቤ ሁለት 420 ሜጋ ዋት እና በጊቤ ሶስት 1870 ሜጋ ዋት በጠቅላላው ከ2400 ሜጋ ዋት ሀይል በላይ ይመነጭበታል። ከሰራንበት የአንድ ወንዝ በረከት የት ድረስ እንደሆነ ገምቱት።ጥምዝምዙን ያን የጊቤ በረሀ መንገድ ትዘልቁና የጣሊያን ከተማ የምትመስለውን ጅማ ወደ ማምሻው ላይ ትደርሳላችሁ። ጅማን ስታዩ ከለመዳችሁት አዲስ አበባ የወጣችሁ አይመስላችሁም። ጅማ ከድምቀቷም በላይ የከተማዋ በፕላን መሠራት እውነትም ዳግማዊ

ሮማ አደርጋታለሁ ብለው ዝተው የነበሩትን የአካባቢው ገዥ ፋኪራ ከንቱ አለመሆኑን ያስገነዝባችኋል፡፡ ብቻ ምን ያረጋል ሁሉም አልፎበታል፡፡ ደርግም የቡናን ንግድ በሞኖፖል በመያዙ ዳግም አቀዝቅዟታል፡፡ ድሮማ ተማሪዎች ሳይቀሩ መጠጥ ቤት ሲገቡ መምህራቸው ቢራ እየጠጣ ሲያገኙት ጋሼ ውስኪ ቀይር እንጂ እስከማለት ይደርሱ ነበር አሉ፡፡ ያን አረንጓዴ ወርቅ በቀላሉ ያፍሱ ስለነበር፡፡ አሁን ቀርቷል የወደፊቱም እንጃ!!

የአጋሮም ድምቀት ከጅማ አያንስም፡፡ ከተማዋ ብዙ የጉራጌ ተወላጆች በንግድ ሥራ ተሠማርተውባት እንቅስቃሴዋና ድምቀቷ ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ ስለ አጋሮ የንግድ ማዕከልነትና ውበት የአበሻው የሙዚቃ ንጉሥ ጥላሁን ገሰሰ ሳይቀር ያዜመላት ናት፡፡ ታላቅ እህቴ አጋሮ ሄዳ በትዳር እዚያ ስለምትኖር ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነቴ ጊዜዬ ጀምሮ ልጠይቃት እየተመላለስኩ ብዙ ጊዜ አሳልፌባታለሁ፡፡ ከሁሉ የማትረሳኝ ደግሞ ጅፍምቤ (ጅማና ፍሬው ምግብ ቤት) ናት፡፡ አሁን መኖሯን አላውቅም፡፡ ታዲያ የጅማ መንገድ ቅያስ አጋሮን ትንሽ ስለነካካት መሰለኝ መጀመሪያ ጊዜ ታሳስተኝ ነበር፡፡ ከአጋሮ 100 ኪሎ ሜትር ወደ ምትርቀው በደሌ ብንዘልቅስ፡፡

በደሌ የተባለችው ከጊዜ ብዛት ነው፡፡ በጥንት ጊዜ አንዲት ሴት ወደ ገበያ ስትሄድ አንዷ ገበያተኛ የት ትሄጃለሽ ብላ ብትጠይቃት በዳ ኤሌ አለቻት፡፡ ይህም ማለት ትንሽ የሸክላ ምጣድ ለመግዛት መሄዷን ብትገልጽላት ያ የምጣድ ገበያ ቦታ ከጊዜ ብዛት በደሌ ተብሎ እንደቀረ በአፋዊ ታሪክ ይነገራል፡፡ ከተማዋን ለማረፊያነት

በ1918 ዓ.ም. የቆረቆሯት ደጃዝማች ገሠሠ ብጡል የተባሉ በልጅ እያሱ ጊዜ የነበሩ የአካባቢው ገዥ ናቸው፡፡ ከጥንት ጀምሮ በአካባቢው የሚኖሩ ኦሮሞዎች ሲሆኑ፣ አመጣጣቸው ከጉለሌ፣ ከአመያ፣ ከጪቱ፣ ከአምቦ፣ ከሌቃና ከጉድሩ ነው ይባላል፡፡ ልብ በሉ ከአዲስ አበባ 480 ኪሎ ሜትር እየራቃችሁ ነው፡፡

በደሌ አቀማመጧ እንደ ሻሸመኔ ነው፡፡ የወለጋን ዋና ከተማ ነቀምቴን ከበደሌ ወደ አርጆ በሚወስደው መንገድ ስታገናኝ ከአዲስ አበባ ጋምቤላ የሚወስደው አውራ ጐዳናም በሷው ነው የሚያልፈው፡፡ በዚህም በአሁኑ ዞን አሰያየም ከፋን ጋምቤላንና ወለጋን የምታገናኝ ማዕከላዊ ቦታ ነች፡፡ ከዚህም የተነሳ ይመስላል ለአካባቢው የቢራ ጥማተኛ እንድታዳርስ ተብሎ አምስተኛውና ትልቁ የቢራ ፋብሪካ ተገንብቶላታል፡፡

በደሌ የንግድና የግብርና እንቅስቃሴዋ ከፍተኛ ነው፡፡ ሁሉም ይሠራል የቀድሞውን የገበሬዎች ማህበር /መኢገማ/ ሊቀመንበር የነበሩት አቶ አብደላ ሶኔሳን ጨምሮ፡፡ በከተማው እንደሚገኙ ሰዎች ሲነግሩን አስጠራናቸውና ሻይ ቡና እያልን ቁጭ ብለን ተጫወትን፡፡ የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ ወደ መንደሬ በደሌ መጣሁና እዚህ ለሚገኙት ኢህአዲጎች ሪፖርት አደረኩ፡፡ ስንፈልግህ ትመጣለህ ወደ ቤትህ ግባ አሉኝ ብለው አጫወቱን፡፡ በሰላም ወደ እርሻቸው ተመልሰው በሰፊው እንደተያያዙትና ድሮም ገበሬ ነበርኩ ብለው የቆረፈደውን እጃቸውን አሳዩን ፡፡ በጣም ትሁት ሰው ናቸው፡፡ አቶ አብደላ ሲያጫወቱን “ፖለቲካ ገደል ነው” አሉን ፡፡

እኚህ ሰው ለረጅም ዓመታት የገበሬዎች ማህበር ሊቀመንበር ሆነው ያገለገሉ ናቸው:: በወቅቱ ዘወትር ከዜና የማይጠፉ ነበሩ:: በነዚህ ዓመታት ከወጡበት ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ቁርኝት ባለመበጠሳቸው ይመስለኛል በነፃነት ወደ ቀያቸው ተመልሰው ኑሮአቸውን የቀጠሉት:: የሥልጣንን ከንቱነት የሚያሳዩን አንዳንድ ባለ መርህ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ለሥልጣንና ለገንዘብ ዘወትር ሲለፉ የምናያቸው ግለሰቦች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: ይህን ማለቴ አንድ ከእኔው ጋር በአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ የተማረ የማውቀው ሰው ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት በአንድ አጋጣሚ የነገረኝን ለብዙ ሰው አጋርቼዋለሁ::

ከተመረቅን በኋላ በሙያው አንድ ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ ይመደብና ከተራ ሰራተኛነት ተነስቶ የፋብሪካው ዋና ሥራ አሥኪያጅ እስከመሆን ደረጃ ይደርሳል:: ቆይቶ ምክንያቱን ባላውቅም ከሥልጣኑ ይወርዳል:: አንድ እለት ከሥራ በኋላ ከቢሮዬ ስወጣ ከቢሮአችን ፊለፊት መንገድ ላይ በእግሩ ሲሄድ አገኘሁት:: ምነው በእግርህ አልኩት? ሥራውን ተዉኩ እኮ አለኝ:: ጎሽ ከጭቅጭቅ ተገላገልክ አልኩት:: በመከፋት እንዲህማ አትበል አለኝ:: ለምን አልኩት:: “ሥልጣን እንዴት እንደሚመች ባታውቅ ነው” አለኝ:: እንዴት እንደሆነ ሲያስረዳኝ ሥራ ላይ ጉዳይ ወደ ቢሮህ ሲመጣ አባክህ አስተናግደው (Please handle) ብለህ ትመራበታለህ፣ ዓርብ ማታ ኮብራህን ቆስቁሰህ ወደ ቤተሰቦችህ ጋ አዲስ አበባ ትመጣለህ (ከከተማችን ከ100 ኪሎ ሜትር በላይ ርቀት ላይ ነው ሥራው)

ወ.ዘ.ተ. በመገረም አዳምጬው ተሰነባብተን ተለያየን፡፡ ትንሽ ጊዜ ቆይቶ በቴሌቪዥን በራሱ ክልል አንድ ስብሰባ ላይ በፓርቲው ለአንድ ኮሚሽን ሰብሳቢነት ሲመረጥ ተመለከትኩ፡፡ ቀጥሎም የአንድ ኮርፖሬሽን ሥራ አሥኪያጅ ሆኖ ተሹሞ አየሁት፡፡ ለካ ያኔ ለደጅ ጥናት ነበር በእግሩ ሲያዘግም ያገኘሁት፡፡

ከዚህ በፊት ያወጋኋችሁ የወልድያ ወሮታ መንገድ ታሪክ እዚህም ከቡሬ (ጐጃም) ወደ ነቀምት (ወለጋ) እና በደሌ (ኢሉባቦር) መንገድ ላይ ተደግሟል፡፡ ደርግ ለምን ይሥራው ባላውቅም በጦርነቱ ጊዜ ጠላቴ ለሚላቸው ግን በጣም ጠቅሟል፡፡ ይህ የቀለበት መንገድ ደርግ ኢህአዴግን በፍቼ በኩል ሲጠብቅ በአቋራጭ በዚህ ተጉዘው በአምቦ አድርገው አዲስ አበባ ዘልቀውበታል፡፡

ወደ መቱ ስትጓዙ ጮራ፣ ያዩ፣ ሁሩሙን አልፋችሁ ነው፡፡ ሁሉም የቡና ሀገር ነው፡፡ አሁን ጨምሮ ነው ይሏችኋል በሃያ አምስት ሣንቲም ወፍራም ቡና ሲያጠጡአችሁ ቅር በመሰኘት፡፡ ወይ አለማወቅ  የአዲስ አበባን የቡና ዋጋ!!

በጥንት ጊዜ ዓመተ ምህረቱ ተለይቶ በማይታወቅበት ዘመን የኦሮሞ ብሔረሰብ ከሸዋ ክፍለ ሀገር ፈልሶ በመምጣት በደጋው ኢሉባቦር ቀድሞ የነበሩትን ሰፋሪዎች የአኝዋክና የመዠንገር ብሔረሰቦችን ወግቶ በማባረር በየጐሳው ቦታ በመምረጥ ሰፍሮ ሞቲ ‹‹ንጉሥ›› እየሾመ ራሱን ያስተዳድር እንደነበር አበው ይተርካሉ፡፡ በዚህ መሠረት በገባና ባሮ ወንዝ መካከል ያለውን ሀገር ይገዙ የነበሩት

ሞቲ ኢሉ አባቦር ይባሉ ስለነበር አገሩም በስማቸው ኢሉ አባቦር ተብሎ ተሰየመና በቀን ብዛት ኢሉባቦር ተባለ፡፡

መቱም እንደዚሁ በጥንት ዘመን ከኦሮሞ ብሔረሰብ ወገን የሆኑ ‹‹መቱ›› የሚባሉ ሰዎች (ጉሳዎች) ሰፍረውበት ስለነበር በነሱ ስም የከተማዋ መጠሪያ ስም መቱ የተባለ መሆኑ ይነገራል፡፡ ለከተማነት የታጨችበት አጋጣሚ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የነበሩት ልጅ ኢያሱ የጊሚራ ሕዝብ አምጾ ስለነበር ጊሚራ ዘምተው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ዛሬ የቴሌኮሚኒኬሽን ሕንፃ የተሰራበት ሥፍራ አድረው ነበር፡፡ ትልቅ ሰው አድሮበት የሄደበት ሥፍራ ረድኤት አለው በሚል እምነት የአገሩ የቆሮ አበጋዝ /ጠቅላይ ባላባት/ የነበሩት ፊታውራሪ ገብረሥላሴ ጉማ ባላባቶችንና የሀገር ሽማግሌዎችን ሰብስበው በዚህ ቦታ ገበያ እንዲቆምበትና ከተማ እንዲቆረቆር ባቀረቡት ሓሳብ መሠረት ስለተስማሙበት ነው፡፡ የልጅ ኢያሱ ድንኳን በተተከለበት ቦታ ላይ በነበረው የአገሩ ባህል መሠረት ጉድጓድ ተምሶ አንድ ቶፋ ማርና አንድ አሞሌ ጨው ተቀብሮበት በየሳምንቱ አርብ ቀን የሚውል ገበያ ተቋቋመና የመቱ ከተማ 1905 ዓ.ም. ተመሰረተች፡፡

ይህ እንግዲህ ከላይ የገለጽኩላችሁ ተመዝግቦ በከተማው ማዘጋጃ ቤት ተቀምጦ ያገኘሁት ታሪክ ነው አትጠሉትም ብዬ ነው ቀንጨብ ያደረግሁላችሁ፡፡

ኢሉባቦር መቱ
አቤት ማማሩ የደንሽ ውበቱ

እንዲሁ በከንቱ የተዜመላት አይደለችም፡፡ አረንጓዴ ጥቅጥቅ ያለ ደን፣ ከዝንጀሮና መልከ መልካሙን ጉሬዛ በስተቀር ምንም አታዩም፡፡ ሰሜንን ባያችሁበት ዓይናችሁ ኢሉባቦርን ከጅማ መግቢያ ጀምራችሁ ስትመለከቱ እነዚያ ግብርና ሚኒስቴር ያሉት የኢትዮጵያ ደን 3 በመቶ ብቻ ነው የቀረው የሚሏችሁን ትጠራጠራላችሁ፡፡ ብቻ እዚህም ከየቦታው ደን አለቀ ኢሉባቦር ሂዱ የተባሉ የግንድ መሰንጠቂያዎች እየተረባረቡበት ነው፡፡

መቱ ርዕሰ ከተማነቱን ከጐሬ ነው የነጠቀችው፡፡ ለሷም ነጣቂ አዞባት በኢሕዲሪ መዋቅር ጊዜ ተቀናቃኝ ተነስቶባት ጂማ ሄዶ ነበር፡፡ መሰንበት ደግ ነው ዛሬ ደግሞ ተመልሳ የኢሉባቦር ዞን ማዕከል ሆናለች፡፡ የማስመለስ ሰላማዊ ሠልፍ እዚህም ነበር አሉ፡፡ በወቅቱ የነበሩት ባለሥልጣኖች ዋና ከተማው ከመቱ ሲነሳ ዝም ያሉት ለነሱ መቱ ትንሽ ከተማ በመሆኗ ለመዝናናቱም ለምኑም ጅማን በመምረጣቸው ነው ብሎ ነዋሪው እስከዛሬም ተቀይሟቸዋል፡፡ በወቅቱ ያሰቡት ጅማ ሳይሆንላቸው ቀርቶ እነሱም ወደ ዳር አርባ ምንጭና የመሳሰሉት ከተሞች መወርወራቸውን ሕዝቡ በእርካታ ያስታውሰዋል፡፡ የሶር ወንዝ ለሁለት ከፍሏት የሚያልፈው መቱ ከአዲስ አበባ 600 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የምትገኘው፡፡ ዛሬ ውሃ፣ መብራት (ከሶር ወንዝ ተጠልፎ)፣ ዲጂታል ቴሌፎን

የመሳሰሉት መሠረታዊ አገልግሎቶች የተሟሉላት ቢሆንም ከተማዋ ወዲህ ወዲያ በመመላለሷ ለሶስትና አራት ዓመታት ቀዝቀዝ ብላ በመክረሟ የከተማውን መንገድ እንኳ የሚጠግን ባለቤት ያጣች መስላለች፡፡ መጤ! እከሌ! የሚለው ያለመረጋጋት ስጋት እንጂ ምንም የጦርነት አስከፊ ገጽታ አላየችም ተመስገን ነው፡፡

መቱን መልቀቅና ወደ ጐሬ ያውም 20 ኪሎ ሜትር መጓዝ ምነው እግሬን ያዘው ኧረ እንደምንም ብዬ እስቲ ወደ ጥንታዊቷ ጐሬ እናዝግም፡፡ ጐሬ የኖረችው ለ110 ዓመት ነው፡፡ ሆኖም ልማቷን ስታዩ ታዝናላችሁ፡፡ ለምን እሱን አንተወውም ብቻ አያስችላችሁም፡፡ ጥንት ሳይሆን በኢጣሊያ ወረራ ወቅት የሀገር ንጉሥ በሌለበት ወቅት ለሃያ አራት ሰዓት በልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ባለአደራነት እየተመራች የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና ነበር፡፡ ይህን ታሪክ ስትሰሙና ዛሬና ትላንት የስንት የኢትዮጵያ ጀግናና ምሁራን ልጆች መፍለቂያ የሆነችው ጐሬን ስታስቡ ብዙ ነገር ይታሰባችኋል፡፡ ዕድል ወይስ ሌላ ትላላችሁ፡፡ ራሳችሁንም ወደ ውስጥ እያያችሁ፡፡ ጐሬ ከሰው ሀገር በፊት ተፈጥራ ዛሬ እንዴት ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንኳ ትጣ ብላችሁ ትጠይቃላችሁ፡፡ የዛሬዎቹ ትላልቅ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሥልጣናት መፍለቂያ ጐሬ ጐሬነቷን ይዛ ቀርታለች፡፡

ከጐሬ አሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በቀደምት ጊዜ በአንድ የግል አራሽ ተይዞ የነበረና ዛሬ ትልቅ የአግሮ ኢንዱስትሪ ማዕከል ያደረጋት

የሻይ ተክል ልማት አዎ የጐመሮ ሻይ ተክል ልማት ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት እጅግ የሚደነቅ የአረንጓዴ ምንጣፍ አልብሷታል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ተክል እዛው ተመርቶ ወደ ሻይነት የሚለውጠውን ፋብሪካ በመሀሉ ላይ አቁሞ ከእዛው እየተቀጠፈ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ይህ በየቤታችሁ የምታፈሉትን ሻይ ቅጠል ያቀርብላችኋል፡፡ እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ምን አግሮ ኢንዱስትሪ አለ!!

ከጐሬ እኮ አልወጣንም፡፡ ምነው ዝም አላችሁኝ ጐሬ ጥንት የውጭ ዜጐች መናኸሪያ ነበረች፡፡ የንግድ ማዕከልም ነበረች፡፡ ድሮ ምፅዋና አሰብ በሌሎች ባዕዳን ቁጥጥር ሥር በነበሩ ጊዜ የወጪ ንግድ የሚካሄደው በጋምቤላ (ከጎሬ 160 ኪ.ሜ) በኩል ስለነበር ነው፡፡ ለወጪ ንግድ የሚላኩት ቡናና ሌሎች ሸቀጦች የሚጓጓዙት በዚሁ በኩል ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት አረቦች፣ ግሪኮች፣ አርመኖች፣ ጣሊያኖች እና ሌሎች የውጭ ዜጐች መኖሪያ ነች፡፡ እነዚህ የውጭ ዜጐች ከአገሬው ጋር ከመኖር አልፈው ተጋብተውና ተዋልደው ደማቸውን ደባልቀው የተከለሰ ሕዝብ በአብዛኛው ይገኝበታል፡፡ የሚገርመው የጊዜው ፖለቲካ በዚህ ምክንያት ተቀባይነት እንዳላገኘ የተነገረኝ ነው፡፡ መጤ ይውጣ ተባለና አንድ ሰሞን የወቅቱ ልክፍት ሊሰራጭ ሲሞክር አገሬው የመለሰው መልስ "የመጣብን የለም ካለናንተ በቀር" መሆኑ ነው፡፡

ጐሬ በጣም ከፍታ ላይ የተቆረቆረች ስትሆን ደጋማ ነች፡፡ በዚህም ምክንያት የብዙ ዕድሜ ባለፀጐች የሆኑ የጐበጡ ሰዎችን

ታገኛላችሁ፡፡ ሰዎች በየክፍለ ሀገሩ እየዞሩ ሲሰሩ ይከርሙና ዕድሜ ለመቀጠል የጡረታ ዘመናቸውን በዚህች ከተማ ነው መኖር የሚወዱት፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች 100 ዓመትን ቀጥ ብለው ነው የሚያልፉት፡፡ እናንተም ለመሞከር ካሰባችሁ 620 ኪሎ ሜትርን መጓዝን እንዳትዘነጉ ላስታውሳችሁ፡፡

ጐሬ ወደ ሞቻ፣ ጋምቤላና መቱ እንዳቅሟ ማከፋፈያ ነች፡፡ እኔ እንኳ የመረጥኩት ወደ ሞቻ ነው፡፡ እስቲ በዚያ ለጥ ባለውና የቅቤ መንገድ 56 ኪ.ሜ በአንድ ሰዓት ጊዜ ለመድረስ ወደ ሞቻ አውራጃ ዋና ከተማ ወደሆነችው ማሻ እንገስግስ፡፡ አቤት ደኑ! አቤት ደስ ማለቱ! ምነው በአንድ ቀን ቀስ እያላችሁ እርምጃችሁን እየቆጠራችሁ ብታዘግሙ፡፡ ብቻ መመነን እንዳያምራችሁ፡፡ አለአረንጓዴ ነገር የማታዩበት ሀገር ነው፡፡ የከለር ዓይነቶችን እንዳያስረሳችሁ ትሰጋላችሁ፡፡ ብቻ እነዚያ መልከ መልካሞቹ ጉሬዛዎች ነጭም ጥቁርም አለ እያሉ ያስታውሷችኋል፡፡

ጐሬ - ማሻ - ቴፒ - ሚዛን መንገድ በኢትዮጵያ አውራ ጐዳና ባለሥልጣን እንደተሰራ ዛሬም የፕሮጀክቱ ካምፕ የነበሩትን ቦታዎች የሚያመለክቱ ምልክቶች ተተክለው ይገኛሉ፡፡ ብዙ መኪና አይሄድበት ወይም ከመሬቱ ጥሩነት ይሁን አላውቅም ብቻ ከአረንጓዴው ምንጣፍ ተቀድዶ የተነጠፈ ነው የሚመስላችሁ፡፡ መጓዝና ሞቻ-ማሻ የማሩ ሀገር መግባት ነው፡፡ ከዚህ አረንጓዴ ነገር ምን ትጠብቃላችሁ አለማር ደግሞስ ከማር ምን የሚበልጥ

ነገር አለ ማር እንደዘይት  እንደውሃ ሲፈስ አይታችኋል? አዎ እንዳይገርማችሁ ነጭ በጣም ነጭ ማር ማሻ ነው ያለላችሁ፡፡

ማሻ ወይ ሞቻ ብላችሁ ይሻላል በዛሬው አጠራር የምትገኘው በክልል 11 ነው፡፡ ይኸውም የሸኪቾ ብሔረሰቦች የሚኖሩባትና ሸክኛ ቋንቋ የሚነገርበት አካባቢ ማለት ነው፡፡ ሞቻ ጥንት ልትሉት ይሆናል አቤ ጉበኛ የኖረበትን ዘመን አዎ ታዋቂው ደራሲ ባሳየው ለገዥዎች የማይስማማ ፀባይ ምክንያት በግዞት እንዲቆይ ተፈርዶበት የተጋዘባት ከተማ ነች፡፡

ታሪካዊቷ ሞቻ ሌላም የታሪክ አጋጣሚ አጋጥሚታል፡፡ ይኸውም በደርግ የግዳጅ መንደር መሰባሰብን በመቃወም አገሬው እንቢ በማለቱ ከፍተኛ የአየር፣ የሞርታር፣ የመድፍና ሌላም ውርጅብኝ በ1978 ዓ.ም. የወረደባት ከተማ ነች፡፡ ለዚህ አብነት የሆኑን በጊዜው የአስር አለቃ ፖሊስ የሆኑት ግርማ ናቸው፡፡ የወቅቱን አውራጃ አስተዳዳሪ አጅቤ ቤት ልናፈርስ ሄደን እሱ ሞትን ሲቀምስ እኔ ይኸው በክንዴ ጥይትን ብለው አሳይተውናል፡፡

በቃን ወደመጣንበት እንመለስ፡፡ እስካሁን ያጓጓዝኳችሁ ዋና መንገድ መንገዱን ይዤ ነው ለምን ይህን የማያልቅ የኢትዮጵያን መሬት ወደ ጉንም እየገባን አንቃኘውም፡፡ ከሁሉም ደግሞ ኢሊባቦር ደርሶ የዚያን ሰማዕት ጋዜጠኛና ደራሲ በዓሉ ግርማን ሀገር ሳይጐበኙ መምጣት ለኔ አልሆነልኝም፡፡ ከመቱ 40 ኪሎ ሜትር ወደ ጉን በኖፖ በኩል ሱጼ ቦሮን እንይ፡፡

ሱጴ ስንጓዝ ቅርብ ነው ብለው ያወጉን ሴት በምናባችን ከሃያ ኪሎ ሜትር ስላላስበለጥነው ብንሄድ ብንሄድ ከተማ ማግኘት ሲያቅተን ጊዜ መሬት ዝርግነቷ አልቆ የምንደፋና የምንጠፋ መስሎን እንመለስ አንመለስም በመሀላችን የሐሳብ ልዩነት ተፈጥሮ ነበር፡፡ እንዳጋጣሚ በእግር የሚጓዙ መንገደኞች አገኘንና ብንጠይቅ መግባባት አልቻልንም፡፡ ቋንቋው ከየት ይምጣ፡፡ ብቻ የእንሰትና የአትክልት ዘር ስላየን ሰው መኖሪያ መድረሳችን ሸተተንና በድፍረት ገፋንበት፡፡

ነዋሪዎቹ ሱጴ ቦሩንና በዓሉን ለያይተው አይነግሯችሁም፡፡ ያውላችሁ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ዋርካዎች ይሏችኋል፡፡ ሁሉም አገራቸውን ለኢትዮጵያውያን ስላስተዋወቀላቸው ባለውለተኛነት ይሰማቸዋል፡፡ አዎ ዋርካዎቹ ፊት ለፊት የሚተያዩና የሚፎካከሩ የሚመስሉ ሁለት ናቸው፡፡ እንደነገሩን አንደኛው አፍርቶ ሲያበቃ ሌላው ማፍራት ይጀምራል አሉን፡፡ አንደኛው ዙሪያውን በድንጋይ በደንብ መቀመጫ ተሰርቶለት አራት ኪሎ የሚል ስም ወጥቶለት የሰው ሁሉ መገናኛ ነው፡፡ ወጣቱ አዛውንቱ ዙሪያውን ከቦ ቁጭ ብሎ ይጫወታል፡፡

የበዓሉ ግርማ እናት በዚያው ከተማ ክልል እንደሚገኙ አጫውተውናል፡፡ እንደገለጹልን ከተሰወረ ከብዙ ጊዜ በኋላ በለውጡ ጊዜም ምንም ፍንጭ ሲጠፋ የቀበሌው ሰዎች ናቸው ወስነው ያረዷቸውና እርማቸውን እንዲያወጡ ወደ አዲስ አበባ ገንዘብ

አዋጥተው የላኳቸው፡፡ በጥንት ጊዜ ጣሊያኖች፣ ግሪኮች፣ ሕንዶች እና ሌሎች የውጭ ዜጎች ይኖሩበት ነበር (በዓሉም ከአንዱ ሕንድ መገኘቱንም አትዘነጉትም)፡፡ እነዚህ የውጭ ዜጎች ሰፋፊ የአትክልት እርሻ ነበራቸው፡፡ ለዚህም የሚረዳቸው የገባ ወንዝ ከሱጴ በቅርብ መገኘቱ ነው፡፡ በቀበሌው ጽ/ቤት ውስጥ ለከተማዋ መስፋፋትና ዕድገት አስተዋጽኦ ያለው ሰው ነው የተባለ ጣሊያናዊ /ዲሚትሪ/ ፎቶ ግራፍ ተሰቅሎ አይቻለሁ፡፡ የሚገርም ነው የአገሬው ውለታ አክባሪነት፡፡ የድሮ የአካባቢው አውራጃ ስም እንግዲህ በሁለቱ ወንዞች መጠራቱን አስተውሉ፡፡ ሶር ከመቱ፣ ገባ ከሱጴ አንድ ላይ ሶርና ገባ አውራጃ ተብሎ ይታወቅ ነበር በቅርቡ እስከቀረ፡፡

ተመልሰን እስቲ ወደ መንገድ እንውጣና ሁሩሙ፣ ያዩ፣ ደንቢ ብለን ቶባ እንግባ፡፡  በቶባ በኩል ነው ሌላው የጊዜው የጦር አውድማ የሆነው ሲግሞ ሰጠማ አውራጃ የሚኬደው፡፡ ሲግሞ ከቶባ ወደ ውስጥ 54 ኪሎ ሜትር ነው የሚርቀው፡፡ ሆኖም መንገዱ በጣም የተበላሸ በመሆኑ አስቸጋሪ ነው፡፡ እስቲ ቀስ እያልን እናዝግም፡፡ መጀመሪያ ሰጠማን ታገኛላችሁ ቀጥሎ ጋቲራን ነው፡፡ ጋቲራ በእህል ምርቷ በጣም የታወቀች ነች፡፡ እንደሌላው የኢሉባቦር ቦታዎች ቡና ሳይሆን የምታበቅለው ጤፍና ሌሎች የአገዳ ሰብሎችን ነው፡፡ የጋቲራ ጤፍ ሲባል ትሰሙ አይደል? ታዲያ በጉ፣ ፍየሉም ሞልቷል፡፡

ጋቲራ ከሶስት ወራት ቀደም ብሎ መምጣት አይቻልም ነበር አሉን፡፡ ምነው ብንላቸው ያ ሰው የሚበላው ሰው የፈጠረው አውሬ ነበር አሉን፡፡ ጦርነት

ማለታቸው ነው። ኦነግ ከሽግግር መንግስቱ ከተለየ በኋላ ወደዚህ ክልል ዘልቆ እንደገባና እስከ ሲግሞ ድረስ በቁጥጥር ሥር አድርጐ ነበር አሉን። ታዲያ ብዙም አልዘለቀበትም። ሲያጫውቱን አህያና በቅሎ በመኪና እየተጫነ መጥቶ በእግር በነዚህ ጋማ ከብቶች መሣሪያ እየተጫነ ‹‹ሽፍታን ሽፍተህ ነው የምትመታው›› በሚል መሪ ቃል መሠረት ኢህአዲጐች ገብተው እንዳፀዱት ገልጸውልናል። ትውስታቸው መሪር ነው። ስንት ወጣት የተማሩ የኦሮሞ ልጆች መስዋዕትነት እንደከፈሉ ያስታውሱታል። በዚህ ጦርነት ምክንያት እስካሁን ድረስ ከአካባቢው የተመረጠ አስተዳዳሪ የለም። በዚህ ምክንያት ያየነው በፈቃደኝነት የተሰባሰቡ ጊዜያዊ አስተዳዳሪዎችን ነው። በተረፈ የሠራዊት ብዛት ነው ያስተዋልነው።

ሲግሞ ጠጅ ቤት ጐራ አልን። የኦሮምኛ አዝማሪ አገኘን። የመጀመሪያዬ ስለሆነ በጣም ነው የተደሰትኩት። ታዲያ ወደ አማርኛ መልሱልኝ ብል እንደማይችሉ ገለጹልኝ። ምን እንደሚል ከሌሎች ሰዎች ጠይቄ ተረዳሁ። ይኸውም ዛሬ ሰላም በመስፈኑ እኔም አዘምራለሁ፣ እርሻም ይታረሳል ነው በአጭሩ....

ከመስከረም 11 እስከ ኅዳር 29 ቀን 1985 ዓ.ም. የተደረገ ጉዞ

ማስታወሻ

## ፳፱. ጉዞ ሲጠቃለል

የትም ዞሮ ከቤት መመለስ አይቀርምና እኔም ይህን ሁሉ ሀገር አንከራትቼአችሁ ሜዳ ላይ አልተዋችሁምና እስቲ ቤታችን እንግባና ለዛሬ ጉዞውን እናጠቃለው:: የእኔ ጉዞ የጀመረው በጦርነቱ ማግስት ነው:: በዓመቱ አንድ ሁለት ቦታ ጎብኝቼ ማስታወሻ ባሰፍርም ከዚያ በኋላ ብዕርና ወረቀት ለማገናኘት ከሃያ ዓመታት በላይ ወስዶብኛል:: ለምን እንደሆነ ራሴንም ጠይቄ ጥርት ያለ መልስ ባላገኝም አዕምሮዬ ነፃ ስላልሆነ ይመስለኛል::

በዚህ ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ በፈጀው ጉብኝታችን ወቅት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ብዙ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ከባቢያዊ ሁኔታዎች ተለውጠዋል:: በኢኮኖሚው ረገድ የታዩ ለውጦችን እንኳ ብናይ ከቴክኖሎጂ ፈጠራ ዘመን በእውቀት ላይ ወደ ተመሰረተ የኢኮኖሚ እድገት ሽግግር ተደርጓል:: በፖለቲካውም ረገድ በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ ከነበረው የምዕራብና ምሥራቅ ጎራ ፍጥጫ ወጥቶ በመጠባበቅም ቢሆን ወደ ትብብርና እየተመራረጡ መቧደን ተሸጋግሯል:: አንፃራዊ ነፃ የሰዎች ዝውውር የነበረው ዛሬ ጥርጣሬና ገደብ የበዛበት ሆኗል:: ድሮም ፍጹም ሰላም ነበር ባይባልም ከነበረው ከፍቶ ሽብርተኝነት፣ አክራሪነትና ስደት ተስፋፍቷል:: በአየር ንብረት ለውጥ (Climate Change) ላይ ሙሉዕ በኩሌኼ የሚባል ዓይነት የአካባቢ ጥበቃ ስምምነት

ባይገኝም ችግሩ አፍጦ በመምጣቱ የዓለም የብዙ ሀገሮች አጀንዳ ሆኗል። በዚህ ጊዜ የማይካደው እውነታ በየመሃሉ ውጣ ውረድ ባያጣውም የዓለም ኢኮኖሚ አድጓል። እንደዚሁም የድሀና ሀብታም ሀገሮችና የሰዎች የኑሮ ልዩነት እጅግ ሰፍቷል።

በአሜሪካ እ.ኤ.አ. 2001 ከደረሰው የአልቃይዳ የሽብር ጥቃት በኋላ የሰዎች ነፃነት በገደብ ሆኗል። በኤርፖርት ያለው ፍተሻ ጠብቋል። እንደ ልብ ይጎበኙ የነበሩ ቦታዎች አሁን በከፍተኛ ቁጥጥርና በወረፋ ሆነዋል። አውሮፓ በስደተኞች ተጨናንቋል። የባህር ላይ የስደተኞች ሞት በርክቷል። የሰዎች ህገ ወጥ ዝውውርና የሰው አካል ንግድ ኢሰባዊነቱ ዘግናኝ ደረጃ ላይ ደርሷል። በአጠቃላይ የሕዝብ ዕድገትና ሥራ አጥነት ጨምሯል። የሰው ኑሮም እጅግ ተወዷል።

በአውሮፓ አህጉር በትብብር የተመሰረተው ህብረት የእንግሊዝ ከህብረቱ መውጣትን ተከትሎ ፈተና ገጥሞታል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እድገቱ ወደ ህብረት ተጉዞ የአፍሪካ ህብረት ተመስርቷል። አዳዲስ ሀገሮችም ኤርትራ፣ ደቡብ ሱዳንና ምዕራብ አረብ ሰሀራዊ ሪፐብሊክ ተወልደዋል። ቀጠናዊ ትብብሮችም የድርጅት ቅርፅ ይዘው እያደጉ ነው።

የእስያውያን ለዘመናት የተጠበቀው ዕሴቶቻቸውና ለዕድገታቸው ያበረከተውን አስተዋፅኦ በአገሬ እየተሸረሸረ ከመጣው ዕሴታችን ጋር

ሳወዳድር ዛሬ በአገሬ ምነው የሞራል ትምህርቱ ከፍታ ቦታ ላይ ተቁሞ በተሰበከ ያሰኘኛል:: ጋናና አፍጋኒስታን በይቅርታና በመቻቻል ላይ ያላቸውን ልዩነት ሳስብ ማህበረሰባቸው የተመሰረተበትን የልቦና ውቅር ሚስጢር ማወቅ ብችል ብዬ እጓጓለሁ:: የሕንዳውያንን በራስ መተማመንና በእውቀት ላይ የተመሰረተው እድገታቸው በትምህርት ጥራት ላይ ምን ያህል መትጋት እንዳለብን ሳስብ የቤት ሥራችን ብዙ እንደሆነ ይሰማኛል:: በዓለም አቀፋዊ ወዛደራዊነት ትብብር መንፈስ በአንድ ሀገር ላይ በወራሪ ጠላት ጦርነት በሚነሳበት ጊዜ ለመርዳት አንዱ ላንዱ ይደርስ የነበረው ዛሬ የቅጥር ወታደር (Mercenary) የሥራ መስክ ሆኗል::

በሀገር ውስጥም የሚስተዋሉ ብዙ ለውጦች አሉ:: አንዳንድ ከተሞች ከብዙ ጊዜ በኋላ ተመልሼ ሳያቸው ከመንገድ መሰረተ ልማት ጀምሮ ብዙ ግንባታዎች ተከናውኖባቸዋል:: በፊት ምሳ መመገቢያ ቦታ ይቸግር የነበሩ ከተሞች ዛሬ ባለ ኮከብ ሆቴል ባለቤቶች ሆነዋል:: ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተዋል ብዙ የባንክ ቅርንጫፎች በገጠርና በከተሞች ተስፋፍተዋል:: ከተሞች በሕዝብ ብዛት በተለይ በወጣቶች ተጨናንቀዋል:: እንደዚሁም ያየኋቸው የማሻ-ቴፒ ጫካዎች በኢንቨስትመንት ስም ተመንጥረው አይቼ አዝኛለሁ::

በዚህ ሁሉ ጉብኝቴ የተገነዘብኩት ቀድመው የነቁና የተጉት ሀገሮች ብዙ የሚጎበኝ ተፈጥሮአዊ መስህቦች ባይኖራቸው እንኳ ያለችውን አሰማምረው በወግ ይይዛሉ ወይም ይፈጥሩታል:: ለዚህ

ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑ በየአገሩ ያየኋቸው ሰው ሰራሽ ሀይቆችና ጋራዎች አሉ:: ለጎብኝዎችም ምቹና ቀላል ያደርጉታል:: በአንፃሩ እኛ ባለብዙ ታሪካዊ ቦታዎችና ድንቅ መስህቦች ባለቤት ሆነን በሃብታችን በአግባቡ አለመጠቀማችን ያስቆጫል::

በሌላው ዓለም ሰዎች ሥራ ከጀመሩበት ዕለት አንስቶ ለጡረታ ዘመናቸው ሀገር የመጎብኘት ዕቅዳቸውን የሚያሳኩበት ጥሪት ይቆጥባሉ:: በቀደመ ጊዜ በአዳዲ ማርያም ጉብኝቴ ወቅት የሀገር ውስጥ ጉብኝት ጅማሮ መኖሩን የገለጽኩት ምን ያህል እንደተገፋበት ባላውቅም ሕዝባችን ሀገሩን የመጎብኘት መልካም ባህል ቢያዳብር ምኞቴ ነው:: በአጠቃላይ በጉብኝቴ እንደተገነዘብኩት የየሀገሩን ባህልና ወግ ማየት ብዙ የግንዛቤ ለውጥ ያመጣል::

በቸር ይግጠመን::

-----------------------------------›አበቃ--------------------------

ጽሑፉ አገሮችንና ባሕላቸውን ከማስተዋወቅ፤ እንዲሁም ታሪክን ከመንገርና እውቀትን ከማሸጋገር አንፃር ጉልህ ፋይዳ አለው። የአጻጻፍ ዘዴው አያዋዛ ገላጭ ነው ። በ‹‹ጉዞ ማስታወሻ›› ዘውግ ለሚጻፉ ድርሳናት ከፍተኛ የአነሳሽነት አስተዋፅዖ አለው።

ገስጥ ተጫኔ (ደራሲ)

የአጻጻፉ ስታይል ለማንበብ የሚመች፤ አንብቡኝ አንብቡኝ የሚል ነው። ትረካውን ከአንባቢው ጋር በቀጥታ ያገናኛል። አንዳንዴም ቢሆን በነገር ትንሽ ጠቅ የማድረግ አዝማሚያ ስላለው ለጽሁፉ የበለጠ ጣእም ሰጥቶታል። ለምሳሌ ልቁጠር ካሉ ኩሬዎችንም አይርሱ የተባለው በሚኒሶታ 10 ሺህ ያህል ሀይቆች አሉ የሚለውን ትንሽ የተጋነነ ቁጥር ለመጥቀስ ይመስለኛል። ሌላ ምሳሌ፤ የኢትዮጵያና የስዊዝ ገበሬ ባንድ ስም መጠራቱ፤ ካሳሻ በልቶ ያደገ ጋናዊና ጤፍ በልቶ ያደገ ኢትዮጵያዊ.... .

ጽሁፉ የብዙ ከተማዎችን ውበት እየጠቀሰ ተያያዥ የሆኑ ትምህርታዊ የሆኑ ነገሮችንም ያነሳል። ለምሳሌ በፓሪስ ከተማ ያለው የከተማ ፕላን፤ የህንፃ ኮድ ለሌሎችም ሀገሮች ትምህርት ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል። እንዲሁም በሰለጠኑ ሀገሮች የሚታዩት የሚያስደምሙ መንገድና ህንጻዎች ባሉባቸው ከተሞች ብዙ አደጋዎችም እንዳሉባቸው ያሳያል። ለምሳሌ እንደ ላስ ቬጋስ የመሳሰሉ አሸብራቂ ከተሞች የቁማር ሱስ ውስጥ ሊከቱ እንደሚችሉ ሹክ ይላል። በተጨማሪም ከሌላ ባህል ለሚመጡ ታዳጊዎች የአሜሪካ ከተሞች አደገኛ የባህል ቅራኔዎች ውስጥ ሊያስገቡ እንደሚችሉም በጫወታ መልክ ያሳያል።

በአጠቃላይ የጉዞ ማስታወሻው የሚጥም የአፃፃፍ ስልት አለው፣ የአንተም የነገሮችን የመታዘብና የማስታወስ ችሎታህ ታይቶበታል። ቋንቋውንም በደንብ ተጠቅመህበታል።

አክሊሉ ኪዳኑ

ሳሙኤል ጆንሰን እንዳለው የጉዞ ጥቅሙ ምናብን በእውነታ ለመቆጣጠርና ነገሮችን እንዴት ይሆኑ ብሎ ከማሰብ ይልቅ በተጨባጭ የሆኑትን ማሳየት መቻሉ ነው። ወንድማችን ታረቀኝ በበርካታ ጉዞዎቹ ማየት ብቻ ሳይሆን እሱ ያየውን በተዋዛ ብእሩ ሊያሳየንም በእጅጉ የጣረ ነው። ተሳክቶለታልም። ጎሽ እንዲያ ነው።

ሁነኛው ጥላሁን

ISBN 978-99944-3-025-3

ዋጋ ብር 120.00